# የመከራ በረከቶች

በሕይወታችሁ በገጠማችሁ መከራ ውስጥ
የእግዚአብሔርን ዓላማ ማወቅ

ቤሪ ሲ. ብላክ

**ትርጉም**
ፓ/ር መልአክ አለማየሁ

**አሳታሚ**
የትንቢት ቃል የወንጌል አገልግሎት

Original Title: The Blessing of Adversity: *Finding Your God-given Purpose in Life's Troubles*
Copyright © 2011 : by Barry C. Black

ደራሲ፡- ቤሪ ሲ. ብላክ
ትርጉም፡- ፓ/ር መልአክ አለማየሁ

ሽፋን ዲዛይን፡- Awesome Grafix
የውስጥ ዲዛይን፡- የትንቢት ቃል የወንጌል አገልግሎት

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
Copyright © 2013 (2005 ዓ.ም.) by
Yetnbit Kal Christian Ministries

አሳታሚ እና አከፋፋይ፡-

የትንቢት ቃል የወንጌል አገልግሎት

ኑረንበርግ

ጀርመን

Website: www.yetnbitkal.org
Email: yetnbitkal@yahoo.com

እዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት
ከ 1954 ዓ.ም. እትም እና ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው፡፡

Printed in Ethiopia

# ማውጫ

የተርጓሚው ማስታወሻ ~ 4

መግቢያ ~ 5

**ክፍል አንድ፡ መሠረታዊ ነገሮችን ጠንቅቆ ማወቅ**

1. በመከራዎቻችሁ ተደሰቱ ~ 9
2. በእግዚአብሔር እቅድ ታመኑ ~ 14
3. የጨለማ ቀናትን ግድድሮሾች ተጋፈጡ ~ 20
4. የፈረሱ ቅጥሮችን ጠግኑ ~ 25
5. ከስብራት በረከት አግኙ ~ 32
6. ስቃይን ማባከንን ተቃወሙ ~ 39
7. የመከራን አይቀሬነት ተቀበሉ ~ 44
8. በመጠበቅ አሸንፉ ~ 58
9. ከስቃይ ውስጥ በረከቶችን አውጡ ~ 66
10. የተባረከውን ሕይወት ኑሩ ~ 75
11. የሕይወትን ጫናዎች በእምነት ተጋፈጡ ~ 83
12. የእግዚአብሔርን ዝምታ ተጋፈጡ ~ 91
13. ተጠቀሙበት ወይም ታጡታላችሁ ~ 97
14. የሕይወታችሁን ካርታ ጠንቅቃችሁ እወቁ ~ 108
15. እርካታ ይኑራችሁ ~ 115
16. ራሳችሁን መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖች አስለምዱ ~ 120

**ክፍል ሁለት፡ የመከራን ምንጮች ማድረቅ**

17. ፈተናዎቻችሁን ግሩአቸው ~ 130
18. ጭንቀትን አሸንፉ ~ 135
19. ከስቃይ ሲሳይን አግኙ ~ 140
20. በፈተናው ጽኑ ~ 148
21. በማጣት አግኙ ~ 154

**ክፍል ሦስት፡ መከራዎቻችሁን ወደ በረከት መለወጥ**

22. እምነታችሁን አግዝፉት ~ 164
23. ማዕበል የማይበግረውን ሕይወት ገንቡ ~ 170

የመጨረሻ ቃል ~ 179

ስለ ጸሐፊው ~ 180

# የተርጓሚው ማስታወሻ

የ*መከራ በረከቶች* በማለት ወደ አማርኛ የተረጎሙኹትን ይህንን የቻፐሌን ብላክ መጽሐፍ በመጀመሪያ ያገኘሁት በሕይወት ጎዳና የመከራ ሸክም አጉብጦኝ ለመውደቅ ስንገዳገድ ነበር፡፡ በቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል ላይ ተመስርተው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ምክሮች በጨለማ ውስጥ ብርሃን እንዳይ፣ በተስፋ ደስ እንዲለኝ፣ እንደዚሁም በእግዚአብሔር አዋቂና አፍቃሪ ማንነት ላይ እንዳርፍ ረድተውኛል፡፡

መጽሐፉን ለመተርጎም ያነሳሳኝም ይኼው እኔ ያገኘሁት በረከት በመከራ ውስጥ ለሚያልፉ ለብዙዎች እንዲደርስ መናፈቄ ነው፡፡ የትርጉም ሥራውን በማረም ትልቅ እገዛ ያደረጉልኝን ወንድም ምንዋጋው ዓለሙን፣ ወንድም ቢያብብ መለሰን እንደዚሁም ፓስተር መስፍን ማንደፍሮንና ባለቤቱን ሃብታምነሽ ተረፈን ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ እላለሁ፡፡ ይህ የአማርኛው ትርጉም መጽሐፍ ይታተም ዘንድ ትልቅ ጥረት ያደረገውንና እግዚአብሔር የሰጠኝን ጸጋ እንድጠቀምበት ከፍተኛ ድጋፍ የሚያደርግልኝን ወንድሜን ዳዊት መሐሪን ‹‹ኑርልኝ›› እለዋለሁ፡፡

በዚህ አጋጣሚ በሕይወት ጎዳና በገጠመኝ ከባድ ጊዜ ከጎኔ በመሆን እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ የተጠቀመባቸውን ወገኖች ሁሉ እግዚአብሔር ይባርክልኝ ስል በተለይ ባለቤቴን ምህረት ተስፋጽዮንን የሰጠኝን እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ፡፡ በመጨረሻም ይህንን የትርጉም ሥራ ገና በለጋ እድሜው የዓይን ብርሃኑን አጥቶ በተለያዩ የጤንነት እክሎች እየተሰቃየ ለሚገኘው ለአንዱ ወንድሜ ለጸጋው አለማየሁ ‹‹በመከራ ውስጥ የተሰወረውን በረከት እግዚአብሔር ይስጥህ›› በማለት ላበረክትለት እወዳለሁ፡፡

*ፓ/ር መልአክ አለማየሁ*
*ጥር፣ 2005*

We would like to thank Tyndel publishing house for giving us the permission to print this Amharic version.

# መግቢያ

ብዙ ሰዎች መከራን እንደ አሉታዊ ክስተት የሚያዩት ሲሆን በተቻለ መጠን ሁሉ ሊያስወግዱት ይሞክራሉ፡፡ ይሁን እንጂ መከራዎቻችንን በደስታ ማስተናገድን ከተማርን ችግሮቻችንን ወደ ጥቅም በመለወጥ የእግዚአብሔርን አላማ በሕይወችን ልንለማመድ እንችላለን፡፡ ይህ እውነት ነው፡፡ በመከራ ውስጥ የእግዚአብሔርን በረከት መመልከት ከቻላችሁ፣ ንጉሥ ዳዊት እንዲህ ብሎ ሲጽፍ የተናገረውን ማስተዋል ትችላላችሁ፡- ‹‹ያስጨነቅኸኝ ለመልካም ሆነልኝ፡፡›› (መዝ. 119፡ 71)፡፡

ምናልባት ልባችሁን በሃዘን የሰበረ ፍቺ በቅርብ ፈጽማችሁ ይሆናል፡፡ በብቸኝነት ስሜትም ተሞልታችኋል፡፡ ታዲያ ይህንን ስቃያችሁን ታባክኑታላችሁ ወይስ እግዚአብሔር ለክብሩ እንዲጠቀምበት ትፈቅዱለታላችሁ; ወይም ምናልባት ከልጆቻችሁ አንዱ የአደንዛዥ እጽ ሱሰኛ መሆኑን በቅርብ አውቃችሁ ይሆናል፡፡ ታዲያ እግዚአብሔር መጥፎ ነገር ውስጥ ምን መልካም ነገርን ሊያወጣ ይችላል; ይህንን የጭንቅ ጊዜ እንድታልፉት እግዚአብሔር ሊረዳችሁ ይችላል; ወይም ምናልባት ጤና ችግር አልያም ከስራ መባረር ገጥሞአችሁ ይሆናል፡፡ በሕይወት ጎዳና የሚገጥሟችሁን ሸለቆዎች የምታስተናግዷቸው እንዴት ነው; ‹‹እግዚአብሔር ለሚወዱት ነገርን ሁሉ ለበጎ የሚያደርግ ከሆነ›› (ሮሜ. 8፡28)፣ ታዲያ በመከራችሁ ውስጥ የእርሱን በረከቶች እንድታገኙ ሊያደርጋችሁ አይችልምን?

እያንዳንዱ ሰው የሚያልፍበት የራሱ የሆነ የመከራ ጎዳና አለው፡፡ አንዳንዴ የሚገጥመን የገንዘብ ችግር ሲሆን ከወር እስከ ወር የሚያደርሰንን በቂ መጠን በማጣት እንቸገራለን፡፡ ወይም ድንገት ከስራ ልንወጣ እንችል ይሆናል፡፡ ሌላ ጊዜ ደግሞ መከራ የሚመጣብን በመሪር ሃዘን ተመስሎ ነው፡፡ አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ቤተሰባችንን ፣ ደስታንና ሰላምን ልናጣ እንችላለን፡፡

*የመከራ በረከቶች* በሕይወት ከባድ ጊዜያት ውስጥ ሰላምን ልንቀዳጅ የምንችልበትን መንገድ ይጠቁመናል፡፡ ከሕይወት መከራዎች ጋር እየታገላችሁ ቢሆን፣ ተግዳሮቶቹን በቆራጥነት እንድትጨብጧቸውና፣ የመከራንም አይቀሬነት እንድትቀበሉ ያደርጋችኋል፡፡ ምክንያቱም ‹‹›› (2 ጢሞ. 3፡12)፡፡ ቀጥሎ ባሉት ገጾች ላይ ፣ የእግዚአብሔርን ዝምታ እንዴት ማስተናገድ እንዳለባችሁ፣ በሕይወት ማዕበል ውስጥ ስታልፉም ራሳችሁን እንዴት እንደምታበረታቱ፣ እናም በመከራዎቻችሁ ውስጥ እንዴት የእግዚአብሔርን በረከት እንደምታገኙ ትማራላችሁ፡፡

በተጨማሪም፣ ስቃዮቻችሁን ሌሎችን ለመባረክ እንዴት እንደምትጠቀሙባቸው ትማራላችሁ፡፡ በመከራና በሃዘን ጊዜ በተመሳሳይ ልምምድ ውስጥ ቀደም ብሎ ካለፈ ሰው የበለጠ ማጽናናትና የልብን መረዳት የሚችል ሌላ የተሻለ ሰው ከወዴት ይገኛል? ስቃይ ሲደርስባችሁ ስለ ስቃይ ቲዎሪ ብቻ የሚያወራላችሁን ሰው ነው የምትፈልጉት ወይስ እናንተ በተጫማችሁት ጫማ አስቀድሞ የተጓዘን ሰው? በተመሳሳዩም፣ እናንተም በምታልፉባቸው ከባድ ቀናት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኛችሁትን መጽናናት ለሌሎች ማካፈል ትችላላችሁ፡፡

በተጨማሪም፣ ስቃዮቻችሁን ሌሎችን ለመባረክ እንዴት እንደምትጠቀሙባቸው ትማራላችሁ፡፡ በመከራና በሃዘን ጊዜ በተመሳሳይ ልምምድ ውስጥ ቀደም ብሎ ካለፈ ሰው የበለጠ ማጽናናትና የልብን መረዳት የሚችል ሌላ የተሻለ ሰው ከወዴት ይገኛል? ስቃይ ሲደርስባችሁ ስለ ስቃይ ቲዎሪ ብቻ የሚያወራላችሁን ሰው ነው የምትፈልጉት ወይስ እናንተ በተጫማችሁት ጫማ አስቀድሞ የተጓዘን ሰው? በተመሳሳዩም፣ እናንተም በምታልፉባቸው ከባድ ቀናት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኛችሁትን መጽናናት ለሌሎች ማካፈል ትችላላችሁ፡፡

*የመከራ በረከቶች* በሕይወት የሚገጥማችሁን ማዕበሎች ለመጋፈጥ የሚመራችሁ ቀለል ባለ ሁኔታ የቀረበ መሪ ነው፡፡ ለሰላሳ አመታት ያህል በዘለቀው የእረኝነት የማማከር ስራዬ፣ እንደዚሁም በነገረ መለኮትና በስነልቦና ትምህርት ከገበየሁት የዶክትሬት እውቀት የተገኙትን ጥበቦች እያነጠረ በመከራዎቻችሁ ውስጥ የእግዚአብሔርን አላማ ለማግኘት የሚረዷችሁን ተግባራዊ የድርጊት እቅዶ አንደ በአንድ የሚዘርዝር ነው፡፡

ጉዞውን አብረን እንጀምረው፡፡

ክፍል አንድ ፡-

# መሠረታዊ ነገሮችን ጠንቅቆ ማወቅ

# 1

# በመከራዎቻችሁ ተደሰቱ

በሕይወታችሁ ካሳለፋችኋቸው ከባድ ወራት መካከል አንዱን ወደ ኋላ ዘወር ብላችሁ በማሰብ ከአሉታዊ ገጽታው ይልቅ አዎንታዊውን ለመመልከት ሞክራችሁ ታውቃላችሁ? ለመከራዎቻችሁ የምስጋና ቃል ተናግራችሁስ ታውቃላችሁ? ንጉሥ ዳዊት እንደዚህ አድርጓል። እንዲህም አለ፦ «እኔ ሳልጨነቅ ሳትሁ አሁን ግን ቃልህን ጠበቅሁ።» (መዝ. 119፡67)። በሌላ አነጋገር፣ በረከቱን ያገኘው በመከራው ውስጥ ነበር።

በመከራዎቻችሁ ተደስታችሁ የምታውቁ ከሆነ፣ በሐዋርያው ያዕቆብ የተሰጠውን መመሪያ ተከትላችኋል ማለት ነው፦ «ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት፡፡ ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል።» (ያዕ. 1፡2-4)።

ይህ የሚገርም አርፍተ ነገር አይደለምን? «ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት።» በሌላ አነጋገር፣መከራዎቻችሁንና ችግሮቻችሁን ብስለታችሁ እየጎለበተ እንዲሄድ የሚያግዙ፣ እንደዚሁም ለሕይወታችሁ እግዚአብሔር የሰጣችሁን አላማ ለመፈጸም የሚያዘጋጁ ወዳጆቻችሁ እንደሆኑ በማሰብ ተቀበሏቸው።

ከጎረቤቶቼ መካከል አንዱ ከጓሮው በንፋስ እየተንሸዋሸወ ሙዚቃ የሚፈጥር ነገር (ቺም ይባላል) ሰቅሏል። እናም ሃይለኛ ሞገድ ሲነሳና ንፋሱ ሲነፍስ፣ ያ መሳሪያ የሚያወጣውን ሙዚቃ በመስማት እደሰታለሁ። እነዚያ ቺሞች በሞገድ ውስጥ ሙዚቃ እንደሚፈጥሩ ሁሉ፣ እኛም በሕይወት መከራ ውስጥ በሕይወታችን ሙዚቃ ልንፈጥር ይገባል። በሕይወታችሁ እጅግ ከባድ የሆነውን ችግር በምትጋፈጡበት ጊዜ፣ በመከራችሁ እንድትደሰቱ የሚያደርጓችሁ ስድስት ነገሮች አሉ፦ ምላሳችሁን መጠበቅ፣ ቀና ማሰብ፣ አለመዋዠቅ፣ ማደግ፣ ካርታችሁን መጠቀምና ጥርጣሬያችሁን በቁጥጥር ስር ማዋል ናቸው።

**ምላሳችሁን ጠብቁ**

ችግሮቻችንን እያሰብን ማልቀስ በጣም ቀላል ነው። ቀደም ያሉ መንፈሳዊ መዝሙሮች እንደገለጹት፣ «እኔ ያየሁትን መከራ ማንም አላየውም» እያለን ለመጮህ እንፈልጋለን። ያዕቆብ እንዲህ ያለ ልምምድ ነበረው። ለአስራ ሦስት አመት የሚወደው ልጁ ዮሴፍ ሞቷል ብሎ አስቦ ነበር። የደረሰበትን ይህንን ከባድ መከራ አስቦ ሲያለቅስም እንዲህ በማለት ጮኸ፦ «ልጅ አልባ አስቀራችሁኝ ዮሴፍ የለም፥ ስምዖንም የለም፥ ብንያምንም ትወስዱብኛላችሁ ይህ ሁሉ በእኔ ላይ ደረሰ።» (ዘፍ. 42፡36)።

ችግሮቻችንን በተመለከተ በምሬት ማልቀስ የሚያስከትለው ችግር፤ የምንናገራቸው

በጭንቀት የተሞሉ ቃሎቻችን በእኛ በራሳችን ላይ ተፈጻሚ እንዲሆኑ፤ ራሳችን በራሳችን የምንፈጽማቸውን ትንቢቶች አስቀድመን እንድንናገር ማስቻሉ ነው። ምሳ. 18፡21 እንዲህ ይላል፡- «ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው »። ለራሳችሁም ሆነ ለሌሎች የምትናገሩት ቃል መልካም ወይም ክፉ፣ ፈውስ ወይም ስብራት ያመጣል። ስለዚህም «እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፥ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ፥ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፥ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፥ እነዚህን አስቡ» (ፊል. 4፡8)። በዚህም የሚያንጽና የጥበብ ንግግርን ለማድረግ የሚያስችላችሁን መሠረት ትጥላላችሁ።

**ቀና ማሰባችሁን ቀጥሉ**

በችግሮቻችን መደሰት የምንጀምረው ችግሮቻችንን በሕይወታችን በጎ ነገር ሊያመጡልን እንደሚችሉ ስናስብ ነው። ዊንስተን ቸርችል እንዲህ ብለው ነበር፡- «ጨለምተኛ አመለካከት ያለው ሰው በእድሎች ውስጥ ያሉትን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ይመለከታል፤ ቀና አስተሳሰብ ያለው ሰው ደግሞ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ያለውን እድል ይመለከታል» እናንተስ በአስቸጋሪ ሁኔታዎቻችሁ ውስጥ ያሉትን እድሎች ትመለከታላችሁ? የምታልፉበት ነገር ምንም ቢሆን ምን፣ ከዚያ ውስጥ መልካምን ነገር ለማየት ጣሩ።»

ሐዋርያው ጳውሎስ ለፊልጲስዩስ ሰዎች የላከውን ደብዳቤ የጻፈው በሮም ታስሮ እያለ ሳይሆን አይቀርም። ታዲያ ጳውሎስ ስለ ደረሰበት መከራ ከማጉረምረም ይልቅ፣ በአስቸጋሪ ሁኔታዎቹ ውስጥ ስላገኛቸው እድሎች ይናገራል። «ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ይህ የደረሰብኝ በእውነት ወንጌልን ለማስፋት እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። ስለዚህም እስራቴ ስለ ክርስቶስ እንዲሆን በንጉሥ ዘበኞች ሁሉና በሌሎች ሁሉ ዘንድ ተገለጦአል፥»(ፊል. 1፡12-13)። ይህ በእውነት ግሩም አይደለምን? ጳውሎስ በእስር ቤት መወርወሩንና በቅርብም የሚጠብቀውን የሰማዕትነት ሞት ወንጌልን ወደፊት ለማስኬድ የሚያስችል እድል አድርጎ ተመለከተው። ቀና አስተስተሳብ ይሏል ይኼ ነው! ጳውሎስ የቀና አስተሳሰብ አስገራሚ ምሳሌ ነው።

እናንተስ እንዴት ናችሁ? ስለ መከራችሁ ቀና ታስባላችሁ? በእስር ቤት በተጣሉ ጊዜ እንደጸለዩትና ለእግዚአብሔርም የምስጋና መዝሙር እንደዘመሩት፣ እንደ ጳውሎስና ከእርሱ ጋር ለወንጌል ተሰልፎ እንደነበረው ሲላስ መሆን ትችላላችሁ። «እግዚአብሔርን ለሚወዱት ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ » እንደሚደረግ በማስታወስ በመከራዎቻችሁ ውስጥ ያሉትን በጎ ነገሮች አጉልታችሁ ማየት ትችላላችሁ። (ሮሜ. 8፡28)።

ከአገልጋይ ጓደኞቼ መካከል አንዱ፣ በሆስፒታል ተኝታ እግሯ የተቆረጠን የቤተክርስቲያኑን አባል ለመጎብኘት ሄደ። ለዚህች ሴት ሊነግራት የሚችለውን ቀና የሆነ ነገር በማሰብ ብዙ ደከመ፤ ነገር ግን ምንም ሊያገኝ አልቻለም። ያቺ ሴት በተኛችበት የሆስፒታል ክፍል ውስጥ ቁጭ ብሎ ሊያበረታታት የሚችል ሃሳብ እስኪመጣለት እየጠበቀ ሳለ፣ እንዲህ የሚል አስደናቂ ቃላትን በመናገር ዝምታውን ሰበረችው፡- «ፓስተር፣ የደረሰብኝ ችግር እዚህ ላይ በመገታቱ እግዚአብሔርን አመስግን፤ ሁለቱንም እግሮቼን ላጣ እችል ነበር እኮ!» ቀና አስተሳሰቧና ብሩህ ቃላቷ፣ በመከራዎቹ ውስጥ የበለጠ ጠጋ ብሎ በረከቶቹን እንዲያይና ከበፊቱ ይልቅ ስለ ሕይወት ቀና አስተሳሰብ እንዲኖረው ጓደኛዬን አነሳሱት፡፡

### አትታክቱ

ስለ እጣ ፈንታችሁ ማጉረምረም ትታችሁ ስለ መከራችሁ ቀና ማሰብና መናገር ስትጀምሩ ከመታከት ይልቅ መጽናትንና መታገስን ታፈራላችሁ። መታገስ ወይም መጽናት በግሪኩ ሁፖሞኔ የተሰኘ ሲሆን ጳውሎስም ይህንን ቃል በመጠቀም በገላትያ 6፡9 ላይ እንዲህ ጽፎአል፡- «ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት አንታክት።» ይህን ባሕርይ ነበር በ19ኛው ክፍለ ዘመን የብሪቲሽ ጠቅላይ ሚኒስቴር የነበሩት ቤንጃሚን ዲስሬይሊ እንዲህ በማለት ሲናገሩ አጽንኦት የሰጡት፡- «የስኬት ሚስጢር የዓላማ ጽናት ነው።»

ንጉስ ዳዊት የተሳካለት ከዓላማ ጽናት የተነሳ ነበር። እንደ ንጉሥ ሆኖ የተቀባበት ታሪክ በ 1ኛ ሳሙ. 16 ላይ ይገኛል፣ ነገር ግን ይህ ከሆነ ቢያንስ 15 አመታት ካለፉ በኋላ ነበር ወደ ዙፋን የመጣው (2 ሳሙ. 5)። ከተቀባበት እስከ ነገሰበት ጊዜ ድረስ ባሉት አመታት፣ በንጉሥ ሳኦል፣ በዚያን ዘመን በእስራኤል እጅግ ኃያል በሆነው ሰው፣ ስደት ደርሶበት ነበር። ይሁን እንጂ፣ ዳዊት ተስፋ አልቆረጠም፤ ታገሠ። ከእነዚያ የመከራ ምዕራፎቹም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመዝሙር መጽሐፍን አብዛኛውን ክፍል የሸፈኑትን የማይረሱ ግጥሞችንና ሙዚቃዎችን ለማዘጋጀት ቻለ።

የአላማ ጽናት በማጣታችሁ ምን አይነት ስኬቶችን አጥታችሁ ይሆን? በየአመቱ የተለያዩ የትምህርት ዲግሪዎችን ለመያዝ ትምህርት ጀምረው ነገር ግን በመንገዳቸው ላይ ከሚያጋጥማቸው ችግር የተነሳ መርሐ ግብሩን ሳይጨርሱ የሚያቋርጡትን በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች አስቡ። ወይም ክብደታቸውን ለመቀነስ ጥረት ማድረግ ጀምረው ያሰቡበት ግብ ላይ ሳይደርሱ የሚያቆሙትን አስቡ። በመከራቸው መደሰትን የተማሩ ሁሉ ግን ጽናትን ከችግሮቻቸው ያገኛሉ፤ እንደዚሁም አስቸጋሪ ጊዜዎቻቸውን ማሸነፍ ይችላሉ።

ብዙ ጊዜ፣ የአላማ ጽናት ያላቸው ተራ የሆኑ ሰዎች ከእነርሱ ይልቅ ብዙ ችሎታ ካላቸው ጓደኞቻቸው እጅግ የበለጠን ነገር ማከናወን ሲችሉ አይቻለሁ። በኤሶፕ የተረት መጽሐፍ ላይ እንደምትገኘው ከጥንቸል ጋር እንደተወዳደረችው ኤሊ፣ በትዕግስት ጉዟችሁን በመቀጠልና በማያቋርጥ ጽናት እያንዳንዱን መሰናክል ካለፋችሁ ሩጫችሁን ማሸነፍ ትችላላችሁ።

### ዕደጉ

በመከራዎቻችሁ በምትደሰቱበት ጊዜ ለማደግ ይረዳችኋል። ሐዋርያው ጳውሎስ እንደዚህ በማለት ያውጃል፡- «ጎልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ።» (1 ቆሮ. 13፡11)። ያዕቆብም «ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም» (ያዕ. 1፡4) ሲል ይህንን ማለቱ ነበር።

ወደ ብስለት ለመድረስ በሚደረግ ጉዞ ሁሉም ሰው ሊቀረፍለት የሚገባ አባጣ ጎርባጣ አለው። ሁላችንም የልጅነትን ጠባይ መሻር ያስፈልገናል። ይህንንም ለማድረግ እንዲቀሰቅሰን መከራ ያስፈልገን ይሆናል። የዮሴፍ ወንድሞች የተለወጡት በመከራ ውስጥ ነበር። ራሱ ዮሴፍም ቢሆን እንደዚያው ነው። (ዘፍ. 42 እና 50)። ሁሉም በህይወታቸው መከራዎችንና አስጊ ሁኔታዎችን፣ ስቃይንና ውድቀትን ከተለማመዱ በኋላ የበለጠ ሩህሩሆችና አንዱ ለሌላው የሚያስብ ሆኑ።

የዮሴፍን ወንድሞች ታሪክ የሚያስታውሰኝ በውትድርና ቤት ውስጥ የማውቀው

አንድ ወዳጅ ነበረኝ። ይህ ሰው በጣም ብዙ ሻካራዎች ነበሩበት። የሚናገረው አፉ እንዳመጣለት ሲሆን፣ ቀጠሮ ለማክበር እምቢተኛም ነበር። በጊዜው አይደርስም፤ በቋንቋውም የሰዋሰው ሕግን አይጠብቅም። አመታት ሲከንፉም፣ አልፎ አልፎ እየተገናኘን እንነጋገር ነበር። ጊዜ እንዳለፈ መጠንም በዚህ ሰው ሕይወት ውስጥ በጎ የሆኑ ለውጦች ብቅ ብቅ ሲሉ አየሁ። አስቦ መናገርን ጀመረ፤ ሰአት ማክበርን ተለማመደ፤ ነገሮችን በቀጠሮ ማድረስ ጀመረ፤ የሰዋሰው ሕግንም ማክበር ተማረ። እነዚያን መሻሻሎች ለማሳየት የጠየቀውን ከባድ የሆነ ሥራም ይነግረኝ ጀመረ። የልጅነት ጠባይን በመሻር መብሰል ጀመረ።

እናንተስ በብስለት ጎዳና ወደ ፊት እየገሰገሳችሁ ነውን? ኤሊይኖር ሩዝቬልት ብስለታችሁን የምትለኩበትን መመሪያ አንዲህ አስቀምጦአል፡- «ብስል ሰው ማለት ስለ ነገሮች በአንድ አቅጣጫ ብቻ የማያስብ፣ ስሜቱ እጅግ ከባድ ነውጥ ቢደርስበትም አመዛዝኖ የሚፈርድ፣ በሁሉም ሰው ዘንድና በሁሉም ነገሮች ውስጥ ጥሩና መጥፎ ሁለቱም እንዳሉ የተረዳና በትህትና የሚመላለስ፣ እንዲሁም በሕይወት የተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ በትእግስት የሚጓዝ ነው።» (Eleanor Roosevelt, *It Seems to Me* (New York: Norton, 1954).)

**ካርታችሁን ተጠቀሙ**

ካርታ ካለን፣ ልክ ረዥም ርቀት እንደሚሸፍን ማንኛውም ጉዞ፣ ካሰብንበት ቦታ ለመድረስ ቀላል ነው። ወደ ብስለት መዳረሻ ለመድረስ የሚያስፈልገን ካርታ ምን አይነት ነው? የእግዚአብሔር ጥበብ ካርታ ያስፈልገናል። በአስቸጋሪ ጊዜያት ስለመደሰት በተናገረበት አውድ ውስጥ ያዕቆብ ይህንን ካርታ ስለመጠቀም ይገልጻል። «ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል። ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና» (ያዕ. 1:5-6)።

ሰለሞን እንደዚህ አይነት ጥበብ እንዲሰጠው ፈልጎ ነበር። በንግሥና ዘመኑ መጀመሪያ፣ ትክክለኛውን ከተሳሳተው መለየት የሚችልበትን ችሎታና የእስራኤልን ሕዝብ ለመምራት የሚያስፈልገውን ጥበብ እግዚአብሔር እንዲሰጠው ጠይቆ ነበር። እግዚአብሔርም መጠይቁን ሊያሟላለት ወደደ (1 ነገ. 3)። ሰለሞን ሌሎች ብዙ ነገሮችን- ረዥም እድሜን፣ በጠላቶቹ ላይ ድል መንሳትን፣ ወይም ታላቅ ሃብትን- መጠየቅ ይችል ነበር። ነገር ግን ይህንን አላደረገም። ይልቁንም ጥበብ ለሌሎች ለሚያስፈልጉት ነገሮች ሁሉ ቁልፍ እንደሆነ በማመን እርሱን ብቻ ጠየቀ። እኛም እንደዚህ አይነቱ ጥበብ ያስፈልገናል። ፕላቶ እንዲህ ብሎ ነበር፡- «ጠቢብ ሰዎች የሚናገሩት፣ የሚናገሩት ነገር ስላላቸው ነው፤ ተላሎች ግን መናገር ስላለባቸው ብቻ ይናገራሉ።» ስንት ጊዜ ነው ዝም ማለት ሲገባን የምንናገረው፣ መናገር ደግሞ ሲገባን ዝም የምንለው? የእግዚአብሔር ጥበብ ልክ አቅጣጫን እንደሚጠቁምና የደረሳችሁበትን ቦታ እንደሚናገር መሳሪያ (GPS) ነው። በሕይወት ጠመዝማዛ መንገድ በትክክለኛው አቅጣጫ እንድንሄድ ያግዘናል። በሕይወት መከራዎች ውስጥ የእግዚአብሔርን ዓላማ ለመረዳት ከባለጸጋው አምላካችን ጥበብን ልንጠይቅ ይገባል።

የእግዚአብሔርን ጥበብ መፈለግ ትህትናን የሚያሳይ ሲሆን እግዚአብሔርንም ያከብራል። « ጌታ ሆይ፣ «ያለ አንተ ምሪትና እንክብካቤ የትኛውን መንገድ መምረጥ እንዳለብኝ እንኳን አላውቅም። ምን ማድረግ እንዳለብኝ እንድታሳየኝ እፈልጋለሁ» ማለታችን ነው። ታዲያ እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ልመና ለማክበር እንዴት ሰማይና ምድርን አያንቀሳቅስ?

**ጥርጣሬያችሁን አስወግዱ**

የእግዚአብሔር ጥበብ የሚመጣልን የጥርጣሬን መንፈስ ከውስጣችን ለማስወገድ ዋጋ ስንከፍል ነው። ያዕቆብ የሚጠራጠሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር አንዳች እንደማይቀበሉ ያስታውሰናል (ያዕ. 1፡6-7)። ከጥርጣሬ የተነሳ የጥበብ በረከት አያምልጣችሁ።

በማር. 9፡14-24 በአጋንንት የተያዘውን ልጁን እንዲያድንለት ኢየሱስን የጠየቀን አባት ታሪክ እናገኛለን። ይህ አባት ግን የኢየሱስን ልብ ያሳዘነ መጠራጠርን አሳይቶ ነበር። እርሱም የኢየሱስን ማዘን ተመልክቶ እንደዚህ አለ፡- «አምናለሁ፤ አለማመኔንም አንተ አግዝ» (ማር. 9፡24)።

ልክ ተጨንቆ እንደነበረው አባት ጥርጣሬዎቻችን እምነታችንን ያደናቅፋሉ። በልባችን ውስጥ በማመንና በአለማመን መካከል የእርስ በርስ ጦርነት ይካሄዳል። ጥርጣሬዎቻችን ምን ያህል ውስብስብ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሲ.ኤስ ሊዊስ እንዲህ ብለዋል፡- «እግዚአብሔር ለእኛ ምርጥ የሆነውን ነገር እንደሚያደርግልን የግድ ላንጠራጠር እንችላለን። ነገር ግን ያ ምርጥ የሆነው ነገር እስከሚሆንልን ድረስ ምን ያህል ስቃይ እንደሚደርስብን በማሰብ እንጨነቃለን።» (C. S. Lewis, letter to Father Peter Bide, April 29, 1959, in *Letters of C. S. Lewis*, Walter Hooper, ed. (Orlando, FL: Harcourt, 1993), 477.) መከራዎቻችንን ስንጋፈጥ ጥርጣሬዎቻችንን በመቆጣጠር፣ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ለሚሰራው ምርጥ የሆነ ስራ ራሳችንን እናዘጋጃለን።

**በመከራችሁ እንድትደሰቱ የሚያስችላችሁ ወሳኝ እርምጃዎች፡-**

- ምላሳችሁን ጠብቁ
- ቀና ማሰባችሁን ቀጥሉ
- አትታክቱ
- ዕደጉ
- ካርታችሁን ተጠቀሙ
- ጥርጣሬያችሁን አስወግዱ

# 2

# በእግዚአብሔር እቅድ ታመኑ

አንድ ቀን፣ እናቴ፣ በቤት ሰራተኝነት ትሰራ ከነበረበት ከሥራ ቦታዋ በእጇ ቦርሳ ይዛ መጣች፡፡ እኔና ወንድም እህቶቼ የሆነ ነገር አውጥታ ትሰጠናለች በማለት ከበብናት፡፡ በመጀመሪያ ያወጣችው ወፍራም የካሴት ቅጂ ነበር፡፡ ሌሎች ነገሮችን ከቦርሳው ያወጡ ዘንድ ለወንድምና እህቶቼ ትቼ ያንን ካሴት ለማጫወትና የስምንት አመት እድሜ ያላቸውን ጆሮዎቼን የሚያስደስት ሙዚቃ ይኖረው እንደሆነ ለማዳመጥ ወደ ትንሽዋ ማጫወቻችን ሮጥሁ፡፡ ከሙዚቃ ይልቅ ግን በዚያ ካሴት ላይ በ1947 እስከ 1949 ድረስ የዩናይትድ ስቴትስ ሴኔት (ምክር ቤት) ቻፕሌን የነበረውን የፒተር ማርሻል ሁለት ዜማ ያላቸው ስብከቶች አዳመጥሁ፡፡

በዚያን ጊዜ፣ ፒተር ማርሻል ማን እንደሆነ የማላውቅ ሰው ብቻ ሳልሆን፣ ምክር ቤቱ ቻፕሌን እንዳለውም እንኳ አላውቅም ነበር፡፡ አንድ ነገር ግን አውቅ ነበር፤ የማርሻል በግጥም የተሞላ ቋንቋ አእምሮዬን ተቆጣጥሮት ነበር፡፡ ካሴቱን እስኪፋፋቅ ድረስ ደጋግሜ አጫወትሁት፡፡ እነዚያንም ስብከቶች በቃሌ በመያዝ፣ የማርሻልን የስኮቲሽ የቃል አጣጣል እያስመሰልኩ ስናገር ደስ ይላቸው ለነበረው የከተማ ጓደኞች አንድ ሙሉ አንቀጽ በቃሌ እልላቸው ነበር፡፡ አንድ ቀን ፒተር ማርሻል በቆመበት የአሜሪካ ሴኔት 62ኛው ቻፕሌን ሆኜ እቆማለሁ የሚል ህልም ፈጽሞ አልነበረኝም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ለእኔ ሕይወት እቅድ ነበረው፤ ያንንም እቅዱን አስመልክቶ በቅድሚያ ጨረፍታውን አሳይቶኝ ነበር፡፡

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሕይወት እቅድ አለው፡፡ ማንም ሰው የማይዘጋውን በር ይከፍታል፡፡ በችግሮቻቸው ውስጥ መደሰትን መማር የሚችሉ ሰዎች በእግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን የማዘጋጀት ችሎታ፣ ሉዓላዊነትና እቅዶች ላይ መታመንን መማር አለባቸው፡፡ ምንም እንኳን መንገዱ በጌተሰማኔ አትክልት ቦታ ወይም ቀራኒዮ በሚባል ተራራ በኩል የሚወስድ ቢሆንም፣ ለሕይወታቸው የእግዚአብሔርን እቅድ መቀበል አለባቸው፡፡

እግዚአብሔር ለግለሰቦች ሕይወት እቅድ እንዳለው ሁሉ፣ ለመንግስታትም እቅድ አለው፡፡ ለእስራኤል ሕዝብ በባቢሎን ምርኮ ሳሉ እንኳ እቅድ ነበረው (ኤር. 29)፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከቤታቸው ርቀው በመቅበዝበዝ ላይ ቢሆኑም፣ በነብዩ ኤርሚያስ ቃላት በኩል በዚያ አትክልት እንዲተክሉ፣ ቤት እንዲሰሩ፣ እንዲያገቡ፣ ልጅ እንዲወልዱ፣ እና በግዞት ለወሰዷቸው ገዥዎቻቸውም ብልጽግና ይጸልዩ ዘንድ ተናገራቸው (ኤር. 29፡ 5-7)፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር እስራኤልን ለማበልጸግ፣ ብሩህ የሆነ የወደፊት ተስፋ ሊሰጣቸውና ምርጥ ወደ ሆነ መዳረሻም ሊያደርሳቸው ያለውን

እቅድ ገለጸ (ኤር. 29፡11-13)፡፡ አንድ ቀን ከግዞት ነጻ እንደሚወጡም ቃል ገባላቸው፡፡

ያው እግዚአብሔር እኛም በመከራዎቻችን ውስጥ ደስተኞች እንድንሆንና አስቸጋሪ ጊዜያትንም እንድናሸንፋቸው ይፈልጋል፡፡ ለእያንዳንዱ ሕይወት እቅድ አለው፤ ሁላችንንም ምርጥ ወደሆነ መዳረሻ ለማድረስ የቀየሰው እቅድ አለው፡፡

**የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ የማዘጋጀት ችሎታ ላለው እግዚአብሔር ራሳችሁን አስረክቡ**

እስራኤል፣ በግዞት ሳለ፣ የሚስፈልገውን ለሚያዘጋጅለት እግዚአብሔር እጅ መስጠትና በዚያም ላይ መደገፍን መማር ነበረበት፡፡ ብዙ የሐሰት ነብያት ከሚተነብዩት በተቃራኒ፣ በባቢሎን የሚኖራቸው ቆይታ አጭር ብቻ አልነበረም፡፡ ለሰባ አመታት በዚያ በግዞት መቆየት ነበረባቸው (ኤር. 29፡10)፡፡ ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር አትክልት እንዲተክሉ፣ ቤት እንዲሰሩ፣ እንዲያገቡና ልጆቻቸውንም እንዲያሳድጉ ነገራቸው፡፡

ካህኑ ኤሊ የሚያስፈልገውን ለሚያዘጋጅለት ብርቱ የእግዚአብሔር እጅ ራሱን መስጠትን የተማረው ልጆቹን ለመቅጣት በመዘንጋቱ ምክንያት ከመጣበት መዘዝ የተነሳ ነበር፡፡ በወጣቱ ነብይ በሳሙኤል በኩል እግዚአብሔር ፍርዱን በገለጸ ጊዜ፣ ኤሊ ለሰማው ዘግናኝ ዜና ምላሽ የሰጠው በሚከተሉት ቃላት ነበር፡- ‹ እርሱ እግዚአብሔር ነው ደስ ያሰኘውን ያድርግ፡፡› (1 ሣሙ. 3፡18)፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ለእግዚአብሔር በፍቅር የተሞላ ነገር ግን ሕመም ያለበት ዝግጅት እጅ ሰጠ፡፡ እግዚአብሔር እኛን ለመባረክ በእርግጥ የሚፈልግ አምላክ መሆኑን ስናስታውስ የእርሱን የማዘጋጀት ብቃት ለመቀበል ይቀለናል፡፡ ኦስካር ዊልዲ እንዳስተዋለው፡- «ለእኛ መራራ ፈተና የሚመስሉን ነገሮች ብዙ ጊዜ ተሸፍነው የመጡ በረከቶች ናቸው፡፡ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና ጥበብ መታመን በስቃይና በውድቀቶች ውስጥ መልካምን ነገር እንድናገኝ አቅም ይሆነናል፡፡»

**በእግዚአብሔር ርህራሄ ተማመኑ**

በእርሱ ርህራኄ ላይ የምንታመን ከሆነ ለእርሱ ዕቅድ ራሳችንን መስጠት ይቀለናል፡፡ በግዞት የነበሩት እስራኤላዊያን እግዚአብሔር ስለ እነርሱ እንደሚያስብና እርሱ ከሚሰጠው ነገር ምርጥ የሆነውን ቢያገኙ ምኞቱ እንደሆነ ተነግሯቸው ነበር (ኤር. 29፡11 -12)፡፡ እግዚአብሔር ጠላታችሁ አይደለም፡፡ እርሱ ወዳጃችሁ ነው፡፡ ለእናንተ ድጋፍ የሚሰጥን ነገር እያደረገ ነው፡፡ እንዲህ በማለትም ያውጃል፡- «እኔ ሕያው ነኝና ኃጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ኃጢአተኛው ይሞት ዘንድ አልፈቅድም፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር የእስራኤል ቤት ሆይ፥ ተመለሱ፥ ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ ስለ ምንስ ትሞታላችሁ? በላቸው።» (ሕዝ. 33፡11)፡፡ እግዚአብሔር ማዳን እንጂ ማጥፋት አይፈልግም፡፡

ዳዊት የእግዚአብሔርን አባታዊ ርህራሄ ያውቅ ነበር፡፡ እንዲህም በማለት ጻፈ፡- «ጐለመስሁ አረጀሁም ጻድቅ ሲጣል፥ ዘሩም እህል ሲለምን አላየሁም።» (መዝ. 37፡25) ፡፡ በእግዚአብሔር ኃይልና ፍቅር እንደዚህ ያለ መተማመን አላችሁ? ጻድቅ ሰው ተትቶ አይታችኋል?

ስምንተኛ ክፍል ተማሪ ሳለሁ፣ አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ስመለስ የቤተሰባችን የቤት እቃ ከመንገድ ዳር ወጥቶ ተዘርግፎ አገኘሁ፡፡ የቤት ኪራይ መክፈል ስላልቻልን ባላባቱ ከቤታችን እያስወጣን ነበር፡፡ የወደፊት እጣፈንታችን ጨላለመ፡፡ በገንዘብ አድማሳችን ላይ ከተከማቸው ጥቁር ደመና በተቃራኒ፣ በእናቴ ላይ እምነት ስለነበረኝ ብዙም ጭንቀት አልተሰማኝም፡፡ የእናትነት ርህራኄዋና ፍቅሯ በራሳችን መጠለያ የሚሆን ጣሪያን እንደሚያስገኝልን፣ በዚህ በገጠመን ፈተና ውስጥ መልካም እድል እንደምታገኝ አውቅ ነበር፡፡

በተመሳሳዩ፣ ባለጸጋው ሰማያዊ አባታችን፣ በአእምሮአችን በሙላት ሊስተዋል በማይችል ፍቅር የሚወደን፣ ለእኛ ምርጥ የሆነውን ነገር እንድናገኝ ለማድረግ ይፈልጋል፡፡ መዝ. 31፡15 እንደሚነግረን ዘመናችን በእጁ ውስጥ ነው፡፡ ኢየሱስም እንዲህ ብሏል፡- ‹እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሣር እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ፥ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ እናንተንማ ይልቁን እንዴት?› (ማቴ. 6፡30)፡፡

ጭንቀቶቻችሁ የእግዚአብሔርን አባታዊ ፍቅር እንድትጠራጠሩ አድርገዋችኋልን? ተበረታቱ፡፡እርሱ ለእናንተ የዘላለም ሕይወትን ለማስገኘት እስኪሞትላችሁ ድረስ ወዷችኋል፡፡ የሰማይን ምርጥ የሆነውን ሥጦታ ይኼውም ልጁን ሰጥቶናል፡፡ አንድ ልጁን ለእኛ ለመስጠት ካልሳሳ፣ ከሚያስፈልገን ነገር ለእኛ የሚያስቀርብን ሌላ ነገር ሊኖር ይችላልን?

**የእግዚአብሔርን ተግሳጽ ተቀበሉ**

ምንም እንኳ በእግዚአብሔር አባታዊ ርህራኄ ላይ በመታመን መደሰት ብንችልም፣ የእርሱንም ተግሳጽ ለመቀበል ዝግጁዎች መሆን አለብን፡፡ መልካም ወላጆች ልጆቻቸውን በፍቅር ይቀጣሉ፡፡ በራዕ. 3፡19፣ ሞትን አሸንፎ የተነሳው ክርስቶስ እንዲህ ይላል፡- «የምወዳቸውን እቀጣቸዋለሁ፡፡» እስራኤላውያን ወደ ባቢሎን በግዞት መወሰዳቸው የእግዚአብሔ ተግሳጽ አካል ነበር፡፡ ህዝቡም ስለ እነርሱ ከሚገደው አካል የተሰጠ እርምት እንደሆነ አድርጎ ሊቀበለው ይገባ ነበር፡፡

ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ካመነዘረ በኋላ፣ ቤርሳቤህ ያረገዘችው ልጅ እንደሚሞት እግዚአብሔር ነገረው ( 2 ሳሙ. 12፡14)፡፡ ዳዊት ጾመ ጸለየ፤ ነገር ግን ልጁ ሞተ (2 ሳሙ. 12፡14-23)፡፡ ዳዊት ልጁ እንደሞተ በሰማ ጊዜ፣ ተነሳ፣ ታጠበ፣ በላም፡፡ አገልጋዮቹም ዳዊት የልጁን ሞት እንዲህ በእርጋታ እንዴት ሊቀበለው እንደቻለ ተገረሙ፡፡ ከዚያም ዳዊት እንዲህ አለ፡- «እርሱም፡- ‹ሕፃኑ ሕያው ሳለ። እግዚአብሔር ይምረኝ፥ ሕፃኑም በሕይወት ይኖር እንደ ሆነ ማን ያውቃል? ብዬ ጾምሁ አለቀስሁም። አሁን ግን ሞቶአል የምጾመው ስለ ምንድር ነው? በውኑ እንግዲህ እመልሰው ዘንድ ይቻለኛልን? እኔ ወደ እርሱ እኼዳለሁ እንጂ እርሱ ወደ እኔ አይመለስም አለ።»

ከእግዚአብሔር ተግሳጽ መቀበልን ተምራችኋል? ከሰማይ የሆነ ቁንጥጫን እግዚአብሔር እንዲቀጣችሁ ያነሳሳው ፍቅሩ እንደሆነ በማስተዋል ለመቀበል ትችላላችሁ?

**በተስፋ ኑሩ**

ምን ያህል ተስፈኛ ናችሁ? በግዞት የነበሩት እስራኤላውያን እግዚአብሔር ፍጻሜና ተስፋን ሊሰጣቸው እንደሚፈልግ ተነግሯቸው ነበር (ኤር. 29፡11)፡፡ ተመሳሳዩን ለእናንተም ሊያደርግላችሁ ይፈልጋል፡፡ይህም በተስፋ እንድትኖሩ፣ እውነት በሂደት እንደሚያሸንፍ በማመን ችግሮቻችሁን ሁሉ እንድትጋፈጡ ሊያደፋፍራችሁ ይገባል፡፡ በእርግጥም፣ መጽሐፍ ቅዱስ «በተስፋ ድናችኋል» ይላል (ሮሜ. 8፡24)፡፡

ተስፋ በክፉ ቀናት አእምሯችሁ በትክክል እንዲያስብ ይረዳችኋል፡፡ ዳዊት እንዲህ ሲል ጮኸ፡- «የእግዚአብሔርን ቸርነት በሕያዋን ምድር አይ ዘንድ አምናለሁ።» (መዝ. 27፡13፡፡) የእግዚአብሔር እቅድ እንደሚያሸንፍ ታምናላችሁ? እንግዲያውስ በተስፋ ነው የምትኖሩት ማለት ነው፡፡

ኤሚሊ ዲክንሶን የተባሉት ገጣሚ እንዲህ በማለት ተናግረዋል፡- «ተስፋ በልብ ጎጆ ውስጥ የሚቀመጥ ወፍ ሲሆን ያለ አንዳች ቃላት ዜማውን የሚያቀነቅንና ማቆሚያም የሌለው ነው፡፡» በተስፋ የሚኖሩ ሰዎች ቃል ባይኖረውም እንኳን በልባቸው ዜማ ይኖራቸዋል፡፡ የሚያደርገውን ነገር እንኳን ባይገባቸው በእግዚአብሔር ግን ይታመናሉ፡፡

**ከሰዎች መላምት ይልቅ የእግዚአብሔርን መገለጥ እመኑ**

በግዞት የነበሩት እስራኤላውያን የሐሰተኛ ነብያትን መላምቶች ሰምተው ነበር (ኤር. 29፡ 8-9)፡፡ ለእግዚአብሔር ትንቢት እንናገራለን በሚሉ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ባልሆኑ ሰዎች የበለጠ የመከራቸው ጊዜ ከብዶባቸው ነበር፡፡ እነዚህ ሃሰተኛ ነብያት የእስራኤል የመከራ ጊዜ አጭር እንደሚሆን፣ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲቀበሉ ይገዳደራቸው በነበረው በእውነተኛው ነብይ በኤርሚያስ የመጣውን የእግዚአብሔርን ቃል በመቃረን ይተነብዩ ነበር፡፡

የሕይወትን ግድድሮሽ ስትጋፈጡ፣ ብዙ አዋቂ ነን ባዮች ስኬት የምታገኙበት የታመነ መንገድ ይኼ ነው በማለት ሊመሯችሁ ይፈልጋሉ፡፡ አንዳንዶች ገንዘብንና ስልጣንን እንድታሳዱ ይነግሯችኋል፤ ሌሎች ደግሞ እውነተኛ ደስታ ያለው ከሰዎች ጋር በምታደርጉት ግንኙነት ነው ይሏችኋል፡፡ አሁንም ሌሎች በተፈጥሮአዊ ስሜታችሁ የፈለጋችሁትን ነገር ስታደርጉ የመታቀብ ስሜት እንዳይሰማችሁ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይል እንዳለ የምታምኑትን እምነት እንድትተው አሳብ ያቀርቡላችኋል፡፡

እግዚአብሔርን በማይፈሩ ሰዎች ምክር አትሂዱ (መዝ. 1፡1)፣ ይልቁንም ምሪትን ፍለጋ የእግዚአብሔርን ቃል ተመልከቱ፡፡ በ1ነገ 13 የንጉሥ ኢዮርብአምን የጣኦት አምልኮ ድርጊት እንዲያወግዝ ወደ እስራኤል ሰሜናዊው መንግስት ተልኮ ስለነበረ እውነተኛ ነብይ እናነባለን፡፡ እግዚአብሔርም ነብዩን ከማንም ጋር እንዳይበላ ነገር ግን ፈጥኖ ወደቤቱ እንዲመለስ ነግሮት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሐሰተኛው ነብይ እውነተኛውን ነብይ እግዚአብሔር የተለየ መልእክት እንደሰጠው ይህም እውነተኛ ነብይ ወደ ሐሰተኛው ቤት ገብቶ ከእርሱ ጋር ሕብረት እዲያደርግ እንደሆነ አሳመነው፡፡ እውነተኛውም ነብይ እግዚአብሔር በቀጥታ ለእርሱ የነገረውን የእግዚአብሔርን አመራር ተላለፈ፤ ለሐሰተኛው

ነብይም እሺ አለ፡፡ በውጤቱም፣ እግዚአብሔር ለእውነተኛው ነብይ በሐሰተኛው ነብይ በኩል የፍርድን መልእክት ላከ፡፡ ይህ ታሪክ ከምድራዊ ድምጾች በላይ እግዚአብሔር ቃል ላይ መታመን ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ያስተምረናል፡፡

ማንን ትሰማላችሁ? ምሪታችሁንስ ከየት ትቀበላላችሁ? ለድነት በሚያበቃ ጥበብ የሚሞሏችሁን ቅዱሳት መጻሕፍት ያዙ፡፡ «ሰው ሁሉ ውሸተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን። » (ሮሜ. 3፡4)፡፡

**እግዚአብሔርን በብርቱ ፈልጉት**

በባቢሎን ምርኮ የነበሩትን እስራኤላውያንን ችግራቸውን እንዴት ማሸነፍ እንዳለባቸው እግዚአብሔር እንዲህ ብሏቸው ነበር፡- «ትሹኛላችሁ፥ በፍጹም ልባችሁም ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ።» (ኤር. 29፡13)፡፡ በብርቱ መፈለግ ወሳኝ ነው፡፡ ያዕ. 5፡16 ይህንን ያጎላዋል፡- «የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።» በማቴ. 7፡7 ላይ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዲህ በማለት ቃል ገብቷል፡- ‹ፈልጉ፤ ታገኛላችሁ›፡፡ በመከራ ሸለቆ ውስጥ ስታልፉ፣ እግዚአብሔርን ከልባችሁ ፈልጉት፡፡ ጆን ኬትስ አንድ ጊዜ እንዲህ የሚል አሳብ ሰጥተዋል፡- «የአንድ የጥበብ ስራ ትልቅነቱ በጥልቀቱ ውስጥ ነው፤ ይህም ግድድሮሾቹን ሁሉ ያተንናቸዋል፡፡» የመከራ ንፋስ ግድድሮሽን ስትጋፈጡ፣ እግዚአብሔርን በጥልቀት መፈለጋችሁ ያተንናቸዋል፡፡

**ፍሬያማነታችሁ ይቀጥል**

በግዞት የነበሩት እስራኤላውያን ምርታማ እንዲሆኑ ተመክረው ነበር፤ ያንንም አድርገውታል፡፡ እንዲተክሉ፣ እንዲገነቡ፣ እንዲያገቡ እንዲወልዱ ተነግሯቸው ነበር፡፡ ብዙዎችም ልክ እንደ ዳንኤልና እንደ ጓደኞቹ የመንግስት አስተዳዳሪዎች በመሆን የእነርሱ የትንቢት ቃል መንግስቱን እየጠበቀ በግዞት አገር አብበው ነበር፡፡ እግዚአብሔር በአስቸጋሪ ጊዜዎቻችንም ሳይቀር ፍሬያማዎች እንድንሆን ይፈልጋል፡፡ በመጀመሪያ ለሰው ልጅ የሰጠው ትእዛዝ ‹ብዙ ተባዙ› የሚል ነበር (ዘፍ. 1፡28)፡፡ ኢየሱስም ፍሬያማ ስለመሆን ሲናገር እንዲህ አለ፡- ‹በፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ› (ማቴ. 7፡16)፡፡

ኢንቨስተር ዋረን ባፌት እንዲህ በማለት ያስታውሰናል፤ ‹እጅግ በአደገኛ ሁኔታ በሚያፈስ ጀልባ ላይ ራስህን ብታገኘው፣ የሚያፈስበትን ቀዳዳ በመለጠፍ ከሚጠፋ ጉልበት ይልቅ ጀልባውን መቀየር ይሻላል› (http://investing-school.com/history/52-must-read-quotes-from-legendary-investorwarren-buffett.) በሌላ አነጋገር፣ ሊቀድሙ የሚገባቸውን ነገሮች በማስቀደም ፍሬያማ ጥረት በማድረግ ላይ አተኩሩ ማለት ነው፡፡

በመከራ ወራቶቻችሁ ውስጥ ስታልፉ፣ ፍሬያማ እንደሆናችሁ ትቆያላችሁ? በስሜት እስር ቤት ውስጥ ከመውደቅ ፈተና ጋር ስትፋለሙ፣ እግዚአብሔርን የሚያከብር ምርት ማምረታችሁን ትቀጥላላችሁ?

**ለጠላቶቻችሁ ብልጽግና ጸልዩ**

በግዞት የተወሰዱት እስራኤላውያን ለገዥዎቻቸው ብልጽግና እንዲጸልዩም ተነግሯቸው ነበር፡፡ (ኤር. 29፡7)፡፡ ይህንን ማድረግ እንግዳ ነገር ሊመስለን ይችላል፡፡ ሕይወታችሁ እንዲመሰቃቀልና እንዲታሰር ያደረጉ ሰዎች ደህና እንዲሆኑ ለምን ትፈልጋላችሁ? በእግዚአብሔር ሁሉን የማዘጋጀት ችሎታ ላይ የሚኖረን መታመን የይቅርታ መንፈስ እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ ለጀነራል ንዕማን ሚስት ትሰራ የነበረችው ያቺ እስራኤላዊት ልጃገረድ እንደዚህ ያለ መንፈስ ነበራት (2 ነገ. 5)፡፡ በጦርነት የተማረከች እስረኛም ብትሆን፣ በጣም ክፉ በሆነ ለምጽ በሽታ ተጠቅቶ ለነበረው ለገዢዋ (ለአሳሪዋ) ርህራኄ ነበራት፡፡ ጌታዋን ሊያድን የሚችል ኃይል ያለው ኤልሳዕን ታውቅ ነበር፡፡ እናም ይህንን ለራሷ ምስጢር አድርጋ አልያዘችውም፡፡ ለእመቤቷም ንዕማን እንዴት ሊፈወስ እንደሚችል ነገረቻት፡፡ በዚህም ለገዢዋ ብልጽግና ጸለየች፤ ሰራችም፡፡

ጠላቶቻችሁን የምታስተናግዱቸው እንዴት ነው? ምን ያህል ትጸልዩላቸዋላችሁ? ኢየሱስ እንዲህ በማለት ይገዳደረናል፡- «ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ የሚረግሟችሁን መርቁ፤ ለሚጠሏችሁ መልካም አድርጉ፤ ለሚያሳድዷችሁ ጸልዩ፡፡» (ማቴ. 5፡44)፡፡ ሊጎዷችሁ ለሚፈልጉ ሰዎች መጸለይን ብትማሩ፣ እግዚአብሔርን ታከብራላችሁ፤ እርሱም መታዘዛችሁን ይሸልማል፡፡

**በእግዚአብሔር እቅድ እንድትታመኑ የሚረዳችሁ ወሳኝ እርምጃዎች**

- የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ የማዘጋጀት ችሎታ ላለው እግዚአብሔር ራሳችሁን አስረክቡ፡፡
- በእግዚአብሔር ርህራኄ ታመኑ፡፡
- የእግዚአብሔርን ተግሳጽ ተቀበሉ፡፡
- በተስፋ ኑሩ፡፡
- ከሰው መላምት ይልቅ የእግዚአብሔርን መገለጥ ተቀበሉ፡፡
- እግዚአብሔርን በብርቱ ፈልጉ፡፡
- ፍሬያማነታችሁ ይቀጥል፡፡
- ለጠላቶቻችሁ ብልጽግና ጸልዩ፡፡

# 3

# የጨለማ ቀናትን ግድድሮሾች ተጋፈጡ

መከራችሁ ያመጣባችሁ የጨለማ ቀኖች መቼ እንደሚያልቁ ግራ በመጋባት አስባችሁ ታውቃላችሁ? በአንድ ወቅት የነበራችሁ ተስፋችሁ ሁሉ ተሟጦ እንዳለቀ ተሰምቷችሁስ ያውቃል? አንዱ መከራ በከባድ ፍጥነት ሌላውን እየተከተለ ከሚሰራው ሰንሰለት የተነሳ ተስፋ መቁረጥ ተሰምቶአችሁ ያውቃል? ከእነዚህ ጥያቄዎች ለማንኛቸውም የምትሰጡት መልስ አዎ የሚል ከሆነ፣ በሕይወታችሁ የጨለማ ወቅቶችም ቢሆን በረከት ልታገኙ እንደምትችሉ ታምኑ ዘንድ እንዳደፋፍራችሁ ፍቀዱልኝ፡፡ የበረከት ጎዳና የሚጀምረው በሕይወታችሁ ላይ ያላችሁን ሥልጣን ለእግዚአብሔር አሳልፋችሁ ስትሰጡ፣ የእውነተኛን ጸሎት ባሕርይ ስትማሩ ነው፡፡ እርሱን በይበልጥ መውደድ እየተማራችሁ ስትሄዱ፣ አፍቃሪ የሰማይ አባታችሁ ጨለማችሁን እንዲያስወግድላችሁ ተስፋ ልታደርጉት ትችላላችሁ፡፡ ያን ጊዜም ዘና ማለትና እርሱ ስለ እናንተ ሕይወት ባለው እቅድ መደሰት ትችላላችሁ፡፡

**ትክክለኛን አመለካከት አዳብሩ**

ለጨለማ ቀናት ለመዘጋጀት፣ በሕይወት ውስጥ ደጋግመው ስለሚከሰቱት መከራዎች ትክክለኛ አመለካከትን ማዳበር ያስፈልገናል፡፡ መከራና ጨለማ የሰብአዊነት ክፍል ናቸው፤ ስለዚህም አትረበሹ ወይም በተደጋጋሚ በሚከሰቱት አስቸጋሪ ወቅቶች ምክንያት ተስፋ አትቁረጡ፡፡ ጨለማ ቀናት የሕይወት ተፈጥሮአዊ አካል ናቸው፡፡

የእምነት ጀግኖች ለአስርት አመታት ከእግዚአብሔር ጋር አካሄዳቸውን ካደረጉም በኋላ እንኳ፣ መከራ ደርሶባቸዋል፡፡ ታማኝና ፍጹም የተባለው ኢዮብ በመጨረሻ እንዲህ በማለት ነበር የደመደመው፡- ‹‹ከሴት የተወለደ ሰው የሕይወቱ ዘመን ጥቂት ቀን ነው፥ መከራም ይሞላዋል።›› (ኢዮብ 14፡1)፡፡ ሙሴ በሕይወቱ የመጨረሻ ጊዜያት በእስራኤላውያን ማጉረምረም ተሰናክሎ፣ እግዚአብሔር እንዲናገረው ብቻ ያዘዘውን አለት በቁጣ ውስጥ ሆኖ ባለመታዘዝ መታው (ዘኁ. 20)፡፡ ዳንኤል ቢያንስ ሰማንያ አመቱ አካባቢ ወደ አንበሳ ጉድጓድ ተጣለ (ዳን. 6)፡፡

መከራን በተመለከተ ትክክለኛን አመለካከት በማዳበር፣ በመንገዳችሁ ላይ በሚገጥሟችሁ ክፉ ነገሮች ሁሉ ላይ እግዚአብሔር ገደብ እንዳስቀመጠባቸው ትዝ ይላችኋል፡፡ ይህ ደግሞ የሕይወትን አስቸጋሪ ሁኔታዎች በድፍረት እንድትጋፈጡ ሊያደርጋችሁ ይገባል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር አስቀድሞ የችግራችሁን ክብደት

መጥኖ፣ ልትቋቋሙት እንደምትችሉ አምኖአልና፡፡ ዲያቢሎስ ኢዮብን ለማሰቃየት በፈለገ ጊዜ፣ ለዚህ ፈተና ድንበር ያዘጋጀለት እግዚአብሔር ነበር(ኢዮብ 1)፡፡ ለመቋቋም ከምትችሉት ከአቅማችሁ በላይ ትፈተኑ ዘንድ አይፈቅድም (1 ቆሮ. 10፡13)፡፡

ስለ ችግሮቻችን ትክክለኛ የሆነ አመለካከት ሲኖረን፣ መከራዎቻችንን እግዚአብሔር ኃይሉን ለመግለጽና የበለጠ የእርሱን ጥንካሬ ለማሳየት የሚሰጠን እድሎች አድርገን እንመለከታቸዋለን፡፡ እስቲ አስቡት፡- በሕይወታችሁ በገጠማችሁ ካባባድ ሁኔታዎች ውስጥ እንድታልፉ ባይፈቅድ ኖሮ፣ የእግዚአብሔርን የኃይሉን ታላቅነት ለማወቅ ባልቻላችሁ ነበር፡፡ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የአልአዛር መሞት ለእነርሱ እምነት እንደሚሆንላቸው (ዮሐ. 11) እንደዚሁም ዕውር ሆኖ የተወለደው ሰው የእግዚአብሔር ስራ በእርሱ ሕይወት እንዲገለጥ በጨለማ እንደኖረ ነገራቸው (ዮሐ 9)፡፡

እኛ የምናልፍበት ስቃይ ምንም አይነት ቢሆን፣ ሌሎች ሰዎችም ተመሳሳይ ሸክም እንዳለባቸው ስናስታውስ በዚህ የስቃይ ሕብረት መጽናናት እንችላለን፡፡ የኤልያስን «እኔ ብቻ ቀረሁ» የሚለውን አመለካከት እናስወግድ (1 ነገ. 19)፡፡ እርሱ ተስፋ በመቁረጥ እያለፈ ባለበት መከራ ውስጥ የሚያልፈው እርሱ ብቻ እንደሆነ በስህተት አሰበ፡፡ ለእግዚአብሔርም እንደዚህ አለ፡- «ለበዓል ያልሰገድሁ እኔ ብቻ ቀረሁ፡፡» ለስቃይ፣ ለመከራና ወይም ለስደት እናንተ ብቻ እንደተመረጣችሁ አድርጋችሁ በስህተት አታስቡ፡፡ የደረሰባችሁ ፈተና ምንም ቢሆን ምን በሰው ሁሉ ላይ የሚደርስ ነው (1 ቆሮ. 10፡ 13)፡፡

አንዳንድ የምንጋፈጣቸው ግድድሮሾች ውጫዊ ናቸው፤ ለምሳሌ፣ ጠላቶች፣ ጥቃቶች፣ ስደቶችና የመሳሰሉት፡፡ ነገር ግን ሌሎቹ ደግሞ ወደ ልባችን ሰርጾው በመግባት የሚቆጣጠሩን ናቸው፡፡ ያዕቆብ የምንፈተነው በገዛ ራሳችን ምኞት ስንሳብ እንደሆነ ይነግረናል (ያዕ. 1፡ 14)፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ስለ ሁሉም ነገር ዲያቢሎስን መወንጀላችሁን አቁሙ፡፡ «በአመጻ ተጸንሰን በኃጢአት እንደተወለድን» (መዝ. 51፡5) ፍጥረታት፣ አንዳንዶቹ መከራዎቻችን በውስጣችን ሥር የሰደዱ ናቸው፡፡ ፌይደሩስ (*Phaedrus)* በተባለው ጽሁፉ ፕላቶ «የሰው ልጅ ነፍስ በሁለት ክንፍ ባላቸው ፈረሶች የምትጎተት ሠረገላ ናት፤ አንደኛው መልካም ሲሆን ሌላው ደግሞ ክፉ ነው፡፡ ሁለቱም ደግሞ ነፍስን ይዘው ለመሄድ የሚፈልጉት ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ ነው» በማለት ጽፎአል፡፡ በሌላ አነጋገር፣ በሁላችንም ውስጥ የእርስ በርስ ጦርነት እየተካሄደ ነው ማለት ነው፡፡

ችግርን በተመለከተ ትክክለኛውን አመለካከት ማዳበር መከራችንን ወደ ማድነቅ ይመራናል፡፡ መከራዎች በትእቢት የተወጠረውን ልባችንን በማስተንፈስና በእግዚአብሔር ላይ በእጅጉ እንድንደገፍ በማድረግ ራሳችንን እንድናዋርድ(ትህትናን እንድንላበስ) ይረዱናል፡፡ ቀደም ብለን የሰራናቸውን ስህተቶች ያስታውሱናል፤ የተሻለ ለመስራት ጠንክር አድርገን ወደ መወሰንም ይመሩናል፡፡ ለሌሎች ሰዎች እንድናዝን ያደርጉናል፡፡ በሌሎች ላይ ፍርድን ለመስጠት የሚቸኩልን ድንቁርና ወደ ቆሻሻ መጣያ አሽቀንጥረን በመጣል፣ የሌሎችን ስሜት መረዳትና ለሌሎችም መራራት እንድንችል ይረዱናል፡፡ ጴጥሮስ በሉቃስ 22 ላይ ኢየሱስን ሦስት ጊዜ ከካደ በኋላ በዮሐ. 21 ላይ ከመካዱ በፊት ከነበረው በበለጠ ራሱን ዝቅ አድርጎና በኢየሱስም ላይ ተደግፎ ነበር፡፡

ካለፈበት የመከራ ጊዜ ትህትናን አትርፎ ወጣ፡፡

### ሥልጣናችሁን አስረክቡ

ችግሮቻችሁን በተመለከተ ትክክለኛውን አመለካከት ካዳበራችሁ በኋላ፣ በሕይወታችሁ ላይ ያላችሁን ስልጣን በመተዉ ጨለማ ቀኖቻችሁን ተጋፈጡ፡፡ ኢየሱስ «ሕይወታቸውን ሊያድኑ የሚፈልጉ ያጠፏታል፣ ነገር ግን ሊያጠፏት የሚፈልጉ ያገኟታል» በማለት በተናገረ ጊዜ ይህንን መርሆ ጠቀም አድርጎአል (ማቴ. 16፡ 25)፡፡ እግዚአብሔር አካሄዳችንን እንዲመራና ጎዳናችንንም እንዲያቀናልን በእርሱ እንድታመን ይፈልጋል፡፡ ለዚህ ነው በራሳችን ማስተዋል እንዳንደገፍ (ምሳ. 3፡5-6)፣ ነገር ግን መንገዳችንን ሁሉ እርሱ እንዲያበጅልን ለእርሱ እንድንሰጠው የተመከርነው፡፡ ሮሜ. 8 ከዚሁ ጭብጥ ጋር በመስማማት፣ ምን እንደምንጸልይና እንዴት እንምንጸልይ እንደማናውቅ ይነግረንና፣ «ታዲያ ለምን ስለ እኛ መማለድን ለሚያውቅበት ለመንፈስ ቅዱስ ራሳችንን አሳልፈን አንሰጠውም?» ይለናል፡፡ ለእግዚአብሔር ስልጣንን አሳልፎ አለመስጠት ሞኝነት ነው፡፡ ምክንያቱም እርሱ የወደፊቱን ያውቃል፤ እኛ ግን አንዳች አናውቅም፡፡ ቀኑ እንኳን ምን ይዞብን እንደሚመጣ አናውቅም(ምሳ.27፡1)፤ እግዚአብሔር ግን ያውቃል፡፡ ነገ የሚሆነውን የማወቅ ችሎታ ቢኖረን እንኳን፣ ለእኛና ለምንወዳቸው ሰዎች ምርጥ የሆነውን ነገር ለይተን አናውቅም፡፡

እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ አይሆንም ሲለን እጅግ ታድለናል፡፡ አንድ ጊዜ እግዚአብሔርን በሳምንት ገቢዬን 100 ዶላር ያደርግልኝ ዘንድ ለምኜው ነበር፡፡ ከዚያም ቀጥዬ እንዲህ አልኩት፡፡ «ይህንን ካደረግኽልኝ፣ ሌላ ምንም ነገር በሕይወቴ አልጠይቅህም፡፡» እግዚአብሔር ለዚህ ጸሎቴ አይሆንም የሚል መልስ ስለሰጠኝ ደስተኛ ነኝ፡፡ እግዚአብሔር ያንን ጸሎቴን መልሶ ገቢዬን በዚያው መጠን ብቻ ገድቦት ቀርቶ ቢሆን ኖሮ አሁን እጅግ በችግር ውስጥ ከሚወድቁ ሰዎች መካከል አንዱ እሆን ነበር፡፡

### የእውነተኛ ጸሎትን ምንነት አስተውሉ

ስለ ጸሎት ምን ያህል ጉጉት አላችሁ? እንደ ታላቅ እድል ትቆጥሩታላችሁ? እስቲ ምን ያህል ግሩም ነገር እንደሆነ አስቡ፡፡ ወደ እግዚአብሔር ዙፋን መቅረብ የሚያስችለን ነው፡፡ ከፈጣሪ ጋር በግላችን ለመነጋገር እድል የሚሰጠን ነው፡፡ ከስልጣናትና ከኃይላት ተጽእኖ ነጻ ሊያወጣን የሚያስችለንን ሁሉን ቻይ የሆነውን የእርሱን ክንድ የምንደገፍበት ነው፡፡ ይህንን ታላቅ ባርኮት ትልቅ ዋጋ ትሰጡታላችሁን?

ይህ እንዲህ ከሆነ፣ የጸሎት ተማሪዎች እንድትሆኑ አደፋፍራችኋለሁ፡፡ ሲ. ኤች ዶድ አንድ ጊዜ «ጸሎት በእኛ ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኛ በላይ ካለው እግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንዲያደርግ ያደርገዋል» በማለት ተናግሮ ነበር፡፡ ሮሜ. 8፡26 ይህንኑ ተመሳሳይ ሃሳብ እንዲህ በማለት ያንጸባርቃል፡- « እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤ እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅምና፥ ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤» በእርግጥም በበላያችን ካለው እግዚአብሔር ጋር የሚያገናኘን በውስጣችን ያለ የእግዚአብሔር መንፈስ አለን፡፡

መንፈስ ቅዱስ ስለ እናንተ እንዲጸልይላችሁ ትታመኑታላችሁ? ያንን ስታደርጉ፣ «ጌታ ሆይ፣ ካንተ በበለጠ በራሴ እውቀት አልታመንምና፣ አንተ የወደድከው በሕይወቴ ይሁን» በማለት ለእግዚአብሔር ጥበብ እጅ ትሰጣላችሁ፡፡ እንዲህ በማለት መዝሙር ከጻፈው ሰው ጋር ትተባበራላችሁ፣ «እኔ ሸክላ ነኝ፣ አንተ ሰሪ ነህ» እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለእናንተ እንዲጸልይላችሁ ስትታመኑት፣ የነገሩ ውጤት ምንም ቢሆን ለእርሱ የፍቅር እንክብካቤ ራሳችሁን አሳልፋችሁ መስጠታችሁን በማሳየት እርሱን ታከብሩታላችሁ፡፡ የእውነተኛ ጸሎት ባሕርይ ይህ ነው፤ እግዚአብሔርን ለመለወጥ ሳይሆን፣ እኔንና እናንተን ለመቀየር፣ ከዋክብትን በሕዋ ላይ ላንጠለጠለ ለእርሱ ፈቃድ ራሳችንን እንድንሰጥ የሚያደርገን ነው፡፡

## እግዚአብሔር የትላንትና ጨለማ ቀኖቻችሁን እንዲለውጥላችሁ ፍቀዱለት

እግዚአብሔር ያለፉትን ጨለማ ቀኖቻችንን ሊለውጣቸው ቃል ገብቷል፡፡ በሮሜ. 8፡28 ላይ እንዲህ ይላል፡- «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።» እንዴት ያለ አስደቀናቂ ተስፋ ነው! እግዚአብሔር ከውስጡ መልካም ነገር ሊያወጣበት የማይችል በእኛ ላይ የሚደርስብን አንዳች ነገር የለም፡፡ ከሕመማችን፣ ከስራ ማጣታችን፣ ከሃፍረታችን፣ ከበደለኛነት ስሜታችንና ከሐዘናችን በረከቶችን ማውጣት ይችላል፡፡ ትላትን ያጨለመባችሁ ጨለማ ምንም ቢሆን ምን ዛሬ ሊነሳላችሁ ይችላል፡፡ ምናልባትም መዝ. 27፡1 ይህንን አስመልክቶ ሳይሆን አይቀርም እንዲህ የሚናገረው፡- «እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው የሚያስፈራኝ ማን ነው? እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው የሚያስደነግጠኝ ማን ነው?» እግዚአብሔር ብርሃናችን ነው፡፡ እርሱ በሚመራን መንገድ ላይ ብርሃኑን ያበራልናል፡፡ ከዚያም ወደ ደልዳላ ሜዳ ያደርሰንና ስቃያችንን ሁሉ በእርሱ እይታ እንድንመለከታቸው ያደርገናል፡፡ ያን ጊዜ የመከራችንን በረከት እንመለከታለን፤ እኛ ተዘጋጋ ባልንበት ሁኔታ ውስጥ የሚመጣውን የእግዚአብሔርን በረከት እንቀምሳለን፡፡ እኛም ከዮሴፍ ጋር እንዲህ ለማለት እንችላለን፡፡ «እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው።» (ዘፍ. 50፡ 20)፡፡

ጀምስ ራስል ሎውል እግዚአብሔር ከክፋት መልካም ነገርን ሊያወጣ እንደሚችል ተረድቶ ነበር፡፡ «እውነት ሁልጊዜ በመሰቀያ ሥፍራ ላይ አለች፤ ሃሰት ደግሞ በዙፋን ላይ ዘላለም ትቀመጣች፤ ነገር ግን የወደፊቱን ነገር የሚወስነው እውነት ያለችበት የስቅላት ስፍራ ነው፡፡ ከማናውቀው ጨለማ በስተጀርባ በጥላው ውስጥ እግዚአብሔር ይቆማል፤ እኛንም ሁላችንን ይመለከተናል» (James Russell Lowell, “The Present Crisis,” *Yale Book of American Verse*, Thomas R. Lounsbury, ed. (New Haven: Yale University, 1912), 128.) ሎወል እያለ ያለው የእግዚአብሔር አለማ በምንም አይነት አይገደብም የሚለውን ሐሳብ ነው፡፡ ልክ ዛሬ እንደነጋው ማለዳ ፣ ይህም ሊከለከል አይችልም፡፡ በመጨረሻ የሚያሸንፈው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡

## አፍቃሪውን እግዚአብሔርን በሕይወታችሁ አስቀድሙት

የእግዚአብሔር አላማ በሕይወታችሁ በመጨረሻ እንደሚያሸንፍ እርግጠኛ ለመሆን፣ እርሱን መውደድ ግንባር ቀደም ተግባራችሁ ይሁን፡፡ ሮሜ. 8፡28 የእግዚአብሔር በጎ

አላማ ተፈጻሚ የሚሆነው እርሱን በሚወዱት ሕይወት እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ይህም ማለት በእግዚአብሔር አላማ የሚጸኑት ከእርሱ ጋር በቅድሚያ ሕብረት ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ በእርሱ አላማ ከመጽናታቸውም የተነሳ፣ ይህ የእርሱ አላማ በመጨረሻ ያሸንፋል፡፡ ዮሴፍ ለእግዚአብሔር የነበረውን ፍቅር ለጶጢፋራ ሚስት እንደዚህ በማለት በተናገረ ጊዜ አሳይቷል፡- «በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?» (ዘፍ. 39፡9)፡፡ በዚህ ተቃውሞው መጽናቱ ዮሴፍን ወደ እስርቤት እንዲጣል አደረገው፤ በዚያም ቅን ፍርድን በመጠባበቅ አመታትን አሳለፈ፡፡ እግዚአብሔር ግን መንቀሳቀስ ሲጀምር፣ ከሃያ አራት ሰአት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ነበር ከእስር ቤት ወደ ጠቅላይ ገዢነት የተሻገረው፡፡ እግዚአብሔር ከእስር ቤት ወደ ከፍተኛ ስልጣን በቀጥታ ሊወስዳችሁ ይችላል፡፡

እግዚአብሔርን መውደድ በሕይወታችሁ ግንባር ቀደም ስፍራን የሚይዝ ጉዳይ ነውን? ይህም ከእርሱ ጋር ወዳጅነት መፍጠር ሲሆን፣ በጸሎትና ቃሉን በማጥናት በእርሱም መገኘት ውስጥ በደስታ በመገኘት የሚመጣ ነው፡፡ ይህንን ስታደርጉ፣ እግዚአብሔርም እጅግ አስከፊ የሚባለውን ችግራችሁን ወደ ምድረበዳ ገነትነት በመለወጥ ጨለማ ቀናት የሚያመጡባችሁን ግድድሮሾች ለመጋፈጥ የምትችሉበትን ብርታት የሚያስታጥቃችሁ መሆኑን ትረዳላችሁ፡፡

## የጨለማ ቀናትን ግድድሮሾች ለመጋፈጥ የሚያግዟችሁ ወሳኝ እርምጃዎች

- ትክክለኛውን አመለካከት አዳብሩ
- ሥልጣናችሁን አስረክቡ
- የእውነተኛ ጸሎትን ምንነት አስተውሉ
- እግዚአብሔር የትላንትና ጨለማ ቀኖቻችሁን እንዲለውጥላችሁ ፍቀዱለት
- አፍቃሪውን እግዚአብሔርን በሕይወታችሁ አስቀድሙ

# 4

# የፈረሱ ቅጥሮችን ጠግኑ

ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር እንደገና የገነባበት ታሪክ መከራ ወደ በረከት ከተለወጠባቸው ታላላቅ ምሳሌዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ ታላቅ መሪ ሌሎች አንድ ክፍለ ዘመን የሚጠጋ ጊዜ የፈጀ ሙከራ አድርገው ያልተሳካላቸውን ሥራ እርሱ ግን በሃምሳ ሁለት ቀናት ጨረሰው፡፡ ይህ አስገራሚ አይደለምን? ታሪኩ እንደዚህ ነው፡፡

ኢየሩሳሌምና መቅደሷ በ586 ዓ.ዓ. ተቃጥለው ተደመሰሱ (2 ነገ. 25)፡፡ ጠላት የኢየሩሌምን ቅጥሮች አፍርሶ ነበርና ይህም ከባድ ችግሮችን አስከትሎ ነበር፡፡ ያለ ቅጥር፣ ሕዝቡ ለጥቃት የተጋለጠ ሲሆን፣ ከጠላቶቻቸውም ስጋት ነጻነት ሊሰማቸው አይችሉም፡፡

ለአስርት አመታት፣ የኢየሩሌምን ቅጥር እንደገና ለመገንባት ሦስት ታላላቅ ጥረቶች ተደርገው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሁሉም ከሽፉ፡፡ አራተኛው ሙከራ፣ በ445 ዓ.ዓ. የተደረገው፣ ስኬትን አገኘ፡፡ ሥራውንም ከሁለት ወራት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ጨረሰ፡፡

የነህምያ ስኬት ተቃውሞ ገጥሞት ነበር፡፡ ጽኑና ሃይለኛ የሆነ የማደናቀፍ ጥረት ሲያደርጉ ከነበሩ ብዙ ጠላቶች ማስፈራሪያና ጥቃት ደርሶበታል፡፡ ነህምያ ከእነዚህ ብርቱ ጠላቶች ጥረት በተቃራኒ ቅጥሮቹን መጠገን መቻሉ በሕይወታችን ሌሎች «የፈረሱ ቅጥሮችን» ለማደስ የሚያስችለንን ስልት ያሳየናል፡፡

ከባድ በሆኑ ጊዜያት ውስጥ አልፋችሁ ከሆነ፣ የፈረሱ አጥሮች በሕይወታችሁ የሚኖሩበት እድል ከፍተኛ ነው፡፡ እነዚህ የፈረሱ ቅጥሮች፣ በአንድ ወቅት ደህንነት እንዲሰማን የሚያደርጉ አሁን ግን የፈረሱ፣ የተቃጠሉና የተደመሰሱ ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የግንኙነት ቅጥሮቻችን ይፈርሱና ለጎረቤቶቻችን፣ ወይም ለምንወዳቸው ቅርብ ቤተሰቦቻችን እንኳ ሊኖረን የሚገባው ፍቅር ይጠፋብናል፡፡ በሌሎች ጊዜያት፣ በሕይወታችን የሚከሰቱ ከባድ ሁኔታዎች የእምነታችንን ቅጥሮች ለማፈራረስ ያስፈራሩናል፡፡

በእግዚአብሔር የፍቅር ዝግጅት ላይ ያለንን መተማመን እናጣለን፡፡ ንግግራችንም በጨለምተኛና በጥርጥር በተሞሉ ቃላት ይሞላል፡፡ ሌሎች ደግሞ የሃቀኝነት አጥራቸው ላይ የመፍረስ አደጋ እንደደረሰበት ያውቃሉ፡፡ ምንም እንከን የሌለበት የሃቀኝነትን ሕይወት ከመሩ በኋላ፣ ሥነ ምግባራዊ መደናቀፍ ይደርስባቸውና እጅግ የሚያናድድ ግብረገባዊ ስህተት ይፈጽማሉ፡፡ በዚህም ለመገንባት አመታት የፈጀባቸውን የመልካም

ስም ቅጥራቸው የመፍረስ አደጋ ውስጥ ይወድቃል ወይም ይፈርሳል፡፡ እነዚህን ሁሉ የፈረሱ ቅጥሮች እንደገና ልንጠግናቸው ይገባል፡፡

የቅድስና አጥርስ? ከዚህ ቀደም ለእግዚአብሔር የነበራችሁ ቅንዓት ምን ያህል ጥልቅ እንደነበረ ትዝ ይላችኋል? አሁን ግን እንደ ኤፌሶን ቤተክርስቲያን አባላት (ራዕይ 2)፣ የመጀመሪያ ፍቅራችሁን አጥታችኋል፤ እናም የቅድስና ቅጥራችሁን እንደገና መልሳችሁ መገንባት ያስፈልጋችኋል፡፡ ለሌሎች ደግሞ የጸሎት ቅጥሮች በድርድር ፈርሰዋል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር በመነጋገር ጥራት ያለው ጊዜ ለማሳለፍ በጣም ባተሌ ሆናችኋል፡፡ ከዚህም የተነሳ የጸሎት ቅጥራችሁ እንደገና መገንባት ያስፈልገዋል፡፡ ነህምያ ታዲያ የፈረሱ ቅጥሮችን ስለመገንባት የሚያስተምረን ምንድን ነው?

**ለለውጥ ጥልቅ ጉጉት ይደርባችሁ**

ከኢየሩሌም ጥፋት የተረፉት የአይሁድ ቅሬታዎች ስቃይ ነህምያ ለውጥን በጥልቅ ጉጉት እንዲፈልግ አደረገው (ነህ. 1፡1-4)፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ «ተቀምጦ፣ አለቀሰ፤ ጾመ፤ ጸለየም» ይለናል፡፡ ይህ በእርግጥም ጥልቅ ጉጉት ነው፡፡ ይህ መልካም ሰው አለቀሰ፤ ሊፈታ የማይችል የሚመስለውንም ችግር እንዴት መፍታት እንደሚችል ማለም ጀመረ፡፡ መቼ ነው ለመጨረሻ ጊዜ ከአቅማችሁ በላይ ስለሆነ ግድድሮሽ ያለቀሳችሁት?

በመከራ ውስጥ በረከትን ለማግኘትና ችግሮቻችንን ወደ ደስታ ለመለወጥ ጥልቅ የሆነ ጉጉት መኖር ሊያስከትል የሚችለው ውጤት አስገራሚ ነው፡፡ በአስራዎቹ እድሜ ውስጥ ሳለሁ፣ ፕሬዝዳንት ጆን. ኤፍ. ኬኔዲ አሜሪካ ወደ ጨረቃ አንድ ሰውን ያለምንም ችግር ልካ በሰላም እንዲመለስ የማድረግ ታላቅ ህልም እንዳላቸው ተናግረው ነበር፡፡ ይህንን ህልም እውን ለማድረግ የተያዘው ቀን ደግሞ በ1960ዎቹ መጨረሻ ነበር፡፡ ለእኔና ለሌሎችም ሰዎች ይህ ፈጽሞ የማይቻል ተግባር መስሎን ነበር፡፡ ነገር ግን ብዙ ሰዎች የፕሬዝዳንቱ ጥልቅ ጉጉት እንደ ወረርሽኝ ተጋባባቸው፡፡ ወዲያውም ብዙዎች አይቻልም ያሉትን ነገር እንደሚቻል ለማሳየት ተግተው መስራት ጀመሩ፡፡ እናም ምን እንደሆነ ገምቱ? በእርግጥም እውን አደረጉት፡፡ በእርግጥም ጥልቅ የሆነ ጉጉት ልዩነትን ያመጣል፡፡

በቴሌቭዥን ስለ ግለሰቦች የሕይወት ታሪክ የሚቀርበውን ፕሮግራም ማየት በጣም እወዳለሁ፡፡ የታላላቅ ሰዎች የሕይወት መስመር ውስጥ ያሉት ከፍታዎችና ዝቅታዎች ይገርሙኛል፡፡ በተለይም በአልበርት አንስታይን ሕይወት ውስጥ የነበረው ከፍታና ዝቅታ በጣም ይገርመኛል፡፡ በእርሱ ሕይወት ላይ በተሰራ ጥናታዊ ፊልም ላይ፣ የአንጻራዊ ጽንሰሐሳብ ግኝቱን ላይ ለመድረስ ምን ያህል በጥልቅ ጉጉት ይሰራ እንደነበረ ተመለከትሁ፡፡ በተደጋጋሚ፣ አነስታይን ሁለት እርምጃ ወደፊት ሦስት እርምጃ ወደኋላ የሚሄድ ይመስል ነበር፡፡ ወደዚህ ግኝት ያደረገው ጉዞ ብዙ ጠመዝማዛ መንገዶች ነበሩት፡፡ እናም አንዱን አስቸጋሪ ሁኔታ እያለፈ ደግሞ ከሌላው ጋር ሲፋለም፣ አሁንም ሌላው ሲመጣበት ሳይ እርሱን በማየት ብቻ እኔ ደከመኝ፡፡ በመጨረሻ፣ ከግቡ ደረሰ፡፡ ምንም ነገር ሊያቆመው የማይችል ለውጥን ለማየት መጓጓት በውስጡ ከመኖሩ የተነሳ አስቸጋሪ ነገሮችን ሁሉ ወደ ጠቃሚ ነገሮች ለወጣቸው፡፡

ይህ ጥልቅ የሆነ ጉጉት በልባችሁ ከሌለ ህልማችሁን እውነት የማድረጉ ነገር አጠያያቂ ነውና ልብ በሉ፡፡ አንድ ጋዜጠኛ የአሜሪካ ግዛቶች ጸሐፊ የነበሩትን ኮሊን ፓውልን እንዲህ በማለት ጠይቋቸው ነበር፡- «ለምንድን ነው ለአሜሪካ ፕሬዝዳንትነት ያልተወዳደሩት?»

«በልቤ ውስጥ እሳቱ የለም፣» በማለት ኮሊን ፓውል ወዲያውኑ መልስ ሰጡ፡፡ እኚህ ጠቢብ የሕዝብ መሪ የፕሬዝዳንትነትን ተራራ ለመውጣት የሚሞክር ሁሉ ጫፉ ላይ ለመድረስ ትልቅ ጉጉት እንዳለው በቅድሚያ እርግጠኛ መሆን እንዳለበት ያወቁ ይመስላሉ፡፡

እናቴ ፍላጎቶቿን ለማሳካት አስፈላጊ የሆነው ይህ «የልብ ውስጥ እሳት» ነበራት፡፡ ስምንቱም ልጆቿ የክርስቲያን ትምህርት ቤት ገብተው እንዲማሩ ትፈልግ ነበር፡፡ ነገር ግን የክርስቲያን ትምህርት ቤቶች ክፍያ ውድ ሲሆን ለዚያ የሚበቃ ገንዘብ አልነበራትም፡፡ ይሁን እንጂ፣ በፕርላይን ብላክ ልብ የማይቻል የሚመስለውን ነገር ለማከናወን የሚያስችል ሙቀት የፈጠረ እሳት ተቀጣጠለ፡፡ በአንድ ወቅት፣ አራቱም ልጆቿ በተመሳሳይ ጊዜ በክርስቲያን አዳሪ ትምህርት ቤት ገብተው ይማሩ ስለነበር ለእነርሱ ትምህርት ቤት የምትከፍለው ገንዘብ በአመት ከምታገኘው የዌልፌር ገቢ ጋር እኩል እየሆነ መጣ፡፡ ለሁሉም ልጆቿ በክርስቲያን ትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው እንዲማሩ የነበራትን ሕልም እንዴት ልትፈጽመው እንደቻለች እስካሁን ለእኔ ለማስተዋል ይቸግረኛል፡፡ ነገር ግን ለውጥ ለማምጣት የነበራት ጥልቅ የሆነው ጉጉቷ ተራሮቿን እንድታንቀሳቅስና ያለችበትንም ሁኔታ ድል እንድታደርግ ረዳት፡፡

ምን ለማከናወን ሕልም አላችሁ? ልክ እንደ ነህምያ፣ በመከራችሁ ውስጥ የእግዚአብሔርን ባርኮቶች እንድትለማመዱ ይረዳችሁ ዘንድና ከምትገምቱት በላይ ማድረግ ትችሉ ዘንድ ጥልቅ የለውጥ መጓጓት በውስጣችሁ እንዲያድር ትፈቅዳላችሁ? የጥልቅ ጉጉትን ኃይል አሳንሳችሁ እንዳታዩ፡፡ እግዚአብሔር ለእስራኤል እንዲህ ብሏልና፡- «በሙሉ ልባችሁ ከፈለጋችሁኝ ታገኙኛላችሁ፡፡» (ኤር. 29፡11)፡፡

**እግዚአብሔር ሞገስ እንዲሰጣችሁ ጠይቁት**

እግዚአብሔርን ከልባችሁ ስትፈልጉት፣ ሞገስ እንዲሰጣችሁ መጠየቃችሁን እርግጠኛ ሁኑ፡፡ ነህምያ ያደረገው ይህንን ነበር፡፡ ተቀባይነትን ያገኝ ዘንድ ችሎታ እንዲሰጠው እግዚአብሔርን ጠየቀ፡፡ ንጉሡ ለእርሱ መልካም ነገር እንዲያደርግለት በልቡ ፍላጎት ያድርበት ዘንድ ፈለገ፡፡ ነህምያም ጸለየ፣ «ጌታ ሆይ፥ ጆሮህ የባሪያህን ጸሎት፥ ስምህንም ይፈሩ ዘንድ የሚወድዱትን፥ የባሪያዎችህን ጸሎት ያድምጥ ዛሬም ለባሪያህ አከናውንለት፥ በዚህም ሰው ፊት ምሕረትን ስጠው። እኔም ለንጉሡ ጠጅ አሳላፊው ነበርሁ።» እግዚአብሔርም የነህምያን ጸሎት መለሰ፡፡

እናንተስ ተቀባይነትን ለማግኘት ችሎታ ማግኘት ያስፈልጋችኋል? ዳንኤል አስፈልጎት ነበር፡፡ በባቢሎን ሳለ በንጉሡ መብልና መጠጥ ራሱን ላለማርከስ በልቡ ወሰነ (ዳን. 1፡8)፡፡ እግዚአብሔር ለዚህ የታማኝነት ውሳኔ ምላሽ የሰጠው እንዴት ነበር? ዳን 1፡9

እግዚአብሔር ዳንኤልን ከንጉሡ ቁልፍ አስተዳዳሪ ከሆነ ሰው ጋር ጥሩ የፍቅር ግንኙነት እንዲኖረውና ሞገስ እንዲያገኝ አደረገው፡፡ ይህም « አንተ ጻድቁን ትባርከዋለህና አቤቱ፥ እንደ ጋሻ በሞገስ ከለልኸን።» (መዝ. 5፡12)፡፡

እግዚአብሔር ሞገስ እንዲሰጣችሁ መጠየቅ አትፍሩ። ያዕ. 4፡2 እንዲህ ይላል፡- «አልጠየቃችሁምና አላገኛችሁም» መጠየቅ ባለመቻል ብቻ ለምን በረከት ያመልጣችኋል? ነህምያ ችግሩን ወደ ጥቅም የለወጠው ከእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን በመጠየቅ ነበር።

አንድ ጊዜ በአንድ አየር ማረፊያ አቋርጬ ስሄድ፣ አንድ ወጣት በጀርባው ላይ የሚከተለው ጽሁፍ የተጻፈበት ቲ-ሸርት አድርጎ ተመለከትሁ፡- «አትቅናብኝ፣ ሞገስ ለሁሉ የሚሆን አይደለም (ሞገስ ያዳላል)» ይህ ምን ያህል እውነት ነው! የዳዊትና የቤርሳቤህን ልጅ ሰለሞንን ከወንድሞቹ ይልቅ እርሱ ይነግስ ዘንድ እግዚአብሔር ፈቀደ። ሰለሞን ከጸሎቶቹ በአንዱ የእግዚአብሔርን ርህራሄና ሞገስ በማሰብ ተናግሯል(1 ነገ. 3)፤ የማይገባውን የመለኮት ስጦታ ይኼውም ከሌሎች የሚበልጥበትን ሞገስ አግኝቶ ነበር። ሞገስ ለሁሉ የሚሆን አይደለም።

አንድ ጊዜ እኔን ከማይወደኝ ስር ሆኜ እንድሰራ ትዕዛዝ ተሰጠኝ። ይህን የገጠመኝን ችግር በሰሙ ጊዜ ጓደኞቼ ሃዘናቸውን ገለጹልኝ። «ቤሪ፣ እግዚአብሔር ምህረቱን ያውርድልህ» አሉኝ በጨለምተኛ አስተሳሰብ የተሞላውን ጭንቅላታቸውን እየነቀነቁ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር፡፡ ምክንያቱም በውትድርና ደንብ መሰረት የተሰጠኝን አዲስ የስራ ምድብ የግድ መቀበል ነበረብኝና። እናም ጸለይሁና እግዚአብሔር ሞገስ እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት።

አዲሱ የስራ ቦታዬ ላይ ስደርስ፣ ራሴን ለአዲሱ አለቃዬ ማስተዋወቅ ስጀምር ሁኔታው ከበድ ያለ ነበር፡፡ ሥነ ምግባር የጎደለውና ወዳጅነትን የማያውቅ ይመስላል። ሳምንታቱ ይከንፉ ጀመር። ከወታደራዊ ትዕዛዝ ውጪ ሌሎች ቃላትን የሚጠቀመው አልፎ አልፎ ነው። አንድ ቀን ጠዋት ወደ ቢሮዬ ስገባ ረዳት ስራ አስፈጻሚዋ ስገባ «አለቃው አሁኑኑ ሊያይህ ይፈልጋል»የሚል ቃል ተናገረችኝ።

ወደ ቢሮው እየተንቀጠቀጥሁ ገባሁና በጠረጴዛው አጠገብ ቆምሁ። እርሱም ቀና ብሎ ተለመከተና ዝቅ ብሎ ስራውን መስራት ቀጠለ። በመጨረሻም እንዲህ አለ፡- «ለምን እንደሆነ አላውቅም፣ ላንተ ጥሩ አመለካከት አለኝ!» እነዚህን ቃላት በጭንቅ ነበር ከአፉ ያወጣቸው። እኔም«ጌታዬ፣ አልገባኝም» አልኩኝ። «ሊገባህ ይገባ ነበር» በማለት አምባረቀበኝ። ከዚያም እንዲህ አለኝ፡- «ለምን እንደሆነ ባላውቅም እወድሃለሁ፤ አሁን መውጣት ትችላለህ፤ ይኼው ነው፡፡»

የእርሱን ቢሮ ትቼ ስወጣም እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡- «ለምን እንደምትወደኝ እኔ አውቃለሁ። በእግዚአብሔር ሞገስ ስለተባረክሁ ነው። እርሱ ጸሎቴን መልሶልኛል» የእግዚአብሔር ሞገስ ከመከራ ውስጥ በረከት እንድናገኝ ይረዳናል።

**ምቹ ሁኔታዎች ሲገጥሟችሁ ተጠቃሚ መሆን እንድትችሉ በቅድሚያ ተዘጋጁ**

ምቹ የሆነ ጊዜ አሁን ቢመጣ በዚያ ተጠቃሚ ለመሆን ተዘጋጅታችኋል? ብዙዎቻችን ዝግጁዎች አይደለንም። ነገር ግን ነህምያ ዝግጁ ነበር። ለአራት ወራት ያህል በልቡ በጥልቀት ሲያስብ ቆየ። አንድ ቀንም ንጉሡ እንዲህ አለው፡- «ምንድን ነው የምትፈልገው?» (ነህ. 2፡4)።

ነህምያም በፍጥነት ጸለየና እንዲህ በማለት ለንጉሡ መለሰ፡- «ንጉሡን ደስ ቢያሰኝህ፥ ባሪያህም በፊትህ ሞገስ ቢያገኝ፥ እሠራው ዘንድ ወደ ይሁዳ ወደ አባቶቼ መቃብር ከተማ ስደደኝ» (ነህ. 2፡5)። ድንቅ ነው! ነህምያ አንድ ክፍለ ዘመን የፈጀን ችግር ለመፍታት ጥያቄ ያቀረበው እንደዚህ ነበር።

የነበረው ዝግጅት ከጠየቀውም ጥያቄ ይበልጥ ጥልቅ ነበር። በመንገዱም ላይ የሚያቆመው ነገር እንዳይኖር ከንጉሡ ዘንድ ደብዳቤ እንዲሰጠው ጠየቀ። ከዚያም ሁለተኛ ደብዳቤ ጠየቀ። ይኼኛው ደግሞ የንጉሡን ደን ለሚጠብቅ ሰው የሚሰጥ ሲሆን የፈረሰውን ቅጥር ይጠግን ዘንድ ነህምያ የሚያስፈልገውን እንጨት ከዚያ እንዲወስድ ፈቃድ የሚያሰጠው ነበር።

ነህምያ በኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ ዝግጅቱ ቀጠለ። ከጥቂት ሰዎች ጋር በመሆን ምሽት ላይ የፈረሱትን ቅጥሮችና የተቃጠሉትን በሮች በአይኖቹ ለመመልከት ወጣ (ነህ. 2፡11-13)።

አሁንም እንደገና እጠይቃችኋለሁ፣ የእናንተም የእድል (የምቹ ሁኔታ) በር አሁን ቢከፈት ልትጠቀሙበት ዝግጁዎች ናችሁ?

በአንድ ወቅት እንዲህ ያለው በር በተከፈተልኝ ጊዜ ብዙም ዝግጁ እንዳልነበርኹ አስታውሳለሁ። ለአሜሪካ መንግስት ሴኔት የቻፕሌንነት ስልጣን ቃለ መጠይቅ ሊደረግልኝ እንደምፈለግ ተነገረኝ። ነገር ግን የቤት ስራዬን አልሰራሁም ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ ከተደረገልኝ ቃለመጠይቅ ሁለት ቀን በፊት ምንም ያህል ዝግጁ እንዳልነበርሁ ተረዳሁ።

አድሚራሎችንና ጀነራሎችን እንደገና ወደ ሲቪል ሕይወት ለመግባት በሚያዘጋጃቸው ስልጠና ላይ እየተሳተፍኩ ነበር። ከአስተማሪዎቼ መካከል አንዱ በአርባ ስምንት ሰአት ውስጥ ለቻፕሌንነት ስልጣን ቃለመጠይቅ እንደሚደረግልኝ በሰማ ጊዜ «ለምን የቤሪን ቃለመጠይቅ በድራማ መልክ እዚህ አናሳይም?» አለ። በክፍሉ ውስጥ የነበሩ ተማሪዎችም ጎተጎቱኝና፣ እያመነታሁ መቀመጫዬን ለቅቄ ከተማሪዎቹ ፊት ለፊት ባለው የክፍሉ ወንበር ላይ ተቀመጥሁ።

ትክክለኛው ቃለ መጠይቅ ይኼ ስላልሆነ እግዚአብሔር ይመስገን፣ አልሁ ለራሴ።

ጠያቂዬ የመጀመሪያውን ጥያቄ እንዲህ በማለት ተኮሰብኝ፡- «ቤሪ፣ ለአንተ ቃለ

መጠይቅ በሚያደርግልህ የሴኔቱ መራጭ ኮሚቴ ውስጥ ያሉት ሰዎች እነማን ናቸው?»

ከመመለሴ በፊት አሰብኩና እንደዚህ አልኩ፡- «ከሁለት ቀን በኋላ ቃለ መጠይቁ እስከሚደረግልኝ ድረስ ይህንን ላውቀው አልችልም።»

ጠያቂዬም ፈገግ አለ። « በመራጭ ኮሚቴው ውስጥ ያሉትን ሴናተሮች ስም እኔ ካንተ ቀድሜ እያወቅሁ፣ ለምን ይሆን ለዚህ ስራ ለእኔ ቃለ መጠይቅ የማይደረግልኝ አለ?»

«ኧረ፣ እኔ ፈጽሞ አላውቅም፣» አልኩ እየተደነጋገርኩ።

«እንግዲያውስ፣ እኔ መረጃውን ያገኘሁት ከሴኔቱ ድህረ ገጽ ሲሆን አንተም ተመሳሳዩን ማድረግ ትችል ነበር»

የክፍል ጓደኞቼ በሚስቁብኝ ጊዜ ሐፍረት ተሰማኝ። ግን በዚያው ልክ ደግሞ የእፎይታ ትንፋሽ ተነፈስኩ፤ ምክንያቱም ቢያንስ አሁንም ለመዘጋጀት ጥቂት ጊዜ ነበረኝና።

ትርኢቱ ቀጠለ፤ ጠያቂዬ በጥያቄ ሲያጣድፈኝ መልሶቼ ግን ደካማ ነበሩ። ልክ እርሱ እንደጨረሰ፣ ዝግጅት ለማድረግ ወደቤቴ ፈጥኜ ሄድሁ። ቀጣዮቹንም ሁለት ቀናት ልክ ለመጨረሻ ፈተና እንደሚዘጋጅ ሰው ሁሉን ነገር ሸመደድሁ። በፊቴ ቀርቦልኝ የነበረውን እድል የማጣትን ታላቅ ዋጋ ሳልከፍል ወሳኝ የሆነን ትምህርት ለመማር በመቻሌ እግዚአብሔርን አመሰገንሁ። ከመዘጋጀት መውደቅ ማለት ለመውደቅ መዘጋጀት ነው። ከአርባ ስምንት ሰዓታት በኋላ፣ ትክክለኛዎቹ ጠያቂዎች ጥያቄያቸውን ሲተኩሱ፣ ደክሞኝ የነበረም ቢሆን ግን ተዘጋጅቼ ነበር።

ታላቁ ሐዋርያ ጳውሎስ እንኳን በፊት ለፊቱ ለተዘረጉለት እድሎች መዘጋጀት ነበረበት። በደማስቆ መንገድ ላይ ሕይወቱ ከተለወጠ በኋላ (የሐዋ. 9)፣ ለሐዋርያነት ስራው በመዘጋጀት በአረቢያ ምድረበዳ ለሦስት አመታት ያህል ቆየ (ገላ. 1፡16-18)። መዘጋጀት፣ መዘጋጀት፣ መዘጋጀት። በመከራቸው ውስጥ በረከትን የሚያገኙ ሰዎች ምቹ ሁኔታ በራቸውን ሲያንኳኳ የተዘጋጁ ሊሆኑ ይገባል።

ለአፍሪካ አሜሪካውያን ወጣቶች ባደረጉት ንግግር፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር የምቹ ሁኔታዎች በር በሚከፈትበት ጊዜ መጠቀም እንዲችሉ ከወዲሁ የተዘጋጁ እንዲሆኑ ተገዳድረዋቸው ነበር። ይህም ዝግጅት በእጃችን ላይ ያለውን ስራ አቅማችን በፈቀደው ሁሉ ምርጥ አድርገን ለመስራት መጣርን፣ ሥራችንን « በሕይወት ያሉት፣ የሞቱት ወይም ገና ያልተወለዱት ህጻናት ከእኛ የተሻለ አድርገው ሊሰሩት በማይችሉት ሁኔታ» (Martin Luther King Jr., “Three Dimensions of a Complete Life,” a sermon first preached at Dexter Avenue Baptist Church, Birmingham, Alabama, in 1954) መሥራትን ያካትታል። ይህ ነው እንግዲህ በነህምያ መንገድ ምቹ ሁኔታዎችን ለመጠቀም መዘጋጀት ማለት።

**ተቃውሞን ተጠባበቁ**
ለውጥ ልንገታው በማንችለው ጎማ እየተሽከረከረ ወደ እኛ አይመጣም፤ ወደ ክቡር ግቦች ያለ ተቃውሞ መድረስ አስቸጋሪ ነው። በነህምያ ታሪክ ላይ እንዲህ ሆኖ ነበር:- «ሰንባላጥም ቅጥሩን እንደ ሠራን በሰማ ጊዜ እጅግ ተቈጣ፥ ተበሳጨም፥ በአይሁድም አላገጠ።» (ነህ. 4:1)። አዎ ተቃውሞ ገጥሞት ነበር።

ይህንን ጹሁፍ በማዘጋጅበት ጊዜ የአሜሪካ ኮንግረስ የጤና አጠባበቅን በተመለከተ ሕጉን እየለወጠ ነበር። ትሩማን በፕሬዝዳንትነት ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ይህንን ለውጥ ለማጠቃለል ጥረት ሲደረግ ነበር። የግለሰቦች የፖለቲካ አመለካከት ምንም ያህል የተለያየም ቢሆን ይህንን ህግ የማርቀቅ ስራ መስራት ምን ያህል ታላቅ ተቃውሞ አስነስቶ እንደነበረ እናስታውስ ይሆናል።

ዳዊት ጎልያድን ተቃውሞ ሲናገር ተቃውሞ ገጥሞት ነበር (1 ሳሙ. 17)። እስራኤል ሁሉ በፍርሃት ሲንቀጠቀጥ፣ ዳዊት እንዲህ በማለት ጠየቀ፣ «የሕያውን አምላክ ጭፍሮች የሚገዳደር ይህ ያልተገረዘ ፍልስጥኤማዊ ማን ነው?» (ቁ.26) የዳዊት ትልቅ ወንድሙም እንዲህ በማለት ወዲያውኑ ተቃወመው:- «ታላቅ ወንድሙም ኤልያብ ከሰዎች ጋር ሲነጋገር ሰማ የኤልያብም ቍጣ በዳዊት ላይ ነድዶ:- ‹ለምን ወደዚህ ወረድህ? እነዚያንስ ጥቂቶች በጎች በምድረ በዳ ለማን ተውሃቸው? እኔ ኵራትህንና የልብህን ክፋት አውቃለሁና ሰልፉን ለማየት መጥተሃል አለው።» (ቁ.28)

በእርግጥም ተቃውሞዎች ብዙ የከበሩ ጥረቶችን አኮላሽተዋል። እንዲያውም፣ እግዚአብሔር በትክክለኛው መንገድ የሚመላለሱትን ሁሉ ተቃውሞ እንደሚገጥማቸው አረጋግጦአል። ሁለተኛ ጢሞቲዎስ 3:12 እንዲህ ይላል:- «በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ።» ስለዚህ እንደ ነህምያ በመሆን በመከራችሁ ውስጥ በረከትን አግኙ። ተቃውሞዎችን ሁሉ በማሸነፍ መከራችሁን በደስታ ተቀበሉት።

**የፈረሱ ቅጥሮችን ለመጠገን የሚያግዟችሁ ወሳኝ እርምጃዎች**

- ለለውጥ ጥልቅ ጉጉት ይኑራችሁ
- እግዚአብሔር ሞገስ እንዲሰጣችሁ ጠይቁት
- ምቹ ሁኔታዎች ሲገጥሟችሁ ተጠቃሚ መሆን እንድትችሉ በቅድሚያ ተዘጋጁ
- ተቃውሞ ተጠባበቁ

# 5

# ከስብራት በረከት አግኙ

*እነሆ፥ እግዚአብሔር የሚገሥጸው ሰው ምስጉን ነው*
*ስለዚህ ሁሉን የሚችለውን የአምላክን ተግሣጽ አትናቅ። ኢዮ. 5፡17*

የሕይወትን መከራዎች አይቻለሁ፤ ቀምሻለሁ፡፡ አንድ ጊዜ የሐዘን ድባብ ባጠላበት የሆስፒታል ኮሪደር ላይ በመኪና አደጋ የመጀመሪያ ሴት ልጇን የቀበረች፣ አሁን ደግሞ ከአደጋው ሕይወቱ የተረፈው ባለቤቷ እንዳይሞትባት በተስፋና በጸሎት የምትጠባበቅ አንዲት ሚስትና እናት የሆነች ሴት በከባድ ሁኔታ ውስጥ ስታልፍ ተመልክቼ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ እርሱም ሞተ፡፡

በሣምንቱ መጨረሻ አካባቢ የእርሱ የቀብር ስነስርአት እየተካሄደ ደግሞ፣ በእንባ ጎርፍ ፊቴ እንዲታጠብ ያደረገ ሌላ ሃዘን ወደቀብኝ፡፡

በአባቴ አልጋ አጠገብ ቆሜ ሲሞት ሳይ፣ ዶክተሮች እየሞቱ የነበሩትን የሰውነት ክፍሎቹን ወደ ሕይወት ለመመለስ የሚያደርጉትን ጥድፊያ የተሞላበት ሩጫ ስመለከት፣ የልብ ስብራት ተሰማኝ፡፡ እንዲያውም ከሚሞቱት ተርታ ለተመደበ ሰው እንዲህ ባለ ትጋት መሯሯጣቸው ገረመኝ፡፡

አንድ የሃያ ሦስት አመት ወጣት ክርስቶስን ከተቀበለ ከሦስት ቀን በኋላ የግድያ ወንጀል በተፈጸመበት ጊዜ የልብ ስብራት ምን እንደሚመስል አይቼ ነበር፡፡ በቀብሩ ስነሥርአት ላይ የእግዚአብሔርን ቃል በማካፍልበት ጊዜ፣ በእርግጥ «እግዚአብሔርን ለሚወዱ ሁሉ ነገር ተያይዞ ለበጎ ይሆናል» (ሮሜ. 8፡28) የሚለውን ጥያቄ ውስጥ ከትቼው ነበር፡፡

በጦርነት ምክንያት የሚከሰቱ አሳዛኝ ሁኔታዎችን ሳነብና በዘመነ ኒኩሊየር ያለውን የጦርነት ጥበብ እንዳውቅ ያደረገኝን የሃያ ሰባት አመታት የሚሊተሪ አገልግሎቴን ሳስታውስ ልክ እንደሚነዘንዝ የጥርስ ሕመም ያለ ስብራት ይሰማኛል፡፡ በአሜሪካ ከተሞች ወሮበሎች የሚያደርሱትን ጥቃት ስመለከት፣ ወይም በብዙ ከተሞች የተስፋፋውን አሳዛኝ ድህነት ፣ ወይም አናሳ በሚባሉት ዘሮች መካከል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የሚያቋርጡት ቁጥር መበራከት፣ ወይም እጅግ ቁጥሩ እየጨመረ የመጣውን የፍቺ ብዛት የሚያባብሰውን የቤት ውስጥ ግጭት ሳይ የልብ ስብራት ይሰማኛል፡፡

ምስቅልቅሏ በወጣችው አለም ውስጥ የሚከሰተውን ቀውስ የሚያትቱትን ዜናዎች ስጋፈጥ ይህ ስብራት ይሰማኛል፡፡ ብዙ መልካም ሰዎች አላስፈላጊ በሆነ ስቃይ ውስጥ እንዳሉ በሚሰማኝ ጊዜ ልቤ ይሰበራል፡፡ ብዙ የተሰበሩ ልቦችን አይቻለሁ፤ ለማጽናናትም ሞክሬአለሁ፡፡ ምናልባት እናንተም አድርጋችሁ ይሆናል፡፡

ከፋት እርግጥ እንደሆነ፣ ኃጢአትም ትልቅ ተጽእኖ እንዳለው፣ ሞት ደግሞ በሰብአዊ ሕይወት ውስጥ በቋሚነት ደጋግሞ የሚመጣ ነጣቂ እንደሆነ የሚያሳምነኝን ብዙ ሥቃይ አይቻለሁ፡፡ ነገር ግን በዙሪያ ከከበበኝ ስብራትና ስቃይ በተቃራኒ፣ እግዚአብሔር ህመማችንን መጠቀምና ከስቃያችንም ተጠቃሚዎች ሊያደርገን እንደሚችል አምናለሁ፡፡

ምንም እንኳ ብዙ ሰዎች በመከራቸው ውስጥ በዋናነት የሚያዩት አሉታዊ ገጽታዎችን ቢሆንም፣ እንደዚህ ካሉት መከራዎች ውስጥ የሚገኙ በረከቶች አሉ፡፡ ራሳችንን እንድናዋርድ ይረዱናል፤ ስለ እግዚአብሔር ጥልቅ እውቀት እንዲኖረን ያግዙናል፤ የጸሎት ሕይወታችንን ያጠነክራሉ፤ መለኮታዊ ጸጋን እንድንቀበል ይረዱናል፤ የእግዚአብሔርን ታማኝነት እንድናይ ያስችሉናል፤ ወደ ቅዱሱ ቃል ይመሩናል፤ የመለኮት እንክብካቤን እንድናደንቅ ያግዙናል፤ ወደ ኋላ ከማፈግፈግ ይጠብቁናል፡፡ እግዚአብሔር ስቃያችንን የሚጠቀምባቸው መንገዶች ጣፋጭ ናቸው፡፡

**ስቃይ ትህትናን እንዲያስተምራችሁ ፍቀዱለት**

መከራ ትዕቢታችንን አስወግዶ ትህትናን ያመጣልናል፡፡ ይህንን በቀድሞው የአላባማ ገዢ ጆርጅ ዋላስ ሕይወት ተመልከተናል፡፡ ይህ ጠንካራ የሆነ የመከፋፈል ሥራን የሚሰራ ሰው፣ እንደዚሁም ክፍፍልን የሚያመጡ የፖለቲካ ዘዴዎችንና መድሎን የሚያስፋፉ ባሕርያትን የሚያራምድ ሰው፣ የግድያ ሙከራ እንደሆነ በሚታሰብ ተኩስ ተከፍቶበት ለጥቂት ተርፎ ነገር ግን የአካል ጉዳተኞች በሚገፉበት ተሽከርካሪ ወንበር ላይ እንዲቀመጥ ያደረገው ከፍተኛ ጉዳት ደረሰበት፡፡ በውጤቱም፣ ዋላስ የማያቋርጥ ስቃይን የተለማመደ ሲሆን የግል ሕይወቱን የሚመዝንበት ጊዜ አግኝቶ ነበር፡፡ ከዚህም የመከራ ልምምድ ፍጹም የተለየ ሰው ሆኖ ወጣ፡፡ ከዚህ ትራጄዲ በኋላ፣ ዋላስ ስለ ቀድሞ ባሕርይው ጥልቅ የሆነ ሐዘንና መጸጸት በማሳየቱ፣ በሂደት ከፍተኛ የሆነ የአፍሪካ አሜሪካዊያንን ድምጽ በማግኘት የአላባማ ገዢ ሆኖ እንደገና ተመረጠ፡፡ በአንድ ወቅት ያንቋሸሻቸው ሰዎች አሁን የሥራ አጋሮቹ ሆኑ፤ ዋላስም መጥፎ የነበረውን ስሙን ወደ መልካም ለመለወጥ ቻለ፡፡

የጆርጅ ዋላስ ታሪክ የቅርብ ጊዜ ሲሆን ከረዥም ጊዜ በፊት፣ በራሱ እጅግ ይተማመን የነበረው ጴጥሮስ የተባለ አሳ አጥማጅ ስቃይ ትህትናን እንደሚያፈራ ተምሮ ነበር፡፡ ጴጥሮስ ኋላ ላይ በጴንጤቆስጤ ቀን ሊሰብክ (የሐዋ. 2)፣ በእርሱም ምስክርነት ከሦስት ሺህ ሰዎች በላይ ወደ ክርስቶስ ሊመጡ ነበር፡፡ ነገር ግን ያ ከመሆኑ በፊት፣ ጌታውን ሦስት ጊዜ በመካድ አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ በማለፍ ራስን ዝቅ ማድረግን መማር ነበረበት፡፡ ይህ ክህደት የተከሰተው ስለ ኢየሱስ ለመሞት እንደተዘጋጀ በጉራ ከተናገረ በኋላ ነበር፡፡ በዚህ አሳፋሪ በሆነው ኃጢአቱ ከባድ የሆነ ሃዘን ደርሶበት ጴጥሮስ መራራ የሆነ የንስሐ ለቅሶ አለቀሰ (ሉቃ. 22፡ 62)፡፡ ኋላ ላይ፣ ትህትናን የተማረው ጴጥሮስ ከኢየሱስ ጋር ከትንሳኤው በኋላ ሲገናኝ፣ ኢየሱስ እንዲህ በማለት ጠየቀው፣ «ጴጥሮስ፣

ከሌሎቹ አብልጠህ ትወደኛለህን?» ብሎ ጠየቀው (ዮሐ. 21፡ 1-17)፡፡

«ጌታ ሆይ፣ እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ፣» በማለት ነበር ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ መልሱን የሰጠው፡፡

ኢየሱስ ተመሳሳዩን ጥያቄ ሁለት ጊዜ ደጋግሞ ጠየቀው፡፡ በእያንዳንዱ ጊዜም፣ ጴጥሮስ ምላሽ የሰጠው ሙሉ እርግጠኝነት በሌለበት እና ትህትናን በተላበሰ መልኩ ነበር፡፡ እንዲያውም እንዲህ የሚል ይመስል ነበር፡- «ጌታ ሆይ፣ ልቤን ታውቃለህ፡፡ በእርግጥ አንተን እወድህ እንደሆነ አንተ ራስህ ንገረኝ፡፡» በራሱ በመተማመን ተሞልቶ በጉራ ከሚናገርባቸው ከእነዚያ ቀናት ጋር ሲስተያይ ይህ አስገራሚ ለውጥ ነው፡፡ አሁን እግዚአብሔር በኃይል ሊጠቀምበት የሚችል ሰው ሆነ፤ ምክንያቱም ስቃይ ራሱን እንዲያዋርድ አድርጎት ነበርና፡፡

**ስቃይ ስለ እግዚአብሔር ያላችሁን እውቀት የጠለቀ እንዲሆን እንዲያደርገው ፍቀዱ**

ስቃይ ከእግዚአብሔር ጋር የበለጠ ወደምንጠጋጋበት ግንኙነት ውስጥ በመጨመር፣ ስለ እርሱ ያለንን እውቀት ጥልቅ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ይህንን የጠበቀ ግንኙነት አስመልክቶ ኢዮብ ሲያውጅ እንዲህ ይላል፡- «አሁንም ከእርሱ ጋር ተስማማ(የበለጠ ተዋወቅ)፥ ሰላምም ይኑርህ በዚያም በጎነት ታገኛለህ።» (ኢዮብ. 22፡21)፡፡ ይህ የኢዮብ ንግግር እግዚአብሔርን ማወቅ እንደሚያስፈልገን ያስታውሰናል፡፡ ስቃይ ደግሞ ከመታወቅ የሚያልፈውን አምላክ ለማወቅ በምናደርገው በዚህ እንቅስቃሴያችን የሚያስፈልገንን ተነሳሽነት ይሰጠናል፡፡ በስቃይ እቶን ውስጥ በማለፍ የእግዚአብሔር እንክብካቤ በፊታችን ሲዘረጋ እናየዋለን፡፡ ኢዮብ እጅግ ከባድ በሆነ ሀዘንና እጦት ውስጥ ባለፈ ጊዜ፣ ስለ እግዚአብሔር የነበረው እውቀት በእጅጉ ጨመረ፡፡ ለእግዚአብሔርም እንዲህ አለ፡- «መስማትንስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፤» (ኢዮ. 42፡5)፡፡

ሳሙኤል በልጅነቱ ተመሳሳይ ልምምድ ከእግዚአብሔር ጋር ነበረው፡፡ ሳሙኤል ከእግዚአብሔር ጋር የተዋወቀው ከባድ በሆነ የፍርድ ድምጽ በኩል ነበር (1 ሳሙ. 3)፡፡ እግዚአብሔር የኤሊን ቤተሰብ ለመቅጣት ባሰበበት ጊዜ ነበር ሳሙኤል ከካህኑ ከኤሊ ጋር ይኖር የነበረው፡፡ አንድ ምሽት፣ ሳሙኤል ድምጽ ሰማ፡፡ የአለቃው የኤሊ ድምጽ መስሎት፣ ወደ ካህኑ አልጋ በፍጥነት ሄደ፡፡ ኤሊ ሳሙኤልን ሊገናኘው እየሞከረ ያለው እግዚአብሔር ራሱ እንደሆነ በተረዳ ጊዜ፣ ለሳሙኤል እንደዚህ እንዲል መከረው፡- « ጌታ ሆይ፣ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር፡፡» ሳሙኤል በታዘዘ ጊዜ፣ እግዚአብሔር በኤሊ ልጆች ላይ በቅርቡ ሊመጣባቸው ስላለው ከባድ ፍርድ ተናገረው፡፡ ሳሙኤል በመፍራትና በመንቀጥቀጥ፣ ነገሩን ከመቀበል ውጪ ሌላ ምንም ሊያደርግ እንደማይችል የገባውን ኤሊን አስጠነቀቀው፡፡ ሳሙኤልም የኤሊ ቤት ሲፈርስ ተመለከተ፤ ነገር ግን ከእነዚህ ሁሉ የስቃይ ምዕራፎች በረከቶች ሊወጡ ይችላሉ፡፡ እነዚህ የስቃይ ትዕይንቶች፣ ሳሙኤልን ከእግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ምስጢራዊ ከሚሆኑት አሰራሮቹ ጋር እንዲተዋወቅ በማድረግ በእስራኤል መካከል ታላቅ መንፈሳዊ ኃይልን የሚገልጥ ሰው እንዲሆን አደረጉት፡፡

**ስቃይ የጸሎት ሕይወታችሁን እንዲያጠነክረው ፍቀዱ**

ስቃይ የጸሎት ሕይወታችሁን ሊያጠነክረው ይችላል፡፡ አንድ ጊዜ አንድ ሰው ጸሎት የነፍስ እስትንፋስ ነው በማለት ተናግሮ ነበር፤ በእርግጥም ነው፡፡ ነብዩ ኤልያስ የከነዓናዊያን አምላክ የሆነውን የባኣልን ጣዖት አምልኮ መንገድ ለመከተል እስራኤል መወሰኗን በተመለከተ ጊዜ በስቃይ ውስጥ ወድቆ ነበር፡፡ ይህ በሀዘን የሚሞላ አስቸጋሪ ሁኔታ ነብዩን በጉልበቱ እንዲቆይ አደረገው፡፡ ኤልያስ እግዚአብሔር እስራኤልን ወደ ንስሐ እንዲያደርስ በእጅጉ ከመፈለጉ የተነሳ፣ ዝናብን እንዲያቆምና በአገሪቱ ድርቅን እንዲሰድ እግዚአብሔርን ጠየቀው፡፡ እግዚአብሔርም ጽኑ ጸሎቱን መለሰለት (ያዕ. 5፡17-18)፡፡ የነብዩን የጸሎት ሕይወት ያቀጣጠለው የስቃዩ እሳት ነበር፡፡

ኢየሱስ ጸሎት የተስፋ መቁረጥ መድኃኒት ስለሆነ ሰዎች «ሳይታክቱ መጸለይ» እንዳለባቸው (ሉቃ. 18፡1) በማስረገጥ ተናግሮአል፡፡

ሃዘን የጸሎታችንን ብዛት ይጨምረዋል፤ በዚህም ሰዎች የተሻሉ የምልጃ ጸሎት ጸላዮች መሆን የሚችሉበትን እድል ያሰፋል፤ አንድን ነገር ደጋግሞ ማድረግ ፍጹም ያደርጋልና፡፡ ስቃያችንን አስመልክተን ወደ እግዚአብሔር በተደጋጋሚ በጸሎት በምንቀርብበት ጊዜ፣ እርሱን በመስማትና የሚያሳስቡንንም ነገሮች ለእርሱ በመንገር እያደግን እንሄዳለን፡፡ በዚህ መሠረት፣ ስቃይ የጸሎት ሕይወታችሁን ሊያጠነክረው ይችላል፡፡

እናቴ በቤተክርስቲያን ሰዎች ዘንድ የምትታወቀው በጸሎት ጓድነቷ ነው፡፡ አንድ ጊዜ «እንዲህ ያለውን የጸሎት ሕይወት ልታዳብሪ የቻልሽው እንዴት ነው?» ብዬ ጠየቅኋት፡፡

«ለሠላሳ አመታት ለአባትህ በመጸለይ ነው» በማለት መለሰችልኝ፡፡ የጸሎት ሕይወቷ የተጠናከረው በአልኮል ሱስ ይቸገር ለነበረው ባለቤቷ በትጋት በመማለዷ ሲሆን፣ ይህም ከእግዚአብሔር ጋር የነበራትን ግንኙነት አሻሻለው፡፡

**ስቃይ የእግዚአብሔርን ጸጋ እንድትቀበሉ እንዲረዳችሁ ፍቀዱ**

ሌላው የስቃይ ትርፍ የእግዚአብሔርን ጸጋ እንድናገኝ ማድረጉ ነው፡፡ «ኃጢአት በበዛ መጠን፣ ጸጋ አብልጦ ተትረፈረፈ» የተባለበት አንደኛው ምክንያት ይሄ ነው (ሮሜ. 5፡20)፡፡ እግዚአብሔር በችግራችን ጊዜ ወደ እኛ ሲቀርብ ጊዜ፣ በየማለዳው አዲስ ስለሆነው የእርሱ ምህረት የሚኖረን ግንዛቤ ይጨምራል፡፡

በዮናስ ታሪክ ውስጥ፣ እግዚአብሔር የፍርድ መልእክትን አስይዞ አንድ ዳተኛን ነብይ ሲልክ እናያለን፡፡ ነገር ግን ነብዩ በተቃራኒ አቅጣጫ ለመኮብለል መረጠ፡፡ በሂደትም፣ በታላቅ አሳአንባሪ ሆድ ውስጥ ካሳለፈው የስቃይ ጊዜ በኋላ፣ እግዚአብሔር እንዲያደርግ የሰጠውን ሥራ ለመስራት ወሰነና ለነነዌ ሰዎች የፍርድ መልእክትን አስተላለፈ፡፡ ነገር ግን ሕዝቡ የዮናስን ቃል ሲሰሙና ንስሓ ሲገቡ፣ ዮናስ በእግዚአብሔር ላይ ተቆጣ፡፡ «አንተ መሐሪ መሆንህን በፊትም አውቄ ነበር» አለ፡፡ ዮናስ የተናደደው የነነዌን ጥፋት አስመልክቶ እርሱ የተናገረው ትንቢት ተፈጻሚ ባለመሆኑ ምክንያት ነበር፡፡

አንድ ቀን ዮናስ ከጸሐይ በታች ተቀምጦ ሳለ፣ አንድ ተክል በአጠገቡ በፍጥነት አደገ፡፡ ጸጉር አልባ የሆነውን የራስ ቅሉንም ከጸሐዩ ቃጠሎ አስጠለለው፡፡ ነገር ግን፣ ተክሉ ባደገበት ፍጥነት ወዲያው ደረቀ፤ ይህም የዮናስን ቁጣ አባባሰው፡፡ እግዚአብሔር ግን ዮናስን ትምህርት እየሰጠው ነበር፡፡ ለዮናስም እንዲህ አለው፤ « እግዚአብሔርም፦ አንተ ትበቅል ዘንድ ላልደከምህባት ላላሳደግሃትም፥ በአንድ ሌሊት ለበቀለች፥ በአንድ ሌሊትም ለደረቀችው ቅል አዝነሃል። እኔስ ቀኛቸውንና ግራቸውን የማይለዩ ከመቶ ሀያ ሺህ የሚበልጡ ሰዎችና ብዙ እንስሶች ላሉባት ለታላቂቱ ከተማ ለነነዌ አላዝንምን? አለው።» (ዮና. 4፡10-11)፡፡ የእግዚአብሔርን አስገራሚ ጸጋ በተሻለ ሁኔታ እንዲያስተውል ዮናስን የረዱት ስቃይ ውስጥ የጨመሩት የጸሐይ ጨረሮች ነበሩ፡፡

## ስቃይ የእግዚአብሔርን ታማኝነት እንዲገልጥላችሁ ፍቀዱ

ሥቃይ የእግዚአብሔርን ታማኝነት በይበልጥ ግልጽ ሆኖ እንድናይ ይረዳናል፡፡ እግዚአብሔር አብርሃምና ሳራን ልጅ እንደሚኖራቸው በነገራቸው ጊዜ፣ አላመኑም ነበር፡፡ እንዲያውም፣ ሳራ ሳቀች (ዘፍ. 18)፡፡ የእግዚአብሔርን ታማኝነት ገና አልተማሩም ነበር፡፡ አብርሃም የሳራን ግብጻዊት ደንገጡር አጋርን እንደ የጭን ገረዱ አድርጎ ሲወስድ የእግዚአብሔርን ተስፋ ለመፈጸም ፈልጎ ነበር፡፡ አጋርም እስማኤልን ወለደች፤ በቤቱም ውስጥ ብዙ ችግር ተፈጠረ፡፡ ኋላ ላይ ግን አብርሃም ይስሐቅን ለመሰዋት ተጥሎበት በነበረው ሸክም ስቃይ ውስጥ ባለፈ ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ታማኝነት መጠን አስተዋለ፡፡ ያለፈበት ስቃይ ወሳኝ የሆነን ትምህርት አስጨበጠው፡፡

ዳዊትም ተመሳሳዩን ትምህርት አግኝቶ ነበር፡፡ በመዝ. 37፡25 ላይ እንዲህ በማለት ጻፈ፦ «ጐለመስሁ አረጀሁም ጻድቅ ሲጣል፥ ዘሩም እህል ሲለምን አላየሁም።» በሕይወት ውጣ ውረድ የሞላበት ጎዳና፣ እግዚአብሔር የእርሱ ለሆኑት እንደሚጠነቀቅ መዝሙረኛው አስተውሏል፡፡ ለመሆኑ የእርሱ የሕይወት ጎዳና በምን በምን ውስጥ ነበር ያሳለፈው? ለብዙ አመታት፣ ዳዊት ከንጉስ ሸሽቶ በጢሻ ውስጥ የሚኖር ሽፍታና በቃላት ሊገለጽ የማይችል ከባድ ልምምድ ውስጥ ያለፈ ሰው ነበር፡፡ ጠላቶቹ ቤተሰቡን አፍነዋቸው ነበር፤ ቤቱን አቃጥለውበታል፤ ንብረቱን ሁሉ አውድመውበታል (1 ሣሙ. 30)፡፡ ነገር ግን በእነዚህ ሁሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ፣ የእግዚአብሔርን አስተማማኝነትና ታማኝነት በማስተዋል ከመከራው ውስጥ በረከቶችን አግኝቶአል፡፡

ሁላችንም በስቃይ ውስጥ እግዚአብሔር ምን ያህል ታማኝ እንደሆነ ማስተዋል እንችላለን፡፡ ስለ ታማኝነቱ እርግጠኞች መሆን እንችላለን፦ «ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፥ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም። እርሱ ያለውን አያደርገውምን? የተናገረውንስ አይፈጽመውምን?» (ዘኁ. 23፡19)፡፡

## ስቃይ ወደ እግዚአብሔር ቃል እንዲመራችሁ ፍቀዱ

ንጉሥ ዳዊት ስቃይ ብዙ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ቃል ሊመራን እንደሚችል አስተውሏል፡፡ በመዝ. 119 ላይ እንዲህ በማለት ይጽፋል፣ «እኔ ሳልጨነቅ ሳትሁ አሁን ግን ቃልህን ጠበቅሁ።» (ቁጥር 67)፡፡ « ሥርዓትህን እማር ዘንድ ያስጨነቅኸኝ መልካም ሆነልኝ።» (ቁጥር 71)፡፡ እና፣ «ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው።» (ቁጥር 105)፡፡

በውኸንብር ተሞልቶ በነበረው የአስራዎቹ እድሜዬ፣ በክርስቲያን ቤተሰቤ ማዕቀቦች ላይ አምጽ ነበር፡፡ ለእናቴም እንዲህ አልኳት፡- «ወደ ክርስቲያን ትምህርት ቤት መሄድ ሰልችቶኛል፡፡ የፈለግሁትን ማድረግ የምችል ሰው ነኝ፡፡» ቀስ በቀስም፣ ሳትፈልግ በእኔ ሃሳብ ተስማማችና የሕዝብ ትምህርት ቤት እንድገባ ፈቀደችልኝ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ከወሮበሎች ጎራ ገባሁ፡፡ ይህ በሞኝነት የተሞላው ውሳኔዬ ወደ አደገኛና ግብረገብነት በጎደላቸው ቦታዎች ወሰደኝ፡፡ ከሌሎች ወሮበሎችጋር ባደረግናቸው ድብድቦች ጉዳቶች ይደርሱብኝ ጀመር፡፡ በአካሌ ላይ የደረሰብኝ ስቃይም ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ስር መሰረቴ እንድመለስ አነሳሳኝ፤ ቶሎ ብዬም ወደ ቤተክርስቲያን ትምህርት ቤት ፊቴን መለስኩ፡፡ ከዚያ በፊት አድርጌ በማላውቀው ሁኔታ በጥናቶቼ ላይ አተኮርኩ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል በቃሌ በላሁት፡፡ ረኀኸም ጽሁፎችን በቃሌ ያዝሁ፡፡ ስቃይ ወደ እግዚአብሔር ቃል መለሰኝ፡፡

**ስቃይ በእግዚአብሔር እንክብካቤ ላይ ያላችሁን እምነት ጥልቅ እንዲያደርገው ፍቀዱ**

እግዚአብሔርን በጥልቀት ከታመናችሁት፤ ሁልጊዜ ፈቃዱን የምትፈልጉ ከሆነ፣ እርሱ እርምጃችሁን ይመራዋል (ምሳ. 3፡ 5-6)፡፡ የእግዚአብሔር ምሪት ብዙ ጊዜ ለእርሱ የእንክብካቤ ምሪት ያለንን አድናቆት ጥልቅ በሚያደርጉ ስቃዮች ውስጥ ወደ እኛ ይደርሳል፡፡

የዮሴፍ ታሪክ ይህንን ግሩም አድርጎ ያሳየናል፡፡ ሕይወቱ በእግዚአብሔር የተመራ ነበርና (ዘፍ. 37-50)፡፡ የወደፊት እጣፈንታው ምን ሊሆን እንደሚችል ይጠባበቅ በነበረበት በተጣለበት ጉድጓድም ሆነ፣ ባሪያ ይሆን ዘንድ በወንድሞቹ በተሸጠበት በግብጽ፣ በጶጢፋራ ሚስት ሲከዳ፣ ወይም ያለአግባብ ሲፈረድበት፣ እምነቱን በእግዚአብሔር የፍቅር እክብካቤ ላይ አደረገ፡፡ በመጨረሻም፣ እግዚአብሔር ሥቃዩን ሁሉ ወደ በረከት እንደለወጠለት መሰከረ (ዘፍ. 50)፡፡

ከብዙ አመት በኋላ፣ ዳዊት የተባለ እረኛ የእግዚአብሔርን ምሪት መታመን በሕይወቱ ተማረ፡፡ እንደ እስራኤል ወደፊት ንጉሥ የተለየ መቀባትን ካገኘ በኋላ (1 ሳሙ. 16)፣ ራሱን ለብዙ አመታት ከንጉሡ የሚሸሽ ሸፍታ ሆኖ አገኘው፡፡ ይህ የበረሓ ቆይታው ዳዊትን በመቀባቱና በንግሥናው መካከል በነበሩት ከሠላሳ ለሚበልጡ አመታት በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ እንዲችል አስተማሩት፡፡ እግዚአብሔር በጠመዝማዛ መንገድ ነበር የመራው፤ ነገር ግን ለታላቅ ኃላፊነት የሚያዘጋጀው መንገድ ነበር፡፡ ስቃይ በመንገዳችን ላይ የእግዚአብሔርን ምሪት እንድናገኝ በማድረግ ይባርከናል፡፡

**ስቃይ ወደ እግዚአብሔር እንዲመልሳችሁ ፍቀዱ**

ብዙ ጊዜ ስቃይ ከኮበለልንበት ሩቅ አገር መልሶ ያመጣናል፡ ይህ እውነታ በጠፋው ልጅ ታሪክ በግልጽ ታይቷል (ሉቃ. 15)። ይህ ከቤቱ የኮበለለ ልጅ ድርሻውን ከተቀበለ በኋላ ወደ ሩቅ አገር በመሄድ አባከነው። ለተወሰነ ጊዜ ነገሮች በጥሩ ሁኔታ ተጓዙ። በወዳጆችና መልካም በሚመኙለት ሰዎች ተከቦ ገንዘቡ እስከሚያልቅ ድረስ የጥራቱ ደረጃ ባለ አምስት ኮከብ የሆነን ሕይወት መራ። ከዚያም የድህነትን ስቃይ መቅመስ ጀመረ። አማራጭ በማጣትም፣ አሳማዎችን የመጠበቅ ሥራ ተቀበለ። ይህ ስራ ስብዕናውን ለሚጠብቅ ለማንኛውም አይሁዳዊ እጅግ የተዋረደ ሥራ ነበር። የመጨረሻ የአዘቅቱ

ወለል ላይ ደረሰ፤ ወደ ላይ እንጂ ከዚያ በታች መውረድ ፈጽሞ አይቻልም። እናም የአባቱን ቤት ሲያስታውስ ፣ ወደ ቤቱ ለመመለስ ወሰነ።

ይህ የሂደቱ ቅደም ተከተል ለብዙ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሚኮበልሉ የሚሰራ ነው። ልክ እንደ ሳምሶን፣ የእግዚአብሔርን ባርኮት ኃጢአት በሞላበት ግንኙነት እንዳባከነው፣ ብዙ የጠፉ ሰዎች ከእግዚአብሔራዊ መርሆዎች በመኮብለል በሂደት በስቃይ ውስጥ የሚጨምሩ መዘዞች ይገጥሟቸዋል። ሳምሶን ከወደቀ በኋላ፣ እንደ ባሪያ አገለገለ፤ በፍልስጤማውያን ጨካኝ እጆች አይኑን አጣ። በዚህ የመከራ ሸለቆ ውስጥ፣ ሳምሶን ወደ ትክክለኛው መንፈሳዊ ቦታ ተመልሶ ለመግባት ቻለ፤ በመጨረሻም በሕይወቱ የእግዚአብሔርን ዓላማ ፈጸመ፡፡ ስቃይ የንስሐንና የመታደስን በረከቶች ይዞለት መጣ።

ጆኒ ኤሬክሰን ታድ የራሷን የመከራ ድርሻ ተቋድሳ ነበር። ገና በአስራዎቹ እድሜ ውስጥ ሳለች በደረሰባት አሰቃቂ አደጋ ከአንገት በታች ያለው ሰውነቷ በሙሉ መንቀሳቀስ እንዳይችል በሚያደርግ quadriplegic ደዌ ተመትታ ነበር። ያለ ሰው ድጋፍ መብላት ወይም መጠጣት እንባዋን እንኳን መጥረግ የማትችል በመሆን፣ ሙሉ በሙሉ በሌሎች እርዳታ ላይ የምትደገፍ ሆነች። ከዚህ ጉዳት የተነሳ በቁጣና በተስፋ መቁረጥ ተሞላች። ይሁን እንጂ፣ በእግዚአብሔር ጸጋ ተበረታትታ ለአካል ጉዳተኞች ጥብቅና የምትቆም፣ ለእነርሱ ንግግር የምታደርግ፣ የምትጽፍ፣ የምትዘምርና እድል ፊቱን ያዞረባቸውን ሁሉ የምታነቃቃ ለመሆን በቃች። ጆኒ አንድ ጊዜ እንዲህ ብላ ነበር፡- «ስቃይ ወይ ወደ መንፈሳዊ ነገር ያነቃቃችኋል አልያም ቀዝቃዞች ሊያደርጋችሁ ይችላል። » ደስ የሚያሰኘው ነገር ታዲያ፣ ስቃይዋ ወደ እግዚአብሔር እንድትቀርብና ለብዙዎችም በረከት እንድትሆን የሚያደርጋትን እሳት በውስጧ እንዲለኩስ ፈቀደች። እኛም ስቃዮቻችንን በተመለከተ ከዚህ ያነሰ ነገር ማድረግ የለብንም።

## በረከት ከስብራት ለማግኘት የሚያግዟችሁ ወሳኝ እርምጃዎች

- ስቃይ ትህትናን እንዲያስተምራችሁ ፍቀዱለት
- ስቃይ ስለ እግዚአብሔር ያላችሁን እውቀት የጠለቀ እንዲሆን እንዲያደርገው ፍቀዱ
- ስቃይ የጸሎት ሕይወታችሁን እንዲያጠነክረው ፍቀዱ
- ስቃይ የእግዚአብሔርን ጸጋ እድትቀበሉ እንዲረዳችሁ ፍቀዱ
- ስቃይ የእግዚአብሔርን ታማኝነት እንዲገልጽላችሁ ፍቀዱ
- ስቃይ ወደ እግዚአብሔር ቃል እንዲመራችሁ ፍቀዱ
- ስቃይ በእግዚአብሔር እንክብካቤ ላይ ያላችሁን እምነት ጥልቅ እንዲያደርገው ፍቀዱ
- ስቃይ ወደ እግዚአብሔር እንዲመልሳችሁ ፍቀዱ

# 6

# ስቃይን ማባከንን ተቃወሙ

ወጣት ሳለሁ የሚከተለውን ግጥም በቃሌ ይዤው ነበር፡፡

አንድ ማይል ስጓዝ ከተድላ ጋር፣
ታጫውተኝና ታስቀኝ ነበር፡፡
ስታወራኝ ውላ አድራ ተለየችኝ፣
ታዲያ ምን ያደርጋል፣ ጠቢብና ብልህ አላደረገችኝ፡፡
ከስቃይ ጋር ስጓዝ ሌላውን ማይል፣
አልተነፈሰችም ከቶ አንድም ቃል፡፡
ግን ብዙ ተማርኩኝ፣ ብዙ ብዙ ነገር፣
ስቃይ አብራኝ ስትሄድ ምንም ሳትናገር፡፡

ከስቃያችሁ ምን ትማራላችሁ? ትምህርት ሳያስተምረን የሚያልፍ ስቃይ ያ የባከነ ነው፡፡ በሕመም በተሞላ ልምምድ ውስጥ አልፋችሁ ምንም ነገር ካልተማራችሁ፣ ያንኑ ተመሳሳይ ልምምድ መልሳችሁ የመድገም እድላችሁ ከፍተኛ ነው፡፡

የልብ ስብራትን መቅመስ ማለት ምን ማለት ነው? አዳምና ሔዋን ልጃቸው ቃየል ወንድሙን፣ አቤል፣ ከገደለው በኋላ የተሰማቸው መሪር ሐዘንና ተስፋ መቁረጥን መለማመድ ማለት ነው (ዘፍ. 4)፡፡ በያዕቆብ ስህተት ልጁ ዮሴፍ በአውሬ ተበልቶ እንደሞተ ባሰበ ጊዜ የተለማመደው ልምምድ ማለት ነው (ዘፍ. 37)፡፡ ኢየሱስ ወዳጁ አላአዛር ከሞተ በኋላ ከባድ ኃዘን ተሰምቶት ነበር (ዮሐ. 11፡35)፡፡ በሕይወት የሚፈራረቁ የተለያዩ ወቅቶች፣እኛ ልናስወግዳቸው የማንችላቸውን የልብ ስብራቶች ያመጡብናል፡፡

ከመከራ የተነሳ፣ የልብ ስብራት ደርሶባችሁ ያውቃል? በሕይወት ጎዳና እግዚአብሔር እናንተን ይባርክ ዘንድ ያስቀመጣቸውን ጠመዝማዛ መንገዶች አይታችሁ ታውቃላችሁ? ያበሳጩአችሁ ወይም ሕመም የፈጠሩባችሁ ነገር ግን እናንተን የተሻለ ሰው አድርገዋችሁ ያለፉ ልምምዶችን ታስታወሳላችሁ? በሽታ ወይም በጣም የምትወዱት ሰው ከእናንተ መለየት ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም አሁን እያለፋችሁ ያላችሁበት የልብ ስብራት፣ በግል ሕይወታችሁ የደረሰባችሁ ውድቀት፣ በትምህርት አለም የገጠማችሁ አስቸጋሪ ሁኔታ፣ ወይም በስራ ሙያችሁ የደረሰባችሁ አሳዛኝ ሁኔታ ያስከተለው ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም የልብ ስብራታችሁ፣ በቢሮአችሁ ወይም በቤተክርስቲያናችሁ ወይም በጎረቤቶቻችሁ ጥሩ ስማችሁን ጭቃ የሚቀባ፣ ለአመታት በታማኝ ልፋታችሁ የገነባችሁትን የሚያፈራርስ አሉባልታ ከመነዛቱ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባት

ስቃያችሁ ሃኪማችሁ እንኳ ሊረዳው ያልቻለው የህመም ምልክት ከመኖሩ የተነሳ ከሚሰማችሁ ጭንቀት የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ የስቃያችሁ ምንጭ ምንም ቢሆን ምን፣ ግን አታባክኑት፡፡

ለምድነው ስቃዮቻችንን ማባከን የሌለብን? በዋናነት ከቆሻሻ ሊያነጹን የሚችሉበት ኃይል ስላላቸው ነው፡፡ የዮሴፍ ወንድሞች እንዲህ ያለውን መንጻት በዘፍ. 37-50 ባለው የቃሉ ክፍል ተለማምደውት ነበር፡፡ በለጋ እድሜያቸው፣ በዮሴፍ ላይ እርሱን እስከመግደል የሚያደርስ የቅናት ስሜት ተሰምቶአቸው ነበር፤ እናም በሂደት ለባርነት ሸጡት፡፡ አባታቸውንም ስለ ሰሩት የፈሪ ሥራ በመዋሸት፣ ወንድማቸውን አውሬ በልቶት ሊሆን እንደሚችል ነገሩት፡፡ አመታት እየመጡ ሲያልፉ፣ የዮሴፍ ወንድሞች ከሰሩት እኩይ ተግባር የተነሳ፣ ከቅንዓትና ከመጎምዠት እድፍ እስኪነጹ ድረስ በበደለኝነት ስሜት ስቃይ ውስጥ ፡፡ ከዚህ የበደለኝነት ስሜት ስቃይ የተነሳ፣ አንዳቸው ለሌላቸው መስዋእት ለመሆን ፈቃደኛ የሚሆኑበት የመልካምነት ብስለት ደረጃ ደርሰው ነበር፡፡ እናም ስቃይ ከሞራል እድፍ አነጻቸው፡፡

የቀድሞው ሊቀጳጳስ ፉልቶን ሺን፣ ሐቀኛ ወይም በእንግሊዘኛው ሲንሲር፣ ስለተሰኘው ቃል ሐሳብ ሲሰጡ እንዲህ ብለው ነበር፡- «ሮማውያውን አንድ የእምነበረድ ቁራጭ ሲያገኙ፣ ያገኙት ቁራጭ ጎድጎድ ያለ ነገር ካለው፣ የተስተካከለ ለማድረግ ያንን ጎድጓዳ ክፍል በሰም ይደፍኑት ነበር፡፡ ሰም በላቲን ቋንቋ ሴራ ነው የሚባለው፡፡ ነገር ግን ምንም ጎድጓዳ ነገር የሌለበት ፍጹም የተስተካከለ እምነበረድ ሲያገኙ ሲን ሴራ ይሉታል፤ ይህም «ሰም የሌለው» ማለት ነው፡፡ ሲንሲር የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል አመጣጡ እንግዲህ ይሄ ነው፡፡ (Fulton J. Sheen, *Life Is Worth Living* (San Francisco: Ignatius Press, 1953) 193–194.) በተመሳሳዩ፣ ስቃይ የእርኩሰትን ሰም ያስወግድና፣ የበለጠ በመንፈሳዊ ሕይወት ገጣሚዎችና በመልካም ሥራም የበሰልን እንድንሆን ይረዳናል፡፡

ያዕ. 1፡2-4 ይህንን አሳብ ይገልጻል፡- «ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት፤ ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም።» በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፣ መፈተን ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል ዶኪሚዮን የተሰኘ ነው፡፡ ይህ ቃል አንድ ገንዘብ እውነተኛ መሆኑን ለማወቅ ሳንቲሙን በእሳት በማቅለጥ መፈተሽን ለማመልከት ጥቅም ላይ የሚውል ነው፡፡ ሥቃዮችም በሕይወታችን ያሉትን ቆሻሻዎች በማቃጠል ለእግዚአብሔር ክብር እውነተኛ የሆንን ገንዘቦች እንድንሆን ያደርጉናል፡፡

ሁለተኛ፣ ስቃዮችን ማባከን የሌለብን ታላላቅ ግድድሮሾችን ለመጋፈጥ የሚያስችል ጥንካሬን ስለሚሰጡን ነው፡፡ ወቅታዊዎቹን መከራዎች በጽናት ለመጋፈጥ ፈቃደኞች ስትሆኑ ለወደፊት ለምትጋፈጧቸው አስቸጋሪ ሁኔታዎች ስኬትን እድታገኙ ያስታጥቋችኋል፡፡ ዳዊት በንጉሥ ሳኦል ፊት በመቅረብ ጎልያድን ለመጋጠም ፈቃደኛ ሲሆን፣ ጥቂት ማደፋፈሪያን ብቻ ነበር ያገኘው (1 ሳሙ. 17)፡፡ አስቀድሞ የሳኦል የጦር እቃ ተሸካሚና ሙዚቀኛውም ነበር (1 ሳሙ. 16)፤ በእርግጥም አንድ ለአንድ ትግል

ለመግጠም ፈጽሞ ተመራጭ ያልሆነ እጩ ነበር፡፡ ንጉሥ ሳኦልም እንዲህ አለው፣ «ሳኦልም ዳዊትን፦ አንተ ገና ብላቴና ነህና፥ እርሱም ከብላቴንነቱ ጀምሮ ጦረኛ ነውና ይህን ፍልስጥኤማዊ ለመውጋት ትሄድ ዘንድ አትችልም አለው። » (1 ሳሙ. 17፡33)፡፡

ዳዊት ግን በዚህ ፈርቶ ወደ ኋላ ማለትን አሻፈረኝ አለ፡፡ ይልቁንም፣ ለሳኦል ከዚህ ቀደም ገጥመውት ስለነበሩት ግድድሮሾችና መከራዎች እንዴት ደግሞ በስኬት እንደተወጣቸው ነገረው፡፡ ዳዊት እንዲህ አለ፦ «እኔ ባሪያህ የአባቴን በጎች ስጠብቅ አንበሳና ድብ ይመጣ ነበር፥ ከመንጋውም ጠቦት ይወስድ ነበር። በኋላውም እከተለውና እመታው ነበር፥ ከአፉም አስጥለው ነበር በተነሣብኝም ጊዜ ጕሮሮውን ይዤ እመታውና እገድለው ነበር። እኔ ባሪያህ አንበሳና ድብ መታሁ ይህም ያልተገረዘው ፍልስጥኤማዊ የሕያውን አምላክ ጭፍሮች ተገዳድሮአልና ከእነርሱ እንደ አንዱ ይሆናል።» (1 ሳሙ. 17፡ 34-36)፡፡ ንጉሥ ሳኦል ዳዊት በዚህ ግዙፍ ተዋጊ ላይ ድልን ለመቀዳጀት ኃይል ስለሆኑት አስቀድሞ ስለተጋፈጣቸውና ስላሸነፋቸው ስቃዮችና ግድድሮሾች ምንም የሚያውቀው ነገር አልነበረም፡፡

አንድ የጥንት መዝሙር እንዲህ ይገልጸዋል፦ «ለፈተና እጅ አትስጥ፤ ይህ ኃጢአት ነውና፤ እያንዳንዱ ድል ሌሎች ድሎችን እንድታገኝ ይረዳሃልና» (H. R. Palmer, “Yield Not to Temptation” (1868)) ይህ እውነት ነው፡፡ በወቅቱ እያለፍን ባሉት ፈተናዎች መጽናታችን፣ ወደፊት ለምንጋፈጣቸው ግድድሮሾች ያጠነክረናል፡፡ ኤርሚያስ በሌላ አገላለጽ እንዲህ ያስቀምጠዋል፦ «ከእግረኞች ጋር በሮጥህ ጊዜ እነርሱ ቢያደክሙህ፥ ከፈረሶች ጋር መታገል እንዴት ትችላለህ? በሰላምም ምድር ታምነህ ብትቀመጥ፥ በዮርዳኖስ ትዕቢት እንዴት ታደርጋለህ?» (ኤር. 12፡5)፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ለታላላቅ ግድድሮሾች ለመዘጋጀት ትንንሽ ድሎችን መቀዳጀት ያስፈልገናል ማለት ነው፡፡

ሦስተኛ፣ ስቃዮቻችንን ማባከን የሌለብን የእግዚአብሔርን ሀልዎት (መገኘት) በረከት በሕይወታችን ስለሚያመጡልን ነው፡፡ ይህንን በክርስትና ከመጀመሪያዎቹ ዲያቆናት አንዱ በሆነውና የመጀመሪያው ሰማዕት በሆነው በእስጢፋኖስ ታሪክ ውስጥ እንመለከታለን (የሐዋ. 6-7)፡፡ እስጢፋኖስ ተደጋጋሚና እጅግ ከባድ የሆኑ ተቃውሞዎችን በመጋፈጥ፣ በታማኝነት እግዚአብሔርን አገልግሎአል፡፡ ተይዞ በከፍተኛ ሸንጎ ላይ ለፍርድ በቀረበበት ጊዜ፣ ደግፎ የሚያቆመው የእግዚአብሔር ክብር መገኘት ተሰምቶት ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ፊቱ እንደመላአክ አበራ በማለት ጽፎልናል (የሐዋ. 6፡15)፣ ከዚያም ሰማያት ተከፍተው ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ ተመለከተ (የሐዋ. 7፡ 56)፡፡ የእስጢፋኖስ ጠላቶች እርሱን ለመውገር ድንጋይ ሲያነሱና ሲገሉት በወሰኑ ጊዜ እንኳ፣ ስቃዩ ግሩም ወደሆነው የእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ አስገባው፡፡

እንግዲህ እስካሁን ለምን ስቃያችሁን ልታባክኑ እንደማይገባችሁ ሦስት ምክንያቶችን አግኝታችኋል፡፡ ስቃዮች ቆሻሻን ከእኛ ያስወግዳሉ፤ የበለጡ ታላላቅ ግድድሮሾችን እንድንጋጠም ያጠነክሩናል፤ የእግዚአብሔርንም በግርማ መገኘት ወደ ሕይወታችን ያመጡልናል፡፡ እንደ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ዮሴፍ፣ ሙሴ፣ አስቴር፣ ሩት፣ ኤልያስና ኢዮብ ያሉት ስቃያቸውን ያላባከኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ወንድና ሴት ጀግኖችን ታሪክ ስንመለከት እነዚህን ተመሳሳይ ሶስት ነገሮችን እናገኛለን፡፡

**ስቃይን ተጠባበቁ**

ስቃዮቻችሁን ሳታባክኑ ስትቀሩ እነዚህን ሁሉ በረከቶች የምታገኙ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ምን ልታደርጉ ይገባል? ስቃይን ተጠባበቁ፡፡ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ መከራ እንደሚደርስባቸው አስጠንቅቋቸው ነበር፡፡ እንዲህም አለ፡- «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፡፡» (ማቴ. 16፡33)፡፡ ጳውሎስም በ2 ጢሞ. 3፡ 12 ላይ ተመሳሳይ ስሜትን ያንጸባርቃል፡- «እግዚአብሔርን እየመሰሉ ለመኖር የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ፡፡» አይቀሬ የሆነውን ስቃይ ለማምለጥ መሞከርን አቁማችሁ፣ ከስቃያችሁ ለማትረፍ ተማሩ፡፡

**ስቃይን እንደ ፈተና ተመልከቱ**

ስለ ስቃይ ትክክለኛ አለመካከት ካለን፣ እንደ ፈተና እንመለከተዋለን፡፡ «ጌታ የሚወደውን ይቀጣዋልና፥ የሚቀበለውንም ልጅ ሁሉ ይገርፈዋል» (ዕብ. 12፡6)፡፡ ምናልባትም ይህ ኢየሱስ ለጴጥሮስ እንዲህ በማለት የተናገረው ሊሆን ይችላል፡- «ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤» (ሉቃ. 22፡31)፡፡ ኢየሱስ ጴጥሮስን ከፊት ለፊቱ የሚጠብቀውን መከራ በመጨረሻ ለትልቅ በረከት እንደሚያበቃው ፈተና እንዲቆጥረው ፈልጎ ነበር፡፡

እንዲህ ላሉት ፈተናዎች ምላሽ ልንሰጥ የሚገባን እንዴት ነው? አንዳንድ ጥያቄዎች መጠየቅ እዚህ ላይ ይረዳናል፡፡ በመጀመሪያ፣ ለዚህ ፈተና ምላሽ እየሰጠሁ ያለሁት እንዴት ነው? ሁለተኛ፣ እንዴትስ ምላሽ ልሰጥ ይገባኛል? እንደዚሁም በመጨረሻ፣ከዚህ በስቃይ ከተሞላ ሁኔታ ምን እየተማርኩ ነው? እነዚህ ጥያቄዎች ለስቃይና ለፈተና ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት እንድንችል ያግዛሉ፡፡

**ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ጥልቅ የሆነ ሕብረትን ተለማመዱ**

ስቃይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዚህ በፊት ከተቋቋማቸው መከራዎች ጋር የእናንተንም ልምምድ በማመሳሰል፣ ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ወደ ማድረግ ሊመራችሁ ይችላል፡፡ ያመናችሁት ሰው ከድቶአችሁ ያውቃል? ኢየሱስም ይህ ደርሶበታል፡፡ ክብራችሁ ተገፎ ያውቃል? ኢየሱስም ይህ ደርሶበታል፡፡ በወዳጆቻችሁ ተትታችሁ፣ ወይም በስህተት ተወንጅላችሁ፣ ወይም ቃሎቻችሁ በስህተት ተተርጉመው፣ ወይም አጥፊ የሆነ ሐሜት ሰለባ ሆናችሁ ታውቃላችሁ? ኢየሱስም ይህ ሁሉ ደርሶበታል፡፡

ከአዳኛችን ሕይወት ጋር የራሳችንን አመሳስለን እንድናይ የሚያደርጉን ስቃዮች ናቸው፡፡ ምንም እንኳን እጃችን በሚስማር ባይቸነከር፣ ጎናችን በጦር ባይወጋ፣ እኛም ስቃዮቻችንን እርሱ ሰቆቃውን በተቀበለበት ተመሳሳይ መረጋጋት በመቀበል ለኢየሱስ ያለንን ፍቅር ልናሳይ እንችላለን፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ጥማቱን የገለጠው በሚከተለው መንገድ ነበር፡- «እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፥ በመከራውም እንድካፈል፥ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፥ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ።» (ፊል. 3፡ 10-11)፡፡ ከኢየሱስ ጋር ያላችሁን ግንኙነት የበለጠ ጥልቅ እንዲያደርጉት ለስቃዮቻችሁ በመፍቀድ ዋጁዋቸው፡፡ ታላቅ የሆነ ሕይወት መከራን ለመጋጠምና በዚያም በጽናት ለማለፍ ያነቃቃናል፤ ያበረታናል፡፡ ኑት ሮክኒ በ1920ዎች የነበሩ የዩንቨርስቲ ኦቭ ኖተርዳም የእግር ኳስ ቡድን አሰልጣኝ ሲሆኑ፣ ጂዎርጅ ጊፐር ደግሞ ቁልፍ ተጫዋቻቸው ነበር፡፡ ታሪኩ ሲቀጥል ጊፐር ታመመ፤ እንደሚሞትም ባወቀ

ጊዜ፣ አሰልጣኙን ሮኪኒን አንድ ነገር ቃል እንዲገቡለት ጠየቃቸው፤ ይኼውም ቡድኑ ችግር በሚገጥመው ጊዜ፣ «አንድ ጊዜ ለጊፐር ስትሉ አሸንፉ» እያለ እንዲያነቃቃቸው ነበር፡፡ በእርግጥም፣ የኖተርዳም ቡድን እየተሸነፈ በነበረበት አንድ ግጥሚያ ላይ አሰልጣኛቸው የጆርጅ ጊፐርን መጠይቅ አስታወሳቸው፡፡ የዚያ የቡድናቸው አባል ትዝታና ፍቅር እየተንገዳገደ የነበረውን ቡድን እንደገና ጠንክሮ ለድል እንዲበቃ ኃይል ሆነው፡፡ እንደ ክርስቲያኖች እኛንም ሊያነቃቃን የሚችል የኢየሱስ ሕይወት አለን፡፡ ስቃዮቻችን ከዚህ ሞትን አሸንፎ ከተነሳው ጌታችን ጋር ያለንን ሕብረት ጥልቅ እንዲያደርጉት ብንፈቅድላቸው፣ በተደጋጋሚ እኛም ድልን ለጌታችን እንቀዳጃለን፡፡

ስቃያቸውን የሚያባክኑ ሰዎች በሌሎች ነገሮች ሁሉ ውስጥ ያለውን መልካም መዓዛ ለማሽተት የሚያስችላቸውን በመከራ ውስጥ ያለውን ሽቶ አያሸቱም፡፡ ከዚህ የተነሣ፣ ጳውሎስ እንዲህ በማለት የተናገረውን ደስታ የመለማመድ እድሉ ያመልጣቸዋል፡- «እግዚአብሔርን ለሚወዱ እንደ አሳቡም ለተጠሩ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ ይደረጋል፡፡» (ሮሜ. 8፡28)፡፡

### ስቃያችሁን ላለማባከን የሚያግዟችሁ ወሳኝ እርምጃዎች

- ስቃይን ተጠባበቁ
- ስቃይን እንደፈተና ተመልከቱ
- ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ጥልቅ የሆነ ሕብረትን ተለማመዱ

# 7

# የመከራን አይቀሬነት ተቀበሉ

በ1970ዎቹ በሊን አንደርሰን አቀራረብ ዝነኝነትን አግኝቶ የነበረው የጥንቱ የጆሳውስዝ ዜማ ቃላት እንዲህ በማለት እውነታን የሚያውጁ ናቸው፡- «ይቅርታ እጠይቅሻለሁ፤ አላልኩም እኮ በጽጌሬዳ የአትክልት ቦታ አኖርሻለሁ፡፡» እነዚህ ቃላት በሕይወት ውስጥ የመከራን አይቀሬነት በተመለከተ የሚናገሩ ናቸው፡፡

ሕይወት የጽጌሬዳ የአትክልት ቦታ እንድትሆንላችሁ ጠብቃችሁ ታውቃላችሁ? «የሕይወት መዝሙር» በተሰኘው ግጥማቸው ሄነሪ ዋደስወርዝ ሎንግፌሎው እንዲህ ብለው ነበር፣ «ሕይወት እውን ናት! ሕይወት ጥልቅ የሆነ ቁምነገርን ያዘለች ናት፡፡» ሕይወት ከማንኛውም ተባይና አጥፊ አውሬ ነጻ የሆነ በጥንቃቄ የተያዘ የአትክልት ቦታ ሳትሆን፣ መከራ፣ ችግርና ፈተና ይደርስብናል ብለን የምንጠባበቅባት ጥቅጥቅ ብሎ እንዳደገ ጫካ ናት፡፡ የኢዮብን አመለካከት አስታውሱ፡- «ከሴት የተወለደ ሰው የሕይወቱ ዘመን ጥቂት ቀን ነው፥ መከራም ይሞላዋል።» (ኢዮብ 14፡1)፡፡ በእርግጠኝነትትክክለኛ የሆነ ሕይወት ለመኖር ከፈለጋችሁ መጽሐፍ ቅዱስ መከራ እንደሚደርስባችሁ ይነግራችኋል፡፡ የሐዋርያው ጳውሎስን ቃላት አዳምጡ፣«በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ።» (2 ጢሞ. 3፡12)፡፡

ጳውሎስ እንደሚጠቁመው ከመከራ ነጻ የሆነ ሕይወት ካለን፣ ወይ የክርስቶስ አይደለንም አልያም እግዚአብሔርን እየመሰልን በቀናው መንገድ ለመኖር ፍላጎቱ የለንም፡፡ ነገር ግን ማንኛውም በእግዚአብሔር ፈቃድ እየተመራ ለመኖር የሚፈልግ እውነተኛ ክርስቲያን ከሌሎች ዘንድ መከራ እንደሚደርስበት መጠባበቅ ይችላል፡፡

መከራ ሁልጊዜ የሚመጣው በሌላ ሰው እጅ አይደለም፡፡ በጥጋብም ጊዜ ሆነ በእጦት ጊዜ ሊከሰት ይችላል፡፡ ሉቃ. 12 እጅግ ለየት ባለ ሁኔታ የተትረፈረፈ ምርት ሰብስቦ ስለነበረ አንድ ሃብታም ሰው ይገልጻል፡፡ እርሻው እጅግ ብዙ ምርት ከመስጠቱ የተነሳ የሚያስቀምጥበት ቦታ አልነበረውም፤ ከዚህም የተነሳ ተጨማሪ ጎተራ መስራት አስፈለገው፡፡ ሁሉም ሰው ሊያይ በሚችለው ሁኔታ ሁሉንም ነገር ተቆጣጥሮ ነበር፤ ሊያጋጥመው የሚችልን ማንኛውንም ምድራዊ ችግር ለመፍታት በቂ ገንዘብ ነበረው፡፡ ነገር ግን አንድ ወሳኝ የሆነ እውነታን በተመለከተ ፍጹም ጨልሞበት ነበር፤ ይኼውም ገንዘቡን ሁሉ ወደ ኋላ በመተው ያን ቀን እንደሚሞት አለማስተዋሉ ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ መትረፍረፍ ራሱ መከራን ያመጣል፡፡ ልክ ንጉስ ሳኦል በዳዊት ስኬት እንደቀናው ሰዎችን በቅናት በእኛ ላይ ሊያነሳሳቸው (1 ሳሙ. 18፡ 8-9)፣ ወይም ጤናማ ያልሆነ የአኗኗር ዘይቤን እንዳይከተሉ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ የብሪታኒያው ገጣሚ፣ ሩድያርድ ኪፐሊንግ፣ የሚከተለውን የጻፉት ስኬት ስለሚያመጣው ልዩ ችግር እኛን ለማስጠንቀቅ ነው፡- «ድልንና ሽንፈትን፣ እነዚህን ሁለቱን አጥፊዎች በተመሳሳይ መልኩ

ልናስተናግዳቸው ይገባል፡፡» ኪፐሊንግ ግልጽ የሆነ ስኬት ልክ ግልጽ የሆነ ሽንፈት የሚያመጣቸውን ብዙ መሰናክሎች ይዞ እንደሚመጣ አስተውለው ነበር፡፡

**ተስፋ ቆርጦ መተውን አስወግዱ**

ሕይወት የጽጌሬዳ አትክልት ቦታ ትሆናለች ብሎ ከመጠበቅ ይልቅ፣ መከራዎቻችሁን እጃችሁን ዘርግታችሁ በመቀበል እንዴት ልታደንቋቸው እንደምትችሉ ተማሩ፡፡ ቅንነትን የተላበሰ ሰው ለመሆን ከፈለጋችሁ፣ መከራ አይቀሬ ነው፤ እናም በደስታ ተቀበሉት፡፡ «በሁሉ አመስግኑ» ይላል ጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች ሲመከራቸው (1 ተሰ. 5፡18)፡፡

ኢዮብ ታላቅ መከራ በደረሰበት ጊዜ፣ በመጀመሪያ ፍጹም በመረጋጋት ነበር ነገሮችን የተቀበለው፡፡ ሃብቱን፣ ልጆቹንና ጤናውን ቢያጣም እንኳ፣ እግዚአብሔርን መርገምን አሻፈረኝ አለ፡፡ የልጆቹን ማለቅ ከተረዳ በኋላ ሲቃ እየተናነቀው እንዲህ አለ፡- « እግዚአብሔር ሰጠ፣ እግዚአብሔር ነሳ፣ የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን» (ኢዮ. 1፡ 21)፡፡ ከዚያም የሆነ ነገር ሆነና ኢዮብ የድምጹን ቃና ለወጠ፡፡ በኋላ ኢዮብ «አሳዛኝ አጽናኞች» በማለት የጠራቸው ሦስቱ ወዳጆቹ ሊጎበኙት መጡ፤ እግዚአብሔር የሰራው ሥራ ፍትሐዊ እንዳልሆነ እንዲያስብም አደረጉት፡፡

በመጨረሻ ኢዮብ እንዲህ አለ፡- «በፊቱ ሙግቴን አዘጋጅ ነበር፥ አፌንም በማስረጃ እሞላው ነበር።» (ኢዮ. 23፡4)፡፡ ኢዮብ ሳይወድ በግድ የደረሰበትን መከራ ከመቀበል አልፎ ከእግዚአብሔር ጋር መፋጠጥ ሲጀምር፣ እግዚአብሔር ተናገረ፡፡ ኢዮብንም በመስቀለኛ ጥያቄ አጣደፈው (ኢዮ. 38)፡፡ ውስጥን ሰርስረው በሚገቡት ጥያቄዎቹም ኢዮብን ወደ ታላቅ እምነት መራው፡፡

በመከራዎቻችሁ መደሰት ከፈለጋችሁ፣ መቼስ ምን አደርጋለሁ በሚል መንፈስ ልትቀበሏቸው አትችሉም፡፡ ግልጽነትን በተሞላ ትጋት ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገሩ፡፡ እርሱ ደግሞ አስቀድሞ የእናንተን አሳብ ያውቃል፡፡ ባላችሁ ውስን እውቀትና ስቃይ ጉዳያችሁን ለእርሱ አቅርቡ፡፡ እርሱም አይጥላችሁም፡፡

እናቴ በሞተች ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ እጅግ ተቆጥቼ ነበር፤ ያንንም ለመደበቅ አልሞከርኩም፡፡ ምን ያህል እንዳዘንኩኝ ነገርኩት፤ ነገር ግን ጸሎቶቼ ያልተመለሱ መሰሉ፡፡ የተመኘሁት አንድ ነገር ቢኖር እናቴ ራሷን ከማታውቅበት ሁኔታ አንድ ጊዜ ብቻ ወጥታ ልሰናበታት እችል ዘንድ ነበር፡፡ ነገር ግን ያ አልተሳካም፡፡ «አንተ ራስህን አምላክ ብለህ ትጠራለህ» አልኩ በማጉረምረም ተሞልቼ፣ « ይሁን እንጂ እንዲህ ያለውን ቀላል ጸሎት እንኳ መመለስ አትችልም፡፡ ታዲያ ለምን አገለግልሃለሁ?»

በራሱ ጊዜ እግዚአብሔር ያንን ያደረገበትን አላማ ግልጽ አደረገልኝ፡፡ የእናቴ ሞት ፈጽሞ ያልተጠበቁ በረከቶችን ይዞልኝ እንደመጣ እንድመለከት አደረገኝና ምንም አይነት ስህተት እንዳልሰራ አሳየኝ፡፡ ከዚህ በፊት አይቼ የማላውቀውን፣ አንድ ሰአት የሚፈጅ፣ የእናቴን ቪዲዮ እንዳይ ሁሉ አደረገኝ፡፡ ያም ታላቅ መጽናናት አመጣልኝ፡፡ ልክ እርሱ ራሱን ለኢዮብ እንደገለጸ ፈቃዱን ለእኔም በግልጽ አስቀመጠልኝ፡፡

ምንም እንኳ መከራዎችን ልናስወግዳቸው ባንችልም፣ መቼስ ምን ይደረጋል?! በሚል መንፈስ ተቀብለን ራሳችንን አለማግለል ያስፈልጋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በሁሉ እንድንጸልይና ጥያቄያችንንም በእርሱ ፊት እንድናሳውቅ ይነግረናል (ፊል. 4፡6-7) ፡፡ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት በጸሎት በድፍረት መቅረብና መጽናናትንና ምሪትን መቀበል

ትችላላችሁ (ዕብ. 4፡16) ፡፡

**ቁጣችሁን ግሩት**

ምናልባት መከራዎቻችሁን በተመለከተ መቼስ ምን ይደረጋል በሚል የማፈግፈግ መንፈስ ለመቀበል አትፈተኑ ይሆናል፤ በተቀራኒው፣ በቁጣ ተሞልታችሁ እያስተናገዳችኋቸው ይሆናል፡፡ ኤሳው ያደረገው ያንን ነበር፡፡ ያዕቆብ አታልሎት ብኩርናውን ከወሰደበት በኋላ፣ ኤሳው በቁጣ ተሞልቶ ወንድሙን ሊገለው ፈለገ፤ እንዲህም አለ፡- «አባቴ ከሞተ በኋላ፣ ያዕቆብን እገለዋለሁ፡፡» (ዘፍ. 27፡ 41)፡፡ ኋላ ላይ ግን እንዲህ ያለው አስተሳቡ ስህተት እንደነበረ በማስተዋል ከወንድሙ ጋር ታረቀ፡፡ ለመከራዎቻችሁ በቁጣ የተሞላ ምላሽ አትስጡ፡፡

በ 9/11 (መስከረም 1) በዩናይትድ ስቴትስ ላይ ከደረሰው የአሸባሪዎች ጥቃት በኋላ፣ ከብዙ አሜሪካውያን የሚገነፍል ቁጣ ነበር፡፡ አንዳንዶች እንዲያውም የሕገ መንግስቱን የዜጎች መብት ሕግ በመጣስ የበቀል እርምጃን ለመውሰድ ሁሉ ፈለጉ፡፡ ይህ ሁሉ ታዲያ ለአሸባሪዎቹ ስለ ሰሩት ክፉ ድርጊት ዋጋቸውን ለመክፈል ነበር፡፡ ሌሎች ዜጎች ደግሞ፣ ከቁጣቸው ግለት የተነሳ፣ እስረኞችን ማሰቃየትን በመደገፍ ተናገሩ፡፡ ቁጣ (ንዴት) እምብዛም የሚገነባ ምላሽ አይሆንም፡፡

ዮናስ ገጠመኝ ብሎ ላሰበው መከራ የሰጠውን በቁጣ የተሞላ ምላሽ ታስታውሳላችሁ? እግዚአብሔር የፍርድን መልእክት ይሰብክ ዘንድ ወደ ነነዌ ላከው፡፡ በመጀመሪያ ከፐሪው ለመሸሽ ጥረት ካደረገ በኋላ፣ ዮናስ በዳተኝነት መንፈስ ታዘዘ፤ ከተማዋም ንስሐ ገባች፡፡ ነገር ግን ከዚያ በኋላ ዮናስ ተናደደ፡፡ እግዚአብሔር ከተማዋን ያጠፋታል ብሎ ተስፋ አድርጎ ነበር፡፡ በሃዘን ስሜት ተሞልቶ ከከተማዋ ቅጥር ውጪ ወጥቶ አንድ ኮረብታ አገኘ፡፡ በዚያም እግዚአብሔር ቀጥሎ ምን እንደሚያደርግ ለመመልከት ተጠባበቀ፡፡ እግዚአብሔርም በተአምራዊ መንገድ አንዲት ተክል እንድትበቅል አደረገ፤ ተክሏም ከበጋው ጠራራ ጸሐይ ቃጠሎ አስጠለለችው፡፡ ነገር ግን ተክሏ ባደገችበት ፍጥነት ወዲያው ደርቃ ረገፈች፡፡ ዮናስንም በቁጣ ተሞልቶ ምላሽ እንዲሰጥ አደረገው፡፡ እግዚአብሔርም ለዮናስ እንዲህ አለው፣ «ስለዚህች ተክል ለመቆጣት መብቱ አለህን?» በማለት ጠየቀው፡፡

እርሱም እንዲህ በማለት መለሰ፡- «እስከ ሞት ድረስ እቈጣ ዘንድ ይገባኛል» (ዮናስ 4፡9)፡፡ እግዚአብሔርም ለዮናስ እንዲህ በማለት ትልቅ ትምህርት ሰጠው፡- «አንተ ትበቅል ዘንድ ላልደከምህባት ላላሳደግሃትም፥ በአንድ ሌሊት ለበቀለች፥ በአንድ ሌሊትም ለደረቀችው ቅል አዝነሃል። እኔስ ቀኛቸውንና ግራቸውን የማይለዩ ከሙቶ ሀያ ሺህ የሚበልጡ ሰዎችና ብዙ እንስሶች ላሉባት ለታላቂቱ ከተማ ለነነዌ አላዝንምን? አለው።» (ዮናስ 4፡10-11)፡፡

ለመከራዎቻችሁ በቁጣ የተሞላን ምላሽ ለመስጠት እምቢ ስትሉ በጥበብ የተሞላ ውሳኔን ትወስናላችሁ፡፡ ይህ ማለት ግን በምትጸልዩበት ጊዜ ስለ ስቃያችሁና ምሬታችሁ በመግለጽ በእግዚአብሔር ፊት በሐቀኝነት መጸለይ አትችሉም ማለት አይደለም፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ቅሬታም ካለ አክብሮትን በተሞላ መንገድ በእርሱ ፊት ማሳወቅ አትችሉም ማለትም አይደለም፡፡

**ደስተኛ ሁኑ**

ያዕቆብ ከኤሳው ቁጣና ከኢዮብ መቼስ ምን ይደረጋል በማለት ችግርን ከመቀበል ይልቅ

የተሻለ ምላሽ መስጠት እንደምንችል ይጠቁመናል፤ ይኼውም በደስታ መቀበል ነው፡፡ እንዲህ በማለትም ይጽፍልናል፡- ‹‹ወንድሞቼ ሆይ፥ …ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት›› (ያዕ. 1፡2)፡፡ ይህ በእውነት ለመከራ ልንሰጠው የምንችለው አስገራሚ ምላሽ አይደለምን? በእርግጥም እየተናገረ ያለው፣ ‹‹በመከራዎቻችሁ ደስ ይበላችሁ›› የሚል ሃሳብን ነበር፡፡

ምናልባት መከራዎቻችሁ ካለፉ በኋላ በእነርሱ መደሰት ቀላል ሊሆንላችሁ ይችላል፡፡ ብዙ ጊዜ የኋሊት ስትመለከቱ ነው የእግዚአብሔርን አላማ በበለጠ በግልጽ አይታችሁ ከዳዊት ጋር እንዲህ ማለት የምትችሉት፡- ‹‹ሥርዓትህን እማር ዘንድ ያስጨነቅኸኝ መልካም ሆነልኝ።›› (መዝ. 119፡ 71)፡፡ የኋላውን በማሰብ ዮሴፍ ለወንድሞቹ የተናገራቸው እነዚህ ቃላት በእናንተም ውስጥ ያስተጋቡ ይሆናል፡- ‹‹ እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው።›› እግዚአብሔር ምን አስቦ እንዳደረገው ምንም አይነት ፍንጭ ሳይኖራችሁ የመከራ ማዕበል ሕይወታችሁን ሲያላጋ በመከራዎቻችሁ መደሰት በጣም ከባድ ይሆንባችኋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ እንዲህ ባለው ሁኔታ ውስጥ በደስታ በምትሞሉበት ጊዜ እርሱን በበለጠ ታከብሩታላችሁ፡፡

ጳውሎስና ሲላስ በፊልጲስዩስ እስርቤት በተወረወሩ ጊዜ እግዚአብሔር ቀጥሎ ሊሰራ ስላለው ሥራ የሚያውቁት ብዙ ነገር አልነበረም፡፡ በቁስላቸው ላይ ደማቸው እስኪረጋ ድረስ ገርፈዋቸው ነበር፡፡ ከዚያም እጅና እግራቸውን እንዳይነቃነቁ አድርገው ከግንድ ጋር በማሰር በእስር ቤት ውስጥ አስገቧቸው፡፡ ነገር ግን ከመከራና ከስቃያቸው በተቃራኒ በመከራቸው ተደሰቱ፤ የወህኒ ቤቱ መሠረት በተአምራዊ የመሬት መናወጥ እስኪነቃነቅ ድረስ በእኩለ ሌሊት ለእግዚአብሔር በምስጋና ዘመሩ፡፡ እነዚህ ታላላቅ ክርስቲያኖች በመከራቸው ከመደሰታቸው በፊት የእግዚአብሔር ፈቃድ ግልጽ ብሎ እስኪታያቸው ድረስ አልጠበቁም፡፡ የከበባቸውን አስቸጋሪ ሁኔታ በምስጋና ተቀበሉት፡፡

በእርግጥም ሊያደርጉት የሚገባቸው ነገር ያንን ነበር፤ ኢየሱስ እንዲህ እንዲያደርጉ አዞአቸው ነበርና፡፡ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ በማለት ነበር የመከራቸው፡- ‹‹ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፥ ሐሴትም አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና።›› (ማቴ. 5፡ 11-12)፡፡

ይሄ ምክር ምን አይነት ትርጉም ይሰጠናል? በእጅጉ መደሰት አለባችሁ፡፡ በእርግጥም ምክሩ መደሰት እንደሚያስፈልግ ነው የሚነግረን፡፡ በክርስቲያኖች መቃብር ላይ ብዙ ጊዜ ስሳተፍ የሚደንቀኝ ወደቤት መሄድ ተብሎ በተለምዶ በሚጠራው ሥርአት ላይ ያለው የደስታ ገጽታ ነው፡፡ ሰዎች የደስታ ዝማሬዎችን ይዘምራሉ፤ የሞቱት ሰዎችም አበርክቶት ይታወጃል፡፡ እንደነዚህ ያሉ አገልግሎቶች በ1 ተሰ. 4፡13 ላይ ያሉትን ቃላት ያስታውሱኛል፡- ‹‹የክርስቲያኖች ሐዘን ተስፋ እንደሌላቸው እንደሌሎቹ አይደለም፡፡››

መከራዎቻችሁን ደስታ በተሞላ አቀባበል ትቀበሏቸዋላችሁ፤ ደግሞስ በምስጋና ሐሴት ታደርጋላችሁ? የዶር. ማርቲን ሉተር ኪንግ ሕይወት በብዙ የሞት ስጋት ውስጥ ተሞልቶ የነበረም ቢሆን በመጨረሻ ያደረጉት ንግግር ግን የምስጋና ቃላትን የሚያስተጋባ ነበር፡፡ በንግግራቸውም ወደተራራው ጫፍ ላይ እንደወጡና የተስፋይቱን ምድር እንደተመለከቱ ተናገሩ፡፡ ‹‹ወደዚያ ከእናንተ ጋር አልገባም ይሆናል›› አሉ በንግግራቸው፡፡ ‹‹ነገር ግን እኛ

እንደ ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ አገር እንገባለን፡፡» መከራቸውን በደስታ በመቀበል ስቃያቸውን ወደ ትርፍ ለወጡት፤ የእርሳቸውም አርአያነት እስከዛሬ ከእኛ ጋር የሚኖር ሲሆን፣ ደግሞም ያነቃቃናል፡፡

**በትዕግስት የመጽናትን ፍሬ ሰብስቡ**

መከራን በምትጋፈጡበት ጊዜ የደስታ ዘሮችን ስትዘሩ ምን አይነት ፍሬ ለመሰብሰብ ትችላላችሁ? ከምትሰበስቧቸው ፍሬዎች መካከል አንዱ በትእግስት የመጽናት ፍሬ ነው፡- «ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥» (ያዕ. 1፡3)፡፡ በመከራ ውስጥ በጽናት ማለፍ መቻል አስገራሚ የሆነ በረከት ነው፡፡ መልካም ለማድረግ እንዳንዝል ያደርገናል፤ ምንም አይነት መልካም ነገር እንዳልጎደለብንና መኸሩም እርግጥ እንደሆነ እንድናስታውስ ያደርገናልና፡፡

ጽናት ቶሎ ብለን እንዳናቋርጥ ያደርገናልና ግሩም የሆነ ጠባይ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ፣ ከሥጋ ድካም የተነሣ፣ የእግዚአብሔር እቅድ ፍሬ ከማፍራቱ በፊት ለማቆም እንፈተናለን፡፡ ዮሴፍ ወደ ግብጽ ከተሸጠ በኋላ ሁሉን እርግፍ አድርጎ ቢተወው ኖሮ ምን ይሆን ነበር? በጣም በማዘን በእግዚአብሔር ላይ ተስፋውን ቆርጦ ቢሆን ኖሮስ? ይህ ታላቅ የእምነት አባት እንቅፋቶችን እያለፈ ለመቀጠል ባለመቻል ብዙ ግሩም በረከቶችን ያጣ ነበር፡፡ በጽናት ባይሻገር ኖሮ የግብጽ ጠቅላይ ሚኒስቴር መሆን ባልቻለ ነበር፡፡

መከራዎቻችንን በደስታ መቀበላችን ጽናትን እንደሚያስገኝልን፣ ጽናት ደግሞ ብስለትንና ፍጽምናን ያመጣልና (ያዕ.1፡4)፡፡ ማቹር(ሙብሰል) የተሰኘው የእንግሊዘኛ ቃል(በተለይም እንደ ግስ ጥቅም ላይ ሲውል) ቴሌዮኦስ ከሚለው የግሪክ ቃል የተተረጎመ ነው፤ ይህ ደግሞ እግዚአብሔር እኛን የፈጠረበትን አላማ መፈጸምን የሚገልጽ ቃል ነው፡፡ እግዚአብሔር የፈጠረን ምልዑና ፍጹም እንድንሆን ነው፤ እናም በምንጸናበት ጊዜ ወደ ሙላትና ስኬት እንደርሳለን፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ብስለትንና ምልዑነትን በሕይወቱ የተቀዳጀ ሰው ነበር፡፡ ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ ለመንፈሳዊ ልጁ ለጢሞቲዎስ ሲጽፍለት እንዲህ ነበር ያለው፡- « መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።» (2ጢሞ. 4፡7-8)፡፡ ጳውሎስ እግዚአብሔር ለእርሱ ሕይወት ያለውን አላማውን እንዳሟላ ያምን ነበር፤ መልካሙን ገድል ተጋደለ፤ ሩጫውን ጨረሰ፤ እምነቱንም ጠበቀ፡፡ ከሞት ባሻገር እግዚአብሔር ለዘላለም እንዲኖር በሚባርከው ጊዜ የሚቀበለውን የጽድቅ አክሊል ሲጠባበቅ ሳለ ፍጹም እርካታ ተሞልቶ ነበር፡፡

ሌላስ እግዚአብሔር ለሕይወቱ ያዘጋጀለትን አላማ ከግቡ ያደረሰ ወይም ያደረሰች ሰው ልታስቡ ትችላላችሁ? ምናልባት የቢሊ ግርሃም ስም ወደ አእምሮአችሁ ይመጣ ይሆናል፡፡ እኚህ ታላቅ ወንጌላዊ የመንፈሳዊ ልእቀት ተጠቃሽ ሞዴል መሆናቸው ጥርጥር የለውም፡፡ ከእርሳቸው ሥም ጋር ምንም አይነት ቅሌት እስካሁን አልተቆራኘም፡፡ ምክንያቱም ቀለል ያለና ፍሬያማ ሕይወት ስለነበራቸው ነው፡፡ ከመስከረም 11፣ 2001 በአሜሪካ ሕዝብ ላይ ከደረሰው አሳዛኝ ጥቃት ማግስት ለሕዝቡ ንግግር ያደርጉ ዘንድ የተጠየቁበትም ምክንያት ምናልባት ይኸ ሊሆን ይችላል፡፡

የሕይወቱን አላማ ከግብ በማድረስ ረገድ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ የትም አይገኝም፡፡ ጄምስ አለን ፍራንሲስ «አንድ ብቸኛ ሕይወት» በማለት የኢየሱስ ሕይወት ያሳደረውን ተጽእኖ አስመልክተው አንድ ጽሑፍ ጽፈው ነበር፡፡ ገና ልጅ ሳለሁ ነበር እነዚህን ቃላት በቃሌ የሸመደድኳቸው፡- «እስከ ዛሬ ወደ ጦር ሜዳ የዘመቱ ሠራዊቶች ሁሉ፣ የባሕር ኃይል ተዋጊዎች ሁሉ፣ የምክር ቤት አባላት ሁሉ እንደዚሁም የነገሡ ነገስታት ሁሉ፣ አንድ ላይ ቢጨፈለቁ፣ ያ አንድ ብቸኛ ሕይወት በሰዎች ላይ ያሳደረውን ተጽእኖ አላሳደሩም፡፡» (James Allen Francis, “One Solitary Life,” Palmer G. Brown, ed. (Glendale, CA: Karen Brown Agency, 1973).) ታሪክ ከኢየሱስ ሕይወት የተነሳ ከክርስቶስ ልደት በፊትና ከክርስቶስ ልደት በኋላ በማለት ተከፈለ፡፡ በዚያም መስቀል ላይ «ተፈጸመ» በማለት ሲጮኽ፣ ምንም እንኳ በሰማይ ለዘላለም ቢቀጥልም፣ በምድር ላይ ከኖሩት ሁሉ ታላቅ የሆነው ሰው ሕይወት አለፈ፡፡

አዳኛችን ወደ ምድራችን በመምጣትና የጽናትና የብስለት መንፈሳዊ ፍሬን የሚፈልገውን ድርጊት በመፈጸም፣ ይኼውም ለኃጢአታችንም በመሞት፣ የሕይወቱን አላማ አከናወነ፡፡ ዕብ. 12፡2 ኢየሱስ «መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።» እንዳለፈ ይናገራል፡፡ የሕይወታችሁን አላማ መፈጸም ትችሉ ዘንድ የጽናትን ፍሬ ለማጨድ ዝግጁ ናችሁን?

**በጸሎት ኃይል ተጠቀሙ**

ምንም ማድረግ በማትችሉበት ጊዜ ምን ታደርጋላችሁ? የጸሎትን ኃይል በመጠቀም በመከራዎቻችሁ ደስ ተሰኙ፡፡ ሳንታክት ሁልጊዜ መጸለይ እንዳለብን ለማስረዳት በተጠቀመበት የፈራጁና የጽኑዋ መበለት ምሳሌ ላይ የተሰፋ መቁረጥ መፍትሔው ጸሎት መሆኑን ኢየሱስ ተናገረ (ሉቃ. 18፡ 1-8)፡፡ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ስንጋፈጥ ልንጠቀምባቸው ከምንችላቸው ወሳኝ ነገሮች መካከል አንዱ ጸሎት ነው፡፡

በአስራዎቹ እድሜዬ አመጸኛ ነበርሁ፡፡ ለእናቴ እንዲህ አልኳት፤ «አሁን እኔ ወንድ ነኝ፤ እንደፈለግሁ መውጣትና መግባት እችላለሁ፡፡» መጥፎ ከሆኑ ልጆች ጋር ጓደኝነት ፈጠርኩ፤ በጎረቤታችን ካሉት ወሮበሎች ጎራም ተቀላቀልኩ፡፡ እናቴ አቅም አጣች፤ ምክንያቱም በቤታችን ለእኔ አርአያ ሊሆነኝ የሚችል ማንም ወንድ አልነበረምና፡፡ ማድረግ የምትችለው ነገር ቢኖር ጸሎት ብቻ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለእኔ ስትጸልይ ስሰማት ለእኔ የምታደርገው መማለድ ጊዜ እንደ ማጥፋት አድርጌ እቆጥረው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን ጸሎቷን ሰማትና ወደ ቅድስና ወደ ትክክለኛ አኗኗር በሩጫ እንድመለስ አደረገኝ፡፡ ዛሬ ሰባኪ ልሆን የቻልኩት መልካሟ እናቴ ስለጸለየችልኝ ነው፡፡

እናንተስ ልትጸልዩለት የሚገባችሁ ሰው አለ? የጸሎትን ኃይል መቼም ቢሆን አሳንሳችሁ አትዩት፡፡ ታላቁ የ19ኛው ክፍለ-ዘመን እንግሊዛዊ ገጣሚ አልፍሬድ ሎርድ ቴኒየሰን እንዲህ ብለው ነበር፣ « ይህች አለም ከምታልመው በላይ ብዙ ነገሮች በጸሎት ተከናውነዋል፡፡» በጸሎት ኃይል በመከራችሁ ተደሰቱ፡፡ ኢየሱስ ከቀራኒዮ መስቀል የሰነዘራቸው የመጀመሪያ ቃላት ለጠላቶቹ የጸለየው ጸሎት መሆኑ በአጋጣሚ አልነበረም፡፡

### እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣችሁ ጠይቁት

በጸሎት ኃይል በመከራችሁ ስትደሰቱ ስለምንድን ነው መጸለይ ያለባችሁ? ስለ ጥበብ፡ያዕ. 1፡5 እንዲህ ይላል፡- «ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል።»፡፡ ታዲያ እግዚአብሔር ለመስጠት እንዲህ የሚጓጓ ከሆነ ለምንድን ነው ማንም ሰው እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጠው የማይጠይቀው?

ጥበብ በጣም ወሳኝ ነገር ከመሆኑ የተነሳ ሰለሞን ከእግዚአብሔር ዘንድ የፈለገውን ነገር እንዲጠይቅ እድሉ በተሰጠው ጊዜ፣ የለመነው ጥበብ እንዲሰጠው ነበር (1 ነገ. 3)፡፡ ኋላ ላይም እንደዚህ በማለት አወጀ፡- «ጥበብ ዓይነተኛ ነገር ናትና ጥበብን አግኝ» (ምሳ. 4፡7)፡፡ እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣችሁ በምትጠይቁበት ጊዜ በእውነትም በመከራዎቻችሁ እየተደሰታችሁ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጥያቄያችሁ በኩል እያላችሁ ያላችሁት፡- «አንተ ታላቁ ይሆዋ፣ ምራኝ» ነው፡፡ ተፈጥሮአዊው እውቀታችን ውስን እንደሆነ ስናስተውል የጥበብ ምንጭ የሆነውን የእርሱን እቅድና አላማ ማየት እንድንችልና በመከራዎቻችን እንዲመራን ልንጠይቀው እንችላለን፡፡

### ያለፈውን አስታውሱ

ላደርገው አይገባኝም ነበር፤ ነገር ግን አድርጌዋለሁ፡፡ በአፍላ ወጣትነት እድሜዬ የልጅነት ጓደኞቼን እያስፈራራሁ ገንዘብ እቀበላቸው ነበር፡፡ ማስፈራሪያዬ በጣም ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሳ ይህንን ምስጢር ለሳምንታት ለማንም ትንፍሽ አላሉም ነበር፡፡

ነገር ግን አይደርስ የለምና የፍርድ ቀን ደረሰ፡፡ ድፍረት አግኝተው በመጫወቻ ሜዳችን ላይ ስለማደርገው ዝርፊያ በተናገሩ ጊዜ ወላጆቻቸውና እናቴ ፍትህን ፍለጋ ወደ ሜዳው መጡ፤ ፍትህም አገኙ፡፡ ቅጣቴም ከማስበው በላይ በጣም የሚያም ነበር፤ ይኼውም የእናቴ እንባ ነበር፡፡ በእኔ ስህተት ምክንያት እናቴ ስታለቅስ በማየት ከተሰማኝ ከፍተኛ ስቃይ ይልቅ መደብደብን እመርጥ ነበር፡፡

አስርት አመታት አልፈዋል፤ ነገር ግን የልጅነት ኃጢአቶቼና ውድቀቶቼ አሁን ድረስ ይጎረብጡኛል፡፡ ይሁን እንጂ፣ የዚህ ስህተት ትውስታ የምወዳቸውን ሰዎች መልሼ ማሳዘን እንደሌለብኝ እንድወስን እረድቶኛል፡፡ ትውስታ ሕይወታችንን በትክክለኛው መንገድ እንድንመራና ውድቀትን ከሚያመጣብን ክፋት እንድንርቅ ይረዳናል፡፡

ምናልባትም እግዚአብሔር ማስታወስ ትልቅ ኃይል እንዳለው በማሰብ ሊሆን ይችላል ለእስራኤላውያን በግብጽ ባሮች እንደነበሩ እንዲያስታውሱ በሙሴ በኩል የነገራቸው (ዘዳ. 5፡ 15፤ 15፡15፤ 16፡12፤ 24፡ 18-22)፡፡ በአሁኑ ወቅት የምትጋፈጡትን መከራ በደስታ ለመጋጠም ከሚረዷችሁ ነገሮች መካከል አንዱ ከዚህ ቀደም ገጥሞአችሁ የነበረውን አስቸጋሪ ሁኔታ እንዴት እንዳለፋችሁት ማስታወስ ነው፡፡ ሙሴ ይህንን የነገራቸው የዮርዳኖስን ወንዝ አልፈው ወደ ተስፋይቱ ምድር ሊገቡ ሲሉ ነበር፡፡ እንደ ሕዝብ ሊደራጁ በነበረበት በዚያ ጊዜ፣ ሙሴ ሥር መሰረታቸው ከባርነት እንደሆነ እንዲያስታውሱ ተገዳደራቸው፡፡ ወደ ምድሪቱ ገብተው ሃብታምና ሃይለኛ ሲሆኑ እንደዚሁም በነጻነት መኖር ሲጀምሩ፣ ከየት እንደመጡ እንዲረሱ አልፈለገም፡፡ ለአራት መቶ አመታት በጭቆና ስር እንደነበሩ፣ ስራቸውንም ሆነ የት ማምለክ እንዳለባቸው መምረጥ የማይችሉ እንደነበሩ እንዲያስታውሱ ፈለገ፡፡ ይህም ትዝታቸው ደካሞችን፣ መበለቶችንና ነጻነትን ፍለጋ ወደ እነርሱ ነጻ አገር የሚመጡትን ሁሉ እንዴት ማስተናገድ

እንደሚገባቸው እንዲያስተምራቸው ፈለገ፡፡

ግብጽ የተጎዳንባቸውን፣ የወደቅንባቸውን፣ የታገልንባቸውን፣ ያጣንባቸውን ወቅቶች ይወክላል፡፡ ሙሴ ለእስራኤላውያን የሰጠው መልእክት ለእኛም ይሰራል፡፡ ያለፈ ሕይወታችሁን ጥላ ዳግም ለመመልከት አትፍሩ፤ ነገር ግን ቀድሞ በተቀበላችሁት ነጻ መውጣትና ለወደፊትም መቀበል ስለምትቀጥሉት አስቡ፡፡ እግዚአብሔር የሰጣችሁ ነጻነት ያለፈውን ነገራችሁን በማጤን የወደፊቱን እርምጃችሁን አቃንታችሁ ለማድረግ የሚያስችላችሁን ትምህርት እንድትቀስሙ ይረዳችኋል፡፡ እናም ግብጽን አስታውሱ፡፡

‹‹ግብጾቻችንን›› ማስታወሳችን እግዚአብሔር በአሁኑ ወቅት እየሰጠን ያለውን በረከት እንድናደንቀው ያግዘናል፡፡ ምን ያህል ጊዜ ነው ረዥሙን መንገድና በዚያም የነበሩትን የሚታዩም ሆነ የማይታዩ አደጋዎች እንዴት እንዳሻገረን የምንረሳው? እስራኤላውያን በምድረ በዳ ስለነበራቸው ሁኔታ ሲያጉረመርሙ (ዘጸ. 17፡ 1-2) ምናልባትም በግብጽ የነበራቸውን የባርነት ልምምድ አስታውሰው ቢሆን ኖሮ መልካም ነበር፡፡ ግብጽን ለቀው ከመውጣቸው በፊት ጨካኝ በሆኑ ባሪያ አሳዳሪዎች ይገረፉ ነበር፡፡ ያለ ጭድ ሸክላ እንዲሰሩ ይገደዱ ነበር፡፡ ልጆቻቸውንም በአባይ ወንዝ ውስጥ በማስገባት ይገድሉባቸው ነበር፡፡ ነገር ግን የፈርኦንን የእልከኝነት ልብ ለማሸነፍ እግዚአብሔር መቅሰፍቱን በግብጽ ላይ አዘነበ (ዘጸ. 7-11)፡፡ የግብጽን የበኩር ልጆች ገደለ፤ ታላቁን ሠራዊትም በቀይ ባሕር ውስጥ አሰጠመው፡፡ ለአመታት በባርነት ለፈሰሰው ጉልበታቸው የካሳ ክፍያ እንዲቀበሉ ካደረገ በኋላ እግዚአብሔር ሕዝቡ ግብጽን ለቆ እንዲወጣ አደረገ፡፡ በግብጻውያን ላይ ሞገስ ሰጣቸውና በመለያያ ስጦታ መልክ ያሏቸውን ወርቅ፣ ብርና እንቁ  አዘነቡላቸው፡፡

በምድረበዳ፣ በበረሐው ጸሐይ፣ እግዚአብሔር እስራኤልን በደመና በማስጠለል፣ ቀዝቃዛውን ሌሊት ደግሞ ብርሃን እያበራና ሙቀት እየሰጠ በሚመራቸው ጊዜ ሁሉ መሄድ እንዲችሉ አድርጎ መራቸው፡፡ ባርነታቸውንና በእነርሱም ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር የሰራውን ታላቅ ሥራ ማስታወሳቸው አሁን ያሉበትን ሁኔታ ያጣፍጥላቸው ነበር፤ነገር ግን እነዚህን ሁሉ ነገሮች ፈጽመው የረሷቸው ይመስላሉ፡፡ ይልቁንም በግብጽ ይበሉ የነበረውን ምግብ ይናፍቁ ጀመረ (ዘኁ. 11፡ 4-6)፤ የእለት ፍላጎታቸውን ማሟላት እንደማይችል አድርገው በእርሱ ባለመታመን እግዚአብሄርን አስቀየሙት፡፡ እኛም ዛሬ ተመሳሳዩን ስህተት እንፈጽማለን፤ በአንድ ወቅት የኃጢአት ባሪያዎች እንደነበርን በመርሳት፣ ያ የእስር ጊዜያችን ተመልሰን ልንሄድበት የምንፈልግ መዝናኛ ቦታ እንደሆነ አድርገን እናስበዋለን፡፡

ጥሩነቱ፣ ያዕቆብ በልጅነት ወራቱ እንዲህ ያለውን ስህተት አልሰራም ነበር፡፡ የእርሱ ‹‹ግብጽ›› የመዝናኛ ቦታ እንዳልነበረ አስታወሰ፡፡ ከመንትያ ወንድሙ፣ ከኤሳው ቁጣ በመሸሽ ወንድሙ እርሱን ሊገድለው እስኪፈልግ ድረስ ቢጠላው ተገቢ እንደሆነ ተሰምቶታል፡፡ የኤሳውን ደካማ ጎን በመጠቀምና አባቱን፣ ይስሐቅን በማታለል ለተቀባዩ ሀብት እና ስልጣን ይዞ የሚመጣውን የቤተሰቡን የብኩርና ስልጣን አገኘ፡፡ ነገር ግን አንድ ምሽት፣ በታላቅ ጭንቀት ተሞልቶ፣ እግዚአብሔር እስከዛሬ እንዴት አስቸጋሪ በሆነ መንገድ ደግፎ እንደያዘው አስታወሰና እንደዚህ አለ፡- ‹‹ለባሪያህ ከሠራኸው ከምሕረትህና ከእውነትህም ሁሉ ትንሽ ስንኳ የማይገባኝ ነኝ በትሬን ብቻ ይዤ ይህን ዮርዳኖስን ተሻግሬ ነበርና፥ አሁን ግን የሁለት ክፍል ሠራዊት ሆንሁ።›› (ዘፍ. 32፡10)፡፡ አሁን ላለው በረከት የሰጠውን ምስጋና ያገኘው እግዚአብሔር አስቀድሞ እርሱን ካተረፈበት ከባድ ሁኔታ ጋር ነበር፡፡ ያለፈውን ማስታወሱ በሽሽት ላይ ከነበረው ተስፋ

የቆረጠ ሽፍታነት ወደ አመስጋኝ የእግዚአብሔር ልጅነት ከፍ ማለቱን እንዲመለከት አደረገው።

ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ ወደ ፕሬዝደንትነት ስልጣናቸው በገቡበት ቀን ለሥርአቱ በተዘጋጀው የምሳ ግብዣ ላይ ለምግቡ ጸሎት ለማድረግ እድሉ ተሰጥቶኝ ነበረ። በዚያም ጠረጴዛ ላይ ተቀምጬ ነበር። ምግቡ በጣም ጣፋጭ ነበር (ምንም እንኳ ለራሴ ሌላ የአትክልት ምግብ ለመመገብ አስተካክዬ የነበረም ቢሆን)። በዚያም በጣም ሃብታምና ኃያል የሆኑ ሰዎች፣ የቀድሞ ፕሬዝዳንቶችና ምክትል ፕሬዝዳንቶች፣ የኮንግረሱና የከፍተኛ ፍርድ ቤት አባላት፣ ዝነኞችና ከሌላ አገር የመጡ እንግዶች ስመለከት የራሴን ግብጽ አስታወስኩ። ሥርዓት ባለው ሁኔታ ስልጣን በሚሸጋገርበት በዚህ ክብረ በዓል ላይ አእምሮዬ ወደ ልጅነት ወራቴ በትዝታ ነጎደ። የምንኖር የነበረው ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች በሚኖሩበት የመንግስት የቤት ፕሮጀት ውስጥ ነበር። አስታውሳለሁ፤ ቤተሰባችን ኪራይ መክፈል አቅቶት ሦስት ጊዜ ከቤት ተባርረናል፣ እቃችንም ጎረቤቶቻችን እንዲያዩት በመንገድ ዳር ተዘርግፎ ነበር። የቤተሰባችን የነጣ ድህነት በጎረቤቶቻችን በመታየቱና እነርሱም ፈጥሮባቸው የነበረው መገረም እንዴት እንዳሳፈረኝ አስታውሳለሁ። አዲሱን ፕሬዝዳንታችንንና ቀዳማዊ እመቤትን ሰላም ስላቸው በአእምሮዬ ብልጭ ይሉ የነበሩት እነዚህ አሳቦች ነበሩ። የቀድሞ የግብጽ አኗኗር ትውስታዬ በወቅቱ እየተለማመድኩት የነበረውን የደስታ ጊዜ የበለጠ ጣፋጭ አደረገው።

ኮንግረስ ማን ጆን ሊዊስ በዚህ የምሳ ግብዣ ላይ ነበሩ። በወጣትነታቸው ለሙብት እኩልነት በተደረገው ሰልፍ ላይ በተሳተፉ ጊዜ በደረሰባቸው ከባድ ድብደባ ምክንያት በራስ ቅላቸው ላይ ያረፈባቸው ጠባሳ አሁንም አለ። እርሳቸውም ለአዲሱ ፕሬዝዳንት የምሳውን ፕሮግራም ወረቀት ሰጡ፤ አዲሱ ፕሬዝዳንትም « በእናንተ ምክንያት፣ ባራክ ኦባማ።» በማለት ፊርማቸውን አኖሩ። የሚደረገው የትግል፣ የቁጣው ወላፈን፣ የፖሊስ ውሾች፣ ጥላቻው፣ ሃዘኑ፣ የዚያን ጊዜው ግብጽ አሁን አልፎአል። የእግዚአብሔር እንክብካቤ እንደገና አሸንፎአልና አሁን መደሰት እንችላለን።

ምናልባት ከዚህ በፊት በግብጽ ወራቶቻችሁ ተቋቁማችሁ ያለፋችሁትን የከፉ መከራዎች በመርሳታችሁ ምክንያት አሁን እያሳለፋችሁ ባላችሁት የመከራ ጊዜ መደሰት አቅቷችሁ ይሆን? ምናልባት የከባድ ድህነት ወይም የአካል ድብደባ ስቃይ አልደረሰባችሁ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ እናንተም ወደ ኋላ ልታዩ የምትችሉት ግብጽ አላችሁ፤ ምክንያቱም በኢየሱስ ክርስቶስ የቀራኒዮ መስቀል እውን ወደሆነው የአሁኑ ጊዜ ድነት ከአስከፊው በኃጢአት የተሞላ ያለፈ ታሪካችሁ አሻግሯችኋልና። በመሆኑም እያንዳንዳችን ለሌሎች የምናካፍለው ምስክርነት፣ አክብረን ልንይዛቸው የሚገባን ትዝታዎች አሉን። ክርስቶስ ከምን ጉድጓድ እንዳወጣን ስናስብ እለት እለት ከእርሱ ጋር ማድረግ በምንችለው ሕብረት ይበልጥ ደስተኞች እንድንሆን ይረዳናል፤ የግብጽን መከራ ወደ ኃይለኛ ምስክርነት ለመለወጥ ብርታት ይሰጠናል።

**ረዳተቢሶችን እርዱ**

የግብጽ ትዝታችን በሕይወት አጣብቂኝ ውስጥ ላሉት ሰዎች እጃችንን እንድንዘረጋ ሊያነሳሳን ይገባል። ድሆችንና ደካሞችን ከችግራቸው ለማላቀቅ ምንም አይነት ጠቃሚ እርምጃ ሳንወስድ በቀላሉ ላናስተውላቸው እንችላለን። ነገር ግን ግብጽን ማስታወሳችን ይህንን ስህተት እንዳንሰራ ይረዳናል። ከአምልኮ አገልግሎት በኋላ እናቴና ልጆቿ

ለሰንበት እራት ምን ያህል ስንጋበዝ እንደነበረ ሳስብ ይገርመኛል፡፡ ከእነዚህ ግብዣዎች ደግሞ አብዛኞቹ ይደርሱን የነበሩት እኛ ከነበረን በጣም ጥቂት የሚበልጥ ነገር ብቻ ባላቸው ሰዎች ነበር፡፡ ነገር ግን የራሳቸውን የግብጽ ልምምድ ማስታዋሳቸው ይህችን ብቻዋን ልጇ ቿን የምታሳድግ እናትንና የተራቡ ልጆቿን ለመርዳት አነሳሳቸው፡፡

በግብጻውያን እስርቤት በሃዘን ተውጠው የነበሩትን የፈርኦንን ጠጅ አሳላፊና እንጀራ አቅራቢ ዮሴፍ እንዲረዳቸው ያነሳሳው እንዲህ ያለው ልምምዱ ይሆንን? (ዘፍ. 40) በጌታው ሚስት ክስ ተመስርቶበት ባልፈጸመው አስገድዶ የመድፈር ወንጀል ነበር ዮሴፍ ወደ እስር ቤት የተወረወረው፡፡ ነገር ግን ስለ ደረሰበት ነገር ከማዘን ይልቅ የእስርቤቱ አለቃ አንዳንድ የተለዩ እስረኞችን አውጥቶ በማናፈስ እስከመርዳት ድረስ ወሳኝ የሆኑ ኃላፊነቶችን እስኪሰጠው ድረስ በትጋት ይሰራ ነበር፡፡ አንድ ቀን ከእነዚህ መካከል ሁለቱ በጣም አዝነው ተመለከተ፤ እርሱም ቀርቦ አናገራቸው፡፡ ስለሁኔታቸው ከጠየቃቸው በኋላ ሁለቱም ባዩት ህልም ምክንያት እንደተጨነቁ ነገሩት፡፡ እርሱም ህልማቸውን በመፍታት ሊያረጋጋቸው ቻለ፡፡ እነዚህ ሁለት እስረኞች እስርቤቱን ለቀው ለመሄድ በተዘጋጁበት ጊዜ ዮሴፍ ከሁለቱ ለአንዳቸው ስለ ራሱ የግል የግብጽ ልምምድ ነግሯቸው ነበር፡፡ ‹‹እኔን ከዕብራውያን አገር ሰርቀው አምጥተውኛልና ከዚህም ደግሞ በግዞት ያኖሩኝ ዘንድ ምንም አላደረግሁም።›› (ዘፍ. 40፡15)፡፡ ዮሴፍ የግብጽ ልምምዱን አልረሳም ነበር፡፡

እናንተስ የግብጽ ትዝታችሁ ሌሎች በሕይወት ፈተና ውስጥ ያሉትን ሰዎች ለመርዳት ያነሳሳችኋል? የሰካራም አሽከርካሪዎች ተቃዋሚ እናቶች የተሰኘውን ድርጅት (Mothers Against Drunk Driving, MADD) የጀመረችው ሴት እንዲህ ያለ ቀስቃሽ ነገር ነበራት፡፡ በአንድ ሰካራም ሹፌር እጅ ሴት ልጇ ከመሞቷ የተነሳ በደረሰባት ሃዘን ፣ ከሀዘኗ ለመዳን፣ ቁጣዋን ገንቢ በሆነ መንገድ ለመጠቀም ፈለገች፡፡ የሰካራም ሹፌሮች ሰለባ የሚሆኑትንና ቤተሰባቸውን ለመድረስ ወሰነች፡፡ ይህንን አይነት አዎንታዊ ለውጥ ለማምጣትም MADD የተሰኘው ድርጅት ተቋቋመ፡፡ የግብጽ ትዝታዋን ረዳተቢሶችን ለመርዳት ያነሳሳት ዘንድ ተጠቀመችበት፡፡

### አስቸጋሪ ሁኔታዎችን በጽናት ተቋቋሙ

የቀድሞውን የግብጽ ልምምዳችሁን ማስታወስ በሕይወት ውስጥ የሚያጋጥሟችሁን መከራዎችና ፈተናዎች በጽናት መቋቋም እንድትችሉ ይረዷችኋል፡፡ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያደረገውን ማሰብ በአሁኑ ወቅት የምትጋፈጧቸውን መከራዎች አስፈሪነት ይቀንሰዋል፡፡ የዩናይት ስቴትስ ባሕር ኃይል ቻፕሌን በመሆን በምሰራበት ጊዜ ለምልመላ ስልጠና ላይ ላሉ የምክር አገልግሎት እሰጥ ነበር፡፡ የምክር አገልግሎት ከምሰጣቸው መካከል አናሳ ከሚባሉት ዘሮች ወደ እኔ የሚመጡ ጥቂቶች ብቻ እንደሆኑ አስተዋልኩ፡፡ በማማከሩ ሥራ ጥቂት ሳምንታትን ካሳለፍኩ በኋላ አፍሪካ አሜሪካውያንና(ጥቁር አሜሪካውያንን) ከደቡብ አሜሪካ የመጡትን ብዙዎቹን ጠጋ ብዬ ‹‹ለምንድን ነው ከእኔ የምክር አገልግሎት ለማግኘት የማትመጡት?›› በማለት ጠየቅኋቸው፡፡

የሰጡኝ ጠቅለል ያለ መልስ ‹‹ምን ፈልገን?›› የሚል ነበር፡፡ ‹‹ቻፕሌን›› አሉኝ ቀጠል አድርገው ‹‹እኛ እኮ የመጣነው ብዙ አደገኛ ቦዘኔዎችና ነፍሰ ገዳዮች ከነበሩባቸው ከተሞች ነው፡፡ እናም ወደ ቤታችን በሰላም ወጥተን እንገባለን ብለን አንድም ቀን በእርግጠኝነት አስበን አናውቅም፡፡ አሁን ያለንበት ቦታ በፊት ከነበርንበት ጋር ሲነጻጸር ለእኛ እንደ ኬክ ቁራጭ ነው፡፡›› ከዚህ በፊት ያለፉባቸውን ከባድ ሁኔታዎች

ማስታወሳቸው ብዙ ከባድ ስልጠና በሚሰጥበት በዚህ የጦር ሰፈር የገጠማቸውን መከራ ቀለል አድርገው እንዲያዩት ረዳቸው፡፡

ከክርስቶስ ስቅላት በፊት፣ ጴጥሮስ ኢየሱስን ካደው (ሉቃ. 22)፡፡ ጴጥሮስም ኋላ ላይ ይህንን የግብጽ ትዝታውን ሌሎች ወገኖችን በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በጸጋ በጽናት ተቋቁመው እንዲያልፉ ለመምከር ተጠቀመበት፡፡ እንዲህ በማለት ይጽፋል፡- «ክርስቶስም በሥጋ ስለ እኛ መከራን ስለተቀበለ፥ ...እናንተ ደግሞ ያን አሳብ እንደ ዕቃ ጦር አድርጋችሁ ያዙት፥ በሥጋ መከራን የተቀበለ ኃጢአትን ትቶአልና።» (1 ጴጥ. 4፡1) ፡፡ የክርስቶስ መስዋዕትነት ትውስታ መንፈሳችንን ሊያነቃቃ ይገባል፡፡ እኛም ከስልጣናትና ከአለቆች ጋር ባለን መንፈሳዊ ውጊያ (ኤፌ. 6፡12) የመስዋእትነትንና የአገልግሎትን ዋጋ ለመክፈል ቆርጠን ልንገባ ይገባል፡፡ እንደዚሁም መከራን እንደ የመስቀሉ መልካም ወታደር ተቋቁመን ማለፍ አለብን፡፡

**የእግዚአብሔርን መልካምነት መስከሩ**

ግብጽን ማስታወሳችን የምንመሰክረውን ምስክርነት ይሰጠናል፡፡ ብዙዎች ያለ ምንም መከራ የሚያወሩት ታሪክ እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ፡፡ ነገር ግን ለሌሎች የምንመሰክራቸው ታሪኮች ብዙ ጊዜ የሚሰሩት እንደ ወርቅ በመከራ የማቅለጫ እሳት ውስጥ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ስለ እርሱ ታላቅነትና መልካምነት ምስክርነት የሚናገሩ ሰዎችን በመፈለግ በሕይወት እሳት ውስጥ ያነጥራቸዋል፡፡ ይህንን ከአጋንንት እስራት ነጻ በወጣው ሰው ሕይወት ውስጥ እንመለከታለን (ማር. 5)፡፡

ይህ በአጋንንት የተያዘ ሰው ለረዥም ጊዜ ጎረቤቶቹን ትልቅ ስጋት ላይ የጣለ ሰው ነበር፡፡ ይኖር የነበረውም በመቃብሮች መካከል ሲሆን፣ ምንም አይነት ሰንሰለት ሊያስረው፣ ማንም ሰው ደግሞ በቁጥጥሩ ስር ሊያደርገው የቻለ አልነበረም፡፡ ከአእምሮው ውጭ አድርገውት የነበሩት አጋንንቶች ከሰው አቅም በላይ የሆነ ጉልበት ሰጥተውት ነበርና፡፡ ቀንና ሌሊት ይሮጥ የነበረው እርቃኑን ነበር፡፡ በጣም ይጮኽ ሰውነቱንም ይቆራርጥ ነበር፡፡ ይህ ሁሉ ታዲያ ከክርስቶስ ጋር ከመገናኘቱ በፊት ነው፡፡ በርቀት አዳኙን ተመለከተው፡፡ ሊገናኘውም ወደ እርሱ ሮጠ፤ ወድቆም ሰገደለት፡፡ ነገር ግን በውስጡ የነበረው የአጋንንት ጭፍራ በእርሱ አፍ በኩል መናገር ጀመረ፣ «የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለኝ?» (ማር. 5፡7)፡፡

ኢየሱስም እርሱን ከአላማው ለማደናቀፍ አላማ ያደረገውን ይህንን ጥረት ችላ በማለት ይህንን ሰው የተቆጣጠሩትን የአጋንንት መንፈስ በስልጣን ተናገራቸው፡- «አንተ ርኩስ መንፈስ፥ ከዚህ ሰው ውጣ » (ማር. 5፡8)፡፡

ወዲያውም ሰውየው ሙሉ በሙሉ ዳነና ከእርሱ ጋር አብሮ መሄድ ይችል ዘንድ ኢየሱስን ለመነው፡፡ ኢየሱስ ግን እንዲህ አለው፡- «ኢየሱስም አልፈቀደለትም፥ ነገር ግን። ወደ ቤትህ በቤተ ሰዎችህ ዘንድ ሄደህ ጌታ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገልህ እንዴትስ እንደ ማረህ አውራላቸው አለው።» (ማር. 5፡ 19)፡፡ ኢየሱስ ግለሰቡ አሰቃቂ የነበረውን የግብጽ ቆይታውንና ከዚያም ነጻ መውጣቱን ስለ እግዚአብሔር መልካምነትና

ጸጋ ለመመስከር እንዲጠቀምበት ፈለገ፡፡

ስለ እግዚአብሔር ጸጋ ከተሰጡ ታላላቅ ምስክርነቶች መካከል አንዱ በጆን ኒውተን የተጻፈ ነው፡፡ ይህ ሰው ከዚህ ቀደም በአንድ በባሪያ ንግድ ላይ የተሰማራች መርከብ ካፒቴን ነበር፡፡ ለአመታት በዚህ አሳዛኝ በሆነ ሰዎችን የመነገድ ሥራ ላይ ከሰራ በኋላ፣ ኒውተን፣ ወደ ክርስቶስ መጣ፡፡ ምናልባትም የኃጢአት ውስጥ ያሳለፈው የግብጽ ቆይታው ትዝታ ሊሆን ይችላል እንዲህ በማለት የሚጀምረውን መዝሙር እንዲጽፍ ያደረገው፡- « አስገራሚ ጸጋ ሲሰሙት የሚጣፍጥ፣ ክፉ እንደ እኔ አይነቱን ከሞት የሚያስመልጥ፤ ጠፍቼ ነበርኩኝ አሁን ግን ተገኘሁ፣ ታውሬ ነበረ አሁን ግን አያለሁ፡፡» ኒውተን ሕግን በመተላለፍ የኖረበት የግብጽ ቆይታው እስካሁን ድረስ በአለም ዙሪያ ያሉ ክርስቲያኖችን ልብ የሚያሞቅ መዝሙር እንዲወለድ አደረገ፡፡

**እያመሰገናችሁ ኑሩ**

ግብጽን ማስታወሳችን በአመስጋኝነት መንፈስ ሊሞላን ይችላል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ልክ ይህች አለም ለእነርሱ ባለዕዳ እንደሆነች በመቁጠር የባለቤትነት መንፈስ በእጅጉ ይሰማቸዋል፡፡ እንደዚህ ያሉ ሰዎች አመሰግናለሁ ለማለት እንኳ በጣም ነው የሚቸግራቸው፡፡ በሕይወት ጎዳና የሚጓዙት በረከቶቻቸውን ሁሉ በዋዛ እንዳገኙት በማሰብ ነው፡፡

በሉቃ. 17 ላይ ኢየሱስ ከፈወሳቸው አስር ለምጻሞች መካከል አንደኛው ግን እንደዚህ አላደረገም፡፡ አስሩም ከለምጽ ነጽተው ነበር፤ ነገር ግን ከአስሩ መካከል አንዱ ብቻ ነበር ከተናቁት ከሰማርያውያን ወገን የነበረ እንግዳ ሰው፡፡ ይህ ሰው ከሌሎች በማይድን በሽታ በመያዛቸው ምክንያት ከማህበረሰቡ ከተገለሉ አይሁዶች ቡድን ውስጥ ገብቶ ነበር፡፡ ተመሳሳይ ስቃይን መጋራት በመልካም ጊዜ የማንፈጥረውን አይነት የጠበቀ ወዳጅነት እንድንመሰርት ያደርገናል፡፡ አስሩ በሙሉ ነጽተው ነበር፤ ነገር ግን አንዱ ብቻ ተመልሶ ከዚያ አስፈሪ በሽታ እስር ቤት ነጻ ባወጣው በአዳኙ ፊት ራሱን በማዋረድ በምስጋና ተሞልቶ ሰገደ፡፡ ያም ሰው ሰማርያዊው ነበር፡፡ ኢየሱስም ብዙዎች ይህ የአመስጋኝነት መንፈስ ስለጎደላቸው ያዘነ ይመስል ነበር፤ እንዲህ በማለትም ጠየቀ፡- «አሥሩ አልነጹምን? ዘጠኙስ ወዴት አሉ?» (ሉቃ. 17፡17)፡፡

ምናልባት ይህ አመስጋኝ ሳምራዊ የመገለልና ያለአግባብ መስተናገድ ግብጽን የሚያውቅ ይሆን? ምናልባት በበሽታውና በዘሩ ምክንያት የተለጠፈበት ድርብ መጥፎ ስም በዘራቸው ከእርሱ ከሚበልጡት ሌሎች ለምጻም ጓደኞቹ በበለጠ የእርሱን ልምምድ ታላቅ በሆነ ስቃይ ሞልቶት ይሆን? ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ልቡ ግን በምስጋና ሞልቶ ፈሰሰ፡፡ እኛም የየራሳችንን ግብፆች ስናስብ በውስጣችን ሊፈጠር የሚችለውን የአመስጋኝነት መንፈስ እንደሞዴል የሚያሳየን አርአያ ነው፡፡

ከብዙ አመታት በፊት በኮርያ እጅግ ከባድ በሆነ ቅዝቃዜ ውስጥ የአንድን ስልጠና አስቸጋሪ ወቅቶች ተቋቁሜ ማለፍ ነበረብኝ፡፡ ውሃን ወደ በረዶ በሚቀይር ቅዝቃዜ ውስጥ መሬት ላይ መተኛት ነበረብን፤ ከወር በላይ ምንም አይነት ሻወር ሳንወስድ ቆየን፡፡

ብዙ ጊዜ ሸክሙ እኔ ከምችለው በላይ እንደሆነ ይሰማኝ ነበር፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ተቋቋምኩት፤ ከሌሎችም ጋር ተረፍኩ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የእነዚያ አስቸጋሪ ቀናት ትዝታዎቼ ለእኔ ትልቅ በረከቶች ናቸው፡፡ አሁን በማልፍበት ጎዳና አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሙኝ፣ ኮርያን አስተውስና ልቤ በምስጋናና በደስታ ይሞላል፡፡ ከወር በላይ ያለ ሻወር የቆየ ሰው ካልሆነ በስተቀር በየቀኑ ሻወር መውሰድ ስለመቻሉ ብዙ ሰው አያመሰግንም፡፡ የግብጽ ትውስታችሁ በልባችሁ አመስጋኝነትን መንፈስ እንዲቀሰቅስ ፍቀዱ፡፡

**ትህትናን ተላበሱ**

ሐዋርያው ጳውሎስ በትዕቢት ተሞልተው የነበሩትን የቆሮንቶስ አማኞች እንዲህ በማለት ይጠይቃቸዋል፣ «ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ?» (1 ቆሮ. 4፡7)፡፡ ችሎታዎቻቸውና ያላቸው ነገር ሁሉ ከላይ የተሰጣቸው መሆኑን በማስታወስ ትምክህታቸውን እንዲተው ፈለገ፡፡

የግብጽ ትዝታችን በልባችን እውነተኛ የሆነ ትህትናን ይፈጥራል፡፡ እግዚአብሔር ከምን አይነት ጉድጓድ ውስጥ እንዳወጣን ስናስታውስ የተለየ መስተንግዶ ይገባናል ብለን እንዴት እንጠይቃለን? ጳውሎስን እጅግ በትህትና መንፈስ የተሞላ እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች መካከል አንዱ የጥንቷን ቤተክርስቲያን የማሳደዱ ትውስታ ሊሆን ይችላል፡፡ በኤፌ. 3፡8፣ ጳውሎስ ራሱን ከሁሉም አማኞች በታች ዝቅ አድርጎ ያስቀምጣል፤ እንዲህ ያለው አመለካከቱ የተመሰረተው ጥሩ ባልሆነው ያለፈው ሕይወቱ ላይ ነበር፡፡ በደማስቆ መንገድ ከኢየሱስ ጋር ከመገናኘቱ በፊት (የሐዋ. 9) ክርስቲያኖችን ያሳድድ እንደነበረ ደጋግሞ ይናገር ነበር፡፡ በሕይወቱ ያሳለፈው የግብጽ ትዝታው ከትምክህት ጠበቀው፡፡

**ከውድቀቶቻችሁ ተማሩ**

ብዙ ጊዜ ከስኬቶቻችን ይልቅ ከውድቀቶቻችን ብዙ እንማራለን፤ በመሆኑም፣ የተሰናከልንባቸውን ግብጾች ማስታወሳችን በረከት ይዞልን ይመጣል፡፡ ኃጢአት ዳግም ላይታይ የሚጠፋበት ቀን እንደሚመጣ መጽሐፍ ቅዱስ ይተነብያል (ናሆም 1፡9)፡፡ ይህ የሚሆንበት አንዱ ምክንያት በኃጢአት ውስጥ መውደቅን የተለማመዱ ሰዎች የማታለያ ጭምብሉ ወልቆ በእውነተኛ ገጽታው ኃጢአትን ስለሚያዩት ነው፡፡ የቀድሞ ስህተቱን ሲመለከት በኃጢአት የተሞላውን ፍሬቢስ ነገር ከማድረግ ይልቅ መልካምና ጠቃሚ የሆነውን ነገር አድርጎ ማለፍን የማይመኝ ማን ይሆን? የዮሴፍ ወንድሞች የውድቀታቸው ትውስታ ከረዥም ጊዜ በኋላ ባረካቸው፡፡ ከባድ በሆነ ሁኔታ ውስጥ በወደቁ ጊዜ በዮሴፍ ላይ ያደረሱት እንግልት ትዝ አላቸውና እግዚአብሔር እየቀጣቸው እንደሆነ ተሰማቸው፡፡ «በእውነት ወንድማችንን በድለናል፥ እኛን በማማጠን ነፍሱ ስትጨነቅ አይተን አልሰማነውምና ስለዚህ ይህ መከራ መጣብን።» (ዘፍ. 42፡ 21)፡፡ ግብጽን ማስታወሳቸው ከወንድማቸው ጋር እንዲታረቁና ለአገልሎትና ለቅንነት ሕይወት እንዲዘጋጁ አደረጋቸው፡፡

ውድቀቶቼን ለማስታወስ የምጥረው በስህተቶቼ ላይ ምርመራ በማድረግ ነው፡፡ ወደ ኋላ መመለስ ወደ ማልችልበት ደረጃ ያለፍኩበትን ነጥብ ለማስተዋል እጥራለሁ፡፡ እንዲህ ያለው ምርመራ ለወደፊት ተመሳሳዩን ስህተት እንዳልሰራ ያደርገኛል፡፡ የውድቀት

ስሜቶቹ ሲጠፉና የወቅቱ ሙቀት ሲቀዘቅዝ « የቱ ጋር ነው የተሳሳትኩት?» ብሎ ማሰብ ቀላል ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚያም ውድቀታችን ለአመታት የሚጠቅሙንን ብዙ መልካም ትምህርቶች ያስተምረናል፡፡ ተመሳሳዩን ፈተና እንደገና ስጋፈጥ ከቀድሞ ውድቀቴ የወሰድኩት ትምህርት ለድል ያበቃኛል፡፡ ቀድሞ የዘረረኝን ላሸንፈው እንደምችል ማወቄ ደግሞ አሁን በሚያጋጥሙኝ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በድል አድራጊነት ደስታ እንድሞላ ያደርገኛል፡፡

**የመከራን አይቀሬነት ለመቀበል የሚያግዟችሁ ወሳኝ እርምጃዎች**

- ተስፋ ቆርጦ መተውን አስወግዱ
- ቁጣችሁን ግሩት
- ደስተኛ ሁኑ
- በትእግስት የመጽናትን ፍሬ ሰብስቡ
- በጸሎት ኃይል ተጠቀሙ
- እግዚአብሔር ጥበብ እንዲሰጣችሁ ጠይቁት
- ያለፈውን አስታውሱ
- ረዳተቢሶችን እርዱ
- አስቸጋሪ ሁኔታዎችን በጽናት ተቋቋሙ
- የእግዚአብሔርን መልካምነት መስክሩ
- እያመሰገናችሁ ኑሩ
- ትህትናን ተላበሱ
- ከውድቀቶታችሁ ተማሩ

# 8

# በመጠበቅ አሸንፉ

ወደ ሥራ ቦታዬ ለመድረስ መኪና እያሽከረከርኩ የነበረ ሲሆን፣ ጉዞውም ደስ የሚያሰኝ ነበር፡፡ ወደ አሜሪካ ዋና ከተማ የሚወስዱት የዲ ሲ መንገዶች ከፍተኛ የሆነ የመኪና መጨናነቅ ይታይባቸዋል፡፡ የመንገዱ መዘጋጋት፣ በካፒቶል ህንጻ ወደ ሚገኘው ቢሮዬ ሳመራ፣ የዘጸአትን መጽሐፍ በድምጽ የሚተርክ ካሴት ደጋግሜ ለመስማት አስቻለኝ፡፡ የተራኪው የሚያስገመግም ድምጽ ከብሪትሽ እግሊዘኛ ቅላፄ ጋር ተዋህዶ ለጆሮ ይጥም ነበር፡፡ ተራኪው ዘጸአት 14ን ማራኪ በሆነ መልኩ በሚተርክበት ጊዜ፣ እስራኤላውያን ቀይ ባሕርን የተሻገሩበትን የተለመደ ታሪክ ለአመታት ተሰምቶኝ በማያውቅ ልዩ ደስታ ውስጥ ሆኜ ሰማሁት፡፡

ምርኮን ለመበዝበዝ የሚቻኮለው የግብጽ ሠራዊት ከኋላ እያሳደዳቸው፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ማምለጫ በሌለው አጣብቂኝ ውስጥ ወደቁ፡፡ ነፍሰ ገዳዮቹ ግብጻውያን ከኋላ እያባረሯቸው ከፊት ለፊታቸው ወዳለው ባሕር ውስጥ ሊጨምሯቸው በደረሱ ጊዜ፣ ሊጋፈጡት የማይችሉት የሚመስል መከራ ደረሰባቸው፡፡

ተራኪው ቁጥር 13 ላይ ሲደርስ «አትፍሩ፤ ጸንታችሁ ቁሙ፤ የእግዚአብሔርንም ማዳን እዩ» የሚለውን ሲያነብ፣ ልቤ በምስጋና ተሞልታ ዘለለች፡፡ እግዚአብሔር እስራኤላውያን እርሱን በተስፋ እንዲጠብቁ እየተገዳደራቸው ይመስላል፡፡ ሰዓቱ ተስፋ በመቁረጥ ተዘልለው የሚቀመጡበት ጊዜ አልነበረም፤ በራስ የመፍጨርጨሪያ፣ በድንጋጤ ወደ ኋላ የማፈግፈጊያ፣ እንደዚሁም የጭንቀትም ጊዜ አልነበረም፡፡ መልእክቱ ግልጽ ነበር፤ «ተረጋጉ፤ ዘና በሉ» የሚል ነበር፡፡ በጸጥታ ቁሙና እግዚአብሔር እንዲሰራ ጠብቁት፡፡ ምንም እንኳን የመኪናውን መሪ በእጆቼ ጨብጬ መያዝ ስለነበረብኝ እጆቼን አንስቼ እግዚአብሔርን መባረክ ባልችም፣ በድምጼ ግን አመሰግነው ጀመር፡፡ እግዚአብሔር እንዲሰራ ጠብቅ የሚለው ታላቅ አባባል በእርግጥም የምስጋና ምላሽ የሚያሰጥ ነው፡፡ የመጠበቅን ጥበብ በመማር መከራችሁን ወደ በረከት መለወጥ ትችላላችሁ፤ በመከራችሁም ደስ ይላችኋል፡፡

ድል ለእያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ የተሰጠ መዳረሻው እንደሆነ አምናለሁ፡፡ ሆኖም ግን ይህ ድል በምድራዊ መለኪያ አይሰፈርም፡፡ ምክንያቱም ስጋዊው አእምሮ ስኬት ብሎ የሚጠራው በእግዚአብሔር ዓይን ውድቀት ሊሆን ይችላልና፡፡ በጥልቀት ካልታየ ኢየሱስ በተሰቀለ ጊዜ የተሸነፈ ይመስል ነበር፤ ነገር ግን የትንሳኤው ማለዳ ባለግርማ የሆነውን ድሉን በድምቀት አሳየ፡፡ የአባቱን ፈቃድ እየጠበቀ በመቃብር አረፈ፤ ከዚያም ፈንቅሎት ተነሳ፡፡ በዚህም የመጠበቅን ጥበብ ተለማመደ፡፡

እግዚአብሔርን ጠብቁ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን እንድንጠብቅ በሚያደፋፍሩን ምክሮች የተሞላ ነው፡፡ ለምን? ለምንድን ነው እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ እንድንጠብቅ የሚያደርገን? ትዕግስትና ጽናት በእርሱ ዘንድ ትልቅ ዋጋ የሚሰጣቸው ለምንድን ነው? አዳምና ሔዋን በኃጢአት በወደቁበት ዕለት ክርስቶስን ሊልከው ይችል ነበር፤ ነገር ግን፣ ይህንን የመዋጀት ተግባር እንዲቆይ በማድረግ በቤተልሔም ይህ እስኪሆን ድረስ በሺጎ የሚቆጠሩ አመታት እንዲያልፉ አደረገ፡፡ እስራኤልን ለማሳደድ የወጣውን ይህንን የግብጽ ሠራዊት በግብጽ ላይ አስር መቅሰፍቶችን እንዳወረደ ሁሉ በአንድ ጊዜ ሊያጠፋቸው ይችል ነበር፡፡ የጠላት ወታደሮች እስራኤላውያንን አባረው ወደ ባሕሩ ውስጥ እንዲገቡ ከማድረጋቸው በፊት የሰረገሎቻቸው ጎማ እየተፈታ እንዲበታተን ማድረግ ይችላል፡፡ ነገር ግን ጸጥ ብሎ ምንም አይነት እንቅስቃሴ ሳያደርግ ቆየ፡፡ ሕዝቡንም እንዲጠብቁ አደረጋቸው፡፡ ብዙ ሰዎች እስራኤልን ከባርነት ነጻ ለማውጣት እቅዱን እንዲመሩ እድል ተሰጥቶአቸው ቢሆን ኖሮ ክስተቶችን በተለየ መንገድ ያስተናግዷቸው ነበር ብለን መናገር እንችላለን፡፡ ታዲያ ለምንድን ነው በጣም የሚወደን እግዚአብሔር ከምክንያት አልባው ፍቅሩ ጋር የማይገጥም በሚመስል መንገድ ምላሽ የሚሰጠው?

ለዚህ ጥያቄ ሊሰጥ የሚችል ቀላል መልስ እንደዚሁም ወደ ቅዱስ ባሕርይ የሚያደርስ አቋራጭ መንገድ የለም፡፡ ነገር ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ንባቤና ከራሴም የሕይወት ተሞክሮ እንደተረዳሁት፣ እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ እነዚህን የመጠበቂያ ጊዜያት የሚጠቀምባቸው ወደ በረከቱ የምንገባበት መግቢያ በር አድርጎ ነው ፡፡ ማለፊያውም ጽናት ነው፡፡ ዘፍጥረት 40 ላይ የሐሰት ክስ ሰለባው ዮሴፍ በእስር ቤት ሲበሰብስ ይታያል፡፡ የእስር ቤት ጓደኞቹ የነበሩትን የፈርኦን ጠጅ አሳለፊንና እንጀራ አሳላፊን ሕልም ፈትቶላቸው እንደነበረ ታሪኩ ይገልጻል፡፡ እናም በመጨረሻ ላይ እግዚአብሔር እርሱንም ሊጎበኘው ጊዜው የቀረበ ይመስል ነበር፡፡ እነዚህን ሁለት ህልሞች ለመፍታት የተሰጠው ከሰብአዊ ተፈጥሮ በላይ የሆነው ችሎታ ኢፍትሃዊ በሆነ መንገድ እየቀመሰ ካለው ከዚህ ስቃይ ለመገላገል ጊዜው ሩቅ እንዳልሆ በማሰብ በተስፋ እንዲሞላ ሳያደርገው አልቀረም፡፡ ከእነዚያ የእስር ቤት ደጆች ነጻ ሰው ሆኖ የሚወጣበትን ቀን በታላቅ ጉጉት በመጠባበቅ ቀኖችን ይቆጥር እንደነበረ አስባለሁ፡፡

ነገር ግን እርሱ እንደጓጓው ፈጥኖ አልሆነም፡፡ ከፈርኦን ምንም አይነት ድምጽ ሳይሰማ ቀኖቹ ያልፉ ጀመር፡፡ «መቼም በዚህ ጊዜ ጠጅ አሳላፊው ከፈርኦን ጋር ተነጋግሮ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም» በማለት ዮሴፍ በአእምሮው ሳያስብ አልቀረም፡፡ ቀኖች ተለጥጠው ሳምንታት ሆኑ፡፡ ሳምንታቱም ወራትን ወለዱ፡፡ ወራቱም ወደ አመታት ተቀየሩ፡፡ እግዚአብሔር ሁለት ምስጢራዊና አስጨናቂ ሕልሞችን ወደ ፈርኦን ከመላኩ በፊት፣ የእነዚህንም ህልሞች ሪፖርት ጠጅ አሳላፊው እስኪሰማና የዘነጋውን ዮሴፍን አስታውሶ የዮሴፍ ጉብኝት እስኪመጣ ድረስ ሁለት የስቃይ አመታት አለፉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ መከራዎቹ የመጠበቅን ጥበብ አስተምረውት ነበርና አንድም ጊዜ አላጉረመረመም፡፡ ለታላቅ በረከቶች የበቃ እንደሆነና ከፍተኛ የሆነም ኃላፊነትን ለመሸከም ታማኝ እንደሆነ በማሳየት የእግዚአብሔርን ፈተና አለፈ፡፡ በእናንተስ ጎዳና ላይ እግዚአብሔር እንድትጠብቁ በማድረግ ለማለፍ ከባድ የሆነ ምን አይነት ፈተና ልኮ ይሆን? እናንተስ መንፈሳዊና ስነ-ምግባራዊ ብቃትን ለማሳየት የሚያስፈልገውን ትዕግስት

ማሳየት የተሳናችሁ በምን መልኩ ነው? ልክ እንደ ዮሴፍ ከፊት ለፊታችሁ ያለውን መንገድ አጥርታችሁ ማየት በማትችሉበት በጨለማ ውስጥ እግዚአብሔርን መታመን ከተማራችሁ፣ ታላቅ የበረከትን መከር ደጋግማማችሁ ትሰበስባላችሁ፡፡

መጠበቅ ባሕርያችንን የሚፈትን ብቻ ሳይሆን እምነታችንንም የሚያጠነክር ጭምር ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ያለንን መታመን የጠነከረ ለማድረግ ፈልጎ ይዘገያል፡፡ በዮሐ. 11፣ አልአዛር ሊሞት እያጣጣረ ተኝቶ በነበረበት ጊዜ፣ ጌታ ግን በሌላ ከተማ በስቃይ ውስጥ የነበረው ወዳጁ እስኪሞት ድረስ ሆን ብሎ ዘገየ፡፡ የአላአዛርንም ሞት በሰማ ጊዜ፣ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ በጣም እንግዳ የሆነን ነገር ተናገረ፡- «አልዓዛር ሞተ፤ እንድታምኑም በዚያ ባለመኖሬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፤ ነገር ግን ወደ እርሱ እንሂድ አላቸው።» (ዮሐ. 11፡ 14-15)፡፡

ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ የእርሱን ሞትና መቀበር አጅበው በሚመጡት ክስተቶች እንደሚፈረካከሱና እስከ ትንሳኤው ድረስ የሚጸና ጠንካራ እምነት ሊያዳብሩ እንደሚገባቸው ያውቅ ነበር፡፡ የሚያዩአቸው ነገሮች ሁሉ ህልሞቻቸውን ሲጨፈላልቁባቸውና በፍርሃት ሲሞሏቸው ጌታን በመታመን እንዲቀጥሉ የሚያደርጋቸው ጠንካራ የሆነ መተማመን ሊኖራቸው ይገባ ነበር፡፡ ኢየሱስ የአይሁድ መሪዎችና ሙሾ ደርዳሪዎች በአላዛርን የቀብር ሥርአት ላይ እንደሚካፈሉ ያውቅ ነበር፡፡ ምንም እንኳን ከደቀ መዛሙርቱ ለተለየ ምክንያት ቢሆንም እነርሱም ቢሆኑ መንፈሳዊ እርዳታ ያስፈልጋቸው ነበር፡፡ እናም አዳኙ ለእነርሱ እምነት መሠረት ሊጥል የሚችልበትን እድል ለመጠቀም ፈለገ፡፡ ኢየሱስ የብዙዎችን እምነት ለማጠንከርና ከፊት ለፊታቸው ላለ ስኬት ለማዘጋጀት የመጠበቅን ጥበብ ተለማመደ፡፡

እግዚአብሔር እየጠበቅን እንድንቆይ የሚያደርግበት የመጨረሻው ምክንያት ትምክህታችንን ለማጥፋት ነው፡፡ የሚያዘገይበት ምክንያት የድሉ ምስጋና ለሰብአዊ ዘር ሳይሆን ለእርሱ እንዲሆን ነው፡፡ እግዚአብሔር በሚዲያማውያን ላይ ድልን ያቀዳጀው ዘንድ የሠራዊቱን ቁጥር መቀነስ እንዳለበት ጌድዮንን ተገዳደረው (መሳ. 7)፡፡ «የገዛ እጃችን አዳነን» ብለው እስራኤላውያን እንዲናገሩ አልፈለገም፡፡ እግዚአብሔርም የጌድዮንን ሠራዊት ከ32 000 አበጥሮ 300 ብቻ እንዲቀር አደረገ፡፡ በዚህም ድል ከመንሳታቸው የተነሳ የትኛውም ሰብአዊ ኃይል ክብር መውሰድ እንዳይችል ሆነ፡፡ የጌድዮን ሠራዊት እርሱን ይጠብቁ ዘንድም ግድ አላቸው፡፡ ቁጥራቸውን በጣም ከማሳነሱ የተነሳ፣ ያለ መለኮት እርዳታ በውጊያው ቀጠና ውስጥ ገብተው ግርማ ያለው ትርዒት ማሳየት የሚችሉበትን ችሎታ ሁሉ ከእነርሱ ገፈፈ፡፡ በአምላካዊ ጥበቡ፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን በግሩም ሁኔታ በተዋጉት ጦርነት ስላገኙት ድል በትምክህት የሚኩራሩበት እድል በሌለበት ሁኔታ ውስጥ አስገባቸው፡፡

**የእግዚአብሔርን አዘጋጅነት ታመኑ**

እግዚአብሔር መጠበቅ እንዳለባችሁ በሚያውጅበት ጊዜ፣ በራሱ ደም ላተመው ኪዳኑ ያለውን ታማኝነትና መሰጠት በማስታወስ ትዕግስታችሁን ማጎልበት ትችላላችሁ፡፡ እኛ እንኳን በቁም ነገር ተስፋዎቹን በማናያቸው ጊዜ እርሱ ግን የተስፋ ቃሎቹን አቅልሎ አያያቸውም፡፡ ትዕዛዛቱን ብንጠብቅ በሞገሱ ጋሻ ሊከልለን ቃል ገብቷል (መዝ. 5፡ 12)፡፡

ስለዚህም በስኬት ተራራ ጫፍ ላይ ብትቆሙ ወይም በተስፋ መቁረጥ ሸለቆ ውስጥ ተሸንፋችሁ ብትዘረሩ፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር እስካለ ድረስ፣ በፍቅሩ ማረፍና በታማኝነቱም ላይ መተማመን ትችላላችሁ፡፡ በማቴ. 14 ላይ፣ አምስት ሺህ ሰዎችን በተአምራዊ መንገድ ከመገበ በኋላ ደቀመዛሙርቱን ሐይቅ አቋርጠው እንዲሄዱ አዘዛቸው፡፡ ተከታዮቹ ከወደቡ ርቀው ሲሄዱ፣ ጌታ ደግሞ በአቅራቢያ ወደሚገኝ ተራራ ሊጸልይ ወጣ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ብዙም ሳይቆይ ኃይለኛ ወጀብ ተነሳ፤ እናም ደቀ መዛሙርቱ በሞገዱ በሚናጠው ባሕር ላይ የሞት ሽረት ትግል ማድረግ ነበረባቸው፡፡ ኢየሱስ በማዕበሉ ስትንገላታ ወደ ነበረችው ጀልባቸው በመምጣት በድጋሚ እስኪገለጥላቸው ድረስ ደቀ መዛሙርቱ በታላቅ ፍርሃት ተውጠው ነበር፡፡ ከተፈጥሮአዊው የፍርሃት ስሜት ውጪ፣ ኢየሱስ ባዘዛቸው ቦታ ላይ ይገኙ ነበርና የእርሱን ተስፋዎች በማሰብ በሞገዱ መካከል ጉዞአቸውን እንደቀጠሉ እንመለከታለን፡፡ እርሱ ያዘዛቸውን ነገር እየፈጸሙ ከቶ ለምን ይፈራሉ?

እግዚአብሔር ለሕይወታችሁ ያለውን እቅድ ተከትላችሁ መጓዛችሁን ማወቃችሁ እርሱ ወደሚፈልገው መዳረሻ እርሱ እንደሚያደርሳችሁ እንድትታመኑበት ይረዳችኋል፡፡ ልጅ እያለሁ፣ አንድ አውቶብስን በማስተዋወቅ ይነገር የነበረ ‹‹ግሬይሃውንድ ይተማመኑና መሪውን ለእኛ ይተውት›› የሚለውን የንግድ ማስታወቂያ አስታውሳለሁ፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥር መጠለል ማለት በግሬይሃውንድ አውቶብስ ውስጥ በሙሉ ደህንነት እንደመቀመጥ ማለት ሲሆን፤ የጉዞውን አደራ ሙሉ በሙሉ ለእርሱ በመስጠት እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ እንዲሰራ መጠበቅ፣ መቼም እንደማያሳፍራችሁ ደግሞ በሙሉ ልብ መተማመን ትችላላችሁ፡፡ የተስፋ ቃሉን እንደ ቀበቶ ታጥቀን የኢዮብን ቃላት እኛም ልንደግማቸው እንችላን፡- ‹‹የምሄድበትን መንገድ ያውቃል፤ ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ።›› (ኢዮ.23፡10)፡፡

በባቢሎን በምርኮ ተወስደው በነበሩት ሦስት ወጣት እስራኤላውያን ላይ የደረሰው ነገር ይሄው ነበር፡፡ የሞት ቅጣት የሚያስከትል ወንጀል እንደሰሩ ተከሰው በንጉሡ በናቡከደነጾር እንዲሞቱ ተወስኖባቸው ነበር፡፡ ከነሕይወታቸው ወደ ሚንበለበል እሳት ውስጥ እንዲወረወሩ ነበር የተፈረደባቸው (ዳን. 3)፡፡ እሳቱም ሰባት እጥፍ ነዶ ነበር፡፡ እንዲህ ያለ ከበድ ቅጣት የተላለፈበት ወንጀል ለመሆኑ ምን ነበር?

በዘመኑ ከነበሩት የሚፈሩ ነገስታት መካከል አንዱ የሆነው ናቡከደጾር፣ በአምሳሉ ቀርጾ በዱራ ሜዳ ላይ ላቆመው ግዙፍ የወርቅ ምስል እንዲሰግዱ በግዛቱ ውስጥ ለሚኙት ሁሉ ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር፡፡ አዲስ በወጣው ሕግ መሠረት የሙዚቃው ድምጽ በተሰማ ጊዜ፣ ሕዝቡ ሁሉ ግልጽ የሆነ የጣኦት አምልኮን በማካሄድ ንጉሡን እንደ አማልእክት ቆጥረው እርሱን ለሚወክለው ለምስሉ እንዲሰግዱ ይደነግግ ነበር፡፡ ነገር ግን ሦስቱ ወጣቶች አንሰግድም አሉ፡፡ እነዚህ ሦስት ሰዎች፣ ምንም እንኳን በባዕድ አገር ግዞተኞች ቢሆኑም፣ ለእውነተኛው አምላክ ታማኞች በመሆን ጸኑ፡፡ ለሰው ምስል ላለመስገድ አሻፈረኝ ሲሉ፣ በንጉሡ ፊት ለእግዚአብሔር ያላቸውን ጥልቅ ፍቅር ገለጡ፡፡ እምቢታቸው ለንጉሡ ሪፖርት ተደረገለት፡፡ እርሱም ካወጣው ሕግ ጋር ይስማሙ እንደሆነ ሁለተኛ እድል አበረከተላቸው፡፡ አቋማቸውን ተከትሎ የሚመጣባቸው መዘዝ ምን ያህል ለከባድ ስቃይ የሚዳርግ መሆኑን ጠንቅቀው ቢያውቁም፣ ከሚሰግዱ ይልቅ

መሞትን መረጡ፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ አሻፈረኝ ባሉ ጊዜ ድርጊታቸው እንደ ወንጀል ተቆጥሮ ለቅጣት ተላልፈው ተሰጡ፡፡ መልካሙ ዜና ታዲያ እግዚአብሔር አስደናቂ የሆነ የመታደግን ስራ በመስራት ታማኝነታቸውን መሸለሙ ነው፡፡

### ማጉምረምና ማማረርን ተቃወሙ

ከፊት ለፊታቸው ቀይ ባሕር ከኋላቸው ደግሞ የግብጽ ወታደሮች እያሳደዷቸው በሥቃይ የተሞላን ሞት በተጋፈጡ ጊዜ የእስራኤላውያን እምነትና ድፍረት ወደ ማጉምረምና ማማረር ተለወጠ፡፡ «በግብፅ መቃብር ስላልኖረ በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ አወጣኸንን?» በማለት በተስፋ መቁረጥ ተሞልተው ጮኹ፡፡ «ከግብፅ ታወጣን ዘንድ ይህ ያደረግህብን ምንድር ነው?» (ዘጸ. 14፡11)፡፡

ይህ ጨለምተኛ አስተሳሰብ የወለደው ትንቢታቸው እግዚአብሔርን አላከበረውም፤ በእርሱ ታማኝነት ላይ ጥልቅ የሆነ መተማመን እንደሚጎላቸው የሚገልጥ ነበር፡፡ ይህ የመታመን እጦት በሂደት ለጥፋት ዳረጋቸው፡፡ ብርቱ የሆነው ማጉምረማቸው ራሳቸው የተነበዩትን ትንቢት ራሳቸው እንዲፈጽሙት አደረጋቸው፡፡ ከግብጽ ያመለጡት አብዛኞቹ ጎልማሶች ወደ ተስፋይቱ ምድር አልደረሱም፡፡ ይልቁንም በምድረበዳ ተንከራተው፣ በመጨረሻ ሞቱ፡፡

በአዲስ ኪዳን በሚገኘው የመክሊቶቹ ምሳሌ ላይ (ማቴ. 25፡ 14-30)፣ የማጉረምረምና የማማረርን አደጋ በግልጽ እንመለከታለን፡፡ እንደምታስታውሱት በምሳሌው ላይ ሦስት አገልጋዮች የተለያየ የገንዘብ መጠን ተሰጥቶአቸው ነበር፤ ለመጀመሪያው ሰው አምስት መክሊት፣ ለሁለተኛው ሁለትና ለሦስተኛው አንድ፡፡ አንድ መክሊት የተሰጠው ሰው ሊያተርፍበት አልወደደም፤ ይልቁንም ገንዘቡን ለመቅበር ወሰነ፡፡ ለምንድን እንደዚህ እንዳደረገ በተጠየቀም ጊዜ በጌታው ላይ እንዲህ በማለት አጉረመረመ፡- «ጌታ ሆይ፥ ካልዘራህባት የምታጭድ ካልበተንህባትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ፤ ፈራሁም ሄጄም መክሊትህን በምድር ቀበርሁት፤ እነሆ፥ መክሊትህ አለ» (ማቴ. 25፡ 24-25)፡፡ በማጉረምረሙ ምክንያት አስቸኳይ ፍርድ ወዲያውኑ በእርሱ ላይ መጣ፤ ብቸኛ መክሊቱ ተወሰደበትና ከእርሱ ይልቅ በትጋት ለሰሩት ተጨመረ፡፡

የምንናገራቸው ነገሮች ወይ ሊገነቡን አልያም ሊያፈርሱን ይችላሉ፡፡ ምሳ. 18፡21 ይህንን እውነታ እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡- «ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው፡፡» እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ በስፍራችን ላይ ሆነን ስንጠብቅ፣ የጊዜ አቆጣጠሩን በተመለከተ በእግዚአብሔር ላይ ሳናጉረመርም በእርሱም ላይ ጥያቄ ሳናነሳ መቆየት አስቸጋሪ ሊሆንብን ይችላል፡፡ ነገር ግን የአንደበታችን ቃል ምን ያህል ከባድ መዘዝ እንደሚያስከትል በመረዳት፣ በጎ የሆነውን ጎን አጉልተን ለማየትና የማጉረምረምን ኃጢአት በመሸሽ አሉታዊ አስተሳሰብን ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡

### እግዚአብሔር ያደረገላችሁን ነገር አስታውሱ

እስራኤላውያን ከኋላ በቁጣ ተሞልቶ የሚገሰግሰው የግብጽ ሠራዊት እያሳደዳቸው ከፊት

ለፊታቸው ደግሞ ቀይ ባሕር ተጋርጦ በነበረበት በዚያ ጊዜ እንዳይደናገጡ ወይም እንዳያጉረመርሙ መጠባበቅ በእውነት እውነታን የተላበሰ ነውን? ለዚህ ጥያቄ መልሱ አዎንታዊ የሚሆነው እግዚአብሔር ከዚህ ቀደም ለእነርሱ ያደረገውን ያሰብን እንደሆነ ነው፡፡ የባርነትን እስራት በጣጥሶላቸው ነበር፡፡ይህንን ሲያደርግ በግብጽ ላይ አስር መቅሰፍቶች ያወረደ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፈርኦን ተዳክሞ እጅ ሰጠ፡፡ የመጨረሻው መዘረር የሆነው የሞት መልአክ መጥቶ የግብጻውያንን የበኩር ልጅ በገደለበት ጊዜ ነበር (ዘጸ. 11)፡፡ እስራኤላውያን ከቀይ ባሕር ጋር ፊት ለፊት በተፋጠጡበት ጊዜ፣ ሞት እንኳን አይቀሬ መስሎ በሚመጣበት ጊዜ በእርሱ መታመን እንዲችሉ የሚያደርጋቸውን ኃይሉን በተመለከተ በቂ የሆነ መረጃ ሰጥቶአቸዋል፡፡

እስራኤላውያን እረኛው ዳዊት እንዳደረገው ከጥርጣሬ ይልቅ እምነትን የሚገልጥ ድርጊት መፈጸም ይችሉ ነበር፡፡ ዳዊት እምነቱን እግዚአብሔር በገለጣቸው ታላላቅ ሥራዎቹ ላይ አደረገ፡፡ ከጎልያድ ጋር ለመጋጠም ፈቃደኛ ሆኖ በቀረበ ጊዜ፣ የቅርብ ሰዎቹ ሊያዳክሙት ሞክረው ነበር፡፡ ንጉሥ ሳኦልም እንዲህ አለው፡- «አንተ ገና ብላቴና ነህና፥ እርሱም ከብላቴንነቱ ጀምሮ ጦረኛ ነውና ይህን ፍልስጥኤማዊ ለመውጋት ትሄድ ዘንድ አትችልም» (1 ሳሙ. 17፡33)፡፡

በጨለምተኛ አስተሳሰብ ተውጠው የነበሩት እነዚህ ሰዎች ከዳዊት እምነትና ብሩህ እይታ ጋር የሚጣጣሙ አልነበሩም፤ እናም እግዚአብሔር አስቀድሞ እንዴት ከአንበሳና ከድብ መንጋጋ እንዳወጣው ለንጉሱ በፍጥነት አስታወቀው፡፡ ከዚያም «ይህም ፍልስጤማዊ ከእነርሱ እንዳንዱ ይሆናል» በማለት ቃል ገባ፡፡ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያደረገውን በማስታወስ፣ ዳዊት ከፊት ለፊቱም ለሚጠብቀው በረከት በእርሱ ላይ ተማምኖ ነበር፡፡ ይኼው ዳዊት ራሱ እንዲህ ብሎ ጽፎ ነበር፡- «ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ» (መዝ. 103፡ 2)፡፡ የመጠበቅን ጥበብ የሚለማመዱ ሁሉ ስለወደፊቱ በእግዚአብሔር ላይ መታመናቸውን የሚቀጥሉት በእነርሱም ሕይወት ሆነ በዓለም ታሪክ ውስጥ ያከናወናቸውን የቀድሞ ድርጊቶቹን በማስታወስ ነው፡፡

**እግዚአብሔር ለሰው የማይቻለውን ሊያደርግ እንደሚችል እመኑ**

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር እስኪሰራ የማንጠብቅበት ምክንያት ግድድሮቮቹ በጣም ከባድ ስለሚመስሉ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሊያከናውናቸው የሚችላቸው ነገሮች እንዳሉ እናምናለን፤ ነገር ግን አንዳንዶቹ ለእርሱም ቢሆን በጣም አስቸጋሪ ይመስሉናል፡፡ በእነዚህ ጊዜያት ታዲያ እኛም ሴት ልጁ በጠና ታማበት ወደ ነበረው የምኩራብ አለቃ ወደ ኢያኢሮስ እንደሄደው ወዳጁ እንሆናለን፤ እንዲህም እንላለን፡- «ልጅህ ሞታለች፤ እንግዲህ መምህሩን አታድክም» (ሉቃ. 8፡49)፡፡ የሚያስደስተው ነገር፣ ኢያኢሮስ እንዲያምንና በእምነትም መንገዱን ወደፊት እንዲቀጥል ከኢየሱስ የተሰጠውን ትእዛዝ ተቀብሎ ኢያኢሮስ በኢየሱስ ላይ መታመኑን ቀጠለ፡፡ ከኢየሱስ ጋር ወደ ቤት በደረሱ ጊዜም፣ የዚህ ሰው እምነት ሽልማትን አገኘ፡፡ ኢየሱስም የማይቻለውን በማድረግ ልጁን ከሞት አስነሳለት፡፡

ተፈጥሮአዊውን አካሄድ ውድቅ በማድረግ፣ ለማርያም መልአኩ ተገልጦላት

በመለኮታዊ ኃይል እንደምትጸንስና ቃል የተገባውን መሲህ እንደምትወልድ እንደገለጸላት የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ይነግረናል፡፡ ያቺም አይሁዳዊ ሴት «ይህ እንዴት ይሆናል፣ እኔ እኮ ወንድ አላውቅም?» በማለት በትህትና ሰማያዊውን መልእክተኛ ጠየቀች፡፡ «ለእግዚአብሔር የሚሳነው አለን?» በማለት መለሰላት፡፡ እግዚአብሔር እስኪሰራ ድረስ በትእግስት የሚጠብቁ ሁሉ እነርሱ ከሚጠይቁት ወይም ከሚያስቡት ሁሉ በላይ ሊያደርግ እንደሚችል ፣ የማይቻልም እንኳን ቢሆን ሊያደርግ እንደሚችል የተማመኑ ናቸው (ኤፌ. 3፡20)፡፡

**በሥራ ላይ ሳይሆን በእምነት ላይ ተደገፉ**

በሥራ ላይ ሳይሆን በእምነት ላይ በምንደገፍበት ጊዜ እግዚአብሔርን እስኪሰራ ድረስ መጠበቅ ቀላል ይሆንልናል፡፡ በቀይ ባሕር ዳርቻ ላይ ቆመው፣ የእስራኤል ልጆች ከተሰጣቸው የሚከተለው ትእዛዝ ጋር ይታገሉ ነበር፡- «ቁሙ፥ ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ።» (ዘጸ. 14፡13)፡፡ በሌላ አነጋገር፣ «መፍጨርጨራችሁን አቁሙ፤ ራሳችሁን ለማዳን መጣጣራችሁ ይቁም፤ የመለኮትን ሂደት ተማመኑ» ማለት ነበር፡፡

የመለኮት ሂደት ደግሞ ጸጋ ነው፡፡ በሰብአዊ ጥረቶች ለመዳን መሞከር ማለት በሁለት ተራሮች መካከል ያለን ጥልቅ ሸለቆ ከአንዱ ጫፍ ተነስቶ ወደ ሌላው ለማቋረጥ እንደመዝለል ያህል ነው፡፡ ሰብአዊ ጥረቶች ይህንን ለማድረግ በጣም ብዙ ነገር ይጎድላቸዋል፡፡ ይህ ታዲያ ያለ እርዳታ አይሞከርም፡፡ ምናልባት አንዳንድ ሰዎች ከሌሎቹ በተሻለ ከአንዳንድ ከፍታዎች ላይ ሊዘሉ ይችሉ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በመጨረሻ ሁሉም ቢሆኑ ይህንን ዝላይ በተሳካ ሁኔታ ማከናወን ሳይችሉ ቀርተው ይሞታሉ፡፡

ኤፌ. 2፡8 ደህንነት የሚገኘው «በጸጋው በእምነት እንጂ በሥራ እንዳልሆነ» ይነግረናል፡፡ ከእግዚአብሔር በነጻ የተሰጠን ነው፡፡ በእምነት ጠንክረን መዝለል እንድንችል ይረዳናል፡፡ የእኛ ጥረቶች ፣ በሰብአዊ ተፈጥሮ ውስንነትና በተፈጥሮ ሕጎች በተገደበ ጊዜ፣ እምነት እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ እንዲከናወን የፈለገውን ሁሉ ማከናወን እንዲችል የመለኮትን ብርታት ይጨብጣል፡፡

በማቴ. 8 ላይ የሚገኘው የጦር አዛዥ ይህ የእምነት ጥንካሬ የነበረው ሰው ነበር፡፡ በእርሱ ዘንድ ተወዳጅ የነበረው አገልጋዩ ታሞበት ስለነበር ኢየሱስ ይፈውስለት ዘንድ ለመለመን ወደ እርሱ ቀርቦ ነበር፡፡ ኢየሱስም «ወደ ቤትህ እሄዳለሁ አለው፡፡» መቶ አለቃው ግን «ይህ አይደረግም» አለ፡፡ «ጌታ ሆይ፣ አንተ ቃል ብቻ ተናገር ባሪያዬ ይፈወሳል፡፡» አለ፡፡ ኢየሱስም በመገረም ተሞልቶ እንዲህ አለ፡- «እንዲህ ያለውን እምነት በእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝቦች መካከል እንኳን አላገኘሁም፡፡ ይህ አይሁዳዊ ያልሆነ ወታደር የኢየሱስ ደቀመዛሙርት እንኳን የጎደላቸውን የክርስቶስን ኃይል መረዳት ችሎ
ነበር፡፡ እምነቱ ኢየሱስን በእጅጉ ስላስደሰተው አገልጋዩን ወዲያውኑ ነበር የፈወሰለት፡፡

እግዚአብሔር ለሥራ እስኪንቀሳቀስ ድረስ ልትጠብቁት ፈቃደኞች ናችሁ? እርሱ

የማይቻል የሚባለውን ሁሉ ሊያደርግ እንደሚችል የሚያምን ጥራት ያለው እምነት አላችሁ? «ጸንታችሁ በመቆም የእግዚአብሔርን ማዳን ለማየት» የሚስችላችሁ መተማመን በእግዚአብሔ የተስፋ ቃላት ላይ አላችሁ? ያን ጊዜ ብቻ ነው ኃይላችሁ የሚታደሰውና በንሥር ክንፍ በከፍታዎች ላይ መብረር የምትችሉት፡፡ ያን ጊዜ ብቻ «ትሮጣላችሁ አትደክሙም፤ ትሄዳላችሁ አትታክቱም፡፡» (ኢሳ. 40፡31)፡፡

የተጠራንበት ሕይወት በሞት ውስጥ ያለፈ እንጂ በጎን አልፎት የመጣ አይደለም፡፡ እናም የተሸከምነው የመከራ ክብደት ተጭኖን በጉልበታችን ሲያንበረክከን፣ በመስቀሉ ኃይል እንጠብቅና እንነሳለን፡፡ ሕይወታችንን ለማግኘት እናጣዋለን፡፡

## በመጠበቅ ለማሸነፍ የሚረዱችሁ ወሳኝ እርምጃዎች

- እግዚአብሔርን ጠብቁ
- በእግዚአብሔር አዘጋጅነት ታመኑ
- ማጉረምረምና ማማረርን ተቃወሙ
- እግዚአብሔር ያደረገላችሁን ነገር አስታውሱ
- እግዚአብሔር የማይቻለውን ሊያደርግ እንደሚችል እመኑ
- በሥራ ላይ ሳይሆን በእምነት ላይ ተደገፉ

# 9

# ከስቃይ ውስጥ በረከቶችን አውጡ

በባልቲሞር ከተማ ሳድግ፣ መከራዎቼ አንድ ቀን ሌሎች ሰዎችን ለመባረክ ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ፈጽሞ ሕልሙ አልነበረኝም፡፡ በጣም አሳዛኝ የምለው እናቴ የሞተችበት ቀን እንኳን ሳይቀር ከሃዘኔ ውስጥ መልካም የሆነን ነገር እግዚአብሔር ሊያወጣበት ችሎ ነበር፡፡ ከምንወዳቸው ሰዎች ያለጊዜ መቀጨት መልካም ነገር እንዴት ሊወጣ እንደሚችል ማየት አልችልም ነበር፤ ነገር ግን በእርግጥም ሆኖአል፡፡

እናቴ ከሞተች ከጥቂት አመታት በኋላ፣ ሁለት ወጣት ልጆቿ ከሞቱባትና በደረሰባት ሃዘን ከደነዘዘች ሴት ጋር ተቀምጬ ነበር፡፡ እነዚያ ውብ ልጃገረዶች የሞቱት በአደጋ ምክንያት ሲሆን፣ እናታቸው ፍጹም መጽናናት አቅቷት ነበር፡፡ የምናገራት ቃላት የሰቆቃዋን ጭጋግ ሰንጥቀው መግባት ተስኖአቸው ነበር፡፡ በወንበሩ ላይ ግትር ብላ ተቀምጣ፣ በፈዘዙ አይኖች እያየች ግን አታይም ነበር፡፡ ከዚያም ስለ እናቴ ሞት መናገር ጀመርኩ፡፡«ታውቂያለሽ» አልኳት «በቁጣ የተሞሉ ጸሎቶችን ጸልዬ ነበር፡፡ ለጠላት እንኳን የሚነገረውን የመሰናበቻ ቃል ተናግሬያት እንዳትሞት ራሷን ከሳተችበት ነቅታ እንድትሞት ባለማድረጉ ትክክል አላደረግህም! ብዬ በእግዚአብሔር ላይ ተናግሬአለሁ፡፡» ከዚያም እግዚአብሔር ከዚያ የብስጭት ጨለማ ሌሊት እንዴት እንደታደገኝ ነገርኳት፤ ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን በመሪር ሃዘን ከተመታችው ከዚህች ሴት ምንም አይነት ምላሽ ላገኝ አልቻልኩም፡፡ አንድም ቃል አልመለሰችልኝም፡፡ ለመሆኑ ሰምታኛለች? ኢላማዬን የሳትኩ መሰለኝ፡፡

ከአንድ ሰአት በኋላ፣ እንዳልተሳካልኝ ያሰብኩት በችኮላ ተሳስቼ እንደነበረ አስተዋልኩ፡፡ ለመሄድ ስዘጋጅ፣ ተነሳችና አቀፈችኝ፡፡ በድርጊቷ ተገርሜ ሳለሁ፣ ከአፏ ቃል እንዲወጣ ተጠባበቅሁ፡፡ ለማስተዋል የሚያዳግቱ ቃላትን በአፏ አልጎመጎመች፤ እኔም ይበልጥ በጥራት ለመስማት ዝቅ አልኩኝ፡፡ ከዚያም ለስለስ ባለ ነገር ግን በደንብ በሚሰማ ድምጽ እንዲህ አለች፡- «በዚህ ሁሉ መከራ ውስጥ በመጠኑም ቢሆን ትርጉም የሰጠኝ ነገር ቢኖር ዛሬ አንተ የተናገርከው ነገር ነው፡፡» ደህና ሁኝ ስላት፣ ጉንጬን ሳመችኝ፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን! ደካማ ቃላቶቼ ከእርሷ ፍላጎት ጋር ተጣምረው መጽናናትን አመጡ፡፡ እግዚአብሔር የእኔን በስቃይ የተሞላ ልምምድ ሌሎች ሰዎችን ለመባረክ ተጠቀመበት፡፡ ከእግዚአብሔር በተቀበልኩት መጽናናት፣ ይህች እናት ተጽናናች፡፡በመከራዬ ውስጥ ካገኘሁት በረከት ተጠቃሚ ሆነች፡፡

**መከራን ተጠባበቁ**

ለምድን ነው መጥፎ ነገር በመልካም ሰዎች ላይ የሚደርሰው? ብዙ ጊዜ በሕይወት ውስጥ የሚሆኑ ነገሮች ይህንን ጥያቄ በመገረም እንድንጠይቅ ያደርጉናል፡፡ ከምፈልገው በላይ ይህንን ጥያቄ ሳሰላስለው ራሴን አገኘዋለሁ፡፡ መልሱም አንዳንድ ጊዜ አጥጋቢ አይደለም፡፡ እርግጥ ነው፣ አንዳንድ ስቃዮች የሚደርሱብን ሰዎች ስለሆንን ነው፡፡ በኢዮ. 14፡1 ላይ ሰብአዊ ፍጥረት የሚኖረው ለአጭር ጊዜ እንደሆነና ይኼውም የመከራ ሕይወት መሆኑን ያስታውሰናል፡፡ ምድራዊ ጉዞአችን በራሱ በግድድሮሾች የተሞላ ነው፡፡ ከሎንግ ፌሎ አሁንም ደግሜ ለመጥቀስ፣ « ሕይወት እውነታ ናት! ሕይወት ቁም ነር ናት! መቃብርም ግቧ አይደለም፡፡»

ኤም፣ ስካውት ፔክ የተሰኘውን ግሩም መጽሐፉን «ሕይወት አስቸጋሪ ናት» በማለት ነው የሚጀምረው፡፡ በዮሐ. 16፡33 ላይም፣ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብላችኋል «በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።»፡፡ በፕላኔት መሬት ላይ ነው የምትኖሩት? እንግዲያውስ መከራ እንደሚደርስባችሁ እርግጠኞች ሁኑ፡፡ ሌሎች መከራዎች ደግሞ የሚመጡብን እግዚአብሔርን በመውደዳችንና እርሱንም በማገልገላችን ሳቢያ ነው፡፡ ብርሃን የጨለማ ጠላት ነው፤ እውነትም የሐሰት ወዳጅ አይደለም፡፡ ውሃና ዘይት መቀላቀል እንደማይችሉ ሁሉ ጽድቅና እርኩሰት እንዲቀላቀሉ መጠበቅ የለብንም፡፡ 2 ጢሞ. 3፡12 እንዲህ ይላል፡- «በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ።» የመከራዎች መከሰት አያስደንቃችሁ፡፡ የነፍሳት ጠላት በእኛ ላይ በመቆጣቱ ምክንያት የሚመጡ ናቸው፡፡

ሌሎች መከራዎች ደግሞ የሚደርሱብን በእነዚያ በምናልፍባቸው አስቸጋሪ ልምምዶች እግዚአብሔር ስለሚከብር ነው፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን እውር ሆኖ የተወለደው ሰው ነው (ዮሐ. 9፡3)፡፡ የደረሰበት ችግር የኃጢአቱ ውጤት ሆኖ የመጣ አልነበረም፡፡ ይልቁንም «የእግዚአብሔር ስራ በእርሱ እንዲገለጥ» ነበር፡፡ እንግዲህ በስቃይ ውስጥ ጥቅም ማግኘት ማለት ይኼ ነው፡፡

**የእግዚአብሔርን ጸጋና ሰላም ተለማመዱ**

እግዚአብሔር በእኛ ስቃይ ሌሎችን መባረክ እንዲችል በቅድሚያ እኛ ራሳችን የእሱን ጸጋና ፍቅር በመለማመድ መንገዱን እናመቻችለታለን፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይጽፋል፡- «ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።» (2 ቆሮ. 1፡2)፡፡ ከዚያም ታላቁ ሐዋርያ ሌሎችን ለማጽናናት እንችል ዘንድ እንዴት እግዚአብሔር እኛን እንደሚያጽናናን ይጽፋል፡፡ ነገር ግን ይህ መጽናናቱን የምንካፈልበት ልምምድ የእግዚአብሔርን ጸጋና ሰላም መካፈልን ያስቀድማል፡፡ ይህ ሰላም በሕይወት ማዕበል ውስጥ የተረጋጋን እንድንሆን እንደዚሁም ስቃያችንን በትክክለኛው እይታ እንድንመለከተው ያስችለናል፡፡ እንዲህ ያለው አመለካከት በአንድ ወቅት ዳዊትን እንዲህ ብሎ እንዲጽፍ አስችሎት ነበር፡- «እኔ ሳልጨነቅ ሳትሁ አሁን ግን ቃልህን ጠበቅሁ።» (መዝ. 119፡ 67)፡፡

ጸጋውንና ሰላሙን መለማመድ ምን ይመስላል? ኤልሳዕ በ 2 ነገ. 6 ላይ

ከተለማመደው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ የሦርያው ንጉስ ከእስራኤል ጋር እየተዋጋ ነበር፤ በቁጥጥር ስር እንዲያውሉት ሠራዊቱን በዶታን ወደሚገኘው የእግዚአብሔር ነብይ ልኮ ነበር፡፡ በምሽትም ወታደሮችንና ሰረገሎች ላከ፤ እነርሱም ኤልሳዕ የሚኖርበትን ከተማ ከበቡ፡፡ በማለዳ፣ የነብዩ ባርያ በመስኮት ወደ ውጪ ሲመለከት የጠላት ወታደሮች መኖሪያቸውን ከብበው አየ፤ እንዲህም ሲል ጮኸ፡- «ጌታዬ ሆይ፥ ወዮ! ምን እናደርጋለን?» (2 ነገ. 6፡15)፡፡

ነገር ግን ኤልሳዕ አልተሸበረም፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋና ሰላም የሚያስገኘውን መረጋጋት ያውቅ ነበር፤ እንደዚሁም አገልጋዩ ሊያይ ያልቻለውን ማየት ይችል ነበር፡፡ እንዲህም ብሎ ጸለየ፡- «አቤቱ፥ ያይ ዘንድ ዓይኖቹን፥ እባክህ፥ ግለጥ» (2 ነገ. 6፡17)፡፡ የአገልጋዩም አይን በተከፈተ ጊዜ፣ በዙሪያቸው ያሉት ኮረብቶች ሁሉ በእሳት ፈረስና ሰረገሎች እንደተሞሉ ተመለከተ፡፡ ከዚያም የእግዚአብሔር ዝግጅት ከእነርሱ ፍላጎት በላይ እንደሆነ አስተዋለ፤ ይህም የእግዚአብሔር ጸጋ ግልጽ የሆነ መገለጥ ሰላምን ሰጠው፡፡

ሰላማችሁን የነሳችሁ ነገር ምንድን ነው? መከራዎቻችሁን እንደ መወጣጫ ደረጃ ሳይሆን እንደ እንቅፋት ድንጋይ እንድታዩዋቸው የሚያደርጓችሁ ነገሮች ምንድን ናቸው? የእግዚአብሔርን ጸጋና ሰላም በመለማመድ፣ የሕይወትን ማዕበል ያለ ፍርሃትና መደናገጥ ለመጋፈጥ ትችላላችሁ፡፡ በምስጋና ተሞልታችሁ በመጸለይ የምትፈልጉትን ነገር ለእግዚአብሔር ስታሳውቁት፣ ከሰው አእምሮ በላይ በሆነው ሰላም ትሞላላችሁ (ፊል. 4፡ 6-7)፡፡

የሚያውካችሁ ነገር ምንም ይሁን ምን አሁኑኑ በጸሎት ይዛችሁት ቅረቡ፡፡ ነገር ግን ስትጸልዩ፣ ምስጋናችሁ ለልመናዎቻችሁ ክንፍ እንዲሆኑላቸው አድርጉ፤ ያን ጊዜ መለኮታዊ ሰላም ልባችሁን ያጥለቀልቀዋል፡፡ ይህ ሰላም ወደ ሁለተኛው ደረጃ ይመራችኋል፤ እርሱም በምስጋና የተሞላ ሕይወት ነው፡፡

**በምስጋና የተሞላ ሕይወት ኑሩ**

ምን ያህል በመደጋገም እግዚአብሔርን ታመሰግናላችሁ? ዳዊት እንዲህ ይላል፡- «እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ፥ ምስጋናውንም ዘወትር በአፌ ነው። ነፍሴ በእግዚአብሔር ትከብራለች፥ ገሮችም ሰምተው ደስ ይላቸዋል። እግዚአብሔርን ከእኔ ጋር ታላቅ አድርጉት፥ በአንድነትም ስሙን ከፍ ከፍ እናድርግ» (መዝ. 34፡ 1-3)፡፡ ይህንን መዝሙር በጻፈበት ጊዜ ዳዊት የምስጋናን ሕይወት መኖርን ተምሮ እንደነበረ ግልጽ ነው፡፡

ለምንድን ነው በምስጋና የተሞላ ሕይወት የምንኖረው? መልሱ ቀላል ነው፡- አምላካችን በምስጋና ስለሚኖር (መዝ. 22፡3)፡፡ አመስጋኝ መሆን እግዚአብሔርን ወደ ሕይወታችንና ወደ ወቅታዊው ሁኔታችን ይጋብዘዋል፡፡ ጳውሎስና ሲላስ ኢፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተገርፈው በተሰቃዩ ጊዜ በምስጋና ዝማሬያቸው መጽናናት ማግኘታቸው ብቻ ሳይሆን፣ ሰማያዊ እርዳታን ለመጋበዝ ምስጋናን መጠቀማቸው በአጋጣሚ አልነበረም፡፡

ምስጋናቸው እነርሱን ከእስር ነጻ ያወጣ እነደዚሁም ለእስር ቤቱ ጠባቂና ለቤተሰቡ መንፈሳዊ ነጻ መውጣትን ያስገኘ የመሬት መናወጥ አስነሳ (የሐዋ. 16)፡፡ እናንተስ ምን አይነት ተገቢ ያልሆነ ሁኔታ ወይም ግፍ እየተጋፈጣችሁ ነው? በወዳጃችሁ ወይም በጣም በምትወዱት የቅርብ ቤተሰብ ክህደት ደርሶባችሁ ይሆን? የሥራ አጥነት ሸክም ትከሻችሁን አጉብጦት ይሆን? የሕይወታችሁ ሰላም በሐዘን ጥቁር ደመና ተከቦ ይሆን? እንግዲያውስ እግዚአብሔርን ማመስገን አትርሱ፡፡ የምትገኙበት ሁኔታ ምንም ይሁን ምን፣ እናመሰግን ዘንድ የተሰጠንን ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ትእዛዝ እንታዘዝ፡- «በሁሉ አመስግኑ፤ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና።» (1 ተሰ. 5፡18)

በግሌ በማልፍባቸው የሰቆቃ ጊዜያት እናንተን ሊረዳ የሚችል ሕይወት ለዋጭ ልምምድ አግኝቻለሁ፡፡ ቆም እልና እግዚአብሔርን የማመሰግንባቸውን ርዕሶች እዘረዝራለሁ፡፡ በአጭሩ፣ ባርኮቴን እቆጥራለሁ፡፡ በምስጋና መኖር የእግዚአብሔርን መገኘትና ኃይል የሚጋብዝ ሲሆን፣ በመከራዎቻችን መካከልም መጽናናትን እንድናገኝ ያግዘናል፡፡

**እግዚአብሔርን ባርኩ**

ጌታን የመባረክ የሥራ ድርሻ እንዳላችሁ ታውቃላችሁ? መከራችሁን ወደ በረከት ለመለወጥ የሚያግዝ እንደሚሆን ታያላችሁ፡፡ «ዳዊትም ጉባኤውን ሁሉ። አምላካችሁን እግዚአብሔርን ባርኩ አላቸው። ጉባኤውም ሁሉ የአባታቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ባረኩ፥ ራሳቸውንም አዘንብለው ለእግዚአብሔርና ለንጉሡ ሰገዱ።» (1 ዜና. 29፡ 20)፡፡ እግዚአብሔርን መባረክ ማለት እርሱን ማመስገንና ለስሙም የሚገባውን ክብር መስጠት ማለት ነው፡፡

ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር መስጠት በጣም ወሳኝ ከመሆኑ የተነሳ ከእያንዳንዱ ፍጥረት ይህንን ማድረግ ይጠበቃል፡፡ መዝሙረኛው እንዲህ በማለት ይጽፋል፡- «እባቦች ጥልቆችም ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ከምድር አመስግኑት፤ እሳትና በረዶ አመዳይና ውርጭ፥ ቃሉን የሚያደርግ ዐውሎ ነፋስም» (መዝ. 148፡7-9)፡፡ በእርግጥ ተፈጥሮ እግዚአብሔርን ማመስገን ይችላል? ኢየሱስ እንደሚችል የሚያስብ ይመስላል፡፡ አንዳንድ ፈሪሳውያን ከመሰቀሉ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ በእሁድ እለት ብዙዎች እያመሰገኑት ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ተከፍተው አጉምርመው ነበር፤ ኢየሱስ ግን እንዲህ በማለት መለሰ፡- «እላችኋለሁ፥ እነዚህ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይጮኻሉ» (ሉቃ 19፡40)፡፡ አዎ፣ ሕይወት የሌላቸው ፍጥረታት እንኳን ሳይቀሩ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ፡፡ እኔ ለእግዚአብሔር ምስጋና ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆንሁት በላይ ድንጋዮቹ እንዲሰጡ አልፈልግም፡፡

አንዳንድ ጊዜ ስብከቴን የምጀምረው ለምን በዚያ እንዳለሁ ጉባዔውን በማስታወስ ነው፡፡ ለማምለክ ተጉዤ የመጣሁት አገልጋይ ስለሆንኩ እንዳልሆነ ፤ ነገር ግን ማመስገን ስራዬ እንደሆነ እነግራቸዋለሁ፡፡ በእያንዳንዱ አምልኮ ውስጥ የሚገኝ የምስጋና ደስታ በጥልቀት ይሰማኛል፤ ለክርስቶስ በሚቀርብ የህብረት አምልኮና ምስጋና መሳተፍም ከፍተኛ ደስታ ይሰጠኛል፡፡ ከዚያም በቤተ ክርስቲያን በማገልገንበትም ጊዜ ቢሆን

እግዚአብሔርን ማመስገን መልመድ እንዳለብን ለጉባዔው እናገራለሁ፤ ምክንያቱም በሳምንቱ መጨረሻ ብቻ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ ሰዎች ለብዙ ቀናት ዳካሞች ይሆናሉና፡፡ በማንኛውም ጊዜ እግዚአብሔርን ማመስገን በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እርሱን የመባረክ ችሎታችሁን ያሳድገዋል፡፡ እንዲህ ያለውን የማመስገን ልምድ የተለማመዱ ሰዎች በመንፈሳቸው ወደ ሰማያዊው ስፍራ ከፍ ለማለት የመዘምራን ቡድን ወይም ሙዚቃ ወይም ጸሎቶች አያስፈልጓቸውም፡፡ ወደ አምልኮ ስፍራዎች ሁሉ ምስጋናቸውን ይዘው ይመጣሉ፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔርን ማመስገን የሕይወታቸው እንደዚሁም የእስንፋሳቸው አንድ አካል ነውና፡፡

ከእርሱ ጋር ልብ ለልብ ለመገናኘት ጊዜ መድባችሁ፣ እግዚአብሔርን በየእለቱ ታመሰግኑታላችሁ? ቀናችሁ በሚጀምርበት ጊዜ ስለ እግዚአብሔር መልካምነት ሳታመሰግኑ በሌሎች ስራዎች የምትጠመዱበት ምን ያህል ጊዜ ነው? ከከንፈራችሁ በማያቋርጥ ሁኔታ በሚፈልቅ የምስጋና ቃል ጌታን ሁልጊዜ ትባርኩታላችሁ? ይህንን የምታደርጉ ከሆነ፣ በመከራችሁ ውስጥ በረከትን ለማግኘት በመንገድ ላይ ናችሁ ማለት ነው፡፡

**ትክክለኛውን አመለካከት ያዙ**

ልጅ ሳለሁ ይህችን ትንሽ ግጥም ሰምቼ ነበር፡- «ሁለት ሰዎች በእስር ቤቱ ብረት ፍርግርግ አሻግረው ያያሉ፤ አንደኛው ጭቃውን ሌላኛው ከዋክብቱን ይመለከታሉ፡፡» ፍሬድሪክ ላንግብሪጅ እንደተናገረው የሚነገርለት ይህ አባባል የአመለካከታችን ኃይል ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ያስታውሰኛል፡፡ ሼክስፒር በሐምሌት አፍ ውስጥ ያሰቀመጣቸውን እነዚህን ቃላት የሚያስተጋባ ነው የሚመስለው፡- «ጥሩ ወይም መጥፎ የሚባል ነገር የለም፤ ጥሩም ሆነ መጥፎ የሚያደርገው አመለካከት ነው፡፡»

ማመስገን አመለካከታችን ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ የእግዚአብሔርን መልካምነትና አስቀድሞ የሰጠንን ባርኮቶች ያስታውሰናል፡፡ እንደገና ዳዊት እንዲህ ይላል፡- «ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ አጥንቶቼም ሁሉ፥ የተቀደሰ ስሙን። ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥ ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ» (መዝ. 103፡ 1-2)፡፡ እያችሁ፣ እስካሁን ከእግዚአብሔር ባርኮቶች እንዴት ተጠቃሚ እንደሆናችሁ ስታስታውሱ፣ አሁን ስለደረሰባችሁ መከራ የሚኖራችሁን አመለካከት ይለውጠዋል፡፡

ስለ አባቴ ከማስታውሳቸው አስደሳች ነገሮች መካከል አንዱ፣ «እንዴት ነህ?» ለሚለው ጥያቄ ይሰጥ የነበረውን መልስ ነው፡፡ ሁልጊዜ ማለት ይቻላል «ላጉረመርም አልችልም» በማለት ነበር የሚመልሰው፡፡ ጊዜያት እያለፉ ሲሄዱ፣ ያ መልሱ ይበልጥ ገጣሚ እየሆነ መጣ፡፡ በእርግጥም እግዚአብሔር ያደረገልንን ነገር ሁሉ ስናስታውስ፣ እንዴት አድርገን ልናጉረመርም እንችላለን?

ማጉረምረም እስራኤላውያን ከግብጽ እስከ ከነዓን ያደረጉት ጉዞ ላይ የፈጸሙት ታላቁ ስህተት ነበር፡፡ ስለገጠማቸው የምግብና የውሃ እጥረት አጉረመረሙ፤ እንደዚሁም በግብጽ የበሉትን ቅመም የበዛበት ምግብ ናፈቁ (ዘኍ. 20)፡፡ ምናልባት እግዚአብሔር

የሰጣቸውን ነገሮች ረስተው ይሆናል፡፡ በበረታች ክንዱ ከግብጽ አውጥቶአቸው ነበርና፣ የባርነት ሕይወትን አምልጠው ነበር፡፡ በደመና አምድ እየመራ ከአለትም ውሃ እያፈለቀላቸው ነበር፡፡ ጫማና ልብሳቸው አላለቀም፤ በምድረበዳ ከሚገኙ አጥፊ አውሬዎችም ጠብቆአቸው ነበር፡፡ ያም ሆኖ ግን አጉረመረሙ፡፡ የእግዚአብሔርን መልካምነት ለማስታወስ ያለመቻላቸው ውድቀትም ብዙዎችን ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዳይገቡ ምክንያት ሆነባቸው፡፡

የሞተው ታላቁ የወንጌል ዘማሪ ጄምስ ክሊቭላንድ እንዲህ የሚሉ ቃላት ያሉበትን መዝሙር ይዘምር ነበር፡- «እስከዚህ ድረስ እየመራ ያመጣኝ እግዚአብሔር ጥሎኝ ሊሄድ ነው ብዬ አላምንም፡፡» እንዴት ያሉ ግሩም በእግዚአብሔር መልካምነት ላይ የመደሰት ቃላት ናቸው፡፡ ክሊቭላንድ እግዚአብሔር እስካሁን መርቶ ያመጣውን አስቸጋሪ ጎዳና መለስ ብሎ በመመልከት እርሱን የሚያመሰግንበት ምክንያት እንደሚያገኝ እየተናገረ ነበር፡፡ በሕመምና ወደ ኋላ በማፈግፈግ፣ በተስፋ መቁረጥና በውድቀት ውስጥ የጠበቀው አምላክ ሕያውና ብርቱ አምላክ ሲሆን፣ አሁንም ቢሆን በእንክብካቤ የተሞላ፣ ምሪቱን መስጠት መቀጠል ይችላል፡፡ ይህንን ማስተዋሉ ክሊቭላንድን በደስታ እንዲሞላ አደረገው፤ የእግዚአብሔርን ባርኮትና ጥቅሞች እንዲያስታውስ ረዳው፡፡

እናንተስ? ሕይወታችሁን መለስ ብላችሁ ስታዩ፣ የእግዚአብሔር እንክብካቤ በሸለቆዎች ውስጥ ሳይቀር እንዴት እንደመራችሁ ትመለከታላችሁ? አሁንም እግዚአብሔር ሊጠብቃችሁና ሊደግፋችሁ እንደሚችል ሙሉ መተማመኑ አላችሁ? ባርኮታችሁን ቆጥራችሁ ሕይወታችሁ ሊሆን ይችል ከነበረው አሁን በተሻለ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አስተውላችኋል? እንዲህ ያለው አመለካከት ከመከራዎቻችን ውስጥ መርዙን ያስወግዳል፡፡

### በምህረት አባት ላይ ተደገፉ

ጳውሎስ እግዚአብሔርን «የምሕረት አባት» (2 ቆሮ. 1፡3) በማለት ይጠራዋል፡፡ ምሕረት ወሳኝ የሆነ መለኮታዊ ባሕርይ ነው፤ ምክንያቱም ሰብአዊ ዘር ከምድረ ገጽ ያልተወገደው በእግዚአብሔር ምህረት ነውና(ሰቆ. ኤር. 3፡22)፡፡ እግዚአብሔር ለእኔ ያሳየው ምሕረት የማያቋርጥ ውዳሴን ለማቅረብ ልቤን ያነሳሳኛል፡፡

በማቴ. 9፡27-29፣ ሁለት ማየት የተሳናቸው ሰዎች ከኢየሱስ ኋላ እየተከተሉ ምህረት እንዲያደርግላቸው ይለምኑ ነበር፡፡ ኢየሱስም ወደ እነርሱ ዘወር ብሎ ስለ እምነታቸው የሚከተለውን ጥያቄ ጠየቀ፡- «ይህን ማድረግ እንድችል ታምናላችሁን?» እነርሱም ለጥያቄው አዎንታዊ መልስ በሰጡ ጊዜ፣ ዐይኖቻቸውን በመንካት እንዲህ አለ፡- «እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ» (ማቴ. 9፡29)፡፡ ይህ ኢየሱስ ደግሞ እርሱን ተመለከቱ ማለት እግዚአብሔርን ተመለከቱ ማለት እንደሆነ ለደቀ መዛሙርቱ ነገሮአቸው ነበር(ዮሐ. 14፡9)፡፡ የክርስቶስ ሕይወት የእግዚአብሔርን መልክ ያሳየናል፤ በክርስቶስ በኩልም ይህንን አምላክ አባታችን ብለን ልንጠራው እንችላለን፡፡ ኢየሱስ ለሰብአዊ ዘር ያሳየውን አይነት ምህረት አሁንም ሆነ ለዘላለም ከሰማዩ አባታችን መጠባበቅ እንችላለን፡፡

እግዚአብሔር የእርሱን ምህረት እንድናስታውስ ይጠብቅብናል፡፡ ለእስራኤላውያን እንዲህ ነበር ያላቸው፡- «አምላክህ እግዚአብሔር ይፈትንህ ዘንድ፥ በልብህም ያለውን ትእዛዙን ትጠብቅ ወይም አትጠብቅ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ፥ ሊያስጨንቅህ በእነዚህ በአርባ ዓመታት በምድረ በዳ የመራህን መንገድ ሁሉ አስብ።» (ዘዳ. 8፡2)፡፡

የእግዚአብሔርን ምሕረት ማስታወሳችን በምስጋና እንድንሞላ ብቻ ሳይሆን፣ ፈተናን እንድንቋቋምም ያግዘናል፡፡ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ኃጢአት ከሰራ በኋላ፣ ነብዩ ናታን ወደ እርሱ ቀርቦ እግዚአብሔር በስውር የፈጸመውን በደል እንደሚያውቅ በማሳሰብ ከቀደመው ታሪክ ትምህርት ሰጠው፡፡ «የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡ በእስራኤል ላይ ንጉሥ ልትሆን ቀባሁህ፥ ከሳኦልም እጅ አዳንሁህ የጌታህንም ቤት ሰጠሁህ፥ የጌታህንም ሚስቶች በብብትህ ጣልሁልህ የእስራኤልንና የይሁዳን ቤት ሰጠሁህ ይህም አንሶ ቢሆን ኖሮ ከዚህ የበለጠ እጨምርልህ ነበር። አሁንስ በፊቱ ክፉ ትሠራ ዘንድ የእግዚአብሔርን ነገር ለምን አቃለልህ?» (2 ሣሙ. 12፡ 7-9)፡፡ እግዚአብሔር ለዳዊት እጅግ ቸርና መሐሪ አምላክ ሆኖ እስካሁን ረድቶት ሳለ እንዴት እንደዚህ ያለ አስቀያሚ ኃጢአት ሊሰራ እንደቻለ እየጠየቀው ነበር፡፡

እናንተስ የእግዚአብሔርን ምሕረት በሕይወታችሁ ምን ያህል ተገንዝባችሁታል? ይህስ ግንዛቤያችሁ እርሱ ለዋለላችሁ ውለታ ገጣሚ የሆነን ሕይወት በመኖር እርሱን ለማክበር እንድትፈልጉ ያነሳሳችኋል? ለእርሱ ክብር ከመኖር ይልቅ ለራሳችን በመኖር የእግዚአብሔርን ምህረትና በረከቶች እንደዋዛ ከመመልከት እግዚአብሔር ይሰውረን፡፡

ትክክለኛ የሆነን ሕይወት እንድትኖሩ ያነቃቃችሁ ዘንድ ለእግዚአብሔር ምሕረት መፍቀዳችሁ ከባድ በሆኑ ጊዜያት በረከቶችን እንድታገኙ ይረዳችኋል፡፡ በእግዚአብሔርና በሌሎች ሰዎች ላይ ከፈጸማችሁት በደል ክስ ህሊናችሁ ነጻ ሲሆን፣ በሕይወት አይቀሬ የሆኑትን የመከራ ሸክሞች ክብደት ለመሸከም አቅማችሁ ይጨምራል፡፡

**መለኮታዊ መጽናናትን ተቀበሉ**

ከስቃያችሁ በረከቶችን ለማግኘት አስፈላጊ የሚሆነው ሌላው ታላቅ ማበረታቻ እግዚአብሔር እናንተን በመከራዎቻችሁ ሁሉ ያጽናናበትን መጽናናት ለሌሎች ጥቅም በሚሆንበት መልኩ በማካፈል የአምላክን ምሳሌ መከተላችሁ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ቀደም ብላችሁ ባለፋችሁበት የመከራ ልምምድ ውስጥ እግዚአብሔር ስላጽናናችሁ፣ ይህንን ልምምድ ሌሎችን ለማጽናናት ስትጠቀሙበት፣ ይበልጥ መከራችሁ እየቀለላችሁ ይሄዳል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል፡- «እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል፥ ስለዚህም እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን።» (2 ቆሮ. 1፡4)፡፡

እግዚአብሔር መፍትሔ ሊሰጠው የማይችል ምንም አይነት በስቃይ የተሞላ ነገር አይደርስባችሁም፡፡ ሰማይ ሊፈውሰው የማይችል ምንም አይነት ሃዘን በምድር የለምና፡፡ ዕንባቆም ይህንን አውቆ ነበር፡፡ በእግዚአብሔር ማዳን በመጽናናት እጅግ ከመደሰቱ የተነሳ በዙሪያው ከከበቡት ሁኔታዎች አእምሮውን ፍፁም ነጻ አድርጎ ነበር፡፡ በፈተናም

ጊዜ የእግዚአብሔር ማጽናናት እንዴት አርነት እንዳወጣው እንዲህ በማለት አውጆአል፡- «ምንም እንኳ በለስም ባታፈራ፥ በወይንም ሐረግ ፍሬ ባይገኝ፥ የወይራ ሥራ ቢጐድል፥ እርሾችም መብልን ባይሰጡ፥ በጎች ከበረቱ ቢጠፉ፥ ላሞችም በጋጡ ውስጥ ባይገኙ፥ እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል በመድኃኒቴ አምላክ ሐሤት አደርጋለሁ።» (ዕንባ. 3፡17-18)፡፡ የእግዚአብሔር ማዳን ነብዩን በእጅጉ ስላጽናናው በሕይወት ውስጥ ሊደርሱ የሚችሉ የከፉ ነገሮችን እንኳን ሳይቀር ለመጋፈጥ ዝግጁነት ሊሰማው ቻለ፡፡ ከመከራው ውስጥ መርዙ ወጥቶ ነበር፡፡

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ማጽናናቱን በሰዎች በኩል ወደ እኛ ይልካል፡፡ ጳውሎስ እንዲህ ይጽፋል፡- «ነገር ግን ኀዘንተኞችን የሚያጽናና አምላክ በቲቶ መምጣት አጽናናን» (2 ቆሮ. 7፡6)፡፡ ቲቶ ለታላቁ ሐዋርያ ለጳውሎስ የእግዚአብሔርን መጽናናት የሚያመጣ መልእክተኛ ሆኖ ነበር፡፡

በፓስፊክ ውቂያኖሶች አካባቢ ለስድስት ወራት ለስራ በሄድኩበት ጊዜና የቤተሰብ ናፍቆት ባስቸገረኝ ጊዜ በፊሊፒንስ አገር የእኔን ብዙ ቲቶሶችን አግኝቼ ነበር፡፡ ሊሊቤትና ኤደን የተባሉ ሁለት እህቶችን በክርስቲያኖች አገልግሎት ማዕከል ተዋወቅሁ፤ እነዚህ እህቶችም የእግዚአብሔር መጽናናት ምንጭ ሆነውልኝ ነበር፡፡ ብዙ ወዳጆች ያሏቸው ምግብ አብሳዮች ቢሆኑም፣ እኔንም ወዳጃቸው አደረጉኝ፤ እንደ ወንድማቸው አስተናገዱኝ፤ ብቸኝነቴንና ጭንቀቴን በእጅጉ ቀነሱልኝ፡፡ እግዚአብሔር መጽናናቱን ወደ እኔ ለመላክ እነርሱን መሳሪያ አድርጎ ተጠቀመባቸው፡፡

በሕይወታችሁ የእግዚአብሔርን ማጽናናት ተለማምዳችኋል? ይህስ በምስጋና የተሞላ ሕይወት ለመኖር ምክንያት ሆኖአችኋል? በወዳጆቻችሁ በኩል ይህንን የእግዚአብሔርን መጽናናት የተለማመዳችሁበትስ ሁኔታ አለ? አይናችሁን ከፍታችሁ ተመልከቱ፤ እግዚአብሔር፣ ለዕንባቆም እንዳደረገው፣ ከመከራችሁ ውስጥ መርዙን የሚያወጣ መጽናናት ሊያመጣላችሁ እየተጠባበቀ ይገኛል፡፡

**እግዚአብሔር መጽናናቱን ለእናንተ የሰጠበትን አላማ ፈጽሙ**

በመከራዎቻችሁ መካከል እግዚአብሔር ሰላምና መጽናናት ሲያመጣላችሁና ስትደሰቱ፣ እርሱ የሚያጽናናን ሌሎችን እንድናጽናና እንደሆነ መዘንጋት የለብንም፡፡ (2 ቆሮ. 1፡4) ዮሴፍ ኢፍትሐዊ በሆነ መንገድ ወህኒ በወረደ ጊዜ የፈርኦንን ጠጅ አሳላፊና እንጀራ አሳላፊ አጽናናቸው፤ እንዴት እንዳሉ፣ ያዘኑበት ነገር ምን እንደሆነ ይጠይቃቸው ነበር (ዘፍ. 40)፡፡ የዮሴፍን ታሪክ ስናነብ በተደጋጋሚ ተጠቅሶ የምናገኘው ሃሳብ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንደነበረ ነው፡፡ ይህ የእግዚአብሔር በሕይወቱ መገኘትም ለሌሎች መጽናናትን ለማምጣት የሚያስችለውን መጽናናት ወደ እርሱ ይዞ ይመጣ ነበር፡፡

በ1968 ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር ከመሞቱ አንድ ቀን በፊት በሃያኛው ክፍለ ዘመን ከቀረቡ ታላላቅ ስብከቶች መካከል አንዱ የሆነውን ስብከት ሰብኮ ነበር፡፡ ርዕሱም «በተራራው ጫፍ ላይ ነበርኩ» የሚል ነበር፡፡ በዚህ ስብከቱ፣ እርሱ ከእግዚአብሔር

በተቀበለው መጽናናት በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን አጽናንቶ ነበር፡፡ ዶ/ር ኪንግ ከአትላንታ ወደ ሜምፊስ ለመምጣት ከባድ የሆነ የአየር ላይ ጥበቃ እንደተደረገለት ይናገራል፡፡ ዘረኞች በሆኑ ሰዎች በሕይወቱ ላይ የተዛተበትንም ዛቻ አስመልክቶ ተናግሯል፡፡ ከዚያም ከሰማይ ሰለተቀበለው ማጽናኛ መናገሩን ይቀጥላል፡- «እኔ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ነው የምፈልገው፡፡ እርሱም ወደ ተራራው ጫፍ እንድወጣ ፈቀደልኝ፡፡ ከዚያም አሻግሬ ተመለከትሁ፡፡ የተስፋይቱንም ምድር አየሁ፡፡ ከእናንተ ጋር ወደዚያ ምድር አልገባ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በዚህ ምሽት ልነግራችሁ እወዳለሁ፤ እኛ ፣ እንደ ህዝብ፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንገባለን!» በሺዎች የሚቆጠሩ አፍሪካ አሜሪካውያን እግዚአብሔር ለዶ/ር ኪንግ ከሰጠው መጽናናት የተነሳ እነርሱም መጽናናትን አግኝተው ነበር፡፡

በአሜሪካና በመላው አለም፣ ብዙ ድጋፍ ሰጪ ቡድኖች በቋሚነት ይሰባሰባሉ፡፡ የእንዲህ አይነት ቡድን አባላት ተመሳሳይ ትግል ያለባቸው ወይም ተመሳሳይ ስቃይ ያለባቸው ሰዎች ናቸው፡፡ አዲስ አባል ወደ ቡድኑ ሲገባ፣ በቡድኑ ውስጥ ካሉ ተመሳሳይ ፈተናና ትግል ውስጥ ከሚያልፉ ሰዎች ልምምድ መጽናናትን ያገኛል፡፡

በጉዳት ውስጥ ያለውን ሌላ ሰው ለመርዳት ትችሉ ዘንድ እግዚአብሔር የሰጣችሁ መጽናናት ምንድን ነው? ታማችሁ ከዚያም ፈውስን አግኝታችሁ ታውቃላችሁ? እግዚአብሔር ከሌሎች ጋር የነበራችሁን ግንኙነት፣ ተበላሽቶ የነበረውን፣ እንዲታደስ አድርጎት ይሆን? በወላጅነት ኃላፊነታችሁ ዙሪያ እግዚአብሔር የፈታው ቋጠሮ ገጥሟችሁ ያውቃል? በእግዚአብሔር መጽናናት የተጎበኛችሁበት ነገር ምንም ይሁን ምን ፣ በምስጋና ሕይወት ለመኖርና ሌሎችንም ለማጽናናት ብቁ ያደርጋችኋል፡፡ ይህንን እድል አታባክኑት፡፡

**ከስቃይ ውስጥ በረከቶችን ለማውጣት የሚያስችሏችሁ ወሳኝ እርምጃዎች**

- መከራን ተጠባበቁ
- የእግዚአብሔርን ጸጋና ሰላም ተለማመዱ
- በምስጋና የተሞላ ሕይወት ኑሩ
- እግዚአብሔርን ባርኩ
- ትክክለኛውን አመለካከት ያዙ
- በምህረት አባት ላይ ተደገፉ
- መለኮታዊ መጽናናትን ተቀበሉ
- እግዚአብሔር መጽናናቱን ለእናንተ የሰጠበትን አላማ ፈጽሙ

# 10

# የተባረከውን ሕይወት ኑሩ

የኮልድፕሌይ «ቪቫ ላ ቪዳ» የተሰኘው ቅኔ ለአስራ ሰባት ሳምንታት ከፍተኛ ዝናን አትርፎ ነበር፡፡ የዚህ ቅኔ አስተማሪ ቃላት የተባረከ ሕይወትን ፍለጋ የተደረገን ያልተሳካ ጥረት ይናገራሉ፡-

> ዓለምን ሁሉ አስተዳድር ነበር፤
> እኔ ትእዛዝ ስሰጥ በባህር ላይ ሞገድ ይነሳ ነበር፡፡
> አሁን ግን በማለዳ ብቻዬን ተኝቻለሁ፤
> አስተዳድር የነበረውን መሬት እጠርጋለሁ፡፡
> በአንድ ቅጽበት ላይ ሁሉን የሚከፍት ቁልፍ ይዤ ነበርሁ
> ወዲያው ደግሞ በሮች ሁሉ ተዘግተውብኝ መውጣት አቃተኝ
> እናም አስተዋልኩኝ ቤተመንግስቴ የቆመው
> በአሸዋ አምድ ላይ እንደሆነ
> (Guy Berryman, Jonny Buckland, Will Champion, and Chris Martin, "Viva La Vida" (Universal Music Publishing, 2008).)

እነዚህ ቃላት ኢየሱስ በማቴ. 7፡ 26-27 ላይ ሁሉን ነገር በእጁ የጨበጠ መስሎት ስለነበረ ነገር ግን ቤቱን በአሸዋ ላይ ስለ ሰራ ሰው የተናገረውን አያስታውሷችሁም? የባሕርንም ሞገድ በእርሱ ትዕዛዝ ማስነሳት እስከመቻል ድረስ ኃይል እንዳለው ያስብ ነበር፡፡ ነገር ግን፣ ሞገድ በባህሩ ላይ በተነሳ ጊዜ፣ ነፋሱ ሲነፍስ ዝናቡም ሲወርድ አንዱንም መቆጣጠር አልቻለም፡፡ ኃይል አልባ የመሆኑ እውነታ ፍንትው ብሎ ተገለጠለት፡፡

እኛስ ከሕይወት ምንጠባበቀው ነገር ያልተሳኩ ህልሞችና የባከኑ አመታትን ብቻ ነውን? ህልሞቻችን ሁሉ ጸሐይ እንደሚያተነው የማለዳ ጤዛ ሊሆኑ ይገባልን? ለቅጽበት ብቻ ቁልፉ ያለን መስሎን ከዚያ በኋላ ግን በቅዠት አለም ውስጥ እንደነበርን ማስተዋላችን ምን ይጠቅማል?

"Bishop Blougram's Apology" በተባለው ጽሑፍ ገጣሚ ሮበርት ብራውኒንግ እንዲህ በማለት ያስቀምጠዋል፡- «በጣም ደህና እንደሆንን ሲሰማን፣ የቀኑ ብርሃን እንደሚጨልም፣ በመቃብር ላይ የሚቀመጥ አበባም እንዳለ ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡»

ያገኘን ሲመስለን እንደገና መልሰን ከእጃችን እናጣዋለን፡፡ ቀና አስተሳሰባችንና ውበታችን ከወዲሁ ሊተነበዩ በማይችሉ በሕይወታችን በሚገጥሙን እውነታዎች ድንገተኛ ጥቃት ሊደርስባቸው እንደሚችል እየተጠባበቁ ያሉ ይመስላል፡፡ ይህ ግን

እውነት አይደለም። በመከራዎቻችን ውስጥ በረከትን ማግኘት እንደዚሁም የተትረፈረፈውንም ሕይወት መለማመድ እችላለን (ዮሐ. 10፡10)። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ህልማችንን እውን ለማድረግ የሚያስችሉንን ጠቅለል ያሉ መርሆዎች ያቀርብልናል።

በተራራው ስብከት ላይ (ማቴ. 5-7)፣ የተባረኩ ሰዎች ማለት ልባቸው ንጹሕ የሆነ፣ የሚያለቅሱ፣ ሰላምን የሚያደርጉ፣ ገሮች፣ ለጽድቅም ሲሉ የሚሰደዱ እንደሆኑ ከኢየሱስ እንማራለን። በመከራ ውስጥ በረከትን ለማግኘት ይህ ትልቅ ካርታ ነው። እንደዚሁም መዝሙረ ዳዊት አንድ ክፉ ምክርን የማይከተል ሰውና የእግዚአብሔርን ቃል የሚያሰላስል፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሪትን በመከተል የሚደሰት ሰው የተባረከ እንደሆነ ይናገራል። እናንተስ የተባረከ ሕይወት መኖር ትፈልጋላችሁ? ወደዚያ ግብ መድረስ የሚያስችሉ ጥቂት መንገዶችን አብረን እንመልከት።

## ችላ ልትሏቸው የሚገባችሁን ነገሮች እወቁ

መዝሙረ ዳዊት 1 የሚጀምረው በእነዚህ ቃላት ነው፡- «ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥» የተባረከውን ሕይወት መኖር ከፈለጋችሁ፣ ክፉ ምክሮችን ችላ ማለትን መማር አለባችሁ። ክፉ ምክሮችን በምትሄዱበት ቦታ ሁሉ ልትሰሙ ትችላላችሁ። በመገናኛ ብዙኃን ትሰሟቸዋላችሁ፤ ስለ አለባበስ፣ ስለ አነዳድ፣ እና ስለ አኗኗር በሚሰጡ አስተያየቶች ውስጥ ክፉ ምክሮች ይደመጣሉ። የምክሮቹ አንዳንድ አሳቦች ጠቃሚ ናቸው፣ ነገር ግን አብዛኛው ክፍል ወደ ተትረፈረፈና ስነ ምግባርን ወደ ተላበሰ ሕይወት ሊያደርሱ ከሚችሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎች የሚያርቁ ናቸው። «በክፉዎች ምክር እንዳትሄዱ» የሚለውን የመዝሙረኛውን ተግሳጽ መስማት ስኬትን ሊያጎናጽፋችሁና በሕይወታችሁም ወሳኝ በሆኑ ነገሮች ከመውደቅ ሊጠብቃችሁ ይችላል። በዚህ ረገድ ስኬት በመቀዳጀት ዳዊት ራሱ ምሳሌ ይሆነናል። ምክንያቱም የአቢጊያን ምክር በመስማት ባሏን ከመግደል እጁን ሰብስቦ ነበርና። አቢጊያ እንዲህ በማለት ነበር የመከረችው፡- «እግዚአብሔርም ለጌታዬ የተናገረውን ቸርነት ሁሉ ባደረገልህ ጊዜ፥ በእስራኤልም ላይ አለቃ አድርጎ ባስነሣህ ጊዜ፥ አንተ በከንቱ ደም እንዳላፈሰስህ፥ በገዛ እጅህም እንዳልተካስህ ይህ ዕንቅፋትና የሕሊና ጸጸት በጌታዬ አይሆንልህም እግዚአብሔርም ለጌታዬ በጎ ባደረገልህ ጊዜ፥ ባሪያህን አስብ። » (1 ሣሙ. 25፡ 30-31)። ዳዊትም በናባል ደም ታሪኩም ሆነ ህሊናው ሳይቆሸሽ ንጉሥ ለመሆን በቃ።

አለመታደል ሆኖ፣ የዳዊት ልጅ አምኖን ክፉ ምክርን መከተል ለምን አይነት ውድቀት እንደሚዳርግ አሳዛኝ የሆነ ምሳሌ ነው (2 ሣሙ. 13)። እርሱም የገዛ እህቱን፣ ትዕማርን፣ አስገድዶ ይደፍር ዘንድ የሚመክረውን የዘመዱን የኢዮናድብን ክፉ ምክር ሰማ። «ልክ የታመምክ ምሰል» አለው ኢዮናዳብ «እህትህ ትዕማር መጥታ ምግብ ስታዘጋጅልህም፣ ያን ጊዜ የወደደከውን ማድረግ ትችላለህ።» ይህንን ክፉ ምክር መስማት ነበር አምኖንን ሕይወቱን ያስከፈለው። ወንድሙ አቤሴሎም የእህቱን መናቅና መነወር ለመበቀል የአምኖንን ግድያ አቀነባበረ። አምኖን ክፉ ምክርን በመከተሉ ምክንያት ሞተ።

በ1 ነገ. 12፣ የንጉስ ሰለሞን ልጅና አልጋወራሽ በመሆን በእርሱ እግር ተተክቶ በእስራኤል ላይ የነገሠውን ኢዮርብዓምን ታሪክ እናገኛለን። ወደ ዙፋን በወጣ ጊዜ፣ ኢዮርብዓም ከአባቱ ሽምግል ያሉ አማካሪዎችና እንደርሱ ካሉ ወጣት ጓደኞቹ ምክርን

ፈለገ፡፡ ሽምገል ያሉትና በልምድ የበለጸጉቱ አማካሪዎች መልካም ምክር ሰጡት፡- ‹‹ለዚህ ሕዝብ አሁን ባሪያ ብትሆን ብትገዛላቸውም፥ መልሰህም በገርነት ብትናገራቸው፥ በዘመኑ ሁሉ ባሪያዎች ይሆኑልሃል ብለው ተናገሩት።›› (1 ነገ. 12፡7)፡፡ ወጣት አማካሪዎቹ ግን ክፉ ምክርን እንዲህ ሲሉ መከሩት፡- ‹‹አባትህ ካሳየው ጭካኔ በላይ የሆነን ጭካኔ አሳያቸው፤ አንተም አለቃቸው መሆንህን በዚህ ይወቁ›› (1 ነገ. 12፡10)፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ወጣቱ ንጉስ ይህንን ክፉ ምክር ለመከተል ወሰነ፡፡ በውሳኔውም፣ ከባድ ቀውስ ያስከተለን መዘዝ ተጋፈጠ፡፡ ሕዝቡ አመጸ፤ ከአስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች መካከል ሁለቱን ብቻ እንዲያስተዳድር አሥሮቹ ጥለውት ሄዱ፡፡

እናንተስ ማንን ነው የምትሰሙት? ምክርስ የምትቀበሉት ከማን ነው? ሃይማኖት አልቦ የሆኑ ባለሙያዎችን ከመጽሐፍ ቅዱስ መርሆዎች ይልቅ ለመስማት ትፈልጋላችሁ? የራሳችሁንም ሃሳብ ሆነ የሌሎችን ምክር ለመቀበል መለኪያው መሆን ያለበት የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ ነብዩ ኢሳያስ ይህንን ሃሳብ እንዲህ ያቀርበዋል፡- ‹‹ወደ ሕግና ወደ ምስክር ሂዱ! እንዲህም ያለውን ቃል ባይናገሩ ንጋት አይበራላቸውም። ›› ምክሮችንና ሃሳቦችን ሁሉ በሕጉና በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት በመመርመር የመጡት ከብርሃን ነው ወይስ ከጨለማ የሚለውን ለዩ፡፡

## ለኃጢአተኞች ምክር እምቢ በሉ

የተባረከውን ሕይወት ለመኖር ለኃጢአተኞች እምቢ ማለትን መማር አለባችሁ፡፡ ምሳ. 1፡10 ላይ እንዲህ ተቀምጧል፡- ‹‹ልጄ ሆይ፥ ኃጢአተኞች ቢያባብሉህ እሺ አትበል።›› ይህ ያልተወሳሰበ ቀላል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በአፍላ የጉርምስና እድሜዬ ሁለት ጓደኞቼን እንዳልከተል ጠብቆኛል፤ እነርሱም በሂደት አንድን ሰው እስከመግደል ደርሰው ነበር፡፡ ይህንን ጥቅስ በቃሌ ባጠናሁበት በዚያው እለት ከእነዚህ ወዳጆቼ ጋር ላለመሄድ ወሰንኩ፡፡ ያም ውሳኔዬ ዕድሜዬን በሙሉ በወህኒ ቤት ለመጨረስ ከመወርወር አተረፈኝ፡፡ እነዚያ ሁለት ወዳጆቼ ለፈጸሙት ወንጀል የተፈረደባቸው ቅጣት ይኼ ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያዎች የተዘጋጁት እኛን ለመጠበቅ ነው እንጂ፣ ደስታችንን ለማጥፋት አይደለም፡፡ እርሱም ኃጢአተኞችን መከተልን እምቢ እንድንል ይገዳደረናል፡፡

ይህንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትእዛዝ ታዞ ቢሆን ኖሮ የሳምሶን ሕይወት ይበልጥ ያማረ በሆነ ነበር፤ ነገር ግን እንዲህ አላደረገም፡፡ ደሊላን በቁጥጥሩ ስር የሚያውላት መስሎት ነበር፤ እናም አላዋቂነቱ ሕይወቱን አጠፋው (መሳ. 16)፡፡ ልክ እንደ ሳምሶን፣ ፈተናን ለመቋቋም ያለንን ችሎታ ከልክ በላይ አግነን እናስበዋለን፡፡ አንደኛ ቆሮንቶስ 10፡12 እንዲህ በማለት ያስጠነቅቀናል፡- ‹‹ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ።›› ከኃጢአት ልንጠበቅ የምንችልበት አንዱ ምርጥ መንገድ ፈተናን ለመቋቋም በራሳችን ላይ ያለንን መተማን መተው ነው፡፡

በስነምግባር ረገድ ገጣሚ የሆነ ሕይወት ይዤ ለመቆየት በማደርገው ጥረቴ፣ ለሞራል ውድቀት የሚዳርጉ ሦስት ቅድመ ሁኔታዎች እንዳሉ በማስታወሴ ተጠቃሚ ሆኛለሁ፡፡ እነዚህም ፈተና፣ ፍላጎትና ምቹ ሁኔታ ናቸው፡፡ እነዚህ ሦስቱ በተናጠል በሚታዩበት ጊዜ ልክ እንደ ኬሚካል ምንም ጉዳት የማያደርሱ ሲሆኑ፣ በተዋሃዱ ጊዜ ግን ገዳይ የሆነ ፍንዳታ የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ በፈተና የጦር አውድማ ውስጥ ፈተናው ከውስጥ

ከሚገፋፉ ፍላጎትና ከምቹ ሁኔታ ጋር በሚገጣጠምበት ጊዜ በጦርነቱ መሸነፍ በጣም ቀላል ነው የሚሆነው፡፡ ነገር ግን ምቹ ሁኔታን፣ ፍላጎትንና ፈተናን እንዳይቀናጁ ስናደርጋቸው፣ በመንፈሳዊ ው አለም ከጉዳት ልንጠበቅ እንችላለን፡፡

**በአክብሮት ኑሩ**

‹‹የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤ ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ።›› (ምሳ. 1፡7)፡፡ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ በአክብሮት የተሞላ ሕይወት ልንኖር እንደሚገባን ለስለስ አድርጎ የሚያስደምጠን ማስታወሻ ነው፡፡ ይህም የተባረከ ሕይወት ለመኖር ሌላው ወሳኝ የሆነ አመለካከት ነው፡፡ አክብሮት ማለት እግዚአብሔር ሊከበር እንደሚገባው ሙሉ በሙሉ በመረዳት ለእርሱ ክብር መስጠት ማለት ነው፡፡ መላዕክት ለፈጣሪያቸው አክብሮት መስጠትን ያለ ማስተዋል የሚያደርጉት ይመስላል፡፡ ኢሳያስ 6 በሰማይ ስድስት ክንፍ ያላቸው መላእክት ስማቸውም ሱራፌል የተባለ እንዳሉ ይዘግባል፡፡ እነዚህ መላእክት በሁለቱ ክንፋቸው እየበረሩ በሌሎቹ አራቱ ደግሞ እግርና ፊታቸውን ይሸፍኑ ነበር፡፡ በጢስ በተከበበ ዙፋኑ ፊት እግዚአብሔርን እንዲህ በማለት ያመልኩት ነበር፡- ‹‹ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች›› (ቁጥር 3)፡፡ እነዚህ ኃያል ፍጥረታት ለእግዚአብሔር ያላቸው አክብሮት ይህንን ይመስላል፡፡

ሰዎች፣ ብዙ ጊዜ፣ የዩንቨርስ ፈጣሪ ለሆነው ሉዓላዊ አምላክ አክብሮት አለማሳየታቸው እንዴት የሚያሳዝን እውነታ ነው፡፡ የየእለቱን የልብ ምቶች ከእርሱ መበደራችንን ዘንግተን፣ ‹‹እጅና እግሩን አጣምሮ ከላይ የተቀመጠ ሰው›› አድርገን እንቆጥረዋለን፡፡ በአክብሮት ስንኖር፣ ልክ ሙሴ በእግዚአብሔር ፊት በሚቃጠለው ቁጥቋጦ ፊት እንደነበረው ትሁታን እንሆናለን (ዘጸ. 3)፡፡ እርሱም እንዲህ ተብሎ ነበር፡- ‹‹የቆምክባት ምድር የተቀደሰች ናትና ጫማህን ከእግርህ አውልቅ፡፡››

ከጥቂት ቀናት በፊት፣ በዩ. ኤስ ካፒቶል ሮቱንዳ አንድ ፕሮግራም ተካፍዬ ነበር፡፡ ፕሮግራሙ የጀመረው በሚሊተሪ ሊሻናቸው የተንቆጠቆጡ ጠባቂዎች ባቀረቡት አሸብራቂ ትዕይንት ነበር፡፡ የአሜሪካ ባንዲራ ወደ ክፍሉ ሲገባ፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ቀኝ እጃቸውን ልባቸው ላይ ለጥፈው፣ ለባንዲራቸው ያላቸውን ክብር አሳዩ፡፡ እንዲህ ባሉ አገራዊ ስሜትን በሚቀሰቅሱ ሁኔታዎች ውስጥ ለሰው ሰራሽ ተቋማት የምንሰጠው አክብሮት ለመንፈሳዊ ነገሮች ከምንሰጠው እጅግ የላቀ መሆኑን ታዘብኩ፡፡ ለእግዚአብሔር እንዲያውም ከዚህ የሚበልጥ አክብሮትን ልናሳይ ይገባናል፡፡ የዚህ አክብሮት ወሳኝ የሆነ ክፍል ታዲያ በፈቃዳችን አስቀድመን አውጥተን አውረድን የምንሰራውን ኃጢአት ማስወገድን ያካትታል፡፡ በመዝ. 19፡13 ላይ ዳዊት እንዲህ በማለት ይጸልያል፡- ‹‹የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ፡፡›› እንደዚህ አይነት ኃጢአቶች እኛ አስቀድመን የምናቅዳቸው፣ በደንብ አድርገን የምንዘጋጅባቸው ናቸው፡፡ ኃጢአቶቹን ለመፈጸም እድሉ ወዲያው ስለማይገኝ፣ ከፈተናዎቹ ከመሸሽ ይልቅ የፈለግነውን ኃጢአት ለመፈጸም እድሉን እኛው ራሳቸውን ለመፍጠር እንዘይዳለን፡፡ እንዲህ ሆነ ብለን ኃጢአት ስንሰራ ራሳችንን አደገኛ የሆነ ቀጠና ውስጥ እንጨምራለን፡፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከባድ ፍርድን እንደተቀበሉት ፣ ከድፍረት ኃጢአታቸው የተነሳ በአንድ ቀን እንደሞቱት፣ እንደ ኤሊ ልጆች እንሆናለን (1 ሣሙ. 2)፡፡

**በእግዚአብሔር ቃል ደስ ይበላችሁ**

የተባረከውን ሕይወት መኖር በእግዚአብሔር ቃል ደስታን ከማግኘት ጋርም የተያያዘ ነው፡፡ ይህ ቃሉን ለማንበብ ራስን ከማስለመድ ወደ ቃሉን በማንበብ መደሰት እንድንሻገር የሚያስችለን ልናዳብረው የምንችል ችሎታ ነው፡፡ ራስን ማስለመዱ የሚጀምረው የምንወደውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በመያዝ በየዕለቱ በማንበብ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ወሳኝ የሆነ ልማድ ነው፤ ኢየሱስ በማቴ. 6 ላይ « ፣የዕለት እንጀራችንን ስጠን› ብላችሁ ጸልዩ» በማለት ያስተማረውን የሚከተል ነው፡፡ ይህ የእርሱ ልመና ዕለታዊ የሆነውን ሥጋዊ ምግብ ብቻ የሚጠቅስ አልነበረም፡፡ ዕለታዊውን መንፈሳዊ ምግባችንን መውሰድንም ጨምረን ማስታወስ ያስፈልገናል፡፡ የእኔ ልምምድ የሚያሳየኝ ይህንን በየዕለቱ ለማድረግ ራሴን ማስለመዴ በእግዚአብሔር ቃል ወደ መደሰት እንዳሸጋገረኝ ነው፡፡

የእግዚአብሔርን ቃል የመውደድ ሂደቱ በልጅነቴ በአትክልት ላይ የነበረኝን ጦርነት ያስታውሰኛል፡፡ በልጅነቴ ወራት፣ ብዙ አትክልትን እጠላ ነበር፤ በተለይም ምንም እንኳን እናቴ በአይብና በፓስታ እያሳመረች ልታበላኝ ብትጥርም፣ የአትክልቱን የተለየ ሽታ ለይቼ በማሽተት ለመብላት አሻፈረኝ እል ነበር፡፡ በግሌም ጎልማሳ በምሆንበት ጊዜ ይህንን በፍጹም ከምግቤ እንደማልጨምረው ለራሴ ማልኩ፡፡ ነገር ግን ወደ ጉልምስና ባደረግሁት ጉዞ ላይ አንድ ነገር ተከሰተ፡፡ አትክልቱን መውደድ ጀመርኩ፤ ከመጥላት ወደ መውደድ ተሻገርኩ፡፡ ልክ እንደ እግዚአብሔር ቃል አትክልትን መብላት ማዘውተሬ የሚያስደስት ልማድ ሆነልኝ፡፡

በዩ. ኤስ. ኔቪ ውስጥ ለሃያ ሰባት አመት ባገለገልኩበት ዘመን፣ ከስራ ግዳጅ የተነሳ ወደ ተለያዩ ቦታዎች በመሄድ ከባለቤቴ ጋር በተለያየንባቸው ጊዜያት የተቀበልኳቸው ብዙ የፍቅር ደብዳቤዎች ነበሩ፡፡ ልክ እንደሌሎቹ የመርከብ ተጓዦች እኔም በመርከብ ላይ ሳለሁ የተቀበልኳቸውን እነዚህን ደብዳቤዎች ደግሜ ደጋግሜ አነባቸው ነበር፡፡ የተወሰነውንም ክፍል በቃሌ እሸመድደው ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ቃልም ከፈጣሪያችን የተጻፈልን የፍቅር ደብዳቤ ነው፡፡ እንዲህ ባለ አክብሮትና ፍቅር ልናስተናግደው ይገባል፡፡

የእግዚአብሔርን ቃል የምናከብርበት አንዱ መንገድ ስናሰላስለው ነው፡፡ ማሰላሰል ተብሎ የሚተረጎመው የዕብራይስጡ ቃል አንድን ነገር ቀስ ብሎ መደጋገምን የሚያመለክት ነው፡፡ ሁላችንም በአንድ ወቅት አንድን ነገር ድምጻችንን ዝቅ አድርገን ደጋግመን እናውቃለን፡፡ እንደነዚህ አይነት ቃላት ኋላ ላይ ባንናገራቸው የምንመርጥ ቃላት ናቸው፡፡ ጥድፊያ በሞላባቸው ሰአታት የመኪና ጭንቅንቅ በሚኖርበት ጊዜ እኔም እንዲህ ቀስ ብዬ የምናገራቸውና ኋላ ላይ የምጸጸትባቸው ቃላት ገጥመውኛል፡፡ ነገር ግን እንዲህ ያሉ በነሲብ የምንናገራቸውን ቃላት በእግዚአብሔር ቃል ጥቅስ መለወጥን ተምሬአለሁ፡፡ ልክ ነው፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ቀስ ብዬ መናገርን ስለምድ ተገቢ ያልሆኑ ቃላትን ድንገት ከማልጎምጎም የሚያተርፍ መሳሪያ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ጥቅሶቹን ድምጽ አውጥቶ መናገርም ወደ ህሊናዬ ዘልቀው እንዲገቡ ይረዳኛል፡፡ ከአመታት በፊት የሚስቴ ደብዳቤዎች የእኔ አካል ሆነው እንደነበረ እነዚህ ጥቅሶችም አካሌ ሆነዋል፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል በአፋችን አውጥተን መናገር በእግዚአብሔር ቃል ለመደሰት የሚረዳ ዘዴ መሆኑን ለማስተዋል እንችላለን፡፡

**የሕይወትን ወቅቶች አክብሩ**

የሕይወትን ወቅቶች ታከብራላችሁ? የተባረከውን ሕይወት የሚኖሩ ሰዎች ይህንን ያደርጋሉ፡፡ ምርታማ ለመሆን ምርጥ የሚሉት ጊዜ እስከሚመጣ ቁጭ ብሎ የመጠበቅን ስህተት ያስወግዳሉ፡፡ መክ. 11፡4 ይህንን ግድድሮሽ እንዲህ ያስቀምጠዋል፡- «ነፋስን የሚጠባበቅ አይዘራም፥ ደመናንም የሚመለከት አያጭድም።» ይህ አስገራሚ የሆነ ጥቅስ የመዝሪያንና የመሰብሰቢያን ጊዜ የመጠበቅን አስፈላጊነት ስለማክበር ያስተምራል (ዘፍ. 8፡22)፡፡ ይህንን ስናደርግ የሕይወትን ወቅቶች ካለማክበር እንቆጠባለን፡፡ በተለይም በወጣትነት ወራት የመዝሪያ ወቅት ተሰጥቷችኋል፤ ይህ በአካላችሁ፣ በማህበራዊ፣ በአእምሮአዊና በመንፈሳዊ ጎናችሁ የምታጭዱበትን ነገር የምትዘሩበት ጊዜ ነው፡፡ በወጣትነታችሁ ጊዜ ያጠናችሁት ነገር ለማታ ስኬታችሁ ትልቅ ዋጋ ሊኖረው ይችላል፡፡

ለዩ. ኤስ ሴኔትነት ስራ በተደረገልኝ ቃለ መጠይቅ ላይ፣ ከሴኔቱ የብዙኃን መሪ የሚሰነዘርልኝን ጥያቄ በመመለስ ወደ ሁለት ሰአት አጠፋሁ፡፡ የጠየቀኝ ጥያቄዎች አስቀድሜ ካነበብኳቸውና ከተለማመድኳቸው ነገሮች በመነሳት እንድመልስ የሚያደርጉኝ ነበሩ፡፡ በወጣትነቴ ከዘራኋቸው ላይ ለመሰብሰብ ቻልኩ፡፡ በምስጋና እንድሞላ የሚያደርገኝ ነገር ታዲያ፣ በወጣትነቴ እንዲህ ኋላ ልተማመንበት የቻልኩትን ሰብል ለማዘጋጀት የሚያስችል ሕይወትን ለመኖር መምረጤ ነበር፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከማደንቃቸው ጀግኖች መካከል አንዱ ዳንኤል ነው፡፡ ልክ እንደ እኔው፣ ዳንኤል ለብዙ አስርት አመታት የመንግስት ኃላፊነት ተሰጥቶት ነበር፡፡ ጠላቶቹ ወደ አንበሳ ጉድጓድ እንዲጣል የሚያስደርገውን ነገር ባቀነባበሩበት ጊዜ እንኳን ሳይቀር እርሱ ሁልጊዜ ታማኝ ሰው ነበር (ዳን. 6)፡፡ የሚያስደስተው ነገር ታዲያ፣ በወጣትነቱ ጊዜ ከንጉሡ ማዕድ በመብላት ራሱን እንዳያረክስ በልቡ በመወሰን ለእግዚአብሔር ታማኝ የመሆንን ዘር መዝራት ነበር (ዳን. 1)፡፡ ዳንኤል የሕይወትን ወቅቶች ያከበረ ሰው ሲሆን፣ ከአንበሳ አፍ ያስመለጠውን የመለኮት ትድግና (መታደግን) ለማግኘትም ችሎ ነበር፡፡

እናንተስ? የሕይወትን ወቅቶች ታከብራላችሁ? ለወደፊቱ ሕይወታችሁ አሁን ማቀድ ጀምራችኋል? በመንፈሳዊ፣ በአእምሮአዊ፣ በማህበራዊና በአካላዊ እድገታችሁ ላይ «ኢንቨስት» እያደረጋችሁ ከሆነ፣ የሕይወትን ወቅቶች እያከበራችሁ ነው ማለት ነው፡፡ ይህም ወደ ተባረከው ህይወት ይመራችኋል፡፡ ወቅቶችን ከማክበር እውነታ መካከል አንዱ የመዝሪያውን ወቅት ችላ ብላችሁ አሳልፋችሁ መከሩ ከሚሰበሰብበት ወቅት ትንሽ ቀደም ብላችሁ መሬቱን በዘር ብትጠቀጥቁት ምንም ልታመጡ አለመቻላችሁ ነው፡፡ ልክ እንደ ገበሬ፣ ልትሰበስቡ በሚባችሁ ጊዜ ለመሰብሰብ በትክክለኛው ጊዜ መዝራትን መማር አለባችሁ፡፡

**ምርታማ በመሆን ቀጥሉ**

የተባረከውን ሕይወት መኖር ምርታማ በመሆን መቀጠልን ያካትታል፡፡ እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን የሰጣቸው የመጀመሪያው ትዕዛዝ «ብዙ ተባዙ» የሚል ነበር (ዘፍ. 1፡28)፡፡ እግዚአብሔር ምርታማ፣ ችግር ፈችዎችና ፍሬ ተሸካሚዎች እንድንሆን ይፈልግብናል፡፡ ኢየሱስ እንዳስቀመጠው፣ «ስለዚህም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።» (ማቴ. 7፡20)፡፡

እንዴት ነው ፍሬ የምናፈራው? የመክሊቶቹ ምሳሌ (ማቴ. 25፡ 14-30) ይህንን

በተመለከተ ትምህርት ይሰጠናል፡፡ በዚህ ምሳሌ ላይ ምርታማ ሆነው የተገኙት አገልጋዮች፣ ምንም እንኳን አደጋና ኪሳራ ሊገጥመን የሚችል ቢሆንም በማለት፣ አግባብነት ያለውን ድፍረት ተላብሰው በሥራ ላይ ያዋሉ ናቸው፡፡ እንዲህ ያለው አግባብነት ያለው ድፍረት ከሞኝነት ድፍረት የሚለየው በምንድን ነው? አግባብነት ያለው ድፍረት ከመጽሐፍ ቅዱስ መርሆች በተቀራኒ ምንም ነገር አያደርግም፤ ነገር ግን የተከፈተውን እድል ብቻ ይጠቀማል፡፡ ለምሳሌ፣ ጴጥሮስ በውሃ ላይ ለመራመድ ከጀልባው ወጣ (ማቴ. 14፡ 22-36)፡፡ ይህ አግባብነት ያለው ድፍረት ነበር፡፡ ምክንያቱም ኢየሱስ ከጀልባው ወጥቶ የማይቻል የሚመስለውን ነገር እንዲሞክር ፈቅዶለት ነበርና፡፡ በቀላሉ የኢየሱስን ትእዛዝ ብቻ እየተከተለ ነበር፡፡ እናንተም እግዚአብሔር እናንተን ከምቾት ቀጠናችሁ በማውጣት ሊሰራ ለወደደው፣ ለሕይወታችሁ ላለው እቅድ ፈቃድ ስትሰጡ ምርታማ ትሆናላችሁ፡፡ ደግሞስ፣ ከጀልባው ውስጥ ካልወጣችሁ መቼም ቢሆን በውሃ ላይ መራመድ አትችሉም፡፡

## እግዚአብሔር ሊሰጠን ቃል የገባልንን ስኬቶች ተቀበሉ

የተባረከውን ሕይወት መኖር ብዙ ሰዎች ከሚያስቡት በላይ ቀላል የሆነበት አንደኛው ምክንያት እግዚአብሔር ስኬትን ሊሰጠን ቃል ስለገባልን ነው፡፡ በየዕለቱ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ቃል ክፍት ስለሚያደርጉትና ለክፉ ምክር ጆሮአቸውን ስለማይሰጡት ሲናገር፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- ‹‹እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች፥ ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል።›› (መዝ. 1፡3)፡፡ ይህ ድንቅ አይደለምን? የሚሰሩት ነገር ሁሉ ከሚከናወንላቸው ወገኖች መካከል የምትደመሩ ናችሁ፡፡ ልብ በሉ፣ ይህ ጥቅስ በምታቅዱት ነገር ሁሉ ይሳካላችኋል እያለ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር የሚባርከው የምታደርጉትን ነገር ነው፡፡ ከሙሴ ሞት በኋላ፣ እግዚአብሔር ለሙሴ ተከታይ፣ ለኢያሱ የማበረታቻ ቃል ሰጥቶት ነበር፡፡ ፍርሃት ይታይበት ለነበረው ኢያሱ በቀንና በሌት ቅዱስ ቃሉን እንዲያሰላስል፣ የተማረውንም እንዲታዘዝ ነገረው፡፡ እግዚአብሔርም ቀጥሎ እንዲህ አለ፡- ‹‹የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም።›› (ኢያሱ 1፡ 8)፡፡ ስኬታችሁ የዚህን ያህል ቀላል ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ሰሚዎች ብቻ ሳትሆኑ አድራጊዎችም መሆን አለባችሁ (ያዕ. 1፡22)፡፡

ስኬት ማግኘታችሁን የምታውቁት እንዴት ነው? ስኬት የሚመጣው እግዚአብሔር ለሕይወታችሁ ያለውን አላማ ማከናወን ስትችሉ ነው፡፡ ቢሊ ግርሃም ለዚህ ድንቅ ምሳሌ እንደሆነ አስባለሁ፡፡ አስቀድሜ እንደጠቀስኩት፣ ይህ ግሩም ሰባኪ እንከን ያልተገኘበት የታማኝነት አገልግሎት ፈጽሞ አሁን በዘጠናዎቹ እድሜ ክልል ውስጥ ይገኛል፡፡ ለእግዚአብሔርና ለአገሩ በሰጠው ረዥም ዘመን ያስቆጠረ አገልግሎት ከግርሃም ስም ጋር የሚነሳ አንድም ሞራል የጎደለው ባሕርይ አልነበረም፡፡
የፍሬያማና የተሳካለት የእግዚአብሔር አገልጋይ ምን እንደሚመስል ግሩም ምሳሌ ነው፡፡

## ብሩህ የወደፊት ሕይወት እንዳላችሁ ተጠባበቁ

እግዚአብሔርን ለሚወዱ ሁሉ የእግዚአብሔር እንክብካቤ የተባረከውን ሕይወት ለመኖር ቁልፉን ያስጨብጣል፡፡ ሮሜ. 8፡28 ይህንን እውነታ ያስታውሰናል፡- ‹‹እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ

እናውቃለን።» ለዚህ ነው እንደ ክርስቲያን በሁሉም ሁኔታ ውስጥ ምስጋና ማቅረብ የምትችሉት (1 ተሰ. 5፡18)፤ እግዚአብሔር በእንክብካቤው አሉታዊ ገጽታዎችን ወደ አዎንታዊ ሊለውጥ ስለሚችል፣ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እርሱ ያዘጋጀልንን ምርጥ ነገር ለማግኘት እንችላለን፡፡

ለእናንተስ እግዚአብሔር ያሰበው ምርጥ ነገር ምንድን ነው? እስካሁን ተጉዛችሁ የመጣችሁበትን የሕይወት ጎዳና መለስ ብላችሁ ስትመለከቱ እግዚአብሔር እንዴት እርምጃችሁን እንደመራው ስታጤኑት በግልጽ ልታዩት ትችላላችሁ፡፡ ይህ ሲሆን፣ ከዮሴፍ ጋር እንዲህ ትላላችሁ፡- «እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው።» (ዘፍ. 50፡ 20)፡፡ ይህ አስገራሚ ነበር? ዮሴፍ መለስ ብሎ ሕይወቱን ተመለከተና እግዚአብሔር ለእርሱ ክብርና ለባሪያውና ለሌሎች በሺጎ ለሚቆጠሩ ሰዎች በረከት ይሆን ዘንድ እንደሰራው አየ፡፡ ዮሴፍ ሕይወቱን የኋሊት የመኖር እድል ቢሰጠው ወደ ጉድጓድ ውስጥ መጣሉን፣ ለባርነት መሸጡን፣ በባርነት ቤት መኖሩን፣ ያለ አግባብ የተከሰሰውን ክስ፣ በጭካኔ የተሞላውን የእስር ቤት ቆይታ፣ በጠጅ አሳላፊው መረሳቱን እርሱ ራሱ ይመርጣቸው ነበር፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር እነዚህን ግልጽ የሆኑ ጉስቁልናዎች ለመልካም ሊጠቀምባቸው ችሎ ነበርና፡፡

እግዚአብሔር ወደ መልካም ሊለውጠው የማይችል ምንም አይነት ክፉ ነገር በሕይወታችሁ ላይ ሊደርስ አይችልም፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ወንድና ሴት ጀግኖች በመጨረሻ ወደ ደረሱበት መልካም ምዕራፍ እንዴት እንደደረሱ ተመልከቱ፡፡ አብርሃም፣ አስቴር፣ ዮሴፍ፣ ሩት፣ ኤልያስ፣ ኤልሳዕ፣ ዝረዝሩ ይቀጥላል፡፡ እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር ከለመንነው ወይም ከምናስው የበለጠ፣ በእኛ ውስጥና በኩል በኃይሉ ታላቅን ነገር ሊያደርግ እንደሚችል ያመኑ ናቸው (ኤፌ. 3፡20)፡፡ በመጨረሻ የተባረከውን ሕይወት መኖር ይቻላል ምክንያቱም እግዚአብሔር እርሱን ለሚወዱት እጅግ አስከፊ የሆኑ ሁኔታዎችን ወደ በረከት መለወጥ ስለሚችል ነው፡፡

**የተባረከውን ሕይወት ለመኖር የሚያስችሉ ወሳኝ እርምጃዎች**

- ችላ ልትሏቸው የሚገባችሁን ነገሮች እወቁ
- ለኃጢአተኞች ምክር እምቢ በሉ
- በአክብሮት ኑሩ
- በእግዚአብሔር ቃል ደስ ይበላችሁ
- የሕይወትን ወቅቶች አክብሩ
- ምርታማ በመሆን ቀጥሉ
- እግዚአብሔ ቃል የገባልንን ስኬቶች ተቀበሉ
- ብሩህ የወደፊት ሕይወት እንዳላችሁ ተጠባበቁ

# 11

# የሕይወትን ጫናዎች በእምነት ተጋፈጡ

ለቋቋመው አልቻልኩም፡፡ አሁንም በድጋሚ ለሰፈር የቅርጫት ኳስ ግጥሚያ ማንም ሰው ሊመርጠኝ አልፈለገም፡፡ እርግጥ ነው፣ ሁልጊዜም ቢሆን የሚመርጡኝ መጨረሻ ላይ እየተናደዱና የግድ ሆኖባቸው ነው፡፡ የአንደኛው ቡድን አምበል «እኔ ቢልን ወስጃለሁ» ይላል፡፡ ሌላው ደግሞ «ለእኔ ደግሞ ላሪን ስጠኝ»፡፡ እንዲህ እያለ መመራረጡ ይቀጥልና ሁሉም ልጆች ተመርጠው እኔና አንድ በከራንች የሚሄድ ልጅ እስከምንቀር ይደርሳል፡፡ ከዚያም ከሁለቱ አምበሎች አንደኛው ድል የተቀዳጀ ያህል እየተሰማውና እኔን በቡድኑ ውስጥ ባለማስገባቱ እጅግ እየተደሰተ «እንግዲያውስ፣ ከራንች የያዘውን እኔ እወስዳለሁ» ይላል፡፡ ከዚያም፣ ሌላኛው አምበል እድለቢስነት እየተሰማው በብስጭት ቃላት፣ «እንግዲህ ምን አደርጋለሁ፣ ቤሪ እኔ ቡድን ይግባ፡፡»

በእርግጥ የቅርጫት ኳስ ክህሎቴ እጅግ የከፋ ስለ ነበረ ይሆን? ከሆነ፣ በርትቼ ሰርቼ ችሎታዬን ለማሻሻል ዝግጁ ነበርኩ፡፡ ተግቶ መሥራት ለሽልማት እንደሚያበቃ ተረድቼ ነበር፡፡ የሎንግፌሎን ሥራ የታላቅነት መንገድ እንደሆነ የሚገልጸውን ግጥም የዚያን ሰሞን ሸምድጄው ነበር፡-

> ታላላቅ ሰዎች ከፍታን የወጡት፣
> አይደለም በተምር እንዲሁም በድንገት፡፡
> የእነርሱ ወዳጆች ሳሉ ተኝተው፣
> በመስራታቸው ነው ሌት ተቀን ተግተው፡፡

ገጣሚው ትክክል ከሆነ፣ እኔ ጠንክሬ እሰራለሁ፤ በሂደትም የጓደኞቼን አክብሮት አገኛለሁ ብዬ አሰብኩ፡፡ እቅዶቼን ተግባራዊ ማድረግ ጀመርኩ፡፡ ጸሐይ ከጠለቀች በኋላ፣ በርቀት ከተተከለ የመንገድ መብራት በሚበራ ብርሃን እየተረዳሁ ደክሞኝ እስካቆም ድረስ ኳሱን ወርውሮ ግብ የማስገባት ልምምዴን ቀጠልኩ፡፡ በየምሽቱ ልምምዴን ቀጠልኩ፣ ከሃያ ጫማ ርቀት ከአስሩ ውርወራ ዘጠኙን እስካስገባ ድረስ፡፡ መንፈሴ በደስታ ተሞላ፤ አሁን እንደገና ለመወዳደር ዝግጁ ነበርኩ፡፡ ወዳጆቼ አዲሱን ችሎታዬን ካዩ፣ ከዚህ በኋላ መጨረሻ ላይ ቡድን የማግኘቴ ነገር ይቀራል ብዬ አሰብኩ፡፡ ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ በልምምድ ጨዋታና በእውነተኛ ጨዋታ መካከል ያለውን ልዩነት አሳዛኝ በሆነ መንገድ አስተዋልኩ፡፡

ችሎታዬ ሊታይ የነበረበትን ቀን በጣም በታላቅ ጉጉት ነበር የተቀበልኩት፡፡ ቀደም ብለው በሚደረጉ የሙከራ ውርወራዎች ባሳየሁት ብቃት፣ ወደ ቡድኑ ለመመረጥ ሦስተኛ ሰው ለመሆን በቃሁ፡፡ ይህ ከዚህ በፊት ሆኖ የማያውቅ ክስተት ነበር፡፡ ነገር ግን በከባድ ልፋት ባገኘኋቸው ችሎታዎቼ ላይ የነበረኝ እምነት እውነተኛው ጨዋታ በሚፈጥረው ጫና ሥር በሆነ ጊዜ መናወጥ ጀመረ፡፡ ከሃያ ጫማ ርቀት አካባቢ ኳሷን ወርውሬ ለማስገባት በምመኮርበት ጊዜ የተቀራኒው ቡድን ተጫዋች ከሆኑት የአንዱ እጅ ፊቴ ላይ አረፈ፡፡ ይህ ደግሞ በልምምድ ጊዜ እንደነበረው አይደለም፡፡ በጣም የደነቀኝ፣ አንድ ሌላ ተጫዋች ከባድ የሆነ መከላከል በማድረግ ከሚጥርብኝ ጫና ጋር ሆኜ ኳሷን በምወረውርበት ጊዜ በልምምድ ጊዜ ምንም አይነት ጫና ሳይኖርብኝ እንደምወረውረው ሊሳካልኝ አልቻለም፡፡ ችሎታዎቼ በተፈተኑ ጊዜ፣ ያገኘሁት ፍሬ አጥጋቢ አልነበረም፡፡

ይህ በሕይወት ለሚገጥመን ሁኔታ ገጣሚ የሆነ ምሳሌ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የምንኖረውና የምንሰራው በልምምድ ጨዋታ ሁኔታ ውስጥ ነው፡፡ ጸሐይዋ ደማቅ ብርሃኗን ትሰጣለች፤ በምድር ያለው ነገር ሁሉ ሰላም ይመስላል፡፡ ደስ የሚያሰኝ ሥራ ላይ ተሰማርተን እንሰራለን፤ ቤተሰባችንም እየበለጸገ የሚሄድ ይመስላል፡፡

ከዚያም የልምምዱ ጊዜ ያበቃና እውተኛው ግጥሚያ ይጀምራል፡፡ ሥራችንን እናጣለን፤ ወይም ሃኪሙ ስለ ጤናችን ሁኔታ መርዶ ይነግረናል፡፡ ልጅ በማሳደግ እንደዚሁም ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት ተግዳሮት ይገጥመናል፤ ወይም አገራችን ያልተጠበቀ ቀውስ በድንገት መጋፈጥ ትጀምራች፡፡ ቶማስ ፔይኔ «እንደዚህ ያሉ ጊዜያት የሰዎችን ነፍስ የሚፈትኑ ናቸው» በማለት ይጽፋል፡፡ በእርግጥም ናቸው፡፡ አቋማችን የሚፈተሽባቸው ጊዜያት ናቸው፤ በብዙ ጠላቶች ከሁሉም አቅጣጫ ብንገፋም እምነታችንን ጠብቀን መያዝን መማር አለብን፡፡ ከተለያየ አቅጣጫ ጫና ሲደረግባችሁ በዚህ ሁሉ ውስጥ እምነታችሁን ጠብቃችሁ መቆየት ትችላላችሁ?

መጥምቁ ዮሐንስ በእምነታቸው ላይ የመጣባቸውን ጫና ተቋቁመው በዚያ ውስጥ ማለፍን ከተማሩ ሰዎች መካከል አንዱ ነበር፡፡ ኢየሱስ መሲህ መሆኑን በአደባባይ ያወጀው ይህ ሰው፣ በንጉሥ ሄሮድ እስር ቤት ራሱን ሲማቅቅ አገኘው፡፡ ከባድ የሆነ የጥርጣሬ ስሜት በውስጡ ተጫረ፤ ስለ ኢየሱስ የነበረውንም እርግጥኝነት ጥያቄ ውስጥ ከተተው፡፡ በመጨረሻም ተስፋ በመቁረጥ ተሞልቶ፣ ደቀ መዛሙርቱን ጥያቄ አሸክሞ ወደ ክርስቶስ ላካቸው፡- «የሚመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌላውን እንጠብቅ?» (ሉቃ. 7፡ 20)፡፡ ኢየሱስ የዮሐንስ እምነት ጥርጣሬ እንደተጫነው ያስተዋለ ይመስላል፡፡ ለዮሐንስ አስቸኳይ ጥያቄ ወዲያውኑ ምላሽ አልሰጠም፤ ነገር ግን መልእክተኞቹ ከእርሱ ኋላ እንዲከተሉና የሚሰራውን ሥራ እንዲያዩ አደረገ፡፡ ጸሐይዋ ስትጠልቅም፣ ኢየሱስ ወደ ዮሐንስ መልእክተኞች ፊቱን መለስ አደረገና እንዲህ አላቸው፡- «ሄዳችሁ ያያችሁትን የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አውሩለት፤ ዕውሮች ያያሉ፥ አንካሶችም ይሄዳሉ፥ ለምጻሞችም ይነጻሉ፥ ደንቆሮዎችም ይሰማሉ፥ ሙታንም ይነሣሉ፥ ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል፤ በእኔም የማይሰናከለው ሁሉ ብፁዕ ነው፡፡» ይህ በእምነት የተሞላ የኢየሱስ ምላሽ የዮሐንስን መንፈስ አጠነከረው፤ ምንም እንኳን የጥርጥር ጫና ቢበዛበትም እምነቱን ጠብቆ እንዲያልፍ አስቻለው፡፡

ከዚህ ታሪክ በኋላ፣ ጴጥሮስም በተመሳሳይ የእምነት መፈተን ውስጥ አልፎ ነበር፡፡ ኢየሱስ ወደ ቀራኒዮ ሲገሰግስ፣ ጴጥሮስ ለክርስቶስ ለመሞት ፍጹም ፈቃደኛ መሆኑን አውጆ ነበር፡፡ «ጌታ ሆይ፣ መታሰር ቢሆን ወይም ሞት ካንተ ጋር ልጋፈጥ ዝግጁ ነኝ፡፡» ብሎ ነበር፡፡ ኢየሱስ ግን ለዚህ ንግግሩ በሰጠው ምላሽ ጴጥሮስን አስገረመው፡፡ «ጌታም፡- ስምዖን ስምዖን ሆይ፥ እነሆ፥ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን አጽና» አለ (ሉቃ. 21፡ 31-33)፡፡

ጴጥሮስ በዚህ ምላሽ ተገርሞ፣ እርሱን ግን ከአቋሙ አንዳች ነገር ፍንክች ሊያደርገው እንደማይችል አጥብቆ መናገሩን ቀጠለ፡፡ ምንም አይነት ጫና ቢደርስበት ያለውን ማድረግ እንደሚችል በራሱ መተማመን ተሰምቶት ነበር፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ከእርሱ የሚበልጥ እውቀት ነበረው፡፡ አዳኙም እንዲህ አለው፡- «እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ በዚች ሌሊት ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ አለው።» (ማር. 14፡ 30)፡፡ በሌላ አነጋገር፣ «እምነትህ ጫና ሲበዛበት ጠብቀህ ልታቆየው አትችልም» እያለው ነበር፡፡ በእርግጥም ከጥቂት ሰአታት በኋላ፣ የኢየሱስ ትንቢት እውን ሆነ፤ ጴጥሮስም በሊቀ ካህኑ በቀያፋ ግቢ ውስጥ ጌታን ሦስት ጊዜ ካደው (ሉቃ. 22፡ 54-64)፡፡

ሕይወት ከምቾት ቀጠናችን ገፍቶ የሚያስወጣበት መንገድ አለው፡፡ የአስረኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ፣ ከቤታችን ወጥተን በመንገድ ላይ እቃችን ተዘርግፎ ደርሶብን የነበረውን ሃፍረት አስታውሳለሁ፡፡ እንዲህ ባለ ሁኔታ እቃችን ሁሉ ውጭ ተዘርግፎ ጎረቤቶቻችን ሁሉ ባዩት ጊዜ ስለ ተሰማን ሃፍረት ቀደም አድርጌ ተናግሬአለሁ፡፡ ታዲያ ከቤታችን ወጥተን በመንገድ ላይ እንደዚያ መወርወራችን በእምነቴ ላይ ጫናን አሳድሮ የእግዚአብሔርን መልካምነት ጥያቄ ውስጥ እንድጨምረው አድርጎኝ ነበር፡፡ እናቴ ሕይወቷን በሙላት ለጌታ የሰጠች ክርስቲያን ነበረች፤ አምስቱን ልጆቿን በየቀኑ ጠዋትና ማታ በቤተሰብ የጸሎት መሰዊያ ላይ ይዛ በመቅረብ የምትተጋ ነበረች፡፡ በቤተክርስቲያን በሚደረጉ አገልግሎቶች ሁሉ ደግሞ እንድንካፈል ትወስደን ነበር፡፡ እኔና ሌሎች ወንድም እህቶቼ በክርስቲያን ትምህርት ቤት ተምረን እድንጨርስ ለማድረግ ብዙ መስዋእትነት ከፍላለች፡፡ ታዲያ እንዲህ ባለ ታማኝነት ያገለገለችው አምላክ እንደዚህ ያለ የአደባባይ ሃፍረት እንዳይደርስብን መከልከል አይችልም ነበር? እግዚአብሔር ይህንን ለምንድን እንዳደረገ ሊያብራራልን ይገባል አልኩኝ ለራሴ ግራ በተጋባ አስተሳሰብ ውስጥ ሆኜ፡፡

በእምነቴ ላይ ጫና በበዛብኝ ጊዜ ጥንካሬዬን ጠብቄ ለማቆየት አልቻልኩም ነበር፡፡ እምነቴ በተፈተነ ጊዜ፣ በግራቱ ውስጥ ተንገዳገድኩ፡፡ በዮሐ. 16፣ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ከፊት ለፊታቸው በእምነታቸው ላይ ጫና የሚፈጥረውን ችግር ለመጋፈጥ እንዲችሉ እያዘጋጃቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ስለሚደርስባቸው ስደትና ስለሚጋፈጡት ችግር በነገራቸው ጊዜ ፣ አጋዥ የሆነውን መንፈስ ቅዱስን ከእነርሱ ጋር በእርምጃቸው ሁሉ አብሮአቸው ይጓዝ ዘንድ እንደሚልክላቸው ነግሯቸው ነበር፡፡ ከዚያም እንዲህ አላቸው፡- «በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።» (ዮሐ. 16፡33)፡፡ በዚህ ግልጽ ሆኖ በቀረበ ጥቅስ ላይ፣ ኢየሱስ እምነታችን በተለያዩ ግፊቶች ጫና ሲበዛበት እንዴት ጠብቀን ልናቆየው እንደምንችል ያስተምረናል፡፡

**ከከበባችሁ ነገር ተጽእኖ ነጻ ሁናችሁ ኑሩ**

በከበባችሁ ነገር ቁጥጥር ሥር ያልሆናችሁት በምን ያህል መጠን ነው? «አናደደችኝ፣ አስከፋችኝ፤ ወይም በሃዘን ልቤን ሰበረችው፣» በማለት ሰዎች ሲናገሩ በስሜታቸው ላይ የመቆጣጠር ስልጣን እንደሌላቸው እየጠቆሙ ነው፡፡ ምክንያቱም እንደዚያ እንዲሰማቸው ያደረጓቸው ሌሎች ሰዎች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ የከበቡን ሁኔታዎች ማን እንደሆን ሊነግሩንና ምን አይነት ምላሽ ልንሰጥ እንደሚገባን ሊመሩን አይገባም፡፡ በከበቡን ነገሮች ቁጥጥር ስር እንዳንወድቅ በማየት ሳይሆን በእምነት ልንኖር እችላለን (2 ቆሮ. 5፡7)፡፡

ታሪኳ በ 2 ነገ. 4፡ 8-37 የሚገኘው የሱናማዊቷ ሴት የሕይወት ተሞክሮ እንዴት አመለካከታችንን በከበቡን ነገሮች ከሚገጥመን ተግዳሮት ነጻ አድርገን መጠበቅ እንደምንችል ያሳየናል፡፡ እግዚአብሔር በልጅ ባርኳት ነበር፤ ነገር ግን ያ ልጅ ባደገ ጊዜ፣ ሞተባት፡፡ ይህቺ እናት ሐዘኗን የተጋፈጠችው የሞተውን ልጅ አስከሬን አልፎ አልፎ ወደ ቤቷ እየመጣ ወደ ሚሰነብተው ወደ ነብዩ ኤልሳዕ መኝታ ቤት በማስገባት ነበር፡፡ ከዚያም ነብዩን ለማግኘት በአህያዋ ተጓዘች፡፡ እርሱም ከሩቅ እርሷ መሆኗን በተገነዘበ ጊዜ፣ እንዲህ የሚል ጥያቄ እንዲያቀርብላት አገልጋዩን ወደ እርሷ ላከ፡- «በደኅናሽ ነውን? ባልሽ ደኅና ነውን? ልጅሽስ ደኅና ነውን?»

እናንተ ብትሆኑ እነዚህን ጥያቄዎች እንዴት ትመልሷቸው ነበር? ልጃችሁ በቤታችሁ በነብዩ አልጋ ላይ አስከሬኑ ተጋድሟል፤ ኤልሳዕ ደግሞ ነገሮች ደህና መሆናቸውንና አለመሆናቸውን ለማወቅ እየጠየቀ ነው፡፡ በሚያስገርም ሁኔታ፣ እንዲህ በማለት መልስ ሰጠች «ደኅና ነው!» እምነታችሁ ጫና ሲበዛበት ከእጃችሁ እንዳያመልጥ ይልቁንም ጠብቃችሁ እንድታቆዩት እንደዚህች ሴት በዙሪያችሁ ከከበባችሁ ሁኔታዎች ነጻ ሆናችሁ መቆየት ያስፈልጋችኋል፡፡

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ያለውን ነጻነት እንዲለማመዱት ፈልጎ ነበር፡፡ ሰላምን ሊሰጣቸው እንዳስተማራቸው ነግሯቸው ነበር፡፡ ይህ ሰላም ደግሞ በስሜትም ሆነ በመንፈስ በዙሪያች ከከበበን አለም ቁጥጥር ነጻ የሚያወጣን ነው፡፡ በፊል. 4፡ 12፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ሰላም ሲገልጸው እንዲህ ይላል፡- «መዋረድን አውቃለሁ፤ መብዛትንም አውቃለሁ፡፡» በአጭሩ እያለ ያለው፣ የሚገጥሙት ሁኔታዎች እርሱን እንዲቆጣጠሩት ከመፍቀድ ይልቅ እርሱ ሁኔታዎቹን መቆጣጠር ችሎ እንደነበረ ነው፡፡ በተትረፈረፈ ሁኔታ ውስጥ ያጣጣመውን ምቾት በጎደለበት ጊዜም ቢሆን ከእጁ አላመለጠውም፡፡ ፊል. 4፡ 6-7 ደግሞ በከበበው ነገር ቁጥጥር ስር ሳይወድቅ ሊቆም የቻለበትን ምስጢር ይነግረናል፡- «ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ። አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።» አንድ ነገር በሚያሳስበኝ ጊዜ፣ በምስጋና በተሞላ ጸሎት ፣ እግዚአብሔር ማንኛውንም ችግር እንደሚፈታ በማመን በፊቱ ይገኛው እቀርባለሁ፡፡ በእግዚአብሔር በምታመንበት ጊዜ፣ የእርሱ ሰላም የእኔን ጭንቀት ቦታ እንደሚይዝ፣ በዚህም የሕይወትን ሸክሞች በቀላሉ ለመሸከም እንድችል እንደሚያደርገኝ አስተውያለሁ፡፡

**ጫናዎችን ተጠባበቁ**

ጭንቅና ጫና በሕይወታችን እንደሚመጡብን ስንጠብቅ ለመሸከም እንደሚቀለን ኢየሱስ ነግሮናል፡፡ አንድ ጠዋት በአካባቢዬ በሌላ አዲስ መንገድ የሩጫ ስፖርቴን ለመስራት ወሰንኩ፡፡ ልክ በአንዱ መንገድ እጥፍ እንዳልኩኝ ሃይለኛ የሆነ የውሻ ድምጽ አድሬናሊን የተባለው ሆርሞን በደም ስሮቼ ውስጥ እንዲለቀቅ አደረገ፡፡ ምን እንደሚገጥመኝ ባላውቅም እጅግ ግዙፍ የሆነ ተናካሽ ውሻ አጠገቤ ሊደርስ እንደሚችል በመጠባበቅ ዙሪያዬን ቃኘሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ የተመለከትኩት በአንድ የታጠረ ግቢ ውስጥ አንድ ትንሽ ውሻ፣ እኔን ፈጽሞ ሊጎዳኝ በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ነበር፡፡ ከዚያ ቀን ቀጥሎ በዚያው መንገድ ባደረግኋቸው ሩጫዎቼ፣ ልክ ያቺን መንገድ እጥፍ ስል የውሻውን ድምጽ ለመስማት እጠባበቃለሁ፡፡ አሁንም በጣም በከፍተኛ ድምጽ ይጮኻል፤ እንደዚሁም በታጠረው ግቢ ውስጥ አጥሩን ተከትሎ እስከ አጥሩ ጫፍ ድረስ አብሮኝ ይሮጣል፤ ነገር ግን አገኘዋለሁ ብዬ ስለምጠባበቅ ምንም ክፉ ነገርን አልፈራም፡፡

ልክ እንደዚያው፣ ክርስቲያኖች መከራዎችንና ጫናዎችን መጠባበቅ አለባቸው፤ ኢየሱስ እንዲህ ብሎአልና፡- «ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ፥ ወዮላችሁ፤» (ሉቃ. 6፡26)፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ እንዲህ በማለት ያስጠነቅቀናል፡- «በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ።» (2 ጢሞ. 3፡ 12)፡፡ እንደዚሁም በኢዮብ 14፡ 1 ላይ የሰው ሕይወት አጭርና በሰልፍ የተሞላ እንደሆነ በግልጽ ያስረዳናል፡፡ በ 1 ቆሮ. 10፡13 የሚደርስብን ፈተና በሰው ሁሉ የሚደርስ እንደሆነ ተነግሮናል፡፡ በመሆኑም በትክክለኛው መንገድ ለመራመድ የሚጓዝ ግለሰብ ሁሉ በሕይወቱ ችግር ይገጥመዋል፡፡

በባልቲሞር በማድግበት ጊዜ፣ ከወንድምና ከእህቶቼ ጋር በቤታችን ውስጥ በጨለማ ውስጥ በመደበቅ ምንም ነገር ይገጥመናል ብለው ባልጠበቁት ወንድም ወይም እህት ላይ ዘለን ጉብ በማለት «ጃዝ!» እያልን በማስደንገጥ እንጫወት ነበር፡፡ ታዲያ እንደዚህ አይነት ጨዋታ ከዚህ ቀደም ደጋግመን የተጫወትን ሰዎች ጨለም ያለ መታጠፊያ ላይ ስንደርስ አንድ ሊያስደነግጠን የቆመ ሰው አለን ብለን በማሰብ ብዙም አንፈራም፡፡ ፍርሃቱን ያጠፋው ሊገጥመን የሚችል ነገር አለ ብለን መጠባበቃችን ነው፡፡ ልክ እንደዚሁም፣ በሕይወት ጫና ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁኔታዎች ሊገጥሙን ይችላሉ ብሎ መጠባበቅ ችግሮቹ እኛን የመጉዳት አቅም እንዳይኖራቸው ወይም እምነታችንን እንዳያናውጡ የማድረግ ችሎታ አለው፡፡

**በሕይወታችሁ የሚገጥሟችሁን ጫናዎች በድፍረት ተጋፈጡ**

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በሕይወታቸው ጫናዎች እንደሚመጡ በመጠባበቅ ሰላምን እንዲለማመዱ ከነገራቸው በኋላ፣ ጫናዎቹንም መጋፈጥ ያለባቸው በድፍረት ሊሆን እንደሚገባ አስታወሳቸው፡፡ በከባባቢው ሁኔታ ቁጥጥር ስር ሳይወድቁ ነጻነታቸውን እንዲያስከብሩ የፈለገው በመንገዳቸው ላይ የሚያጋጥሟቸውን እንቅፋቶች ሁሉ በድፍረት እየዘለሉ እንዲያልፏቸው ነበር፡፡ «አይዞአችሁ!» አለ ኢየሱስ «እኔ አለምን አሸንፌዋለሁ» (ዮሐ. 16፡ 33)፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ጫና የሚፈጥሩ ግድድሮሾችን በድፍረት መጋፈጥ በቻሉ ሰዎች

የተሞላ ነው፡፡ ሙሴ ከሚሊዮን የሚበልጥ ቁጥር ያላቸውን ህዝቦች ከግብጽ ባርነት ወደ ተስፋይቱ ምድር የመምራት እጅግ ከባድ የሃላፊነት ጫናን የተቋቋመ ሰው ነበር (ዘጸ. 3) ፡፡ ጌዲዮን ከመንግስታት የተሰባሰቡ ሠራዊቶችን የተጋፈጠው በሦስት መቶ ሰዎች ብቻ ነበር (መሣ. 7)፡፡ ነህምያ በ52 ቀናት የኢየሩሳሌምን ቅጥር ሰርቶ የጨረሰው፣ ታላቅ የሆነን ተቃውሞና አደጋን በመጋፈጥ ነበር (ነህ 6)፡፡ ዳዊት ግዙፉ ጎልያድ በሚናገረው እውቀት የጎደለው የማስፈራሪያ ቃል መበርገግን አሻፈረኝ አለ (1 ሣሙ. 17)፤ ንጉስ ሕዝቅያስም የአሶርያ ንጉስ የሆነውን የሰናክሬብን ማስፈራሪያ ሰምቶ ተስፋ አልቆረጠም (2 ነገ. 18)፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን (መጽሐፍ ቅዱስን) በሙላት ስናነብ፣ ታማኝ የሆኑ ወንዶችና ሴቶች የሕይወት ጫናዎችን በድፍረት መቋቋም የቻሉ ነበሩ፡፡

እናንተስ እነዚህን ጫናዎች ስትጋፈጡ በድፍረት ነው ወይ? ከህክምና ባለሙያው (ዶክተሩ) መጥፎ ዜና ስለጤንነታችሁ ስትሰሙ፣ ወይም ልጃችሁ ወደ ሐጢአት ሩቅ አገር ኮብልሎ ሲሄድ፣ ወይም ትዳራችሁ ሲሰነጣጠቅና ሊፈርስ ጥቂት የቀረው ሲመስል እግዚብሔርን ትታመናላችሁ? አንዳቸውም ቢሆኑ ለመጋፈጥ ቀላል የሆኑ ሁኔታዎች አይደሉም፤ በራሳችንም ብርታት ልንጋፈጣቸው አንችልም፡፡ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር እንደነዚህ ያሉትን አስቸጋሪ ሁኔታዎች በድፍረት እንድንጋፈጣቸው ይፈልጋል፡፡

## ድላችሁን በእምነት ጨብጡ

ግድድሮሾችን ለመጋፈጥ ሊኖረን የሚገባው ድፍረት የሞት ሽረት ትግሉን እንደሚያደርግ ወታደር በተስፋ መቁረጥ የጨለመ ሊሆን አይገባም፡፡ ይልቁንም፣ ጌታው ድል እንደነሳ በማስተዋል የተሞላ ድፍረት ሊሆን ይገባል፡፡

በእግር ኳስ ጨዋታ ላይ፣ ተጫዋቾችና ደጋፊዎቻቸው ገና ጨዋታው ሳያልቅ በታላቅ ደስታ ሊሞሉ ይችላሉ፡፡ በተለይም ጨዋታው ሊጠናቀቅ ጥቂት ደቂቃ ሲቀረው፣ እየመራ ያለው ቡድን ተጫዋቾች አሰልጣኛቸውን ስለተቀዳጁት ድል እንኳን ደስ አለህ ይሉታል፡፡ አንድ የቴሌቭዥን የእግር ኳስ ኮሜንታተር ገና ጨዋታው ሳያልቅ ነገር ግን ስለ ውጤቱ በጣም እርግጠኛ በሚሆንበት ጊዜ « መብራቱን አጥፉ፤ ጨዋታው አልቋል» በማለት ይናገር ነበር፡፡ ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱ የእርሱን ድል መንሳት አስመልክቶ እንዲህ ያለ እርግጠኝነት እንዲኖራቸው ይፈልጋል፡፡ ቀደም ብለን ያየናቸውን የእርሱን ቃላት እንደገና ደግመን እንያቸው፡- «አይዞአችሁ፤ እኔ አለምን አሸንፌዋለሁ፡፡» የህይወትን ጫናዎች ስንጋፈጥ፣ ኢየሱስ አስቀድሞ በተቀዳጀው ድል እጅግ ልንደሰት ይገባል፡፡

እንዴት ነበር ኢየሱስ ድል የነሳው? ዕብ. 4፡15 እንዲህ ይላል፡- «በሁሉ እንደ እኛ ተፈተነ፤ ነገር ግን ያለ ኃጢአት ነበር፡፡» ኢየሱስ ከሰይጣን ሊሰነዘርበት የሚችለውን የከፋ ነገር ሁሉ ተቀበለና በድል አድራጊነት ውጊያውን አጠናቀቀ፡፡ ቀራኒዮ በሚባለው ተራራ ላይ የአለምን የኃጢአት እዳ በሙሉ ከፈለ፤ ይሄ ብቻ እንኳን ለዘላለም በምስጋና ተሞልተን እንድንደሰት የሚያደርግ በቂ ምክንያት ነው፡፡

ማድረግ ከሚያስደስቱኝ ነገሮች መካከል አንዱ እኔ የምደግፈው የቅርጫት ኳስ ቡድን

ያሸነፈበትን እጅግ በከባድ ፉክክር የተሞላ ጨዋታን የተቀረጸ ፊልም መመልከት ነው፡፡ ጨዋታው እንዴት እንደሚያልቅ ሙሉ እውቀቱ ኖሮኝ የማጥቃትና የመከላከሉ ሂደት እንዴት እንደተከናወነ እመለከታለሁ፡፡

ልክ እንደዚያው፣ የህይወትንም ጫናዎች መጋፈጥ እችላለሁ፤ ምክንያቱም ፍልሚያው በመጨረሻ በምን አይነት መልኩ እንደሚጠናቀቅ አውቃለሁና፡፡ ኢየሱስ ለሰብአዊ ዘር በሙሉ ድል መንሳትን መቀዳጀት እንዲችሉ የሚያስከፍለውን ዋጋ ከፍሏል፡፡

**እስከመጨረሻው ድረስ ጽኑ**

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ስከታተል ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶችን እንድቀስም በረዳኝ የሩጫ ውድድር ውስጥ ተሳትፌ ነበር፡፡ የአንድ መቶ ያርድ ፈጣን ሩጫ ላይ ስወዳደር በመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የጥሎ ማለፍ ሩጫዎች ላይ እጅግ ፈጣን የሆነ ሰአትን አስመስግቤ ጨረስኩ፡፡ ከዚያም ወደ ፍጻሜው ደረስን፡፡ ወሳኝ በሆነው በዚያ የፍጻሜ ሩጫ ላይ ታዲያ፣ አሁንም ተንደርድሬ በመሮጥ ከፊት ሆንኩ፤ ነገር ግን ወደ እኔ ተጠግቶ ያለው ማን እንደሆነ ለማየት ወደ ኋላ ዘወር አልኩኝ፡፡ በዚህ ጊዜ የመኝታ ክፍል ጓደኛዬ ለጥቂት ቀድሞኝ ውድድሩን ሲያሸንፍ አየሁ፡፡ የሚገርመው ታዲያ፣ እርሱ ያሸነፈበት ሰአት እኔ ከዚህ በፊት ካስመዘገብኩት በቀነሰ ፍጥነት መሆኑ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እርሱ አሸናፊ ሆነ፤ ምክንያቱም እኔ እስከመጨረሻው መጽናት አልቻልኩም ነበርና፡፡

የሕይወትን ጫናዎች በተሳካ ሁኔታ ለመጋፈጥ፣ ከክርስቶስ ጋር ሕይወታችን አንድ እንደሆነ እንዲቆይ በመፍቀድ እስከ መጨረሻ ድረስ መጽናት ያስፈልገናል፡፡ የአለምን መንገድ ለመከተል ቆርጦ ሐዋርያው ጳውሎስን ትቶት የሄደውን የዴማስን ስህተት ማስወገድ ይኖርብናል (2 ጢሞ. 4፡10)፡፡ ሁለተኛ ጴጥሮስ 2 የጽድቅን መንገድ ካወቅን በኋላ ከዚያ መንገድ ፈቀቅ የማለት አደጋ ሊገጥመን እንደሚችል ያስጠነቅቀናል፡፡ ውድድሩን ለማሸነፍ ወደ ፍጻሜው መስመር በጣም ተጠግታችሁ ነገር ግን ከውድድሩ እንዳትወጡ ተጠንቀቁ፤ አስታውሱ «እስከ መጨረሻ የሚጸና እርሱ ይድናል» (ማቴ. 24፡ 13)፡፡

**ትክክለኛ አመለካከት ይኑራችሁ**

በሕይወት ውስጥ የሚያጋጥሙንን ጫናዎች በእምነት ለመጋፈጥ ትክክለኛ አመለካከት ሊኖረን ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ ጌታችን ኢየሱስ እጅግ ወሳኝ የሆነን ነገር በማቴ. 16፡24 ላይ እንዲህ በማለት ሰጥቶናል፡- «እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።» ይህ ግድድሮሾችንና የሕይወት ጫናዎችን በተመለከተ ትክክለኛ አመለካት እንዲኖረን የሚያደርገን ነው፡፡ የክርስቶስን ፈለግ ተከትለን መሄድ ከፈለግን ጉዞው መስቀል ተሸክሞ መሄድን እንደሚያካትት ይነግረናል፡፡

በዚህ ጥቅስ ላይ ኢየሱስ የራሳችንን መሻት ወደ ጎን ማድረግ እንደሚያስፈልግም ገልጾልናል፡፡ ራሳችንን መካድና ካስፈለገም የሃዘንንና የስቃይ ጎዳና ለመጓዝ ፈቃደኞች መሆን ያስፈልገናል፡፡ በሉቃ. 18 ላይ የሚገኘው ወጣቱ ባለጸጋ ይህንን አመለካከት መማር ነበረበት፡፡ እንዲህ በሚሉ ቃላት ነበር ወደ ኢየሱስ የመጣው፡- «ቸር መምህር፥

የዘላለምን ሕይወት እንድወርስ ምን ላድርግ?» (ሉቃ. 18፡18)፡፡ ኢየሱስ የሚሰጠውን ለማግኘት ፈልጎ የነበረ ቢሆንም የሚያስከፍለውን ዋጋ ግን ለመክፈል አልፈለገም ነበር፡፡

«ትዕዛዛቱን ጠብቅ» በማለት ኢየሱስ መለሰለት (ሉቃ. 18፡20)፡፡

እርሱም በትምክህት ተሞልቶ «ከልጅነቴ ጀምሬ ጠብቄያቸዋለሁ» በማለት መለሰ (ሉቃ. 18፡21)፡፡

ኢየሱስም እንዲህ አለው፡- «አንዲት ገና ቀርታሃለች፤ ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለድሆች ስጥ፥ በሰማይም መዝገብ ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ » (ሉቃ. 18፡22)፡፡

ይህ ግን ያ ወጣት ሊከፍል ከሚፈልገው በላይ ነበር፡፡ በልቡም እያዘነ፣ ምናልባትም ዳግም ላይመለስ፣ ከኢየሱስ ተለይቶ ሄደ፡፡ ለቀረበለት ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥቶ ቢሆን ኖሮ በሕይወቱ ምን ሊገጥመው ይችል እንደነበረ ማን ያውቃል? የግል ፍላጎቶቹን ሁሉ በመካድ ለኢየሱስ ፍላጎት ራሱን ሰጥቶ ቢሆን ኖሮ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ያከናወናቸውን ነገሮች ሁሉ ማከናወን ይችል ይሆን ነበር፡፡ ጌታ ለጳውሎስ እንዳደረገው፣ አብዛኛውን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ለመጻፍ ሊጠቀምበት ይችል ይሆን ነበር፡፡ ነገር ግን ነገሮችን አጥርቶ የሚያይበት ትክክለኛ አመለካከት አልነበረውም፡፡

በሕይወት የሚገጥሙንን ጫናዎች፣ ግድድሮሾችና ሰቆቃዎች አዳኛችን ክርስቶስ እንደተሸከማቸው እኛም ልንሸከማቸው ይገባናል፡፡ እርሱ እንደተሸከማቸው አይነት መስቀሎች፣ እንደ ራስን የማዋረድ፣ የስደት፣ በስህተት የመስተዋል፣ የመከራና የፈተና መስቀሎችን መሸከም ያስፈልገናል፡፡ ጫናዎችን በመጋፈጥ ረገድ በእምነትና በድፍረት ለመጋጠም ታማኞች እስከሆንን ድረስ ኢየሱስ ፍልሚያውን አስቀድሞ እንዳሸነፈው በማወቃችን ዋስትና ሊሰማን ይገባል፡፡ ይህንን ስናደርግ በመከራችን በረከት ማግኘትና በችግሮቻችንም መደሰት እንችላለን፡፡

### የህይወት ጫናዎችን በእምነት ለመጋፈጥ የሚያስችሉ ወሳኝ እርምጃዎች

- ከከበባችሁ ነገር ተጽእኖ ነጻ ሆናችሁ ኑሩ
- ጫናዎችን ተጠባበቁ
- በሕይወት የሚገጥሟችሁን ጫናዎች በድፍረት ተጋፈጡ
- ድላችሁን በእምነት ጨብጡ
- እስከ መጨረሻ ድረስ ጽኑ
- ትክክለኛ አመለካከት ይኑራችሁ

# 12

# የእግዚአብሔርን ዝምታ ተጋፈጡ

እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ከተናገራቸው ነገሮች መካከል በትክክል ያላስተዋላችሁት ነገር እንዳለ አስባችሁ ጥርጣሬ አድሮባችሁ ያውቃል? ምናልባትም ማርያምና ማርታ የተሰማቸው እንደዚህ ነበር፡፡ ወንድማቸው አላዛር እንደታመመ በመጥቀስ ወደ ኢየሱስ መልእክተኛ ልከው ነበር፡፡ ኢየሱስም አስደናቂ ምላሽ ነበር የሰጣቸው፡- ‹‹ይህ ህመም የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት አይደለም አለ።›› (ዮሐ. 11፡4)፤ ይሁን እንጂ አላዛር ሞተ፤ ኢየሱስም ደግሞ ለቀብር እንኳን አልደረሰም፡፡ ለአራት ቀናት ያህል ከሁኔታው ርቆና ዝም ብሎ ቆየ፤ የአላዛር እህቶችም የእርሱን ዝምታ በልባቸው ውስጥ ከሞላው መሪር ሃዘን ጋር መጋፈጥ ነበረባቸው፡፡

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ለምን ዝም እንደሚል በመገረም ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ? አንዳንድ ጊዜ ዝም የሚለው እኛን ከእርሱ ከሚለየን ኃጢአታችን የተነሣ ነው (ኢሳ. 59፡1-2)፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ፣ ዝም የሚለው እኛ እርሱን ለመስማት ስላልተዘጋጀን ነው፡፡ እግዚአብሔር ባናገረው ጊዜ የካህኑን የኤሊን ድምጽ የሰማ መስሎት እንደነበረው እንደ ሣሙኤል ነን፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ እምነት የለሽ መሆናችን እርሱ እንዳይሰማን ይከለክለዋል፡፡ እንደዚሁም አንዳንድ ጊዜ በራስወዳድነት ከመዋጣችን የተነሣ፣ የእርሱን ድምጽ ለመስማት ያዳግተናል (ያዕ. 4፡3)፡፡

**አትሸበሩ**

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ-ባሕርያት በአንድ ጊዜም ሆነ በሌላ የእግዚአብሔርን ዝምታ ተለማምደዋል፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም ይስሐቅን እንዲሰዋለት ከነገረው በኋላ፣ መስዋዕቱን ወደ ሚያቀርብበት ስፍራ ባደረገው ቀናትን የፈጀ ጉዞ ይህ የሃይማኖት አባት መለኮታዊውን ዝምታ ተለማመደ፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር እንደገና መናገር ጀመረና ልጁን ከመሰዋት አብርሃምን አስቆመው (ዘፍ. 22)፡፡

ዮሴፍ በግብጽ ባርነትና በእስረኛነት የታሸባቸውን ጊዜያት አስቡ፡፡ ያለ ምንም ጥርጥር በተደጋጋሚ እግዚአብሔር እንዲያስበው ጮኾ ነበር፤ እግዚአብሔር ግን ምንም መልስ ሳይሰጥ ቆየ፡፡ የእርሱ ዘሮች የሆኑት እስራኤላውያ በፈርኦን ጨካኝ ቀንበር ስር ሆነው ለከፍለ-ዘመናት ወደ እርሱ ሲጮኹ፣ እግዚአብሔር ግን ምንም መልስ አልሰጣቸውም ነበር (ዘጸ.2፡23)፡፡

በመሣ. 6 ላይ የሚገኘው የጠላት ወታደሮችን በመፍራት በመጥመቂያው ውስጥ ሆኖ

ስንዴ ሲወቃ የነበረው ጌዲዎንስ? እግዚአብሔር ተገልጦለት፣ «አንተ ጽኑዕ ኃያል ሰው» ብሎ ሲጠራው፣ ጌዲዮን እንዲህ በማለት ተቃወመ፣ «ጌታዬ ሆይ፥ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ይህ ነገር ሁሉ ለምን ደረሰብን?» ይህ የእስራኤል መሪ በብዙ ጥያቄዎች ተሞልቶ ነበርና አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር ከህዝቡ ጋር ነው ብሎ ለማመን ተቸግሮ ነበር፡፡

ኢየሱስ ራሱ የአባቱን ዝምታ የተጋፈጠበት ጊዜ ነበር፡፡ ከመስቀሉ ላይ እንዲህ በማለት ጮኸ፡- «አምላኬ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ?» (ማቴ. 27፡ 46)፡፡ በተማጽኖ ለተሞላው ለዚህ ጩኸቱ ምንም አይነት መልስ አላገኘም ነበር፡፡

በሥጋው መካከል እሾህ የነበረውና እግዚአብሔርም ይህንን እሾህ እንዲነቅልለት ሦስት ጊዜ የጸለየው ከተርሴስ የመጣው ድንኳን ሰፊስ (2 ቆሮ. 12)? ምንም እንኳን ይህ ሐዋርያ አብዛኛውን የአዲስ ኪዳን ክፍል የጻፈም ቢሆን፣ ከእግዚአብሔር ዝምታ ጋር መኖር ነበረበት፡፡ በሂደትም፣ እግዚአብሔር ዝምታውን ሰብሮ፣ ለጳውሎስ የእርሱ ጸጋ እንደሚበቃው ማረጋገጫ ሰጠው (2 ቆሮ. 12፡9)፡፡

ከዩ.ኤስ. ባሕር ኃይል ጡረታ ከወጣሁ በኋላ፣ ሦስት የሥራ እድሎች አገኘሁ፤ ሁለቱ ደግሞ በጣም የሚያጓጉ ነበሩ፡፡ ለዘጠኝ ወራት ያህል፣ የእግዚአብሔርን ምሪት እፈልግ ነበር፡፡ የትኛውን ሥራ ይሆን መምረጥ ያለብኝ? ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ዝም አለኝ፡፡ የእርሱ ሰላም በልቤ ውስጥ ሰፍኖ እንዲመራኝ ብጠባበቅም፣ ውስጤ ግን መታወኩን ቀጠለ፡፡ ለወራት፣ ከሰማይ ምላሽ ለማግኘት በመፈለግና የእግዚአብሔርን ዝምታ ብቻ በመጋፈጥ ተስፋ አስቆራጭ ልምምድ ውስጥ ቆየሁ፡፡ እናንተስ? ወደ እግዚአብሔር ጮኻችሁ ነገር ግን ያገኛችሁት ምላሽ ዝምታ ብቻ ሆኖ ያውቃል? በመከራችሁ ውስጥ የተሰወረውን በረከት ለማውጣት ከፈለጋችሁ፣ አንዳንድ ጊዜ ዝም ከሚል አዳኝና ጌታ ጋር እንዴት መኳዝ እንደምትችሉ መማር ያስፈልጋችኋል፡፡ እግዚአብሔር ምንም ሳይናገር ዝም በሚልበት ጊዜ ያለመሸበር ችሎታን ማዳበር ያስፈልገናል፤ እንደዚሁም ምንም አይነት ምላሽ እንዳላገኛችሁ በሚሰማችሁ ጊዜ እንኳን እርሱ እየሰማ እንዳለ ማመን ያስፈልጋችኋል፡፡

እነ አብርሃም፣ ዮሴፍ፣ የእስራኤል ህዝብ፣ ጌዲዮን፣ ኢየሱስና ጳውሎስ፣ የጠቀስኳቸው ስሞች ሁሉ፣ የእግዚአብሔርን ዝምታ ተጋፍጠዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህንን ዝምታ እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው የተማሩና እግዚአብሔር ለሚያልፉበት መከራ ምንም ደንታ የሌለው በሚመስልበት ጊዜ እንኳን ሳይቀር በእርሱ በመታመን የሚገኘውን ታላቅ የበረከት መኸር የሰበሰቡ ናቸው፡፡ በአብዛኛው እግዚአብሔር ብቅ ያለው ፈጽሞ ባልጠበቁት ጊዜ ሲሆን፣ እነርሱም ሊሰሙትና ሊያደንቁት በሚችሉት መንገድ ነበር የተናገራቸው፡፡ በእግዚአብሔር ዝምታ ውስጥ በትእግስት በመጠበቅ ሽልማታቸውን አጨዱ፡፡

**የሃዘንና የመከፋት ወቅቶችን ተቋቋሙ**

በማንኛውም የሕይወት ወቅት የእግዚአብሔርን ዝምታ ልንለማመድ እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ጠላት አለንና፤ ውጊያችንም ከስጋና ከደም ጋር ሳይሆን በሰማያዊ ሥፍራ ከሚገኙ የጨለማ ኃይላት ጋር ነው (ኤፌ. 6፡ 12)፡፡ አንዳንድ ጊዜ ይህ የዝምታ ወቅት ልክ እንደ ሳሙኤል በልጅነት ዘመናችን ሊመጣ ይችላል (1 ሣሙ. 3)፡፡ እናቱ ሃና ለእግዚአብሔር ቀድሳ ከሰጠችው በኋላ፣ ሳሙኤል ከካህኑ ከኤሊ ጋር ለመኖር ሄደ፡፡

ሳሙኤልም ወደ ጉርምስናው እድሜ ሲገባ እግዚአብሔር ዝምታውን ሰበረና ተናገረው፡፡ ሳሙኤል የካህኑ የኤሊ ድምጽ መስሎት ነበር፡፡ እግዚአብሔርን እንዴት መስማትና ለእርሱም እንዴት ምላሽ መስጠት እንዳለበት መማር ነበረበት፡፡

ንጉሥ ሳኦል ደግሞ የእግዚአብሔርን ዝምታ ሲለማመድ በመካከለኛ እድሜ ክልል ውስጥ ነበር፡፡ ነብዩ ሳሙኤል ከሞተ በኋላ፣ ንጉሡ ከእግዚአብሔር ሊሰማ ፈለገ፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ዝም አለው፤ በመቅደሱ ውስጥ ያሉ ካህናት ከሰማይ ድምጽን ለመስማት የሚጠቀሙባቸውን ቴክኒኮች ቢጠቀምም እንኳን እግዚአብሔር ግን መልስ አልሰጠውም፡፡ በመጨረሻም ሳኦል በዓይን ዶር የምትገኝን ጠንቋይ ፍለጋ በመሄድ ይጠይቀው ዘንድ የሳሙኤልን መንፈስ እንድታስነሳለት ፈለገ (1 ሳሙ. 28)፡፡ ሳኦል ይህንን ያህል የእግዚአብሔርን ዝምታ ለመስበር በእጅጉ ፈልጎ ነበር፡፡

አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ዝምታ በሕይወታችን አመሻሽ እድሜ ላይም ልንጋፈጥ እንችል ይሆናል፡፡ ከሠላሳ አመት በላይ እናቴ የአልኮል መጠጥ ሱሰኛ ለነበረው አባቴ ትጸልይ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ምንም መልስ አልሰጠም፡፡ እያደግን ስንሄድም እኔን፣ ወንድምና አህቶቼን ለአባታችን መጸለይን እንዳናቋርጥ ታደፋፍረን ነበር፡፡ እኔም እጸልይ ነበር፤ ነገር ግን በሂደት ተስፋ ቆረጥሁ፡፡ አባቴ አሁንም በአልኮል መጠጥ ሱስ ውስጥ ተዘፍቆ የነበረ ሲሆን፣ እግዚአብሔርም ዝም ያለ ይመስል ነበር፡፡ እናቴ ግን መጸለይዋን ቀጠለች፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር በአመሻሹ እድሜዋ ላይ ዝምታውን በመስበር አባቴን በመለወጥ ከሱሱ ነጻ በማውጣት ተአምራቱን ሰራልን፡፡ በሞተም ጊዜ ክርስቲያን ሆኖ ነበር የሞተው፡፡

እናንተስ በየትኛው የእድሜ ወራት ውስጥ ነው ያላችሁት? ምናልባት የመለኮትን ምሪት የምትፈልጉ ወጣቶች ሳላችሁ ነገር ግን ሰማይ ደግሞ ምንም አይነት አቅጣጫን የማይሰጥ መስሎ የሚሰማችሁ ትሆኑ? ወይም በመካከለኛው እድሜ ላይ የምትገኙ ጥሩ ሥራ ነው ብላችሁ በያዛችሁት ውስጥ የገጠሟችሁን ማዕበሎች አቋርጣችሁ ለማለፍ የምትሞክሩ፣ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ዝም ያላችሁ የሚመስላችሁ ትሆኑ? ወይስ ምናልባት በሕይወት አመሻሽ እድሜ ላይ የምትገኙ፣ ምንም እንኳን ቀኑ እየመሸ ቢነጋም ግን በእጅጉ የምትናፍቁት ህልማችሁ ግን መቼም ቢሆን እውነት እንደማይሆን በማሰብ አዝናችሁ ይሆን? በየትኛውም የሕይወት ወቅት ውስጥ የሚገኘውን ተግዳሮት እየተጋፈጣችሁ ራሳችሁን ብታገኙ፣ የእግዚአብሔርን ዝምታ በትዕግስት፣ በጽናትና በእምነት ልትጋፈጡ ትችላላችሁ፡፡

**ተስፋ ማድረግና መጸለይ ቀጥሉ**

የእግዚአብሔርን ዝምታ የሚለማመዱ ብዙዎቹ እግዚአብሔር የሚፈትናቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ክንውን ደረጃ ከመውጣት በፊት የመግቢያ ፈተና እንዳለው ሁሉ፤ እግዚአብሔርም ልዩ ወደ ሆነ በረከት ልጆቹን ከማምጣቱ በፊት ይፈትናቸዋል፡፡ ዮሴፍ የግብጽ ጠቅላይ ሚኒስትር ከመሆኑ በፊት የፈርኦንን ሰዎች ከረዳ በኋላ ሁለት አመት ለሚሆን ጊዜ በእስር ቤት መቆየት ነበረበት፡፡ እግዚአብሔር ዝም ቢለውም፣ ዮሴፍ ግን አላማረረም ወይም አላጉረመረመም፡፡ እናም እግዚአብሔር መናገር በጀመረ ጊዜ፣ ሃያ አራት ሰአት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በተሳካ ሁኔታ ባርያውን ከእስርቤት ወደ ከፍተኛ ስልጣን መሻገር ችሎ ነበር፡፡

ፍርድን ሸሽቶ የተሰደደው ሙሴም ተመሳሳይ ልምምድ ነበረው፡፡ ለአርባ አመታት

ከህጉ ሸሽቶ፣ የአማቱን በጎች በሚዲያም በረሃ ይጠብቅ ነበር፡፡ ቀን በቀን አመት በአመት ተመሳሳይ የሆነውን ስራውን ሲሰራ፣ እግዚአብሔር ምንም ነገር አላለውም ነበር፡፡ ነገር ግን አንድ ቀን፣ ይህ በግዞት ላይ የነበረ መሪ ያለማቋረጥ የሚነድ ግን የማይቃጠል ቁጥቋጦ ተመለከተ፡፡ ከዚያም ውስጥ የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰማ፡፡ እግዚአብሔርም ስለ አንድ ታላቅ በረከት ነገረው፡፡ ምንም እንኳን ባለፈ ዘመኑ በወንጀል ድርጊት ውስጥ የነበረም ቢሆን፣ ሙሴ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከግብጽ ሰንሰለት ፈትቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር የነጻነት ሕይወት እንዲመራቸው ተመረጠ፡፡

በ1950ዎቹ በአላባማ (የአሜሪካ ግዛት ናት) በነበረው የዜጎች ሙብት ንቅናቄ አፍሪካ አሜሪካውያን በአውቶብስ ያለመሄድ አድማ አድርገው ነበር፡፡ ይህንንም ያደረጉት የሕዝብ መመላለሻዎችን በመጠቀም ረገድ የነበረውን የማግለል አሰራር ለመቃወም ነበር፡፡ እናም ይህንን በማድረጋቸው የስማቸውን ክብር ለመጠበቅ በሚፈልጉ ሰዎች ዘንድ ተቃውሞ ገጥሟቸው ነበር፡፡ ከአመት በላይ ለሚሆን ጊዜ ውርደትን ተከናንበው በመኪና ከሚሄዱ ይልቅ በእግራቸው መሄድን መርጠው በአቋማቸው ጸኑ፡፡ ወደ እግዚአብሔርም ጮኹ፤ ነገር ግን ተቃዋሚ ኃይላት የሚያሸንፉ መሰለ፡፡ ሰማይም ዝም አለ፡፡ ጥረታቸው ሁሉ መና የቀረና ጠላቶቻቸውም ያሸነፉ በመሰለበት ጊዜ ግን፣ ታላቅ በረከትን ተቀበሉ፡፡ የዩ.ኤስ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለእነርሱ ፈረደላቸው፡፡ ለወራቶች የቆየው የመለኮት ዝምታ የታላቅ በረከቶች ጅማሮ(አንድ ሙዚቃ ከመጀመሩ በፊት ያለውን የጸጥታ ጊዜ የሚመስል) ሆነ፡፡

በሕይወታችሁ የምትለማመዱት የእግዚአብሔር ዝምታ ለወደፊት ለተዘጋጀ በረከት እጩ መሆናችሁን የሚያሳይ ይሆን? ከሆነስ፣ ፈተናውን እንደምታልፉና እንደማታልፉ የሚወስነው አመለካከታችሁ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን መልካምነት በአንዳች ባለመጠራጠር፣ ለመከራችሁ እጽፍ የሆነ በረከትን ከእርሱ ለመቀበል መዘጋጀት ትችላላችሁ፡፡ ተስፋ ማድረጋችሁንና መጸለያችሁን ቀጥሉ፡፡

**ከእግዚአብሔር ቃል መልስ ፈልጉ**

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ዝም የሚለን እምነታችንን ለማሳደግ ነው፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆነንን ታሪክ በማቴ. 15 ላይ ከአንዲት አህዛብ ሴት ልምምድ እንመለከታለን፡፡ ይህች ሴት ልጇ በአጋንንት ተይዛባት ስለነበረ የኢየሱስን እርዳታ በጥብቅ ፈለገች፡፡ እርሷም ሃዘኗን ለኢየሱስ ነገረችው፤ መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ጽፎልናል፡- «እርሱ ግን አንዳች አልመለሰላትም።» (ማቴ. 15፡ 23)፡፡ ኢየሱስ «ይሆናል» ወይም «አይሆንም» ወይም «ጠብቂ» እንኳን አላላትም፡፡ አንዲትም ቃል አልተነፈሰም፡፡ በመጨረሻ ኢየሱስ መናገር ሲጀምርም የተናገረው ለእርሷ ሳይሆን ለደቀመዛሙርቱ ነበር፡፡ ለደቀመዛሙቱም ከእስራኤል ወገን ለጠፉት ወገኖች እንጂ፣ በዚያን ዘመን ለነበሩት አህዛብ እንዳልመጣ ነገራቸው፡፡ ምንም እንኳን ኢየሱስ የእርሷን ልመና ችላ ያለም ቢመስል፣ ሴቲቱ ግን እርዳታን ፍለጋ ወደ እርሱ መጮኽ ቀጠለች፡፡ በመጨረሻም ለእርሷ መናገር ጀመረ፤ ነገር ግን ለእርሷ ለማስተዋል በሚከብዱ ቃላት ነበር የተናገራት፡- «የልጆችን እንጀራ ይዞ ለቡችሎች መጣል አይገባም » (ማቴ. 15፡26)፡፡ ወይ ጉድ! ኢየሱስ እስቲ ቆይ አንድ ጊዜ፡፡ እንዲህ ብለህ ስትናገር ሴቲቱን እየሰደብካት አይደለምን?

ይህንን በመናገሩ ሊል የፈለገው ነገር ምንም ይሁን ምን፣ ይህች ሴት ግን የዝምታውንና ከላይ ሲታይ ስድብ የሚመስለውን የእርሱን የአቀራረብ ዘዴ አስተውላ ነበር፡፡ ለገጠማት ተግዳሮትም በታላቅ እምነት ውስጥ ሆና እንዲህ በማለት መለሰች፡-

«አዎን ጌታ ሆይ፤ ቡችሎችም እኮ ከጌቶቻቸው ማዕድ የወደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ» (ቁ. 27)፡፡

ኢየሱስም ፈገግ ብሎ እንዲህ በማለት መለሰ፡- «አንቺ ሴት፥ እምነትሽ ታላቅ ነው፤ እንደወደድሽ ይሁንልሽ»(ማቴ. 15፡ 28)፡፡ ልጇም ልክ በዚያው ሰአት ተፈወሰች፡፡ ይህቺ ሴት ለመጽናት ፈቃደኛ መሆኗ የእግዚአብሔርን ዝምታ ለማስተናገድ እድትችል ረዳት፡፡

ይህቺ ሴት ኢየሱስ ዝምታውን እንዲሰብር ያደረገችው እንዴት ነበር? በመጀመሪያ፣ ወደ እርሱ የመጣችው ፍቅር አነሳስቷት ነበር፡፡ የመጣችው ለራሷ ሳይሆን ለልጇ ነበር፡፡ ከዚህች ሴት ምሳሌነት ጸሎታችንን ሊያነሳሳው የሚገባ ፍቅር ብቻ እንዲሆን ማድረግ እንዳለብን፣ በራስ ወዳድነት አለመጸለይንም እንማራለን፡፡ ሁለተኛ፣ ኢየሱስ ምንም ቃል ከአፉ ባልወጣበት ጊዜ እንኳን ይሰማ እንደነበረ ታውቅ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ዝም ባለ ጊዜ እንኳን ጩኸታችሁን ይሰማል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ፣ ለችግሯ እድሏን አላማረረችም፡፡ የእግዚአብሔር ዝምታ ከእኛ ጥፋት ጋር የሚኖረው ቁርኝት በጣም አናሳ ነው፡፡ አንድ ጊዜ ዳንኤል ለፀሎቱ ከእግዚአብሔር ቃል ለመስማት ሦስት ሳምንት ያህል ጠብቆ ነበር፤ በመጨረሻም መልአኩ ተገለጠለት፡- «እርሱም እንዲህ አለኝ፡- ዳንኤል ሆይ፥ አትፍራ ልብህ ያስተውል ዘንድ፥ ሰውነትህም በአምላክህ ፊት ይዋረድ ዘንድ ካደረግህበት ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ቃልህ ተሰምቶአል እኔም ስለ ቃልህ መጥቻለሁ።» (ዳን. 10፡12-13)፡፡ ለዚህ የጸሎቱ መልስ መዘግየት ዳንኤል ተጠያቂ የሚሆንበት ምንም ምክንያት የለም፡፡ አራተኛ፣ ይህች ከአይሁድ ወገን ያልሆነች ሴት ከኢየሱስ ቃላት ውስጥ መልስ አግኝታ ነበር፡፡ ምንም እንኳን በመጀመሪያ በቀጥታ ከእርሷ ጋር ያልተነጋገረም ቢሆን፣ ለደቀመዛሙርቱ የተናገራቸውን በማዳመጥ ተስፋን ተመለከተች፡፡ ከዚያም ውሾችን ስለማብላት የተናገራትን በጥንቃቄ ካዳመጠች በኋላ፣ የራሱን ንግግር በመጠቀም ያላትን እምነት ገለጠችለት፡፡ እግዚአብሔር በሕይወታችሁ ዝም ሲላችሁ በቃሉ ውስጥ መልስን ፈልጉ፡፡

**የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች አጥብቃችሁ ያዙ**

በእግዚአብሔር የዝምታ ጊዜያት ውስጥ በጽናት ለመቆየት ከሚያስችሉ ምርጥ መንገዶች መካከል አንዱ የሰጣቸውን የተስፋ ቃሎች ማንበብና በእምነት የኔ ናቸው ብሎ መቁጠር ነው፡፡ እርሱ ቃሉን እንደሚጠብቅና መቼም እንደማይዋሽ በማወቅ ለልጆቹ ሊያደርግ ተስፋ የሰጣቸውን ነገሮች አጥብቃችሁ ያዙ፡፡

በሂደት፣ በጽናት ያቺ ከአህዛብ ወገን የሆነች ሴት የእግዚአብሔርን ዝምታ ሰበረችው፡፡ እናንተስ እግዚአብሔር ዝም ሲላችሁ በጸሎት ጸንታችሁ ለመቆየት ዝግጁዎች ናችሁ? በ 1 ነገ 18 ላይ በቀርሜሎስ ተራራ ኤልያስ መስዋዕቱን የሚበላ እሳት ከሰማይ እንዲወርድ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አፋጣኝ ምላሽ ነበር የተቀበለው፡፡ ይህ ግሩም ነው፡፡ ይሁን እንጂ በምዕራፉ መጨረሻ ላይ ለዝናብ ሲጸልይና እግዚአብሔር ዝም ባለው ጊዜ የሆነው ከዚህ የተለየ ነበር፡፡ ነገር ግን፣ በጽናት ጠበቀ፡፡ እግዚአብሔር እየሰማው እንዳለ ትንሽ ፍንጭ ማየት እስኪችል ድረስ ሰባት ጊዜ ጸለየ፡፡ እግዚአብሔር ዝም በሚልበት ጊዜ፣ ድምጹን እስኪያሰማ ድረስ በጽናት ጠብቁ፡፡ እግዚአብሔር መልስ እስኪሰጣችሁ በጸሎት ጽኑ፡፡

## የእግዚአብሔርን ዝምታ ለማስተናገድ የሚያስችሉ ወሳኝ እርምጃዎች

- አትሸበሩ
- የሃዘንና የመከፋት ወቅቶችን ተቋቋሙ
- ተስፋ ማድረግና መጸለይ ቀጥሉ
- ከእግዚአብሔር ቃል መልስ ፈልጉ
- የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች አጥብቃችሁ ያዙ

# 13

# ተጠቀሙበት ወይም ታጡታላችሁ

አዲሷ የዩ. ኤስ. ሴናተር የምትማርክ ሴት ነበረች፡፡ ሴናተሮች የህብረት ጊዜ እንዲኖራቸውና ስለ የሥራ ባልደረቦቻቸው የግል የእምነት ጉዞ ለመማር እድል በሚሰጣቸው በሴኔቱ ሳምንታዊ የቁርስ ጸሎት ፕሮግራም ላይ ንግግር ለማድረግ በቆመች ጊዜ የሁላችንም አይኖች በእርሷ ላይ ተተከሉ፡፡ በመጣችበት ክፍለ ሃገር የአነጋገር ዘዬ ታሪኳን በሙሉ መተማመን፣ ኃይልና አሳማኝ በሆነ መልኩ አቀረበች፡፡ ምንም እንኳን ሴናተር ለመሆን ገና ለጋ ወጣት ብትመስለንም፣ ከአፏ የሚወጡት ቃላት ግን እንድንሰማት ግድ ይሉን ነበር፡፡ እንዲህም አለች፡- ‹‹በሁለት ክርስቲያናዊ ምሳሌዎች ውስጥ ታላቅ ምሪትና ብርታት አግኝቻለሁ፤ እነዚህም በማቴ. 25 ላይ የሚኘው የታላንቶቹ (የመክሊቶቹ) ምሳሌና በማቴ. 13 ላይ የሚገኘው የዘሪው ምሳሌ ናቸው፡፡ እነዚህ ታሪኮች ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ደግሞ ብርሃን ናቸው፡፡››

ግሩም ከሆነው ንግግሯ በኋላ፣ እነዚህን ድንቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች እንደገና ለማንበብ በመጓጓት በዩ. ኤስ. ካፒቶል ህንጻ ላይ ወደ ሚገኘው ቢሮዬ በአሳንሰር ተጓዝኩ፡፡ ቢሮዬ እንደገባሁም፣ ዘመናዊ ከሆኑት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች መካከል አንዱን አነሳሁና ሁለቱ ምሳሌዎች ወደሚገኙበት ቦታ ከፈትሁ፡፡ ሴናተሯ የተናገረችውን አንዳንድ ነገሮች በማስታወስ ሳነበው ይበልጥ ሕያው ሆነልኝ፡፡ በመጀመሪያ ያነበብኩት የመክሊቶቹን ምሳሌ ሲሆን ከዚያም የዘሪውን ቀጥዬ አነበብኩ፡፡ ይህ ንባቤ ደግሞ በዮሐ. 6 ላይ የሚኘውን የአምስት ሺህ ሰዎች በድንቅ የመመገብ ተአምርን እንዳነብ አነሳሳኝ፡፡ በሦስቱም ውስጥ አንድ ተመሳሳይ የጋራ ሃሳብ አየሁ፤ ይኼውም ‹‹ተጠቀሙበት አልያ ታጡታላችሁ›› የሚል ነው፡፡ በተለይም ሦስተኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ኢየሱስ የሚከተለውን በመናገር አጉልቶታል፡- ‹‹አንድ ስንኳ እንዳይጠፋ የተረፈውን ቍርስራሽ አከማቹ ፡፡›› (ዮሐ. 6፡ 12) ከዚያም በማቴ. 25 ላይ ወደሚገኘው የመክሊቶቹ ታሪክ መጽሐፍ ቅዱሱን ከፈትኩና ማሰላሰሌን ቀጠልኩ፡፡

የመክሊቶቹ ምሳሌ ወደ ሩቅ አገር ከመሄዱ በፊት ለአገልጋዮቹ መክሊቶችን (የገንዘብ መጠን ነው) ሰጥቶ ስለሄደ ሰው የሚናገር ነው፡፡ ከላይ ሲታይ የመክሊቶቹ ክፍፍል ፍትሃዊ ላይመስል ይችላል፤ ምክንያቱም አንዱ አምስት፣ ሌላው ሁለት ሦስተኛው ደግሞ አንድ ብቻ ነበርና የተቀበሉት፡፡ ጌታው አገልጋዮቹ ገንዘቡን ወስደው ሰርተውበትና አትርፈውበት እንደሚቆዩት አምኖ ሄደ፡፡ ወራቶቹ በረሩ፤ እናም ጌታቸው አገልጋዮቹ

ምን እንደሰሩ ሊጠይቅ መጣ፡፡ የተሰጣቸውን በእጥፍ አትርፈው የቆዩት የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ፣ በስራቸው ከተደሰተው ቀጣሪያቸው የምስጋናና የአድናቆትን ቃላት ተቀበሉ፡፡ ነገር ግን አንድ ታለንት ብቻ የነበረው ሰው እድለኛ አልነበረም፡፡ የተሰጠውን ገንዘብ በምንም አይነት ስራ ላይ አላዋለውም ነበር፡፡ እንዲህም በማለት በማጉምረም መለሰ፡- «ጌታ ሆይ፥ ካልዘራህባት የምታጭድ ካልበተንህባትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን አውቃለሁ፤ ፈራሁም ሄጄም መክሊትህን በምድር ቀበርሁት፤ እነሆ፥ መክሊትህ አለ» ጌታውም እንዲህ በማለት መለሰ፡- «አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ፥ ካልዘራሁባት እንዳጭድ ካልበተንሁባትም እንድሰበስብ ታውቃለህን? ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር፥ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር። ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት አሥር መክሊትም ላለው ስጡት፤» ያ ሰነፍ አገልጋይ የተሰጠውን ነገር አልተጠቀመበትም ነበር፤ እናም ሊያጣው ተገደደ፡፡

የታሪኩ ተራኪ ኢየሱስ ንግግሩን የጨረሰው እንዲህ በማለት ነበር፡- «ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና ይበዛለትማል፤ ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል።» (ማቴ. 25፡ 29)፡፡ የዚህ ምሳሌ ዋና መልእክት ከእግዚአብሔር የተሰጡንን መክሊቶች ወይ የመጠቀም አልያም የመነጠቅ እድል ብቻ እንዳለን ማስገንዘብ ነው፡፡ መሐል ሰፋሪ መሆን አይቻልም፡፡ አስፈላጊውን ጥረት ከማድረግ ከሰነፍን፣ አለን የምንለውም ነገር ይወሰድብንና ለሌሎች ይሰጣል፡፡

አንዳንዶች ይህ ፍትሐዊ አይደለም ብለው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡ እንዲህ የሚሉበትን ምክንያት እናጢነው፡፡ በመጀመሪያ፣ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ከሦስተኛው የተሻለ እድል ነበራቸው፡፡ አምስት መክሊቶች የተሰጠው ሰው አንድ ብቻ ቢያጣ፣ የከሰረው 20 በመቶ ብቻ ነው፡፡ በተመሳሳዩ፣ ሁለት የተሰጠው ሰው አንዱን ቢያጣ፣ ያጣው ከካፒታሉ ግምሹን ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ታለንት ብቻ ኖሮአችሁ እርሱንም ስታጡ፣ ታላቅ ኪሳራ ነው የሚገጥማችሁ፤ ሁሉንም ነውና የምታጡት፡፡ ታዲያ ለምንድን ነው እንዲህ ያለውን በጥንቃቄ የተሰጠውን አንድ ታለንት ጠብቆ ለማቆየት የሞከረ ሰው የተቀጣው? እንዲያውም፣ የተሰጠውን ሳያጠፋው በመገኘቱ ሊመሰገን አይገባውም ነበርን? ምናልባት ጌታው አገልጋዩን የገሰጸው ምንም ሙከራ ስላደረገ ይሆናል፡፡ ኃጢአት ውድቀት ሳይሆን አለመሥራት ነው፡፡ የተሳካላቸው አገልጋዮች የተመሰገኑት የተሰጣቸውን ሳያጠፉ በመጠበቃቸው ሳይሆን፣ ታማኞች በመሆናቸው ነው፡፡ ይህ ታማኝነት የተገለጠበት አንደኛው መንገድ ደግሞ ጥረት ለማድረግና ለመሞከር በነበራቸው ፈቃደኝነት ነበር፡፡

የእግዚአብሔርን መጽናናት የተቀበሉ ሁሉ ለሌሎች የሚያካፍሉት ነገር አላቸው፡፡ ወደ ኋላ መለስ ብለን ያሳለፍናቸውን ከባድ ቀናትና በእነዚያም ቀናት የኀበኘንን የእግዚአብሔርን ምህረት ስናስታውስ፣ ለሌሎች የምናካፍለው ነገር ይኖረናል፡፡ በአስቸጋሪ ቀናት የእግዚአብሔርን መጽናናት የተለማመዱ ክርስቲያኖች ሁሉ ባለፈው ሕይወታቸው የደረሰባቸውን ስቃይ ሌሎች ሰዎችን ለመባረክ መጠቀም የሚችሉበት ምስክርነት አላቸው፡፡ ተስፋ በመቁረጥ ያቀረቀሩትንና ልባቸው በፍርሃት የተሞላውን ሁሉ እግዚአብሔር እናንተን እንዴት እንዳጽናናችሁ በመንገር ከወደቁበት ልታነሷቸው ትችላላችሁ(2 ቆሮ. 1፡4)፡፡ ይህ ሁላችንም ለእግዚአብሔር ክብር ልንጠቀምበት የምንችለው ታለንት ነው፡፡ ሁላችንም የቆሰሉትን ለመፈወስ የሚያበቃን ችሎታ አለን፡፡

**ፉክክርን በጥበብ አስተናግዱ**

ፉክክርን ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ ታስተናግዱታላችሁ? ታለንቶቻቸውን በአግባቡ መጠቀም የሚፈልጉ ሁሉ ፉክክርን በጥበብ ስለ ማስተናገድ መማር አለባቸው፡፡ ስለ ፉክክር ማስተዋል ያብን የመጀመሪው ነጥብ እግዚአብሔር ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ችሎታን እንደሰጠ ነው፡፡ አንዳዶች አምስት ያገኛሉ፤ ሌሎች ደግሞ ሁለት፤ አሁንም ሌሎች ደግሞ አንድ ይሰጣቸዋል፡፡ ሥጦታው በተመሳሳይ መጠን ለሁሉ አይሰጥም፤ ይህ እውነታ ነው፡፡ ይህንን ማወቃችን ታዲያ የፉክክራችንን ትኩረት በሌሎች ላይ ከማድረግ ይልቅ በራሳችን ላይ እንድናደርግ ሊረዳን ይገባል፡፡ የምትፎካከሩት ሰው ቢኖር እራሳችሁን ብቻ መሆን አለበት፡፡

ታላቁ የቅርጫት ኳስ አሰልጣኝ ጆን ውድን በሚሰጠው ስልጠና ላይ የዚህን ጉዳይ አስፈላጊነት በአጽንኦት ይገልጸዋል፡፡ ለጆን ውድን ቡድን ሲጫወት የነበረውና ከእርሱም ጋር በአሰልጣኝነት የሰራው ኤዲ ፓወል እንዲህ በማለት ይናገራል፡- «አሰልጣኝ ውድን የተቻለንን ሁሉ ተጫውተን ከምንሸነፍበት ጊዜ ይልቅ ባለን ችሎታ ልክ ሳንጫወት በምናሸንፍበት ጊዜ የበለጠ ይበሳጫል፡፡» (John Wooden and Steve Jamison, *The Essential Wooden: A Lifetime of Lessons on Leaders and Leadership* (New York: McGraw Hill, 2007), xi.) እንዲያውም ውድን ስኬትን ሲተረጉመው «መሆን የምትችለውን ለመሆን የተቻለህን ሁሉ ማድረግህን በማወቅህ ምክንያት ከሚሰማህ እርካታ የሚያመነጨው የአእምሮ ሰላም ነው» (Ibid., 33.) ይለዋል፡፡

ከራሳችሁ ጋር ብቻ በመፎካከር የፉክክርን መንፈስ በጥበብ መያዝ ከቻላችሁ፣ ሌሎችን በማገልገል በመትጋት ደግሞ ወደሚቀጥለው ደረጃ ትሻገራላችሁ፡፡ ፉክክርን፣ እናንተ አንደኛ ልትሆኑበት ከምትፈልጉት ይልቅ ሌሎችን ለማገልገል ከሚከፍትላችሁ እድል አንጻር ልታዩት ከቻላችሁ፣ የተሻለ አመለካከትን ትጨብጣላችሁ፡፡ ይህ አመለካከት ደግሞ እግዚአብሔር ሌሎችን ማገልገልን ከእኛ እንደሚጠባበቅ ከማወቃችን የሚመነጭ ነው (ገላ. 5፡ 13፤ 1 ጴጥ. 4፡10)፡፡ ደግሞስ እግዚአብሔር የሰጠንን ችሎታዎች ከመጠቀም የሚበልጥ ምን የተሻለ መንገድ አለ?

ሌሎችን እንዳገለግል ከረዱኝ ነገሮች መካከል አንደኛው ባለቤትነት ቅዠት መሆኑን ማስተዋሌ ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ሰብአዊ ፍጡራን ወደ አለም የመጡ ምንም ነገር ሳይዙ እንደሆነና ዓለምን ጥለው የሚሄዱትም እንደዚያው እንደሆነ ያስታውሰናል (1 ጢሞ. 6፡7). «የእኛ ነው» ብለን ባለቤትነት እንዲሰማን ያደረገ ነገር ሁሉ በሂደት ስንሞት ከኋላችን ጥለነው የምንሄድ ይሆናል፡፡ እውነታው ታዲያ፣ «ያልተቀበልከውስ ምን አለህ?» ተብሎ እንደተጻፈ፣ ያሉን ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔር ያበደረንና በኃላፊነት የምንጠቀምባቸው ነገሮች መሆናቸው ነው፡፡

ስለ ፉክክር ጤናማ አስተሳሰብ ሲኖረን ችሎታዎቻችንን የበለጠ ለመጠቀም እድላችን አናሳልፍም፡፡ ይህንን እንዴት ማድረግ እንደምንችል ነህምያ ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል፡፡ ይህ ታላቅ መሪ በፋርስ ቁልፍ ስልጣን የነበረው ሲሆን፣ በቀጥታ ለንጉሡ ነበር የሚሰራው፡፡ በዚህ ጊዜ ታዲያ የኢየሩሌም ቅጥሮች እንደገና መገንባት እንደሚያስፈልጋቸው ዜናው ደረሰው፡፡ (ነህምያ 1) እርሱም ይህንን ከባድ ተግባር

ለመፈፀም ሌላ ሰውን ቁጭ ብሎ ከመጠበቅ ይልቅ፣ ካለው ከፍተኛ ስልጣን የተነሳ፣ ይህንን አላማ ለማሳካት ከሚያስፈልጉት ነገሮች ሊያገኝ የሚችላቸውን ሀብቶች ሁሉ አሰባሰበ፡፡

ታዲያ የፉክክርን መንፈስ ለማሳደግ የሚፈጥረውን እድል በመጠቀምና እንደዚሁም ሌሎችን በተሻለ ሁኔታ ለማገልገል ያላችሁን ችሎታ ለማዳበር እንዲጠቀማችሁ በማድረግ ማስተናገድ ችላችኋል? በገጠሪቱ ፖትስታውን፣ ፔንሳልቫኒያ፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቴ በቆየሁባቸው የመጨረሻዎቹ ሁለት አመታት ውስጥ፣ ሰባኪ ለመሆን ከልቤ እፈልግ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ገና ለጋ ወጣት ስለነበርሁ ብዙ የመስበኪያ እድል አልነበረኝም፤ ነገር ግን አማራጮች ነበሩ፡፡ ቀኑን ሙሉ ጥቅጥቅ ያለ ደን ባለበት ጫካ ውስጥ ገብቼ ብቻዬን መቆየት እችል ነበር፡፡ ከዚያም ዛፎቹን እንደ ጉባዔ አድርጌ በመቁጠር ገና ጨቅላ ስብከቶቼን አሳድጋቸው ነበር፡፡ ኮሌጅ ገብቼ የአሰባበክን ሳይንስ ስማር፣ ለእነዚያ ዛፎች በመስበክ የማጠፋቸው እነዚያ ሰአታት መሆን የምችለውን ምርጥ ሰባኪ ለመሆን እንድጥር መነሻ ሆኑልኝ፡፡ እድሎችን በመጠቀም ችሎታዎቻችሁን በአግባቡ ተጠቀሙባቸው፡፡

**ጥበብ የተሞላበት የድፍረት ውሳኔ ወስኑ**

ታለንቶቻችሁን በሙላት መጠቀም ብዙ ጊዜ ጥበብ የተሞላበትን የድፍረት ውሳኔ መወሰንን ይጠይቃል፡፡ አስቀድሜ በጥበብ የተሞላ የድፍረት ውሳኔን በማድረግና በሞኝነት የሚደረግ የድፍረት ውሳኔን በተመለከተ ያለውን ልዩነት ገልጬአለሁ (ምዕ. 10ን ይመልከቱ)፡፡ ፊተኛው ቀደም ካለ ልምድ በመነሳት የሚደረግና ሊገጥም ለሚችል ችግርም መወጣጫ ሊሆን የሚችል አማራጭ እቅድ ይዞ የሚንቀሳቀስ ነው፡፡ ዳዊት ከጎልያድ ጋር ሊጋጠም በወጣ ጊዜ ጥበብ የተሞላበት የድፍረት ውሳኔ መወሰን ነበረበት (1 ሳሙ. 17)፡፡ ከባላጋራው ጋር ሲነጻጸር ብዙ የጦር ልምምድ አልነበረውም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ቀደም ብለው በሕይወቱ በተከሰቱ ትንቅንቆች ውስጥ ድልን ሰጥቶት ነበር፡፡ የአባቱን በጎች ሲጠብቅ ሳለ፣ አንበሳና ድብ በተለያየ ጊዜ እየመጡ ሊያጠቁት ሞክረዋል፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በእነዚህ የዱር አውሬዎች ላይ እንዲበረታ አድርጎት ነበር፡፡ የአገሩ ሰዎች የገጠማቸው ነገር ደግሞ እጅግ ከባድ ነበርና በቀላሉ ወደ ኋላ ለማፈግፈግና ለመመለስ ማሰብ ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን ባሳለፈው የሕይወት ዘመኑ እግዚአብሔር የሰጠው ባርኮቶች አሁንም ፈጽሞ እንደማይጥለው እርግጠኛ እንዲሆን አደረጉት፡፡

የአሜሪካ ኔቪ (የባሕር ኃይል) ቻፕሌን ለመሆን በወሰንኩበት ጊዜ፣ ምንም እንኳን ብዙ አርአያ የሆኑኝ ሰዎች በጽኑ ቢቃወሙም፣ በእግዚአብሔር ላይ ተመሳሳይ የሆነ መታመን ነበረኝ፡፡ የእነርሱን ምክር ላለመከተል በመወሰን ወደ ሚሊተሪ አገልግሎት ውስጥ ገባሁ፤ በመጀመሪያ ላይ የነበረኝ ውልም ለሦስት አመታት ብቻ ለማገልገል ነበር፡፡ ደግም በሚሊተሪ ውስጥ የሚኖረኝ አገልግሎት ፍሬያማ ባይሆን የቻፕሌንነቱን አገልግሎት በመተው ሌላ ልቀጥልበት የምችለውን ሙያ አዘጋጅቼ ነበር፡፡ እናም በድፍረት የወሰንኩት ውሳኔ ሦስቱን አመት በዚህ በሚለተሪ አገልግሎት ውስጥ ለመቆየት ነበር፡፡ በመጨረሻም፣ ይህ ባይሳካ ብዬ ያስቀመጥኩትን ሌላ አማራጭ እቅድ መጠቀም አላስፈለገኝም ነበር፡፡ የሚለተሪ አገልግሎትን እንደምወድ አስተዋልኩ፤

በዚህም ዘርፍ ከ25 አመታት በላይ ለመቆየት በቃሁ፡፡

ያንን በድፍረት የተሞላ ውሳኔ ለማድረግ ፈቃደኛ በመሆኔ እግዚአብሔር ባረከኝ፤ በዚህም በሚሊተሪ አገልግሎት ውስጥ መሪ ለመሆን በቃሁ፡፡ አደገኛ ነው ተብሎ በሚታሰበው እንዲህ ባለው አገልግሎት ውስጥ እንዳልሳተፍ በመጀመሪያ መከረውኝ የነበሩት ሰዎች፣ በሚሊተሪ ስራ ውስጥ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚጠቀምብኝ በማየት «እንኳን ደስ አለህ» ሊሉኝ ቻሉ፡፡ እንዲያው በዚህ ዙሪያ ምንም ነገር እንዳላደርግ መምከራቸውንም ሳይቀር የረሱት ይመስላሉ፡፡ ይሁን እንጂ ማንም ያልነካውን ውሃ በመንካት አገልግሎቴ ይህ ነው በማይባል መልኩ እንደተባረከ አይቻለሁ፡፡

***ግባችሁ ታማኝ መሆን ይሁን***

*ታማኝ ናችሁ ወይ? ታለንቶቻችሁን ለእግዚአብሔር ክብር መጠቀም ከፈለጋችሁ፣ ግባችሁ ታማኝ መሆን ይሁን፡፡* ዌብስተር መዝገበ ቃላት «ፌዝፉል» የተሰኘውን የእንግሊሊኛ ቃል ሲተረጉመው «ታማኝ መሆን፣ እምነት የሚጣልበት ሰው መሆን፣ በሚያደርገው ነገር ጥንቅቅ ያለን ሥራ የሚሰራ» ይለዋል፡፡ ባጭሩ ታማኝነታችሁ እግዚአብሔር በእናንተ ላይ ምን ያህል እንደሚደገፍ የሚለካበት ነው፡፡ ወላጅ ከሆናችሁ፣ አንዳንድ ልጆች ከሌሎች ይልቅ አደራ የሚጣልባቸው እንደሆኑ ታውቃላችሁ፡፡ አንደኛውን የመኪናችሁን ቁልፍ አምናችሁ ልትሰጡት የምትችሉ ሲሆን ለሌላው ግን እንዲህ አታደርጉም፡፡ አንዱ ከአምስት ጊዜ በሦስቱ ታማኝ ሆኖ ተገኝቶ ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም ከስድስቱ በአራቱ ጊዜ፡፡ በተመሳሳዩ ደግሞ፣ አንዳንድ የእግዚአብሔር ልጆች ከሌሎች ይልቅ ይበልጥ አመኔታ የሚጣልባቸው ሲሆኑ፣ እግዚአብሔርም ለትልቅ ሥራ በሃላፊነት ይሾማቸዋል፡፡ እናንተስ ምን ያህል የምታስተማምኑ ናችሁ? ታማኝነትን በተመለከተ፣ ሁላችንም በእኩል ነው የምንታየው፡፡ የጎደለን ችሎታ አለን ብለን የምናስበው ምንም ነገር በሕይወታችን ቢኖር፣ ታማኝነትን በተመለከተ እግዚአብሔር ያስቀመጠው መመዘኛ ግን በሁሉም ሰው ሊደረስ የሚችል ነው፡፡ ሁላችንም ታማኞች ሆነን መገኘት እንችላለን፡፡ አስተማማኝ መሆን ባሕርይን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው፤ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ዘንድ ትልቅ ግምት ያለው ከንዋኔያችሁ ሳይሆን ባሕርያችሁ ነውና፡፡ በሌላ አነጋገር ጽድቅ ትልቅ ስፍራ አለው ማለት ነው፡፡ ሉቃስ በወንጌሉ እግዚአብሔር እንዴት ዘካርያስንና ኤልሳቤጥን የመጥምቁ ዮሐንስ ወላጆች ይሆኑ ዘንድ እንደመረጣቸው ሲዘግብ፣ ጻድቅ ሰዎች ነበሩ በማለት ይጽፋል (ሉቃ. 1፡6)፡፡ ባሕርያቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ግምት የተሰጠውና ለፈለገው ተግባር ባደረገው ምርጫም ላይ ተጽእኖን እንዳሳደረበት እንመለከታለን፡፡

በአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን የነበረው የነገረ መለኮት ሊቅ ጆናታን ኤድዋርድስ ይህንን ያስተዋለ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም በወጣትነቱ የሚከተለውን የአቋም መግለጫ ጽፎ ነበርና፡- «እግዚአብሔር ለተለየ ሥራ በምድር ላይ አንድ ሰው ቢፈልግ አንተን ሊመርጥ በሚችልበት ህይወት ተመላለስ፡፡» ይህ አስደናቂ የሆነ ታማኝነት ነው፡፡

እንዲህ ያለው ባሕርይና ታማኝነት ያላቸው ሰዎች ማንም የሚመለከታቸው ሰው ሳይኖር እንኳ ሁልጊዜ እምነት የሚጣልባቸው ናቸው፡፡ ልጅ እያለሁ አንድ ሰው «እውነተኛ

ባሕርይ የሚታየው በጨለማ ውስጥ ማንም ሰው በማያይህ ጊዜ ነው» ብሎ ነግሮኝ ነበር፡፡ ይህ እውነት እንደሆነ አምናለሁ፡፡ በራችሁን ዘግታችሁ የምታደርጉት ነገር አለም ሁሉ እያያችሁ ከምታደርጉት እጅግ የተለየ ነው፡፡

**የተለያዩ የመሬት አይነቶችን ልመዱ**

በአዲሷ ሴናተር የተጠቀሰው ሁለተኛው ታሪክ፣ በማቴ. 13 ላይ የሚገኘው የዘሪው ምሳሌ ነው፡፡ ይህም ምሳሌ ከመከሊቶቹ ጋር የሚያመሳስለው መሪ ሐሳብ ያለ ሲሆን፣ ይኼውም፡- ተጠቀምበት አልያ ታጠዋለህ የሚል ነው፡፡ በዚህ በሁለተኛው ታሪክ ላይ፣ ገበሬው አራት የተለያዩ የዐፈር አይነቶች ላይ የወደቀን ዘር እንደዘራ ይናገራል፡፡ እነዚህም፣ የማያሰርግ፣ ጥልቀት የሌለው፣ የተጨናነቀና የተዘጋጀ ዐፈሮች ናቸው፡፡ ከመጀመሪያው ዐፈር ላይ ወፎች ዘሩን ለቀሙት፤ ጥልቀት ከሌለው ዐፈር ላይ ደግሞ ዘሩ ቶሎ ቢበቅልም ነገር ግን በዚያው ፍጥነት ደግሞ ደረቀ፡፡ ሦስተኛው የዐፈር አይነት ደግሞ መልካም ሰብል ሰጥቶ የነበረም ቢሆን ነገር ግን በእሾህ ታነቀ፡፡ የለሰለሰው ዐፈር ግን መልካም ሰብልን ያስገኘ ሲሆን «አንዳንዱ መቶ፣ ሌላው ስልሳ፣ ሌሎቹ ደግሞ ሰላሳ» አፈሩ (ማቴ. 13፡23)፡፡

ይህ ታሪክ ብዙ ጠቃሚ ትምህርቶች አሉት፡፡ የመጀመሪያው፣ ውድቀት ቋሚ ሁነት መሆን እንደሌለበት ይነግረናል፡፡ ታለንቶቻቸውን በአግባቡ የሚጠቀሙ ሁሉ ከሚዘሩት ከመቶ 75 እጁ መልካም መሬት ሊያጣ እንደሚችል ያስተውላሉ፤ ነገር ግን ትልቁ ነገር በመዝራት ታማኝ ሆኖ መቀጠል ነው፡፡ ሁለተኛ፣ ይህ ታሪክ የመጽናትን አስፈላጊነት ያስተምራል፡፡ ገበሬው ምርቱ የዘገየ በሚመስልበት ጊዜ እንኳን መዝራቱን ቀጠለ፡፡ ገበሬው ተስፋ በመቁረጥ መዝራቱን አቁሞ ቢሆን ኖሮ መልካም መሬት ባላገኘ ነበር፡፡ ሦስተኛ፣ ይህ ታሪክ የምናጭደው የዘራነውን ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ ጊዜ ከዚያ በላይ የምናጭድ መሆኑን ያስተምረናል፡፡ ምንም እንኳን ከተዘሩት ዘሮች አብዛኞቹ በመልካም መሬት ላይ ባያርፉም፣ መልካም መሬት ላይ የወደቁት ግን በግሩም ሁኔታ ነበር ፍሬ የሰጡት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፣ ይህ የመዝራትና የማጨድ ህግ ሊገታ የማይችል እስከ ዘመን መጨረሻ ድረስ የሚቀጥል እንደሆነ እግዚአብሔር ተናግሮአል (ዘፍ. 8፡22)፡፡ ታለንቶቻችንን በታማኝነት በምንጠቀምበት ጊዜ ምርት እንደምናገኝ ጥርጥር የለውም፡፡

ከተለያዩ የመሬት አይነቶች ጋር በምንጋፈጥበት ጊዜ መንፈሳዊ ሥሮቻችንን በጥልቀት መዘርጋትን ይጠይቃል፡፡ ይህንን በእሾህ መካከል ከወደቁት ዘሮች መመልከት እንችላለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እሾሆቹ «የዚህም ዓለም አሳብና በባለጠግነት መታለል» እንደሆኑ ይናገራል (ማቴ. 13፡ 22)፡፡ እነዚህ ችግሮች ዘሮቹን የሚያጠፏቸው፤ ሥር ስለሌላቸው ነው፡፡ መንፈሳዊ ሥሮችን ማሳደግ ታዲያ ምን ያህል አስፈላጊ ነው? ጎርፍ ስለገጠማቸው ሁለት ቤቶች በተናገረው ምሳሌ ላይ ኢየሱስ ይህ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ገልጾአል (ማቴ. 7፡ 24-27)፡፡ አንደኛው ቤት ፈረሰ፣ ሌላኛው ግን ጸንቶ ቆመ፡፡ ጸንቶ የቆመው ቤት የሚወክለው የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት፣ በማስተዋልና በመተግበር ጽኑ መሰረት ያላቸውን ሰዎች ነው፡፡ ታለንታቸውን ለእግዚአብሔር መጠቀም የሚፈልጉ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማትና በመታዘዝ የሚገኘው ጠንካራ መሠረት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ በሕይወት ለሚያጋጥሟቸው የተለያዩ የአፈር አይነቶች የተዘጋጁ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል፡፡ እግዚአብሔርን በሳምንቱ የመጨረሻ ቀናት ብቻ

በመፈለግ መንፈሳዊ ሥሮቻችሁን በጥልቀት ማሳደግ አትችሉም፡፡ የክርስቶስን ሕይወት የተመለከተ ሁሉ በነበረው የአምልኮ ሕይወት መደነቁ አይቀሬ ነው፡፡ እጅግ የላቀ መንፈሳዊ ብቃትን አሳይቶ ነበር፡፡ ሉቃ. 5፡ 16 እንደሚነግረን ኢየሱስ ብዙ ጊዜ በገለልተኛ ስፍራ ከአባቱ ጋር በጸሎት ለመገናኘት ጊዜ ያሳልፍ ነበረ፤ አንዳንድ ጊዜ ይህንን ያደርግ የነበረው በማለዳ ነበር (ማር. 1፡35)፡፡ ብዙ ጊዜ፣ ሌሊቱን በሙሉ በጸሎት ያሳልፍ ነበር (ሉቃ. 6፡ 12)፡፡ መንፈሳዊ ሥሮቹ ጥልቅና ጥብቅ ነበሩ፡፡ ይህም «ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ» እንዲያልፍ አደረገው (ዕብ. 12፡2)፡፡ እኛም የክርስቶስን ምሳሌነት በመከተል በመከራዎች እንድንጸና፣ በደስታ እንድንሞላ፣ እንደዚሁም ስቃዮቻችንን ሌሎችን ለመባረክ እንጠቀምባቸው ዘንድ መንፈሳዊ ሥሮቻችን በጥልቀት መዘርጋት አለባቸው፡፡

ሥራችንን በጥልቀት ለመስደድ ስንዘጋጅ፣ በሕይወት ውስጥ ልናደርግ የምንችለው ነገር ቢኖር ዘሩን መዝራትና ውሃ ማጠጣት ብቻ እንደሆነ ልናስታውስ ይገባል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ምንም እንኳን ሰዎች ቢተክሉና ውሃ ቢያጠጡም፣ ፍሬ እንዲያፈራ የሚያደርገው እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ይነግረናል (1 ቆሮ. 3፡6)፡፡ ታለንቶቻችንን በደንብ ስንጠቀምባቸው ዘሮችን እየዘራን ነው፤ እግዚአብሔር ደግሞ የዘራነውን ሊያሳጭደን ቃል ገብቷል፡፡ (ገላ. 6፡7-9) በመሆኑም መልካም በማድረግ እጃችን እንዳይዝል፣ «ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና » በማለት ይመክረናል (ገላ. 6፡9)፡፡

የአስራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን የብሪቲሽ ጠቅላይ ሚኒስተር ዊልያም ፒት በጓደኛቸው በዊልያም ዊልበርፎርስ ልብ ውስጥ የባሪያን ንግድ ማስወገድን በተመለከተ ዘሩን ዘርተውና አጠጥተው ነበር፡፡ ዘሮቹም በቀሉ፤ የብሪቲሽ ፓርላማ እንደ ህግ አድርጎ እስኪያጸድቅ ድረስ፣ ለሃያ አመታትም ዊልበርፎርስ የባርያን ንግድ በመቃወም ንግግር አደረጉ፡፡

እናንተስ ምን አይነት ዘር እየዘራችሁ ነው? እናቴ ወንድሜንና እህቶቼን እንደዚሁም እኔን የእግዚአብሔርን ቃል በቃላችን እንድንይዝ ታበረታታን ነበር፡፡ አመታት እያለፉ ሲሆኑ በእዚህ ዘሮች እንክብካቤን አገኘ ጀመረ፡፡ በዩ. ኤስ. ሴኔት ላይ መጽሐፍ ቅዱስን ካስተማርኩ በኋላ አንድ ሐሙስ ምሽት በዚያ ጥናት ላይ የጠቀስኩትን አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሳሰላስለው ራሴን አገኘሁት፡፡ እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አብዛኞቹን በቃሌ የያዝኳቸው ዘጠነኛ ክፍል ከመግባቴ በፊት እንደሆነ አስታወስኩ፡፡ እናቴ በታማኝነት ትዘራና ታጠጣ ከነበረው እርሻ እግዚአብሔር እንዴት ያለ ታላቅ ዘር ነው ያበቀለው! በሕይወት ውስጥ የተለያዩ የአፈር አይነቶች ሲያጋጥሙኝ እነርሱን ለመጋፈጥ እንድችል አድርጎኛል፡፡

**የተረፈውን አታባክኑ**

የመክሊቶቹና የዘሪው ምሳሌ ሦስተኛውን የወንጌል ታሪክ፣ ምናልባትም ከአንድ ሰፋ ያለ ታሪክ ላይ የተወሰደ መግለጫን ያስታውሰኛል፡፡ ይህም ኢየሱስ አምስት ሺጎ ሰዎች ከተመገቡ በኋላ የተረፈውን ይሰበሰቡ ዘንድ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ያደፋፈረበት ነው፡፡ እጅግ ብዙ ህዝብን ለመመገብ፣ አንድ ትንሽ ልጅ ለራሱ ምሳ ብሎ ይዞ የመጣውን እንጀራና አሳ ተአምራዊ በሆነ መንገድ ካባዛው በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፡

«አንድ ስንኳ እንዳይጠፋ የተረፈውን ቍርስራሽ አከማቹ።» (ዮሐ. 6፡12) እነርሱም አስራ ሁለት ቅርጫቶችን በቁርስራሽ ሞሉ፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የዚህን ታሪክ ክፍል ሳነብ እንቆቅልሽ ሆኖብኝ ነበር፡፡ ምግብን በተአምራዊ መንገድ ማባዛት የምትችሉበት ኃይል ካላችሁ፣ የተረፈውን ቁርስራሽ መሰብሰብ ለምን አስፈለገ? ደግሞስ ያደረ አሳና እንጀራ የሚፈልግ ማነው? ኢየሱስ እንዲህ ያለውን ከሰው በላይ የሆነ ኃይል ይዞ ብዙ ምግብ እንዲኖር ማድረግ አይችልም? ኢየሱስ ግን ከባርኮቱ አንድም እንዲባክን አልፈለገም፤ የመከራና የችግር ስጦታም ቢሆን እንዲባክን አይፈልግም፡፡

ጳውሎስና ሲላስ የስቃያቸውን ትርፍራፊ ሊያባክኑት አልፈለጉም፤ ይልቁንም ለእግዚአብሔር ክብር ተጠቀሙበት፡፡ ተደብድበውና ያለ አግባብ እስር ቤት ተወርውረው ሳለ፣ እኩለሌሊት ገደማ ሌሎች እስረኞች ሰምተው እስኪለወጡ ድረስ ለእግዚአብሔር የምስጋና መዝሙር ይዘምሩ ነበር፡፡ (የሐዋ. 16፡25) ይህ በእስረኞቹ ላይ የደረሰው ለውጥ እጅግ ጉልህ የነበረ ከመሆኑ የተነሣ፣ የመሬት መናወጡ ተከስቶ የእስር ቤቱን ደጆች በመከፋፈት እስረኞቹ ለማምለጥ እንዲችሉ ነገሮች በተመቻቹ ጊዜ እንኳን፣ እነርሱ ግን በዚያው በእስር ቤት ለመቆየት መርጠው ነበር (የሐዋ. 16፡ 28)፡፡ እናንተስ ሳትሰበስቧቸው የቀራችሁና ለእግዚአብሔርም ክብር ያልተጠቀመባችሁባቸው የበረከት ትርፍራፊዎች የትኞቹ ናቸው? ልትጠቀሙባቸው ይገባል፤ አልያ ግን ታጧችዋላችሁ፡፡

ምናልባት እያባከናችሁት ያለው ቁርስራሽ የበረከት ሳይሆን የጊዜ ሊሆን ይችላል፡፡አንድ ጊዜ አንድ ሰው ታዋቂ የሆኑትን ዳኛ ኦሊቨር ዌንዴል ሆልመስን የስኬታቸው ምስጢር ምን እንደሆነ ጠይቀአቸው ነበር፡፡ እርሳቸውም ሲመልሱ፡- «የጊዜያችሁን ቁርስራሽ መጠቀምን ተማሩ» ነበር ያሉት፡፡ ይህ እጅግ የከበረ ምክር ነው፡፡ ምን ያህሉ የጊዜያችን ቁርስራሽ ነው ሳንጠቀምበት እየባከነ ያለው? መኪና ውስጥ ሆነን የተለያዩ ነገሮችን ለማግኘት ሰልፍ እየጠበቅን የምናሳልፋቸው ጊዜያት አሉ፡፡ ታዲያ ልንጠቀምባቸው እንጂ ልናባክናቸው የማይገባን የጊዜ ቁርስራሾች እንዳሉ ማስታወስ አለብን፡፡ ከጥቂት ቀናት በፊት፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሳለሁ፣ ወዳጄ ወደነበረ ሰው ሄድኩ፤ እርሱም የጊዜን ቁርስራሽ በመጠቀም ረገድ እጅግ ጠቃሚ የሆነን ምክር ቸረኝ፡፡ በአንድ ኮንፍራንስ ላይ ንግግር አድርጌ እንደጨረስኩ፣ እርሱ ንግግሬን ወደ ፈረንሳይኛ ቋንቋ ይተረጉም ነበር፡፡ እንደዚሁም ጀርመንኛም ይችል ነበር፡፡ አስደሳች የሆነን የንግግር ልውውጥ አድርገን የነበረ ሲሆን፣ ከዚያም ቆይቼ ወደ ፈረንሳይ ሃገር ሄዶ እንደነበረ የፒኤች ዲ ዲግሪውንም እዚያው እንደጨረሰ አኒከስ ማንሊየስ ቦቲኑስ የተባለ የስድስተኛው ክፍለ ዘመን ፈላስፋንም በደንብ እንደሚያውቅ ተረዳሁ፡፡

‹‹ብዙ ቋንቋ አጥርቼ መናገር ብችል ምንኛ ደስ ባለኝ» አልኩት፡፡ ‹‹ታዲያ ምን ችግር አለው፣ ትችላለህ» አለኝ፡፡ « በየቀኑ ከ15 እስከ 20 ደቂቃ አዲስ ቋንቋ ለመማር ጊዜ እወስዳለሁ፡፡ በአመቱ መጨረሻ ይህችን ትንንሽ ጥረት ካደረግሁ በኋላ በቀላሉ በአዲስ ቋንቋ መናገር እጀምራለሁ፡፡» ይህ በእርግጥ አስገራሚ ነገር አይደለምን? የጊዜ ቁርስራሾቻችንን ሰብስበን በቋሚነት ብንጠቀምባቸው እጅግ ብዙ መኸር ይዞን መምጣቱ የሚገርም እውነታ ነው፡፡

የርህራኄ ቁርስራሾችስ? አምስት ሺህ ሰዎች በተመገቡበት በዚህ ታሪክ ውስጥ ያሉ

ሰዎች ኢየሱስ ምግብ ስጡአቸው ብሎ ባይናገር ኖሮ ባልተመገቡ ነበር፡፡ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ የሌላቸው ርህራኄ ነበረው፡፡ ህዝቡን ሳያበላ ለመልቀቅ ፈጽሞ አልፈለገም፡፡ ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አላቸው፡- «እነዚህ እንዲበሉ እንጀራ ከወዴት እንገዛለን?» (ዮሐ. 6፡5) የርህራኄያችንን ቁርስራሽ ለመጠቀም ባለመቻላችን ምክንያት ምን ያህል ሰዎች እየተጎዱ ይሆን?

ቴሌቭዥናችንን ከፍተን ስንለመለከት በሦስተኛው አለም ስለሚኖሩ የረሃብ ሰለባ የሆኑ ሕጻናት የሚቀርቡ ፕሮግራሞችን በተደጋጋሚ እናያለን፡፡ እንደነዚህ ላሉ ፕሮግራሞች ምንም ስሜት ሳይሰማን የርቀት መቆጣጠሪያውን (ሪሞት ኮንትሮሉን) አንስተን ወደ ሌላ ጣቢያ መቀየር ይቀለናል፡፡ በብዙ ትልልቅ ከተሞች ምግብና ገንዘብ የሚለምኑ አያሌ ሰዎች አሉ፡፡ እንደነዚህ አይነት ሰዎችን ደጋግመን ከመመልከታችን የተነሳ ባጠገባቸው ስናልፍ ምንም አይነት የርህራኄ ስሜት ሳይሰማን ልናልፍ እንችላለን፡፡ ነገር ግን ልክ እንደ ኢየሱስ ባጠገባችን ለሚገኙ በስቃይ ውስጥ ላሉ ሰዎች ርህራኄ ሊሰማን ይገባል፡፡ ይህ ማለት ግን እንዲሁ በጅልነት ልመናን ሙያቸው አድርገው ለተሰማሩ ሰዎች መለገስ ማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን በችግር ውስጥ ያሉ ሰዎችን ስቃይ በቋሚነት መጋራትና ጎዶሎአቸውን ለመሙላት የሚያስችል በፈጠራ የተሞላ ዘዴን መፈለግ ማለት ነው፡፡ በዚህ አለም ውስጥ ያሉ ብቸኛና ግራ የተጋቡ ሰዎች ወንድሞቻችንና እህቶቻችን መሆናቸውን አለመርሳትና አንድ ቀን እግዚአብሔር ከእነዚህ «ከታናናሾቹ» ለአንዱ ባደረግነው ወይም ባደረግነው ነገር እንደሚፈርድብን ማስታወስ ማለት ነው፡፡

**የእምነት፣ የመርካትንና የጸጋ ቁርስራሾችን ሰብስቡ**

እምነታችንንም ቢሆን ካልተጠቀምንበት እናጣዋለን፡፡ ያንን ሁሉ ሕዝብ ለመመገብ የትንሽ ልጅ እምነት ጠይቆ ነበር፡፡ ከዚያ ትንሽ ልጅ ምሳውን ሊወስድበት የሚችል ማንም አልነበረም፤ ልጁ ግን ፈቃደኛ ሆኖ ምሳውን ለኢየሱስ ሰጠ፡፡ ይህ ልጅ ያለ እርሱ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም የተባለለት እምነት ነበረው፡፡ (ዕብ. 11፡6) የእምነታችሁን ቁርስራሽ እየተጠቀማችሁበት ነውን?

ከብዙ አመታት በፊት፣ በአናፖሊስ (ሜሪላንድ) አምሳ የቤተክርስቲያን አባላት ባሉት አንድ ቤተክርስቲያን ተካፍዬ ነበር፡፡ ፓስተሩ የወንጌል ስብከት ጥረት እንዳደርግ ጠየቀኝና እኔም ተስማማሁ፡፡ ከቤተክርስቲያን ሽማግሌዎቹም ጋር ስብሰባዎቹን የት ልናደርግ እንደሚገባን መወያየት ጀመርን፡፡ ከሽማግሌዎቹም አንደኛው እንዲህ በማለት ያስደነቀንን ነገር ተናገረ፡፡ «ለምን የኔቪውን(የባሕር ኃይሉን) ስታዲየም አንከራይም?» እስከዛሬ ቤተክርስቲያኗ ጥሩ በተባለ የሳምንቱ መጨረሻ የአምልኮ ስብሰባ ላይ ትልቅ ቁጥር ተገኘ ቢባል ከ35 አይበልጡም ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ሰው በአስር ሺኅዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን የሚይዝ ስታዲየም እንድንከራይ ነበር ሃሳብ ያቀረበው፡፡ የሆነ ነገር ቀማምሶ ይሆን እንዴ? የሚያስብል ነበር፡፡ ሆኖም በጤነኛ አእምሮው እያሰበ ነበር፡፡ እኛ ልንገምት ከምንችለው በላይ ይህ ሰው እምነት ነበረው፡፡ ስታዲየሙን ከመከራየት ይልቅ፣ ስብሰባዎቹን በአንዲት ትንሽ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነበር ያደረግነው፤ እግዚአብሔርም የወንጌል ስብከት ጥረታችንን በአስር ነፍሳት ባረከልን፡፡ ነገር ግን በእምነት አንድ እርምጃ ወደፊት ሄደን ስታዲየሙን ተከራይተን ቢሆን ኖሮ «ምን አይነት

ፍሬ እናገኝ ይሆን ነበር?» ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ፡፡ የእምነታቸውን ቁርስራሽ ለሚሰበስቡና ለሚጠቀሙበት እግዚአብሔር ምን ሊያደርግ እንደሚችል በሙላት የሚያውቅ ማነው? እርሱ እኛ ከምንጠይቀውም ሆነ ከምንገምተው በላይ ሊያደርግልን የሚፈልግ አምላክ ነው (ኤፌ. 3፡20)፡፡ ነገር ግን እነዚህን በረከቶች ለማግኘት እምነት ሊኖረን ይገባል፡፡

እምነታችሁ ምን ይመስላል? እግዚአብሔር ወዳሰበላችሁ ጫፍ ለመዘርጋት ባለመቻላችሁ ከበረከታችሁ እየጎደላችሁ ይሆን? ባለመጠየቃችሁ ብቻ ከእግዚአብሔር ልትቀበሉት እየቻላችሁ የቀረባችሁ በረከት ስንት ይሆን? (ያዕ. 4፡2) ታዲያ የእምነታችሁን ቁርስራሽ በመሰብሰብ ብዙ በረከትን ለማግኘት ለምን ራሳችሁን አታመቻቹም?

የእምነታችሁን ብቻ ሳይሆን የእርካታችሁንም ቁርስራሽ ሰብስቡ፡፡ ኢየሱስ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን በመገበ ጊዜ እስኪጠግቡ ድረስ እንደበሉ ይነግረናል (ዮሐ. 6፡12)፡፡ ኢየሱስ እርካታንና መጥገብን ይሰጣል፤ ሕይወት እንዲትረፈረፍልን ወደ ምድር መጥቶአልና (ዮሐ. 10፡10)፡፡ ይህ የተትረፈረፈ ሕይወት እርካታን ማግኘትንና ቁርስራሾችንም ሰብስቦ ሌሎችን ለመባረክ መጠቀምን ያካተተ ነው፡፡

እናንተስ ምን ያህል በሕይወታችሁ የረካችሁ ናችሁ? ቅርብ ጊዜ እኔና ባለቤቴ ለተወሰነ ጊዜ ሄደንበት ወደማናውቅ ሆቴል ሄደን ቆይተን ነበር፡፡ በሦስቱም መኝታ ቤቶች ውስጥ የነበሩት ቴሌቭዥኖች ፍላት ስክሪን ሆነው ነበር፡፡ በእነዚያም ግዙፍ ስክሪኖች ላይ በጥሩ የቀለም ጥራት የሚታየውን በመመልከት ተደሰተን፡፡ ታዲያ ወደ ቤቴ ስመለስ የድሮ ሞዴል በሆነው የቤቴ ቴሌቭዥን መመልከት እምብዛም ሊያስደስተኝ አልቻለም፡፡ ባለኝ ነገር የረካሁ ልሆን አልቻልኩም፡፡ ለባለቤቴ «አዲስ ቴሌቭዥን ያስፈልገናል፤እቤት ውስጥ ያለው ያረጀ ነው፤ ፍላት ስክሪኑ በጣም የተሻለ ነው» አልኳት፡፡ ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በመክ. 4፡6 ላይ የተጻፈውን ጥበብ ረስቼ ነበር፡- «በድካምና ነፋስን በመከተል ከሁለት እጅ ሙሉ ይልቅ አንድ እጅ ሙሉ በዕረፍት ይሻላል።» ድንገት ያስፈልገኛል ብዬ ያሰብኩት አዲስ ቴሌቭዥን አያስፈልገኝም ነበር፡፡

አንድ ሴናተር የተናገረውን ንግግር ሳዳምጥ በእርግጥም ግለሰቡ መርካት ምን ማለት እንደሆነ አስተውሏል ብዬ አሰብኩ፡፡ መንግስት እንዴት ቅጥ የለሽ ወጪ እያወጣ እንደሆነ ሲናገር፣ « እኔ ና ሚስቴ የምንኖረው ከ1972 ጀምሮ አንድ ቤት ውስጥ ነው፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን ከምናገኘው ገንዘብ ባነሰ ወጪ ነው የኖርነው፡፡» በእርግጥም ይህ ሰው የረካና በአንድ እጅ መኖር እንጂ ወደ ሁለተኛው እጅ ማለፍን ያላሰበ ነው፡፡

ከእነዚያ የእምነትና የመርካት ቁርስራሾች በተጨማሪ የእግዚአብሔርንም ጸጋ ቁርስራሾች ወይ ልንጠቀምባቸው አልያም ልናጣቸው ግድ ነው፡፡ ጳውሎስ በሥጋው መካከል ከነበረው እሾህ ጋር በሚዋጋበት ጊዜ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎታል «ጸጋዬ ይበቃሃል፡፡» (2 ቆሮ. 12፡9) አምስት ሺኅ ሰዎቹ በልተው የጠገቡት በክርስቶስ ጸጋ ነበር፡፡ ሁላችንም ይህንን ጸጋ የተቀበልን ስንሆን ከሌሎችም ጋር ልንካፈለው ፈቃደኞች

ልንሆን ይገባል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ይህንን ሲያስታውሰን እንዲህ ይላል፡- ‹‹በነጻ የተቀበላችሁትን፣ በነጻ ስጡ፡፡›› (ማቴ. 10፡8) እኛ ባገኘነው መጽናናት ሌሎችን ማጽናናት የሚገባን አንደኛው ምክንያት የጸጋውን ቁርስራሽ የምንሰበስብበትና የምንጠቀምበት መንገድ ስለሆነ ነው፡፡ (2 ቆሮ. 1፡4)

ያ እንዲሞት የተፈረደበት ሌባ እነዚህን የጸጋ ቁርስራሾች የተቀበለ ሰው ነበር፡፡ አንድ አርብ እለት በመስቀል ላይ ሊሞት እያጣጣረ አብሮት የተሰቀለውን ከመካከል የነበረውን ሰው ተመለከተው፡፡ በአጠገቡ የነበረው ሰው የሚያልፍበትን የስቃይ ልምምድ በመመልከቱ ሌባው ሕይወቱ ተለወጠ፡፡ ከዚያም ጥቂት የጸጋ ቁርስራሽ ባገኝ ብሎ ጠየቀ፡- ‹‹ጌታ ሆይ በመንግስትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ፡፡›› (ሉቃ. 23፡ 42)

እናንተስ? የእግዚአብሔርን ጸጋ ተቀብላችኋል? ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣ ‹‹ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል?›› (ማር. 8፡ 36) የዘላለም ሕይወት ለማግኘት ማንኛውንም መስዋዕት መክፈል ተገቢ ነው፡፡ ደግሞም እግዚአብሔር የሰጣችሁን የጸጋውን ቁርስራሽ ብትሰበስቡ የእናንተ ይሆናል፡፡ ከዚያም በመከራችሁ ውስጥ በእርግጥም በረከትን ማየት ትላላችሁ፡፡

## ታለንታችሁን እንድትጠቀሙበት (እንዳታጡት) የሚረዷችሁ ወሳኝ እርምጃዎች

- ፋክክርን በጥበብ አስተናግዱ
- ጥበብ የተሞላበት የድፍረት ውሳኔ ወስኑ
- ግባችሁ ታማኝ መሆን ይሁን
- የተለያዩ የመሬት አይነቶችን ልመዱ
- የተረፈውን አታባክኑ
- የእምነት፣ የመርካትንና የጸጋ ቁርስራሾችን ሰብስቡ

# 14

# የሕይወታችሁን ካርታ ጠንቅቃችሁ እወቁ

ልጄ ከሰጠኝ የገና ስጦታዎች መካከል እጅግ ምርጥ የሆነው ግሎባል ፖዚሽኒንግ ሲስተም (ጂፒኤስ) የተባለው እቃ ነው፡፡ የስብከት ቀጠሮ ሲኖረኝ በማላውቃቸው ቦታዎችና መኪና በበዛባቸው መንገዶች በተሳካ ሁኔታ ከፈለግሁበት ቦታ ለመድረስ እንድችል የምትመራ ግሩም ቃና ያለት ሴት ድምጽን በውስጡ የያዘ እቃ ነው፡፡ ይህ እቃ ታዲያ ብዙ ደስታ ይዞልኝ መጥቶአል፤ ልክ አንድ ሰው አብሮኝ የሚነዳ ነው የሚመስለኝ፡፡ ከቤት እንኳን ርቄ ባለሁበት ስፍራ፣ በማሽኑ ውስጥ የሚሰማው ግሩም የሴት ድምጽ ከከፍተኛ ምንጭ ጋር እንደተገናኘሁ እንዲሰማኝ ያደርገኛል፡፡ አያችሁ፣ ጥሩ አቅጣጫ አመላካቾችን እንኳን ሳይቀር ለመከተል በጣም እቸገር ነበርና፣ ይህ አዲሱ የጉዞ ጓደኛዬ የሆነው መሳሪያ በመንገድ ላይ የማሳልፈውን የሕይወቴን ቆይታ እጅግ ቀላል አድርጎልኛል፡፡

አንድ ቀን ቴኔሲ እሰከምደርስ እንደዚህ ነበር የሚሰማኝ፡፡ ከአውሮፕላን ማረፊያው እስከ የማርፍበት ሆቴል የአምስት ደቂቃ መንገድ መሆኑን አውቅ ነበር፤ ነገር ግን መንገድ ከመጀመሬ በፊት ያቺን የምተማመንባትን መሳሪያ ከመኪናዬ ጋር ገጠምኳት፡፡ ይሁን እንጂ ለወትሮው የምታመንባት መሳሪያዬ አንድ መቶ ማይል ወደፊት ቀጥ ብዬ እንድሄድ ነገረችኝ፡፡ ‹‹አይ፣ አንድ የሆነ እንግዳ ነገር እየሆነ ነው›› ብዬ ለራሴ አንሾካሾኩ፡፡ ኋላ ላይ ጂፒኤስ ማሽኔ ያልጫንኩላት ወሳኝ የሆነ አንድ ካርታ እንደነበረ ተረዳሁ፡፡ከዚህም የተነሳ፣ በመሳሪያው ውስጥ ድምጿ የሚሰማው ሴት፣ የት መሄድ እንዳለብኝ ምንም ፍንጭ አልነበራትም፡፡ ከዚያም ለመዳረሻዬ የቀረኝ ጥቂት ደቂቃ መሆኑን ለማረጋገጥና አቅጣጫውን ለማወቅ ቆም ብዬ ሰዎችን ጠየቅሁ፡፡

ወደ ዘላለማዊ መዳረሻችን ለመድረስ ስንገሰግስ፣ በጉዞአችን የሚረዳን፣ የሕይወት ካርታ ያስፈልገናል፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ስለሚሰጠን ምሪት ልንታመንበት የምንችለውን መጽሐፍ ቅዱስን ሰጥቶናል፡፡ ይህ ግሩም መጽሐፍ ስለ ራሱ እንዲህ በማለት ይናገራል፡- ‹‹ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።›› (2 ጢሞ. 3፡ 16-17) ለምን? ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀን እንድንሆን ያስችለናልና፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ሕይወታችን መምሪያ ካርታ ልንታመነው እንችላለን፤ ምክንያቱም ለትምህርት ይጠቅማልና፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ትክክለኛው መንገድ የትኛው

እንደሆነ ያሳየናል፡፡ ትክክለኛውን ከተሳሳተው የመለየት ችሎታ የተሳካ ሕይወት ለመኖር ወሳኝ ነገር ነው፡፡ እግዚአብሔር ለሰለሞን የፈለገውን እንዲጠይቀው እድሉን በሰጠው ጊዜ (1 ነገ. 3)፣ ወጣቱ የጠየቀው ጥበብንና ትክክለኛውን ከተሳሳተው መለየት የሚችልበትን ችሎታ ነበር፡፡ ሕዝቡን በትክክል የሚመራበትን ችሎታ ይሰጠው ዘንድ ጠየቀ፤ እግዚአብሔርም ደስ አለው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የሞራል አቅማችንን ለማሳደግ ያስችለናል፡፡ ለትምህርት ይጠቅማል፡፡

መጽሐፍ ቅዱን እንደ ሕይወታችን መምሪያ ካርታ ልንታመነው እንችላለን፤ ምክንያቱም ትክክለኛ ያልሆነውን ነገር በማሳየት፣ ለተግሳጽም ይጠቅመናልና፡፡ አንዳንድ ጊዜ በአንድ ጉዳይ ላይ ስንሳሳት፣ በዚያ ጉዳይ ዙሪያ ቀጥተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ስለሌለ፣ በትክክል መሳሳታችንን እርግጠኞች አንሆንም፡፡ ለምሳሌ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሲጃራም ሆነ ማሪዋናን ስለማጨስ ምንም አይነት መመሪያ የለውም፡፡ ትክክል ያልሆነው ነገር ምን እንደሆነ በደንብ ተገልጾ ካልተቀመጠ፣ ደንገዝገዝ ያሉ ጉዳዮች ላይ አፍን ሞልቶ ለመናገር ይከብደን ይሆናል፡፡

ደግነቱ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ካርታችን ትእዛዛትን ብቻ ሳይሆን መርሆዎችንም የያዘ ነው፡፡ መርሆዎች ደግሞ ለምንጠራጠርባቸው የተለያዩ ሁኔታዎች ገጣሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሲጋራ ምንም አይግለጽ እንጂ፣ በ1ቆሮ 6፡12 በዚህ ሁኔታ ላይ ልንጠቀምበት የምንችለውን መርህ ይዞአል፡- «ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን አይጠቅምም። ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም።»

አሁን ምን ያህል ነገሩ እንደሚቀል መመልከት ትችላላችሁ፡፡ ራሳችንን ልንጠይቀው የሚገባን ቀላል ጥያቄ «ሲጃራ ጠቃሚ ነው ወይ?» ይህ ቀላል ጥያቄ ነው፡፡ በእያንዳንዱ የሲጃራ ፓኬት ላይ «ሲጃራ ማጨስ ለጤና ጎጂ ነው» ተብሎ ተለጥፎበታል፡፡ ያንን የጤና ባለሙያውን ምክር ከተቀበላችሁ፣ ማጨስ በእርግጥም ጠቃሚ አይደለም፡፡ ያም ብቻ ሳይሆን፣ የኒኮቲኖች ሱስ የማስያዝ ችሎታ በደንብ የተዘገበ ነው፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስለተጻፉትና ለሕይወት መመሪያን ስለሚሰጡን ትእዛዛትና መርሆዎች እግዚአብሔር ይመስገን፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን ልንተማመንበት የሚገባን ሌላው ሦስተኛ ምክንያት ልብን ለማቅናት የሚጠቅም በመሆኑ ነው፡፡ በሌላ አነጋር፣ ምን ማድረግ እንዳለብንና እንደሌለብን የሚነግረን ብቻ ሳይሆን፣ በትክክለኛው ኑሮ ውስጥ እንድንገባ ግልጽ የሆኑ ደረጃዎችን በማሳየት ያቀናናል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ልጆቻችንን የግብረገብን መርሆዎች ልናስተምራቸው እንደሚገባ ይናገራል፤ ነገር ግን ይህንን ደግሞ እንዴት እንደምናደርግ ያሳየናል፡- «እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው፥ በቤትህም ስትቀመጥ፥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሣም ተጫወተው።» (ዘዳ. 6፡ 6-7)

የሕይወታችን ካርታ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠን አራተኛው ጥቅም ደግሞ

በጽድቅ መምከር ነው፡፡ ይህ ምክር ወይም ስልጠና የጀመርነውን ለመጨረስ የሚረዳን ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚደሰተው በመልካም አጀማመር ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን በተሳካ ሁኔታ ከግብ በማድረስም ነው፡፡ ዕብ. 12፡2 ኢየሱስን የእምነታችን ጀማሪና ፈፃሚ ይለዋል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስን መመሪያዎችና መርሆዎች በመከተል፣ የህይወትን ሩጫ በተሳካ ሁኔታ ለመሮጥ ራሳችንን እናዘጋጃለን፡፡ እነዚህን አራቱን የእግዚአብሔር ቃል ጥቅሞች የተቀበሉ ሁሉ ለበጎ ሥራ የተዘጋጁ ይሆናሉ፡፡

**በየዕለቱ መንፈሳዊ ምግብ ተቀበሉ**

የሕይወታችሁን ካርታ ምን ያህል ደጋግማችሁ ታጠኑታላችሁ? ማቴ. 6፡11 ለዕለት እንጀራችን እንድንጸልይ ያስተምረናል፡፡ ይህ ልመና ለአካላዊ ምግብ ብቻ የቀረበ ሳይሆን ለመንፈሳዊ ምግብም ጭምር ነው፡፡ በቂ የሆነ መንፈሳዊ ምግብ ለማግኘት በየቀኑ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ያስፈልገናል፡፡

በሙዚቃ ክህሎት የተካነች አንዲት ወዳጅ አለችኝ፡፡ ልጆቿም የእርሷን ፈለግ በመከተል በሙዚቃ ጥበብ ልቀው ሄደዋል፡፡ ለስኬታቸው ምክንያት ከሆኑት ነገሮች መካከል አንደኛው እናታቸው ልጆቹ እንዲለማመዱ፣ አሁንም እንዲለማመዱ፣ የበለጠ እንዲለማመዱ ግድ ማለቷ ነበር፡፡ «ልጆችሽን እንዲህ ወጥ በሆነ መንገድ እንዲለማመዱ ያስቻልሻቸው እንዴት ነው?» ብዬ ጠይቄአት ነበር፡፡

እርሷም ፈገግ ብላ፣ « ምግብ የበላችሁ ቀን ሁሉ ልምምድ ማድረግ አለባችሁ ብዬ እነግራቸዋለሁ፤ ደግሞም ይህ ሰርቶልኛል፡፡»

ይህ ምክር ለመንፈሳዊ እድገታችንም ጠቃሚ ነው፡፡ ለአካላችን ምግብ በበላንበት ቀን ሁሉ፣ መንፈሳዊ ምግብም ልንመገብ ይገባናል፡፡ ነገር ግን ስንመገብ ሳለ እንዴት ነው የተለያዩ ነገሮችን ማግኘት የምንችለው? በየቀኑ ተመሳሳይ ነገር ቁርስ ላይ ብንመገብ በቶሎ እንሰለቻለን፡፡ አስገራሚ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል የምንመገብበትን የተለያዩ መንገዶች መፈለግ እንችላለን፡፡ በሲዲ ወይም ተንቀሳቃሽ በሆኑ ማዳመጫዎች ልንሰማው እንችላለን፡፡ ከማንበብ ብቻ ደግሞ አልፈን ልናጠናው እንችላለን፡፡ ጥናት ስንል በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ጠልቀን በመግባት ማጥናት፣ ቁልፍ ሃሳቦችንና ነጥቦችን ማስመር፣ እንደዚሁም ያገኘነውን ሃሳብ በመጽሐፋችን ሕዳግ ላይ መጻፍ ማለት ነው፡፡

በማላውቀው ሰው የቀብር ስነ-ስርአት ላይ እንድሰብክ በምጠየቅበት ጊዜ ፣ የግለሰቡን የግል መጽሐፍ ቅዱስ እንዲያሳዩኝ እጠይቃለሁ፡፡ ብታምኑም ባታምኑም፣ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ የተጻፈውን በመመልከት ብቻ ሰውየው ማን እንደሆነ አውቃለሁ፡፡ ይህ ደግሞ በቀብር ስነሥርአቱ ላይ በማደርገው ንግግር ሰውየውን የማውቀው ያህል እንዲሰማኝ ያደርገኛል፡፡ ብዙዎችም ያቀረብኩት መልእክት ሰውየውን በደንብ እንደማውቀው የሚያሳይ እንደሆነ ይነግሩኛል፤ ነገር ግን ግለሰቡን ያወቀውሁት መጽሐፍ ቅዱሱን አንስቼ በመመልከት ብቻ እንደሆነ አያውቁም፡፡

የእግዚአብሔርን ቃል ልንሰማ፣ ልናነበው እንደዚሁም ልናጠናው እችላለን፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስም ጥቅሶችን በቃላችን መያዝ እንችላለን (መዝ. 119፡11)፡፡ ቆላ. 3፡16 የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ ይለናል፡፡ ይህንን የምናደርገው ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል በቃላችን ስንይዝ ነው፡፡ ያን ጊዜ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል በቃላችን ከመያዝ አልፈን ወደ ማሰላሰል እንሻገራለን፡፡ የምናሰላስለው ደግሞ ከቃሉ የምናውቀውን ነገር በአምሮአችን በማመላለስ በአእምሮአችን ያሉትን መመሪያዎችና መርሆዎች በማውጣትና በማውረድ ይሆናል፡፡ መዝ. 1፡1-2 የተባረኩ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በቀንና በሌሊት እንደሚያሰላስሉት ይናገራል፡፡ ቃሉን በመስማት፣ በማንበብ፣ በማጥናት፣ በቃል በመያዝና በማሰላሰል በየቀኑ ለምንበላው መንፈሳዊ ማዕድ የተለያዩ ነገሮችን ማቅረብ እንችላለን፡፡

**በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ መንፈሳዊ መንጻትን አግኙ**

መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ሕይወታችን ካርታ ስንታመንበት የማንጻት ኃይሉን እናስተውላለን፡፡ እግዚአብሔር የተገለጠው ቃሉ የህዝቡንና የቤተክርስቲያኑን ሕይወት እንዲያጠራ መርጦአል፡፡ ዮሐ. 17፡17 እንዲህ ይላል፡- «በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው።» ቅድስናን የምንለማመደው ለቅዱሳት መጻሕፍት ራሳችንን ክፍት ስናደርግ ነው፡፡ ኤፌ. 5፡25-27 ይህንን ነጥብ በማጥበቅ እንዲህ ይላል፡- «ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ።»

ይህ ግሩም አይደለምን? እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን የሚያነጻት በቃሉ ኃይል ነው፡፡ ምናልባት ብዙ ቤተክርስቲያናት ጉድለት ያለባቸው የሚመስሉበት አንደኛው ምክንያት አባላት በመንጻት ሂደት ላይ ከመሆናቸው የተነሳ ነው፡፡ ማቴ. 13፡30 እስከ መከር ጊዜ ስንዴውና እንክርዳዱ አብረው እንደሚያድጉ ይናገራል፡፡ በሌላ አነጋገር በፍጹም ሰዎች የተሞላች ቤተክርስቲያን እናገኛለን ብላችሁ አትጠባበቁ፡፡ በእግዚአብሔር የማንጻት ሂደት ታመኑ፡፡

አንድ ሰው ታላቁን የብሪቴናዊ ሰባኪ ቻርለስ ስፐርጅንን ቀረብ ብሎ እንዲህ አለው፡- «ፍጹም የሆነችውን ቤተክርስቲያን ማግኘት እንድችል ልትረዳኝ ትችላለህ? ሚስተር ስፐርጀን፣ ያንተ ቤተክርስቲያን ያ ፍጹም የሆነው ቤተክርስቲያን ነውን? «አይደለም» አለ ስፐርጀን ሲመልስ፡፡ «የእኔ ቤተክስቲያን ፍጹም ቤተክርስቲያን ከመሆን በጣም የራቀ ነው፡፡ ነገር ግን ፍጹም የሆነውን ቤተክርስቲያን ስታገኝ እባክህን ያንን ቤተክርስቲያን እንዳትቀላቀል፤ ምክንያቱም አንተ በተቀላቀልክ ጊዜ ፍጹም መሆኑ ያከትማልና፡፡» እውነታው ቤተክርስቲያን ተሰርተው ያለቁ ቅዱሳን ለእይታ የቀረቡባት የአርት ጋለሪ አይደለችም፤ ይልቁንም በሕይወት ጎዳና የቆሰሉና የተቀጠቀጡ ፈውስን የሚያገኙባት ሆስፒታል ናት፡፡ እግዚአብሔር ይህንን ፈውስ ከሚሰጥባቸው ዋንኛ መንገዶች መካከል አንደኛው ደግሞ በቃሉ ኃይል በኩል ነው፡፡

የእግዚአብሔርን ቃል የማንጻት ኃይል ምን ያህል በደስታ ትለማመዱታላችሁ?

ቅዱሳት መጻሕፍት የመቀደስ ኃይል እንዳላቸው ማወቃችሁ ውስጣችሁን በድፍረት ይሞላዋል? የሚሞላው ከሆነ፣ እንደ ቤርያ ሰዎች ሁኑ፡፡ ጳውሎስ ሲሰብክ ይሰሙና ኋላ ግን ሐዋርያው የተናገራቸው ነገሮች ምን ያህል ከቅዱሳት መጻሕፍት አኳያ በትክክል መነገራቸውን ለማወቅ ይመረምሩ ነበር (የሐዋ. 17፡11)፡፡

**የኃፍረት ስቃይን አስወግዱ**

የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ሕይወታችን ካርታ ስንታመንበት ከሚያስገኝልን ታላላቅ በረከቶች መካከል አንደኛው የኃፍረትን ስቃይ እንድናስወግድ መርዳቱ ነው፡፡ መዝሙረኛው እንዲህ በማለት ያውጃል፡- ‹‹ሥርዓትህን ለመጠበቅ መንገዶቼ ይቀኑ ዘንድ እወድድ ነበር። ትእዛዝህን ሁሉ ስመለከት በዚያን ጊዜ አላፍርም።›› (መዝ. 119፡ 5-6)

የኃፍረትን ስቃይ የተጋፈጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ ባለታሪኮች አስቡ፡፡ ኖህ በስካር ምክንያት ርቃኑን በወደቀ ጊዜ የኃፍረትን ስቃይ ቀመሰ፡፡ (ዘፍ. 9) አብርሃም ሚስቱን ሳራን እህቱ እንደሆነች በመዋሸት አስመሰለ (ዘፍ. 12)፡፡ ሙሴ የግድያ ወንጀል ከፈጸመ በኋላ ከአገሩ ለመኮብለል ተገዶ ነበር(ዘጸ. 2)፡፡ ዳዊት ደግሞ የምንዝርና የነፍስ ግድያ እጽፍ በደል ነበረበት(2 ሳሙ. 11)፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ጀግና ብሎ የሚያቀርባቸውን ሰዎች ከላይ ቀባብቶ ብቻ የሚያሳየን ሳይሆን፣ ነገር ግን ጉድለትና ድክመታቸውንም ጭምር በግልጽ የሚያስቀምጥ ነው፡፡

እኛም በራሳችን ሕብረተሰብ ውስጥ ብዙ የፖለቲካና የኃይማኖት መሪዎች የስነ-ምግባር መደናቀፍ ገጥሞአቸው ሲያፍሩ አይተናል፡፡ ኃፍረትን የተከናነበ መሪ፣ ሚስቱ ባጠገቡ ምቾት አጥታ ቆማ፣ በሚዲያዎች ካሜራ ጎልቶ ሲታይ የሚፈጥረውን ትእይንት ሁላችን እናውቀዋለን፡፡ በእርግጥም እንዲህ የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊው ብሂል ምን ያህል እውነት ነው? ‹‹የወስላቶች መንገድ ግን ሸካራ ናት።›› (ምሳ. 13፡15)

የኃፍረትን ስቃይ ለማስወገድ እንድትችሉ በሚረዳችሁ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስን ልታነቡ የምትችሉት እንዴት ነው? በመጀመሪያ ለእናንተ ለማንበብ ቀላልና የሚስተዋልን ትርጉም ፈልጋችሁ አግኙ፡፡ ሁለተኛ፣ በምታነቡት ላይ ሙሉ ትኩረታችሁን አድርጉ፡፡ በጣም ወሳኝ ከሆነ ሰው ጋር ስትነጋገሩ፣ ሌሎች ሃሳባችሁን የሚከፍሉባችሁን ነገሮች ታስወግዳላችሁ፡፡ እስቲ አስቡት! አንድ የሃገር ፕሬዝዳንትን እያናገራችሁ አጭር የጹሁፍ መልክት በስልካችሁ ላይ ስትልኩ (ቴክስት ስታደርጉ)፡፡ ለእግዚአብሔርም ያልተከፋፈለ ትኩታችሁን በመስጠት አክብሩት፡፡ ሦስተኛ፣ በምታነቡበት ጊዜ እግዚአብሔር ምን እየተናገራችሁ እንደሆነ ለይታችሁ እወቁ፡፡ አራተኛ፣ ስለምታነቡት ነገር እግዚአብሔርን መልሳችሁ አናግሩት፡፡በሌላ አነጋገር በቅዱሳት መጻሕፍት ንባብ ተመስርታችሁ ጸልዩ፡፡ እነዚህ አራት ዘዴዎች የሕይወታችሁን ካርታ ጠንቅቃችሁ እንድታውቁና በዚህም የኃፍረትን ስቃይ ለማስወገድ እንድትችሉ ይረዷችኋል፡፡

**ፈተናን ተፋለሙ**

የሕይወታችሁን ካርታ መታመናችሁ ከፈተናና ከኃጢአት ጋር የምትፋለሙበትን መሳሪያ ያስታጥቃችኋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናት አስደናቂው በረከት ይኼ ነው፡- ‹‹አንተን

እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።» (መዝ. 119፡ 11) እናንተስ ይህንን የሕይወት ካርታ የታጠቃችሁና ለጠላት የምታስፈሩ እንድትሆኑ በሚረዳችሁ መልኩ እየተጠቀማችሁበት ነውን?

ኢየሱስ እንደዚህ አድርጎ ነበር፡፡ በምድረ በዳ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ(ማቴ. 4)፣ ራሱን ለመከላከል የተጠቀመበት መሰሪያ አንድ ብቻ ነበር፤ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡ አመክንዮ (ሎጂክ) ወይም ፍልስፍናን መጠቀም ይችል ነበር፤ ነገር ግን ለጠላቱ ደጋግሞ ያውጅ የነበረው «ተጽፎአል» በማለት ነበር፡፡ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲህ ትልቅ ስፍራ ሰጥቶት ከሰይጣን ጋር ባደረገው ፍልሚያ እንደብቸኛ መሳሪያ አድርጎ ከተጠቀመበት፣ እኛስ ተመሳሳዩን ልናደርግ አይገባንም?

በኤፌ. 6 ላይ መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ስለምንጠቀምባቸው መሳሪያዎች ይዘረዝራል፡፡ ሁሉም መሳሪያዎች እንዲህ ከሚለው ከአንዱ በስተቀር መከላከያ ናቸው፡- «የመንፈስ ሰይፍ የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡» (ኤፌ. 6፡17) ከገዥዎችና ከኃይላት ጋር በምናደርገው ፍልሚያ የእግዚአብሔር ቃል ለጠላት አደገኛ ተፋላሚዎች የሚያደርገን ኃይለኛ መሳሪያ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ጦር መሳሪያ አይታችሁት ታውቃላችሁ? በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ስትሳተፉ ለማጥቃት የሚያስችላችሁ መሳሪያ ነው፡፡ ኢየሱስ እንዳደረገው ሰይጣን ለሚያቀርባቸው ውሸቶቹ ሁሉ «ተጽፎአል...» እያላችሁ በመመለስ ከእናንተ ልታርቁት ትችላላችሁ፡፡

ለሃያ አመታት ንጉስ ሳኦል ዳዊትን ሊገድለው ፈልጎ አሳደደው፡፡ ዳዊት ከሚወዳቸው ቤተሰቦቹ ተገልሎ ሕይወቱን ለማትረፍ የሚቅበዘበዝ ሰው ነበር፡፡ ሁለት ጊዜ ንጉስ ሳኦልን ለመግደል እድል አግኝቶ ነበር፡፡ እንዲያውም ወታደሮቹ ንጉሡን እንዲገለው ገፋፍተው ነበር፡፡ ነገር ግን ዳዊት እንዲህ አለ፡- «በእግዚአብሔር የተቀባ ነውና እጄን በጌታዬ ላይ አልዘረጋም፡፡» (1 ሳሙ. 24፡ 10) ዳዊትም የእግዚአብሔር ቃል አካሄዱን እንዲመራው በመፍቀድ በሂደት ጠላቱን ሳኦልን አሸነፈው፡፡ ምናልባትም ይህንን ልምምዱን በማሰብ ሊሆን ይችላል እንዲህ ብሎ የጻፈው፡- «ለዘላለም ለእኔ ነውና ትእዛዝህ ከጠላቶቼ ይልቅ አስተዋይ አደረገኝ።» (መዝ. 119፡98)

በሚያስደንቅ ሁኔታ ዳዊት ጠላቱን ማሸነፉ ብቻ ሳይሆን ጠላቱንም መውደድ ችሎ ነበር፡፡ ኢየሱስ ኋላ ላይ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚያሳድዷችሁን ውደዱ በማለት የተናገረውን መርህ የሚታዘዝ ነበር (ማቴ. 5፡44)፡፡ ዳዊት ንጉስ ሳኦልን ይወደው እንደነበረ እንዴት ነው የምናውቀው? ሳኦል በሞተ ጊዜ፣ ዳዊት በእጅጉ አለቀሰ (2 ሳሙ. 1)፡፡ ከእርሱ ቀደም የነበሩትን ሰዎች በማስተናገድ ረገድ ዳዊት የሕይወቱ ካርታ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል ይመራ ነበር፡፡

**ራስን መግዛት ተለማመዱ**

በዚህ አስደናቂ የሆነ የሕይወት ካርታ ስትመሩ አስገራሚ የሆነ ራስን የመግዛት ችሎታ እንድትለማመዱ ያግዛችኋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ለከፋት ኃይል የምንሰጠው ግምት በጣም አናሳ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ከኃጢአት ልንከላከል የምንችልበት ታላቁ መከላከያ ምን ያህል

ኃይለኛ እደሆነ በማሰብ ሲሆን፣ ይህም ይበልጥ ጥንቁቆች እንድንሆን ያነቃናል፡፡ በዚህ ረገድ መዝሙረኛው እንዲህ ይላል፡- «ቃልህን እጠብቅ ዘንድ ከክፉ መንገድ ሁሉ እግሬን ከለከልሁ።» (መዝ. 119፡101) የክፋትን ጎዳና ማስወገድ እንደሚያስፈልገን የሚናገረውን ይህንን ጥቅስ እወደዋለሁ፡፡ ትክክለኛ ጥንቃቄ ማለት ከኃጢአት መዳረሻ መራቅ ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን ህግን ወደ መተላለፍ ሊመራ በሚችል ጎዳና ላይ አለመገኘት ማለት ነው፡፡ ዮሴፍ የጶጢፋራ ሚስት ልታርግ የፈለገችውን ክፋት በመጋፋት ረገድ ብቻ ሳይሆን ከእርሷ ጋር ብቻውን በአንድ ክፍል ውስጥ ላለመገኘት ያደርግ የነበረው ጥረት ይህንን ያሳያል (ዘፍ. 39፡10)፡፡

እግራችሁን ከክፋት መንገድ ሁሉ እስኪከለክል ድረስ የሕይወት ካርታችሁ ኃይል እንዳለው ታምናላችሁ? «ከክፉ መንገድ ሁሉ» በሚለው ጥቅስ ውስጥ «ሁሉ» የምትለዋ ቃል ወሳኝ ናት፡፡ ምክንያቱም ከፊል የሆነ መታዘዝ ካለመታዘዝ ጎራ እንደሚመደብ ያሳያልና፡፡ መንፈሳዊ እድገታችሁን የሚያደናቅፉ ነገሮችን ሁሉ አስወግዱ፡፡

### የሕይወታሁን ካርታ ጠንቅቃችሁ ለማወቅ የሚያግዟችሁ ወሳኝ እርምጃዎች

- በየዕለቱ መንፈሳዊ ምግብ ተቀበሉ
- በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ መንፈሳዊ መንጻትን አግኙ
- የኃፍረትን ስቃይ አስወግዱ
- ፈተናን ተፋለሙ
- ራስን መግዛት ተለማመዱ

# 15

# እርካታ ይኑራችሁ

ዘ ሮሊንግ ስቶንስ» የተባሉት ዝነኛ አቀንቃኞች «ምንም አይነት እርካታ ላገኝ አልቻልኩም።» በሚለው ሙዚቃቸው ይታወቃሉ። ነገር ግን ባለ ብዙ ሚሊዮን ሃብት ያላቸው የሮክ ሙዚቃ ኮከቦች እርካታን ሊጨበጥ የማይችል ቅዠት አድርገው ከተመለከቱት፣ ለእኛ ለተራዎቹ ሰዎች እርካታን የማግኘት እድሉ ምን ያህል የጠበበ ይሆን? ምናልባትም ሄነሪ ዴቪድ ቴሩው የሚከተለውን ሲናገር እውነታን እያንጸባረቀ ሳይሆን አይቀርም፡- «ብዙዎች ሕይወታቸውን እየመሩ ያሉ ጸጥ ባለ (ድምጽ በማያሰማ) ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆነው ነው።» ታዲያ እንዲህ ያለው ሕይወት የብዙዎች እጣ ፈንታ ሊሆን ይገባዋልን? ሕይወትን ያለ ደስታና እርካታ ልንኖራት ይገባልን?

ኢየሱስ የመጣው ለአለማችን እርካታን ለማምጣት ነው። እንዲህም ብሎ ተናግሮአል፡ «ሕይወት እንዲሆንላችሁ እንዲትረፈረፍላችሁም መጣሁ።» (ዮሐ. 10፡10) በመላው ሰብአዊ ዘር ታሪክ ውስጥ እንደ እርሱ በሰዎች ላይ ታላቅ ተጽእኖን ያሳደረ የለም። የእርሱም የልቡ ሃሳብ ሰዎች እርካታን ያገኙ ዘንድ ነው። በማቴ. 11፡ 28 ላይ የደከሙትንና ሸክም የከበደባቸውን ሁሉ ወደ እርሱ መጥተው እረፍት ያገኙ ዘንድ ይጋብዛቸዋል። በዮሐ. 4 ላይ ደግሞ በሰማርያውያን የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ያገኛትን ብዙ አግብታ የፈታችን ሴት ከሃዘን ወደ እርካታ ሲመራት እናያለን። ይህ አስደናቂ የሆነ ግንኙነት በሕይወታችን እርካታን ለማግኘት የሚረዱ ግሩም የሆኑ መርሆዎችን ይሰጠናል። መንፈሳዊ መቀደሳችንን ከአደጋ በመከላከል ረገድ የእርካታን ምስጢር ማወቅና የረካን ሕይወት መኖር ወሳኝ እርምጃዎች ናቸው። በዚያ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ከነበረችው ሴት እርካታን በተመለከተ የምንማራቸው ትምህርቶች ምንድን ናቸው?

### ለየት ካሉ ሰዎች ጋር ተገናኙ

አንዳንድ ጊዜ እርካታን የምናጣበት ምክንያት ለየት ያሉ ሰዎችን ለማግኘት ከመንገዳችን መውጣትን ችላ ስለምንል ነው። ምናልባትም ግንኙነት የምናደርገው በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ ወይም በዘር ከእኛ ጋር ተመሳሳይነት ካላቸው ሰዎች ጋር ብቻ ሊሆን ይችላል። ይህ ኢየሱስ ያልፈጸመው ስህተት ነበር። ከጉዞዎቹ በአንደኛው በሰማርያ መንገድ አድርጎ ሄደ። ይህ ደግሞ በእርሱ ዘመን የነበረ አንድ አይሁድ ፈጽሞ የማያደርገው ነገር ነበር። ኢየሱስ ግን ለሰማርያዋ ሴት ዘላለማዊ እርካታን ለማስገኘት የተከለከለውን መንገድ ተጓዘበት። ኋላ ለደቀ መዛሙርቱ የተሰማውን የግል እርካታ እንዲህ በማለት ነበር የነገራቸው፡- «እናንተ የማታውቁት የምበላው መብል ለእኔ አለኝ።» (ዮሐ. 4፡32) ከዚህች ሴት ጋር በነበረው ጊዜ ረሃቡን የሚያስረሳው ነገር አገኘ። ሴቲቱም ለነፍሷ እርካታ የሚሰጣትን ነገር ተቀበለች።

ከእኛ ለየት ባለ ሁኔታ ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር፣ በተለይም ከእኛ በባሰ ሁኔታ ላይ ከሚገኙ ሰዎች ጋር፣ አብረን ስንሆን በእጃችን ላይ ላለው ነገር የተሻለ ግምትና አድናቆት እንድናዳብር ይረዳናል፡፡ አንድ ሰው እንዲህ ብሎ እንደተናገረው፡- «እግር የሌለው ሰው እስካገኝ ድረስ ጫማ ስለሌለኝ አማርር ነበር፡፡» ስለ እርካታ መማር የሚፈልጉና በሕይወታቸውም እርካታን መለማመድ የሚሹ ሁሉ ከራሳቸው ቀጠና ወጥተው ከሌሎች ጋር መገናኘት አለባቸው፡፡ ሌሎችን መባረክ በጎ የሆነ ዘላለማዊ ውጤት ሊኖረው ይችላል፡፡

**እግዚአብሔር የመጀመሪያውን እርምጃ እንደሚራመድ ተጠባበቁ**

ከዮሐ. 4 የምንማረው ሁለተኛው ትምህርት እግዚአብሔር የመጀመሪያውን እርምጃ እንደሚራመድ መጠባበቅን ነው፡፡ ኢየሱስ በሌላ ስፍራ እንዲህ ብሎአል፣ «የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፡፡» (ዮሐ. 6፡44) ይህ አስደናቂ የሆነ አርፍተ ነገር እግዚአብሔር እኛን ለመሳብ የሚከታተለን አምላክ እንደሆነ ያስታውሰናል፡፡ ከእኛ በላይ ስለ እነርሱ ደህንነት እግዚአብሔር ይበልጥ እያሰበ እያለ በምንወዳቸው ሰዎች ላይ «ምን ይደርስባቸው ይሆን?» እያልን በመጨነቃችን ምን ያህል ሞኞች ነን፡፡ ለሰብአዊ ዘር ያለውን የራሱን አላማ መግለጽ የሚችልበት በሺህ የሚቆጠሩ መንገዶች አሉት፡፡ ሰማያት እንኳን የእርሱን ክብር ያውጃሉ (መዝ. 19፡1)፡፡

ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ከእርሱ ጋር ያላቸው ግንኙነት በእርሱ አነሳሽነት የተጀመረ እንደሆነ እንዲህ በማለት ነገራቸው፡- «እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም፡፡» (ዮሐ. 15፡ 16) በትክክልም፣ የእያንዳንዱን ደቀ መዝሙር መመረጥ አስመልክቶ እንዲህ ሊባል ይቻላል፡፡ በዚያ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ኢየሱስ ከሴቲቱ ጋር ለመነጋገር የመጀመሪያውን እርምጃ እርሱ ተራመደ፡፡ ከእኛም ጋር እንደዚያው ነው፡፡ ፍራንሲስ ቶምሶንን «የሰማይ ፍለጋ» በሚል ርዕስ እግዚአብሔር ሰብአዊ ዘርን እንዴት በትጋትና ተስፋ ባለመቁረጥ፣ ወደ ሚሄድበት ሁሉ በመድረስ እንዴት እንደሚከታተል እንዲጽፍ ያነሳሳው ይሄው እግዚአብሔር ወደ እኛ ለመቅረብ የመጀመሪያውን እርምጃ እርሱ የመውሰዱ እውነታ ነበር፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ድርጊት ደግሞ ደስ ወደሚያሰኝ መዳረሻ እኛን በመምራት እርካታ እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ (ኤር. 29፡11) እርካታን ለማግኘት ስትጠሙ፣ እግዚአብሔር ከሕይወታችሁ ትዕይንት በስተጀርባ እናንተን የሚጠቀም ስራ እየሰራ እንደሆነ አስተውሉ፡፡

**ለአንድነት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን አስወግዱ**

ወደ የረካ ሕይወት ለመድረስ በምናደርገው ጉዞ ልንማረው የምንችለው ሦስተኛ ትምህርት፡- ለአንድነት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ማስወገድ ነው፡፡ መዝ. 133፡1 እንዲህ ይላል፡- « ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ፥ እነሆ፥ መልካም ነው፥ እነሆም፥ ያማረ ነው።» የብዙ ልብ ስብራቶች መንስኤው የአንድነት አለመኖር ነው፡፡ እርካታን የሚፈልጉ ሁሉ ከሌሎች ጋር በአንድነት እንዳይኖሩ እንቅፋት የሚሆኑባቸውን ነገሮች በማስወገድ መልካምን ያደርጋሉ፡፡

አብርሃም እንዲህ ያሉ እንቅፋቶችን ከቤተሰቡ መካከል አስወግዶ ነበር፡፡ (ዘፍ. 13፡8) የአብርሃም እረኞች ከወንድሙ ልጅ ከሎጥ ሰራተኞች ጋር ባልተስማሙ ጊዜ አብርሃም አንድነታቸውን ጠብቆ የሚያቆይ መፍትሄ አቀረበ፡፡ ሎጥ በዚህ ጉዳይ የመጀመሪያውን እርምጃ መራመድ የነበረበት ቢሆንም እርሱ ግን አላደረገውም፡፡ ደግሞስ ሎጥ ከአብርሃም ብዙ መልካምነት ተቀብሎ አልነበረምን? «የታላቅ ሕዝብ አባት አደርግሃለሁ»

ተብሎ በእግዚአብሔር የተመረጠው አብርሃም ነበር፤ ኡርን ለቆ ወደ ከንዓን እንዲያመራ በእግዚአብሔር መንፈስ የተመራው አብርሃም ነበር፡፡ ሎጥ ግን እንዲሁ ተከትሎ የወጣ ነበር፤ ሃብትና ንብረት ለማፍራት የበቃውም ከአብርሃም ጋር ካደረገው ህብረት የተነሳ ነው፡፡ ስለ አጎቱ ሊሰማው የሚገባው የአመስጋኝነት ስሜት ይህንን ግጭት በመፍታት ረገድ የመጀመሪያውን እርምጃ እንዲራመድ ሊያደርገው በተገባ ነበር፡፡ ይልቁንም ከእርሱ በእድሜና በሃብት የሚበልጠው አብርሃም በህብረታቸው ላይ የተጋረጠውን እንቅፋት አስወገደ፡፡

ኢየሱስም በውሃው ጉድጓድ አጠገብ ከነበረችው ሰማርያዊት ሴት ጋር ያደረገው ተመሳሳዩን ነበር፡፡ ሴቲቱ ኢየሱስ መሲህ እንደሆነ ማመኗ በዘርና በታሪክ ልዩነት የተገነባውን የጥል ግድግዳ ለማፍረስ በሂደትም በከተማው ውስጥ ያሉት ሰዎች ሁሉ እርሱን እንደ አዳኛቸው አድርገው ለመቀበል እንዲችሉ ረዳቸው፡፡ በመጀመሪያ ሴቲቱ በዘር ልዩነት ላይ ያተኮረ ንግግር ባደረገች ጊዜ ክርስቶስ ከእርሷ አጀንዳ ጋር ለመራመድ አልፈለገም፡፡ ውሃ እንድታጠጣው ላቀረባለት ጥያቄ መልስ የሰጠችው እንዲህ በሚሉ ቃላት ነበር፡- «አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ? » (ዮሐ. 4፡9)፡፡ አይሁዶች ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና፡፡ ኢየሱስ ይህንን ግድድሮሽ የተጋፈጠው ሴቲቱን ለዘላለም ጥማቷን የሚያረካ የሕይወት ውሃን እንድትጠጣ በመጋበዝ ነበር፡፡ ኢየሱስ ሴቲቱን ትፈልግ የነበረውን፣ ነገር ግን ልታገኘው ያልቻለችውን እርካታ በመስጠት የአንድነት እንቅፋትን አስወገደ፡፡

**እርካታን ተጠባበቁ**

የታሪኩ አራተኛ ትምህርት እርካታን ልናገኝ እንችላለን ብለን መጠባበቅ እንዳለብን የሚያሳስበን ነው፡፡ ኢየሱስ ለሴቲቱ ስለ ሚየረካው፣ የሕይወት ውሃ ሲነግራት፣ ይህንን ውሃ ለመቀበል ውስጧ እንዲነሳሳ አደረገ፡፡ እንዲህም አላት፡- «የእግዚአብሔርን ስጦታና፣ ውኃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን መሆኑንስ ብታውቂ፥ አንቺ ትለምኚው ነበርሽ፤ የሕይወትም ውኃ ይሰጥሽ ነበር፡፡»(ዮሐ. 4፡10) እርካታን ከማግኘት የምንጎድለው ልንረካ እንደምንችል መጠባበቅ ሳንችል ስንቀርና የሕይወት ውሃን ለማግኘት የምናደርገውን ፍለጋ ስናቋርጥ ነው፡፡ ልንደርስ የምንችለውን ከፍታ በጣም ዝቅ አድርገን በመገደብ፣ ልናገኝ ከምንችለው መንፈሳዊ በረከት በጣም ጥቂቱን ብቻ እያገኘን እንኖራለን፡፡

እግዚአብሔር ይህንን የረካ ሕይወት እንዲሰጠን ባለመጠየቃችንም ልናገኝ የምንችለውን በረከት ሳናገኝ እንቀራለን (ያዕ. 4፡2)፡፡ ካለመጠየቅ ስለሚቀርብን ነገር እንዲህ በማለት አስጠንቅቆ ይነግረናል፡- «አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም» ለመጠየቅ የምንሰንፍበት ምክንያት ደግሞ ይሆንልናል ብለን ስለማንጠባበቅ ነው፡፡

እግዚአብሔርን የሚፈልጉ ሁሉ ግን እርካታን እንደሚያገኙ ሊጠባበቁ ይገባል፡፡ «ኮንፌሽንስ» በተባለው መጽሐፉ ቅዱስ ኦገስቲን ለእግዚአብሔር እንዲህ ብሎ አውጆአል፡- «አንተ ለራስህ ፈጥረኸናልና፤ ነፍሳችንም በአንተ ዘንድ እረፍትን እስከታገኝ ድረስ እረፍት የላትም፡፡» (Augustine, *Confessions,* trans. Henry Chadwick (New York: Oxford University Press, 1991), 3.) በአጭሩ፣ ኦገስቲን እያለ ያለው በልባችን ውስጥ ያለውን በእግዚአብሔር ቅርጽ የተሰራ ክፍተት መግጠም የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ምንም እንኳን ይህንን ክፍተት በምግብ፣ በዕጾች፣ ከሰብአዊ ፍጡራን ጋር በምናደርገው ግንኙነት፣ በገንዘብና በሃብት ልንሞላው ብንሞክርም፣

ከእነዚህ አንዳቸውም ሊሞሉት አይችሉም፡፡ እግዚአብሔር ብቻ ነው ሊያረካን የሚችለው፡፡ እኛም ይህንን ማድረግ የእርሱ ፈቃድ እንደሆነ አምነን መጠባበቅ አለብን፡፡

**የእግዚአብሔርን አቅም አሳንሳችሁ አትዩ**

አምስተኛው ትምህርት የእግዚአብሔርን አቅም አሳንሰን እንዳናይ የሚመክረን ነው፡፡ በውሃው ጉድጓድ አጠገብ የነበረችው ሴት ኢየሱስ ማድረግ የሚችለውን ለመገደብ ሞክራ ነበር፡፡ እንዲህ አለችው፡- «ጌታ ሆይ፥ መቅጃ የለህም ጉድጓዱም ጥልቅ ነው፤ እንግዲህ የሕይወት ውኃ ከወዴት ታገኛለህ?» (ዮሐ. 4፡11)፡፡ እናንተስ የእግዚአብሔርን አቅም ለመገደብ በመሞከር እርካታን አጥታችሁ ይሆን?

የእስራኤል ጠላቶች አንድ ጊዜ እንዲህ ያለውን ስህተት ሰርተው ነበር፡፡ የእግዚአብሔርን ህዝብ ተዋጉና በተራራማው የጦር አውድማ ላይ ድል ተመቱ፡፡ከዚያም እንዲህ ብለው ደመደሙ፡፡ «እኛ እየተሸነፍን ያለነው የእስራኤል አምላክ የተራራ አምላክ ስለሆነ ነው፡፡ ወደ ሸለቆ ብንወስዳቸው እናሸንፋቸዋለን» እግዚአብሔርም ለህዝቡ እንዲህ አለ፡- «ጠላቶቻችሁ የእኔን ኃይል ስላቃለሉ፣ በሸለቆም ውስጥ እረታቸዋለሁ፡፡» (1 ነገ. 20፡ 28)

እርካታን የሚያገኙ ሁሉ እግዚአብሔር የተራራ አምላክ ብቻ እንዳልሆነ የተረዱ ናቸው፡፡ በእርግጥም፣ በሕይወት ሸለቆዎች ውስጥ ስናልፍ ነው ይበልጥ እግዚአብሔር ወደ እኛ የሚቀርበውና ስቃያችንን ለሌሎች በረከት እንዲሆን የሚጠቀምበት፡፡ በተስፋ መቁረጥ፣ በመሪር ሃዘን፣ በበሽታና በስቃይ ሸለቆ ውስጥ ድል ያቀዳጀናል፡፡ በሕይወት ሸለቆ ውስጥ እግዚአብሔር የሰራውን ስራ ኢዮብ እንዲህ ብሎ ወደ መናገር መራው፡- «የምሄድበትን መንገድ ያውቃል፤ ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ።» (ኢዮ. 23፡10)

**ከቤት ጀምሩ**

ስድስተኛ ትምህርት፣ ከቤት ጀምሩ፡፡ ማነው በመሞቻ አልጋው ላይ እያጣጣረ፣ « ምነው ብዙ ጊዜዬን በቢሮዬ ውስጥ ቁጭ ብዬ አጥፍቼው ቢሆን ኖሮ?» ብሎ የሚል? ነገር ግን ብዙ ጊዜ የምንኖረው ከቤተሰባችን ይልቅ ሥራችን ትልቅ ዋጋ እንዳለው በማሰብ ነው፡፡ በውሃው ጉድጓድ አጠገብ ለነበረችው ሴት፣ ኢየሱስ እንዲህ አላት፣ «ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነዪ» (ዮሐ. 4፡ 16)፡፡ ኢየሱስ ለምን ይህችን ሳምራዊት ሴት ሄዳ ባሏን ይዛ እንድትመጣ እንደጠየቃት በእርግጠኝነት አላውቅም፡፡ ምናልባት ከዚህ ቀደም ያልተሳኩላትን አምስት የትዳር ሕይወት ሙከራዎች ስቃይ አስታውሳ አሁንም ቢሆን የምትኖረው ሕይወት ፍጻሜው ኪሳራ እንደሆነ እንድታስብ ፈልጎ ሊሆን ይችላል፡፡ የኢየሱስ መነሻ ሃሳቡ ምንም ይሁን ምን፣ ይህችን ሴት ለመለወጥ ስራውን የጀመረው የቤተሰብ ሕይወቷን በቅድሚያ በመዳሰስ ነበር፡፡

በሌላ ጊዜ ደግሞ ኢየሱስ ከአንድ ሰው ውስጥ አጋንንትን ሲያስወጣ ግለሰቡ ወዲያውኑ ከኢየሱስ ጋር አብሮ ለመሄድ ፈለገ፡፡ (ሉቃ. 8፡ 26-39) ለምን እንደዚህ እንደፈለገ ታስተውላላችሁ? እንደ እብድ ይታይ በነበረበት ስፍራ መቆየት አልፈለገም ነበር፡፡ ኢየሱስ ግን ጥያቄውን አላስተናገደለትም፡፡ ይልቁንም፣ ለግለሰቡ ወደ ቤቱ ተመልሶ ለቤተሰቦቹና ለጎረቤቶቹ ከመለኮታዊው ፈዋሽ ጋር ከመገናኘቱ የተነሳ የተለማመደውን የሕይወት ለውጥ እንዲመሰክርላቸው ነገረው፡፡

በሐዋ. 1:8 ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ መምጣት ተስፋ ሲነግራቸው እንዲህ አለ፡- «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።» መልካሙን ዜና በመጀመሪያ በኢየሩሳሌም እንዲያካፍሉ ሲነገራቸው ከቤተሰቦቻቸው ፣ ከዘመዶቻቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር በቅድሚያ እንዲካፈሉት እየተናገራቸው ነበር፡፡ እርካታን ያገኙ ሁሉ በአጠገባቸው ካሉት ጋር ይህንን ምስጢር መካፈልን መርሳት የለባቸውም፡፡

**እንዲታይ አድርጉት**

ኢየሱስ ከውሃው ጉድጓድ አጠገብ ከነበረችው ሴት ጋር ባደረገው ንግግር ላይ በመጨረሻ የተነሳው ርዕስ በአምልኮ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነበር፡፡ ጌታ ለሴቲቱ እንዲህ አላት፡- « እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።» (ዮሐ. 4፡24)፡፡ አምልኳችን የጥንቱን እውነተኛ ትምህርት የሚያንጸበርቅ ሆኖ፣ ግን መንፈሳዊ ግለት የጎደለው ሊሆን ይችላል፡፡

ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ግለት ያመልክ ነበር፡፡ በ2 ሳሙ. 6፡14 ላይ ነቀፋ በደረሰበት ጊዜ እንኳን ያንን ከምንም ሳይቆጥር ያለ ሃፍረት ያልተቆጠበ ምስጋንን በጌታ ፊት እያሸበሸበ አቀረበ፡፡ አንዳንድ ወዳጆቼ እንዲህ ይሉኛል፡- «ቤሪ፣ እኔ ሳመልክ ስከን ብዬ በአእምሮዬ ጠለቅ አድርጌ ማሰብ ነው የሚቀናኝ፡፡ ተፈጥሮዬ እንደዚያ ነው፡፡» ይሁን እንጂ እነዚሁ ወዳጆቼ ኃይማኖታዊ ባልሆኑ ስፍራዎች እንደ ኳስ ሜዳ ባሉ ቦታዎች ሲገኙ፣ ይህ ስክን ብሎ የማሰላሰል ተፈጥሮአቸው ይጠፋና የእነርሱ የማይመስል ግለት ሲያንጸባርቁ ይስተዋላሉ፡፡ ታዲያ በአምልኮ መንፈስ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ቤት ሲመጡስ ምን ያህል በግለት ሊሞሉ በተገባ ነበር? እግዚአብሔር ለእርሱ « እልል» እንድንል ይጠብቅብናል (መዝ. 100፡1)፡፡ ስለዚህም በመንፈስና በእውነት አምልኩ፡፡ በኢየሱስ ደስ ከተሰኛችሁ፣ በፊታችሁ እንዲታይ አድርጉት፡፡ ሮሊንግ ስቶንስ የተባሉት አቀንቃኞች «እርካታን ማግኘት አትችሉም» ብለው ሲያቀነቅኑ ተሳስተው ነበር፡፡ እርካታን ማግኘት ትችላላችሁ፤ ነገርግን እርካታውን የምታገኙበት ብቸኛው መንገድ ከእውነተኛው ምንጭ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፡፡

**እርካታን ለማግኘት የሚያግዟችሁ ወሳኝ እርምጃዎች**

- ለየት ካሉ ሰዎች ጋር ተገናኙ
- እግዚአብሔር የመጀመሪያውን እርምጃ እንደሚራመድ ተጠባበቁ
- ለአንድነት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን አስወግዱ
- እርካታን ተጠባበቁ
- የእግዚአብሔርን አቅም አሳንሳችሁ አትዩ
- ከቤት ጀምሩ
- እንዲታይ አድርጉት

# 16

# ራሳችሁን መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖች አስለምዱ

በቺጋጎ የሚኖሩ ጥቂት የቢሮ ሰራተኞች በሙያቸው የሚሮጡት አድካሚ ሩጫ ሰለቻቸውና ገበሬ ለመሆን ወሰኑ፡፡ የከተማን ሕይወት ወደ ኋላ ትተው ወደ ገጠር ገብተው የእርሻ መሬት ገዝተው ‹‹ከአሁን ጀምሮ ገበሬዎች ነን›› ብለው አወጁ፡፡ ከዚያም ሁሉም ነገር ምቹ መሰላቸው፡፡ በየቀኑ ወደ እርሻ ማሳቸው በመሄድ ገበሬ ስለመሆናቸው የልብ ልብ እየተሰማቸው ይመለሳሉ፡፡ ነገር ግን ምንም አላረሱም፤ ደግሞም አልዘሩም፡፡ ጥቅምት ደርሶ በጎረቤቶቻቸው ያሉ ገበሬዎች ምርታቸውን ሲሰበሰቡ ከቺካጎ የመጡት ገበሬዎች ግን የጫካ አበቦች የሞሉበት አርባ ኤከር መሬታቸውን ታቅፈው ቀሩ፡፡ ‹‹ለመሆኑ በቆሎው የታለ?›› ብለው ጠየቁ፡፡ ‹‹ምንድን ነው የሆነው?››

የሆነውማ እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን የስራ ዲሲፕሊን ሳያስተምሩ ምርት እንሰበስባለን ብለው የመጠባበቃቸው ስህተት ነበር፡፡

እንደዚሁም ሁሉ ብዙ ሰዎች መንፈሳዊ እድገት ያለምንም ጥረት ይመጣል ብለው ይጠባበቃሉ፡፡ ኢየሱስን እንደጌታቸው አድርገው ሲቀበሉ፣ ሕይወታቸው አስማታዊ በሆነ መንገድ ያለ መንፈሳዊ ማረስ መዝራትና ውሃ ማጠጣት (1 ቆሮ. 3፡6) ፍሬ የሚያፈራ ይመስላቸዋል፡፡ ነገር ግን መንፈሳዊ እድገት ሥራን የሚጠይቅ ሲሆን፣ መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን መማርንም ይጠይቃል፡፡

ለመሆኑ መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ምን ያህል በትጋት ትለማመዳላችሁ? ክርስቲያን ከሆናችሁበት ጊዜ ጀምሮ ለእግዚአብሔር ያላችሁ ፍቅር ምን ያህል እየጨመረ እንዳለ ይታያችኋል? ጊዜ እንዳለፈ መጠን፣ እግዚአብሔርን በይበልጥ ልትወዱት ይገባል፡፡

ከሠርጌ ቀን ማግስት ሚስቴን ከህይወት ከራሱ አስበልጬ እንደምወዳት አስብ ነበር፡፡ አሁን ግን ከ36 አመታት የትዳር ቆይታ በኋላ ለሚስቴ ያለኝ ፍቅር ምን ያህል እንደ ጠለቀና እንደጠበቀ ሳስብ፣ ድሮ ድሮ የነበረኝን ብስለት የጎደለው ስሜታዊ ብቻ የሆነ ፍቅር በማሰብ እስቃለሁ፡፡ በተመሳሳዩ በጸጋና እግዚአብሔርን በማወቅ ስናድግ (2 ጴጥ. 3፡18) የበለጠ እርሱን በጥልቀት ልንወደው ይገባል፡፡

መንፈሳዊ አቋማችን እየዳበረ ሲሄድ በፍቅር ማደግ የእርሱ ውጤት ሆኖ ይከሰታል፡፡ አካላዊ አቋማችንን የምናዳብረው የሰውነት እንቅስቃሴ በማድረግና ራሳችንን የተወሰኑ ዲሲፕሊኖችን በማስለመድ እንደሆነ ሁሉ፣ መንፈሳዊ አቋማችንንም ገጣሚ ለማድረግ ማድረግ ያለብን ነገሮች አሉ፡፡ ይህ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ከሚያካትታቸው ነገሮች

መካከል አንዱና ዋንኛው ደግሞ ራስን መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ማስለመድ ነው፡፡

ብዙ ክርስቲያኖች ልክ እንደ ኢየሱስ ለመኖር እንደሚፈልጉ ይናገራሉ፡፡ ይህ ፍላጎታቸው በጣም ጥልቅ ከመሆኑ የተነሳ አንዳንዶቹ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ኢየሱስ ቢሆን ምን ያደርግ እንደነበረ ለመገመት ይሞክራሉ፡፡ እንደ ኢየሱስ መኖር ማለት ግን እርሱ ያዘዛቸውን፣ እንደ «ጠላትህን ወደድ» ወይም «ሌላውን ጉንጭህን አዙርለት» ወይም «ለሚያሳድዷችሁ ጸልዩ» የሚሉትን ከመታዘዝ የበለጠ ነው፡፡ እንደ ኢየሱስ መኖር ማለት ኢየሱስ የሰራውን መስራት ማለት ነው፡፡ የእርሱ ሕይወት ደግሞ በንቃት እንደ መጠበቅ፣ መጸለይ፣ ማጥናት፣ ማሰላሰል፣ ዝምታ፣ አገልሎት፣ ጾም፣ የብቸኝነት ጊዜና አምልኮን የመሳሰሉ መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ራሱን ያስለመደበት ህይወት ነበር፡፡ እንግዲህ እነዚህንና ሌሎችንም መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖች በሕይወታችሁ ስትለማመዱ እናንተም ልክ እንደኢየሱስ በእውነት መኖር ትችላላችሁ፡፡ ለመሆኑ መንፈሳዊ ዲሲፕሊን የምንለው ምንድን ነው? ለክርስቲያኖች ማንኛውም ከክርስቶስና ከመንግስቱ ጋር ውጤታማ በሆነ ትስስር ውስጥ የሚጨምረንን ነገር ያመለክታል፡፡ ይህንን ግብ የሚመታ ነገር ሁሉ ለመንፈሳዊ ዲስፕሊን አበርክቶትን ያደርጋል፡፡

መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖች አስፈላጊ የሆኑት ለምንድን ነው? በመጀመሪያ ኢየሱስ ልናውቀውና ልንለማመደው የሚገባንን መንፈሳዊ ምሳሌ ትቶልን ስለሄደ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የእርሱን የእግር ዱካ በመከተል ኢየሱስ እንደኖረው እኛም መኖር እንዳለብን ይነግረናል (1 ጴጥ. 2፡21፤ 1 ዮሐ. 2፡6)፡፡ ለምሳሌ ክርስቶስ እንደዚያ ብዙ ጊዜውን በጸሎት እያሳለፈ (ሉቃ. 5፡16) ክርስቲያኖች እንዴት ስለጸሎት ሳይማሩ ሊቀሩ ይችላሉ? እርሱ ተከታዮቹ እንዲጾሙ እንደሚፈልግ በግልጽ አስቀምጦ ሳለ (ማቴ. 6፡16-18) ለምንድን ነው አንዳንዶች ለመጾም አሻፈረኝ የሚሉት? በምድር ላይ ከተመላለሱ ሰዎች ሁሉ እጅግ ንጹህ የሆነው ግለሰብ በጸሎትና በፆም መኖር ካስፈለገው፣ እኛ እነዚህን መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖች ቸል የምንልበት ምክንያታችን ምንድን ነው?

ሁለተኛ፣ ራሳችንን መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ማስለመድ ያለብን የተትረፈረፈ ህይወት እንድንኖር ስለሚረዱን ነው (ዮሐ. 10፡10)፡፡ ኢየሱስ ለተከታዮቹ ያለው ፍላጎት የተትረፈረፈ ሕይወት እንዲኖሩ እንደሆነ በግልጽ አስቀምጦ ሳለ ከዚህ ዝቅ ያለን ሕይወት በመኖር ለምን እንረካለን?

ሦስተኛ፣ ራሳችንን መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ማስለመድ ያለብን ወደ መንፈሳዊ ስኬትና ገጣሚ የሆነ አቋም ወደ መያዝ ስለሚመሩን ነው፡፡ በማር. 9 ላይ፣ የኢየሱስ ደቀ መዛሙት አጋንንትን ከአንድ ልጅ ለማስወጣት ስኬት አልቦ ሙከራ እያደረጉ ነበር፡፡ ከዚህ ውድቀት በኋላ ከኢየሱስ ጋር ለብቻቸው ለመሆን እድል ሲያገኙ፣ እንዲህ ብለው ጠየቁት፣ «ለምንድን ነው ይህንን አጋንንት ማስወጣት ለእኛ የከበደን?»

ኢየሱስም እንዲህ በማለት መለሰ፣ «ይህ ወገን በጸሎትና በጦም ካልሆነ በምንም ሊወጣ አይችልም» (ማር. 9፡29)፡፡ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱና ለእኛም ጭምር አንዳንድ መንፈሳዊ ውጊያዎች ከእምነት ያለፈን ነገር እንደሚጠይቁ ግልጽ አድርጎልናል፤ ራስን መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን በማስለመድ ረገድ ማደግ ያስፈልጋል፡፡ በ1 ጢሞ. 4፡ 7-8 ላይ ጳውሎስ ራስን መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ማስለመድ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ገጣሚ የሆነ አቋም ለመያዝ የሚያደርገውን አስተዋጽኦ ሲገልጽ እንዲህ ብሎአል፡- «እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ። ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ

ለጥቂት ይጠቅማልና፤ እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው፥ ለነገር ሁሉ ይጠቅማል።» ለምንድን ነው እንዲህ የተባለው? ምክንያቱም ለአካላችን የምናደርገው እንቅስቃሴ ለዚህኛው ሕይወት ብቻ ነው የሚጠቅመን፡፡ በዘላለም አለም ውስጥ፣ አዲስ አካል ነውና የሚሰጠን፡፡ መንፈሳዊው እንቅስቃሴ ግን ከዚህ በኋላ ላለው ሕይወትም ስለሚያዘጋጀን ትልቅ ዋጋ አለው፡፡

## እግዚአብሔርን ለማወቅ ያላችሁን ፍላጎት አሳድጉ

እግዚአብሔርን በተሻለ መንገድ ለማወቅ የምንዘጋጀው በምን መልኩ ነው? የመጀመሪያው ደረጃ ፍላጎትን ማሳደግ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት ለማድረግ እንደፈለገው እንደ ሙሴ ለመሆን መጣር አለባችሁ (ዘጸ. 33፡7-32)፡፡ እንደዚሁም «ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ፥ አቤቱ፥ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች። ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች መቼ እደርሳለሁ? የአምላክንስ ፊት መቼ አያለሁ?» (መዝ. 42፡ 1-2) ብሎ እንደጻፈው እንደ ዳዊት ለመሆን ፈልጉ፡፡ እግዚአብሔርን ለማወቅ ጠንካራ ፍላጎት ከሌላችሁ፣ ልትወርሷቸው ከምትችሉት መንፈሳዊ በረከቶች ትጎድላላችሁ፤ ወሳኝ የሆነ መንፈሳዊ ስኬት ለማግኘት የሚያስፈልጋችሁን ኃይል ማዳበር እንዳትችሉም በራሳችሁ ላይ እንቅፋት ታኖራላችሁ፡፡

የእውቀትን አስፈላጊነት የሚገልጽ አንድ ታሪክ ልንገራችሁ፡፡ በአሜሪካ ታላቅ የኢኮኖሚ ቀውስ ተከስቶ በነበረበት ወቅት የተፈጸመ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ በቴክሳስ የተበደረውን እዳ ለመክፈል የሚታገል አንድ በግ ሸላች ነበር፡፡ የቀረው ገንዘብ በጣም ጥቂት ከመሆኑ የተነሳ፣ የነበረው አማራጭ ድርጅቱን በኪሳራ ለመዝጋት ማመልከቻ ማስገባት ብቻ ይመስል ነበር፡፡ አንድ ቀን በእርሱ መሬት ላይ ነዳጅ መኖሩንና አለመኖሩን ለማረጋገጥ መሬቱን ለመቆፈር የፈለጉ ቡድኖች ወደ እርሱ መጡ፡፡እርሱም ፈቀደላቸው፤ ብዙም ሳይቆይ በእርሱ መሬት ውስጥ እጅግ የበለጸገ የነዳጅ ክምችት እንዳለ ተደረሰበት፤ እርሱም ለዚያ የነዳጅ ካምፓኒ እጅግ በከፍተኛ ዋጋ መሬቱን ለመሸጥ ቻለ፡፡ የዚህ መሬት ባለቤት የነበረው ሚስተር ያቴ ያንን መሬት ገዝቶ በነበረ ጊዜ እንዲህ የበለጸገ የነዳጅ ክምችት ባለቤት እንደሚያደርገው አላወቀም ነበር፡፡ በዚያ ስፍራ ነዳጅ እንዳለ እስከሚያውቅ ድረስ በታላቅ በረከት ውስጥ ግን በችጋር ይኖር ነበር፡፡ በተመሳሳዩም እግዚአብሔርን ማወቅ ወደ ተትረፈረፈ ሕይወት የሚያመሩ ባርኮቶችን ወደ ማግኘት ይመራናል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ብሎ ሲናገር የፈለገው ይህንን ነበር፡-«እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፥ በመከራውም እንድካፈል፥ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፥ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ።» (ፊሊ. 3፡10)

ነገሮችን በቅደም ተከተል በምታሰልፉበት ዝርዝራችሁ ላይ «እግዚአብሔርን ለማወቅ መፈለግ» ስንተኛ ደረጃ ላይ ነው? ጊዜያችሁን እንዴት እንደምታሳልፉ ስትገመግሙ፣ ለመንፈሳዊ ነገሮች የምትሰጡት ድርሻ ምን ያህል ነው? መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን መልመድ የሚሉጉ ሁሉ እግዚአብሔርን በጥልቀት ለማወቅ ጊዜ ሊመድቡ ይገባል፡፡

## ተስፋችሁን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ላይ አንጹ

ራስን መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ማስለመድ ጠንካራ መሠረት ይጠይቃል፡፡ መዝሙረኛው ልናገኝ የምንችለው ምርጥ የሆነ መሰረት የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ይገልጽልናል፡፡ እንዲህም ብሎ ጽፎአል፡- «አቤቱ፥ ስለ ስምህ ተስፋ አደረግሁህ ነፍሴ በሕግህ ታገሠች።» (መዝ. 130፡5)፡፡ ልክ እንደ መዝሙረኛው፣ ተስፋችንን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ልንመሰረት ይገባል፡፡ ንጉስ ሴዴቅያስ እንዲህ ማድረግን የተማረው በችግር ውስጥ

ተላልጦ ካለፈ በኋላ ነበር፡፡ ሴዴቅያስ ከባቢሎን ጋር ጦርነት በገጠመበት ጊዜ ሕዝቡን ለመጠበቅ ባደረገው ጥረት ከግብጽ ጋር ጥበብ የጎደለው ሕብረት ፈጥሮ ነበር፡፡ ይህንን ያደረገው በባቢሎን ሽንፈት እንደሚደርስበት በነብዩ ኤርሚያስ በኩል የመጣለትን የማስጠንቀቂያ መልእክት ችላ በማለት ነበር፡፡ እንዲያውም ንጉሡ ነብዩን ሃገርን የመከዳት ወንጀል እንደሰራ በመቁጠር ወደ እስር ቤት እንዲጣል አደረገ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሴዴቅያስ በእርግጥም የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያሸንፍ ያውቅ ነበርና፣ እንዲህ የሚል ጥያቄ ይዞ በስውር ወደ ኤርሚያስ ሄደ፡- «በውኑ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ ቃል አለን?» (ኤር. 37፡ 17)፡፡ ነብዩም እግዚአብሔር ሃሳቡን አልቀየረምና ከዚህ በፊት ያሰማውን ለጆሮ የማይጣፍጥ ማስጠንቀቂያ ደገመለት፤ የኤርሚያስም ትንቢት ተፈጸመ፡፡

ማምፊስ በተባለ ቦታ ከጥቂት አመታት በፊት በወንጌል ስርጭት ስብሰባ ላይ እሰራ ነበር፡፡ በዚህ ስብሰባ ላይ ቁልፍ የሆነውን ሚና የሚጫወቱት ሰራተኞች የመጽሐፍ ቅዱስ ሰራተኞች በመባል ይታወቃሉ፡፡ እነርሱም በስብሰባው ላይ የሚካፈሉ ሰዎችን በግል የሚጎበኙና ፍላጎቱ ላላቸውም የእግዚአብሔርን ቃል ጨምረው የሚያብራሩ ናቸው፡፡ እናም በስብሰባዎቹ ላይ የወንጌል ስብከቱን የሚያደርገው ግለሰብ እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ሰራተኞች መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መርህ በመከተል (ሉቃ. 10) ሁለት ሁለት አድርጎ በአጠቃላይ በስድስት ቡድን ላካቸው፡፡ በዚያ የነበሩትን አስራ ሁለት ሰዎች በመጠቀም ረገድ ይህ አካሄድ አመርቂ ውጤት የሚያስገኝ አልመስለኝም ነበር፡፡ ነገር ግን በዚህ ጥረት የተገኘው ስኬት በእግዘአብሔር ቃል ላይ ተስፋን የመመስረትን ጥበብ ቁልጭ አድርጎ አሳየኝ፡፡ በዚያ ቀን የነበረው የተጠማቂዎች ብዛት በማምፊስ አዲስ ሬኮርድ አስመዘገበ፡፡

የእናንተስ የተስፋችሁ መሰረት ምንድን ነው? በሕይወት አስፈሪ ሸለቆ ውስጥ ስትጓዙ የምትጠቀሙበት የሞራል ኮምፓሳችሁ ምንድን ነው? ለእግራችሁ መብራት ለመንገዳችሁስ ብርሃን አግኝታችኋል (መዝ. 119፡105)? ተስፋችሁን ተለዋጭ በሌለው በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንድታንጹ ጠንከር አድርጌ አሳስባችኋለሁ፡፡

**ከፋትን መጥላት ተማሩ**

መጥላት የሚለውን ባለ አራት ፊደል ቃል ለማስወገድ እየታገላችሁ ይሆን? ይህንን አስቀያሚ የሚመስል ቃል በተመለከተ ጠቃሚ የሆነን ነገር ፈልጎ መናገር አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ለክርስቲያኖች ተገቢ የሆነ ጥላቻ አለ፤ እርሱም ክፋትን መጥላት ነው፡፡ ሰለሞን እንዲህ ይገልጸዋል፡- «እግዚአብሔርን መፍራት ክፋትን ይጠላል ትዕቢትንና እብሪትን ክፉንም መንገድ ጠማማውንም አፍ እጠላለሁ።» (ምሳ. 8፡13)

ኃጢአትን በመጥላት ረገድ ህይወታችሁ ምን ይመስላል? ይህንን በተመለከተ ወደ ፍጽምና እንዳልደረስኩ ስለ ራሴ መናዘዝ እፈልጋለሁ፡፡ አንዳንድ ኃጢአቶችን እጠላለሁ፤ ነገር ግን በሌሎቹ ደግሞ ውስጤ ሲሳብ አያለሁ፡፡ ይህ ደግሞ ኃጢአትን መጥላት የሚመጣው እግዚአብሔር በሚያየው አይን፣ ከነ ሙሉ አጸያፊነቱ ስናየው ስለሆነ፣ ይበልጥ ከእርሱ ጋር መንፈሳዊ ግንኙነት ማድረግ እንዳለብኝ የሚጠቁም ነው፡፡

ኃጢአትን ቅዱስ አስመስሎ ለመግለጽ መሞከር ወይም ክፋትን በመልካም ቋንቋ ለመግለጽ መሞከር ቀላል ነው፡፡ ስርቆት ከማለት ይልቅ ንብረት ማጥፋት እንላለን፤ ወይም ምንዝር ከማለት ይልቅ ከሌላ ሰው ጋር ጉዳይ መጀመር እንላለን፡፡ ፖርኖግራፊን

«የጎልማሶች መዝናኛ» በማለት ስንጠራው፣ ውርጃን ደግሞ «የምርጫ ጉዳይ ነው» ስንል እንደመጣለን፡፡ እንዲህ ባለ መልኩ ኃጢአትን በለዘበ ቋንቋ ለመጥራት በምናደርገው ጥረት አስቀያሚነቱን በማደብዘዝ፣ ክፋትን መጥላት እጅግ እንዲከብድብን እናደርጋለን፡፡ ዮሴፍ ግን ለኃጢአት የነበረው ጥላቻ በበቂ ሁኔታ ጠንካራ ስለነበረ የጶጢፋራን ሚስት የምንዝር ግብዣ እንዲህ በማለት ተቋቋመው፡- « ለዚህ ቤት ከእኔ የሚበልጥ ሰው የለም ሚስቱ ስለ ሆንሽ ከአንቺም በቀር ያልሰጠኝ ነገር የለም፡፡ እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?» (ዘፍ. 39፡ 9)

እንደ ዮሴፍ መሆን ከፈለጋችሁ፣ ይህንን ጥያቄ ራሳችሁን ጠይቁ፡- «በግ ነኝ ወይስ እርያ?» ይህ ማለት ምን ማለት ነው? በግንና እርያን በጭቃ ውስጥ ብታደርጓቸው የሚሆኑት ነገር የተለያየ ነው፡፡ አሳማው ምንም አይመስለውም፤ በጉ ግን ደስተኛ አይሆንም፡፡ እናንተም ወደ ክርስቶስ ይበልጥ እንደቀረባችሁ መጠን፣ በኃጢአት ጭቃ በመጨማለቅ የምታገኙት ደስታ እየበነነ ይሄዳል፡፡ በእርሱ ጽድቅ በተቻለ ፍጥነት ለመንጻት ናፍቆት ያድርባችኋል፡፡

ኃጢአትን በመጥላት ደረጃ ላይ እናንተ የምትገኙት የቱ ላይ ነው? እግዚአብሔር በሚያይበት አይን ክፋትን ከነሙሉ ማስጠላቱ ወደመመልከት ምን ያህል ተቃርባችኋል? በአንድ ወቅት ያስደምሟችሁ የነበሩቱ ብዙ ክፋቶች ዛሬ ግን የመሳብ አቅማቸውን አጥተዋልን? መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ስንለማመድ ኃጢአት ውበቱን ያጣል፡፡

## በሰማያዊ ነገሮች ላይ ትኩረታችሁን አድርጉ

ወደ ላይ አይኖቻችንን በማንሳት ራሳችንን መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ማስለመድ እንችላለን፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ጠቃሚ የሆኑ ምክሮችን እንዲህ በማለት ይለግሰናል፡- « በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም፡፡» (ቆላ. 3፡2)፡፡ ይህንን ስናደርግ፣ የሕይወትን ተግዳሮቶች በትክክለኛው አመለካከት ለማየት ያስችለናል፡፡ ጳውሎስ ብዙ ክርስቲያኖች ሊጋፈጡ ከሚችሉት እጅግ የበረታ መከራን የተጋፈጠ ሰው ነበር፡፡ ቢያንስ ሦስት የመርከብ አደጋ አጋጥሞታል፤ በድንጋይ ተወግሮ በሞትና በሕይወት መካከል ሆኖ ተዘርሮአል፤ እንደዚሁም ልክ ኢየሱስ እንደተገረፈው እርሱም በሮማውያን ተገርፎአል (2 ቆሮ. 11፡25)፡፡ ይሁን እንጂ፣ እነዚህን ሁሉ በስቃይ የተሞሉ ክስተቶች የተመለከታቸው «ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን» (2 ቆሮ. 4፡17) በማለት ነበር፡፡ ከሰማያዊው ሽልማቱ ጋር ሲያስተያያቸው በእርግጥም ክብደታቸው ቀላል ነበር፡፡

ወደ ላይ በመመልከት የሚኘውን ኃይል ጳውሎስ የተማረው ከኢየሱስ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ወታደሮች ኢየሱስን ለመያዝ በመጡ ጊዜ፣ ጴጥሮስ የሊቀ ካህናቱን ሎሌ ጆሮ በመቁረጥ ጴጥሮስ ሊከላከልለት ሞክሮ ነበር፡፡(ዮሐ. 18፡10) ኢየሱስም ለደቀ መዝሙሩ እንዲህ አለው፡- « ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ። ወይስ አባቴን እንድለምን እርሱም አሁን ከአሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይቻል ይመስልሃልን?» (ማቴ. 26፡52-53) ምንም እንኳን ኢየሱስ የስቃይ ሞቱ ስዕል በፊቱ ተደግኖ የነበረም ቢሆን፣ እርሱ ግን አይኖቹን ወደ ላይ አነጣጠረ፡፡

የእናንተስ የእይታችሁ ትኩረት ያረፈው የት ላይ ነው? በሳምንቱ ውስጥ ምን ያህል ደጋግማችሁ ስለ ሰማይ ታስባላችሁ? በቀኑ ውስጥስ ስለ መንፈሳዊ ነገሮች ምን ያህል ደጋግማችሁ ታስባላችሁ? የመጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ ጊዜያችሁ ሲቋረጥ ጉድለቱ

ይሰማችኋል ወይ? ምንም እንኳን ሌሎች ምድራዊ ነገሮችን መስዋዕት ማድረግን የሚጠይቅም ቢሆን ከመቋረጡ የተነሳ በውስጣችሁ የሚፈጠረው ረሃብ፣ የቀረባችሁን ለማካካስ ምንም እንኳን ሌሎች ምድራዊ ነገሮችን መስዋዕት ማድረግን የሚጠይቅም ቢሆን እርምጃን ለመውሰድ የሚያነሳሳችሁ ነውን? መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ፈጽማችሁ መለማመድ የምትፈልጉ ከሆነ፣ ትኩረታችሁን ወደ ላይ አድርጉ፡፡

**ለሌሎች ያላችሁን ፍቅር አሳድጉ**

«ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማልና፥ እርሱም፦ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚል ነው።» (ገላ. 5፡14)፡፡ በዚህ ሥፍራ ላይ ሕግ የተባለው የእግዚአብሔር የተገለጠ ፈቃድ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ትዕዛዝ ላይ በቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ላይ የቀረበው ሃሳብ ተጨምቆ «ሕግ» በመባል ቀርቦ እናነባለን፡፡

ባልንጀሮቻችንን መውደድ በጣም አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሳ መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሳችን ሳንዋደድ እግዚአብሔርን ልንወደው እንደማንችል ይነግረናል፡፡ ምን እንደሚለን ስሙ፡- «ማንም፦ እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል?» (1 ዮሐ. 4፡20)፡፡ እነዚህ ከበድ ያሉ ቃላት ቢሆኑም፣ ለሌሎች ሰብአዊ ፍጡራን የምናሳየውን ፍቅር ወሳኝነት ያሳያሉ፡፡

የመልካሙ ሳምራዊ ምሳሌ እንደሚያስተምረን እንዲህ ያለው ፍቅር ከአንደበት ያለፈ ነው (ሉቃ. 10)፡፡ በዚህ እጅግ በሚታወቅ ታሪክ ውስጥ ቆስሎ በመንገድ የወደቀው ሰው በካህኑና በሌዋዊው ችላ ሲባል፣ ወገኑ ባልሆነ ይልቁንም የእርሱ ወገኖች ከሚንቁት ዘር በመጣ ሰው ግን እንክብካቤ ተደረገለት፡፡ ሰማርያዊው የቆሰለውን ሰው ቁስል ያከመለት ሲሆን እስከሚያገግም የሚያስወጣውንም ወጪ በሙሉ ሸፈነለት፡፡ ይህ በጎ ያደረገው ሰው በመንገድ ላይ የወደቀውን በደም የተጨማለቀ ግለሰብ ለመርዳት የራሱን ደህንነት አደጋ ውስጥ ጨምሮ ነበር፡፡ መንፈሳዊ ዲሲፕሊንን ማሳደግ ከፈለግን ልናሳድገው የሚገባን እንዲህ ያለውን ፍቅር ነው፡፡ ምናልባትም ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ «ፍቅር የህግ ፍጻሜ ነው» በማለት የሚነግረን (ሮሜ. 13፡10)፡፡

**ይቅር ማለትን ተለማመዱ**

ይቅር የማለትን ልምምድ እስካላዳበርን ድረስ መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ጠንቅቀን ልንለማመዳቸው አንችልንም፡፡ እንዲያውም ጌታችን ባስተማረው ጸሎት ላይ እንደተጠቆመው፣ መለኮታዊ ይቅርታን መቀበል የምንችልበት እድል እኛ ለሌሎች ከምንሰጠው ይቅርታ ጋር ተቆራኝቶአል፡፡ «እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን፤» (ማቴ. 6፡12)

ጌታችን ኢየሱስ በመስቀል ላይ የተናገረው የመጀመሪያ ቃል ለጠላቶቹ ይቅርታ እንዲደረግ በመጸለይ ያወጣው ቃል ነበር፡- «አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ።» (ሉቃ. 23፡ 34)

ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ስለ ይቅርታ ሲያስተምራቸው፣ ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ጠይቆ ነበር፡- « ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከ ሰባት ጊዜን? » ኢየሱስም ሲመልስ፡- «እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት» አለው፡፡ (ማቴ. 18፡ 21-22) በሌላ አነጋገር፣ ልማድህ እስኪሆን ድረስ ይቅር በል ማለቱ ነበር፡፡

የአልኮል መጠጥ ሱሰኛ የነበረውን አባቴን ይቅር ማለት ለእኔ አስቸጋሪ ነበር፤ እናም እስከሚሞትበት ጊዜ ድረስ በእርሱ ላይ በቁጣ የተሞላ ልብ ነበረኝ፡፡ እርሱ ከሞተ በኋላ ነበር በእርሱ ላይ የነበረኝን ጥላቻ በማንሳት በእግዚአብሔር ጸጋ ይቅር የማለት ችሎታን ያዳበርኩት፡፡ አሁን የኋሊት ሳስበው፣ እርሱን ይቅር ለማለት እንደዚያ የከበደኝ ለምን እንደነበረ ይገርመኛል፤ በተለይም እግዚአብሔር እኔን ምን ያህል ይቅር እንዳለኝ ሳስብ፡፡ ሊኖረን የሚገባውን ትክክለኛ ባሕርይ ኢየሱስ የጠቀለለው እንዲህ በማለት ነበር፡- «አትፍረዱ አይፈረድባችሁምም፤ አትኰንኑ አትኰነኑምም። ይቅር በሉ ይቅርም ትባላላችሁ።» (ሉቃ. 6፡37)፡፡

ሌሎችን ይቅር በማለት ረገድ ሕይወታችሁ ምን ይመስላል? ምናልባት በስሜታችሁ ከረጢት ውስጥ ያሉ ጥላቻዎች በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ እንዳታድጉ እንቅፋት ሆነውባችሁ ይሆን? ይቅር በሉ ይቅር ትባላላችሁ፤ ያን ጊዜም መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ለመልመድ በተሻለ ሁኔታ የተዘጋጃችሁ ትሆናላችሁ፡፡

**እግዚአብሔርን በሙላት ታዘዙ**

መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ለመላበስ በምትሹበት ጊዜ ሁለንተናችሁን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ተዘጋጁ፡፡ « እንዲህም ይሆናል የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ፥ ዛሬም ያዘዝሁህን ትእዛዙን ሁሉ ብታደርግ ብትጠብቅም አምላክህ እግዚአብሔር ከምድር አሕዛብ ሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያደርግሃል። የአምላክህንም የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ እነዚህ በረከቶች ሁሉ ይመጡልሃል ያገኙህማል።» (ዘዳ. 28፡ 1-2)፡፡

አንዳንድ ጊዜ በረከቶችን የምናጣው መታዘዛችን በከፊል ስለሆነ ነው፡፡ ፈውስን ፍለጋ ነብዩ ኤልሳዕን ለመገናኘት ብቻ እምነት እንደነበረው ነገር ግን ነብዩ በመከረው መሰረት በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ሰባት ጊዜ ለመጥለም እንዳመነታው እንደ ንዕማን እንሆናለን(2 ነገ. 5)፡፡ በመጀመሪያ ላይ ንዕማን ያሳየው ከፊል የሆነ መታዘዝ ብቻ ነበር፡፡ ምንም እንኳን በአገልጋዮቹ ገፋፊነት ቢሆንም፣ ሙሉ በሙሉ ለመታዘዝ ተስማማና ተፈወሰ፡፡

በአሜሪካ ባህር ኃይል ውስጥ በቻፕሌንነት ሳገለግል፣ የሚሊተሪን ቤት መሰረታዊ እሴቶች ተማርኩ፡፡ «ከባድም ቢሆን ትክክለኛውን ምረጥ» የሚለው አንዱ ነው፡፡ ይህ ትልቅ ምክር ነው፡፡ ራሳችሁን ሙሉ በሙሉ ለማስረከብ ከፈለጋችሁ ለምን ትክክለኛ የሆነውን ነገር፣ ምንም ከባድ ቢሆን፣ አትመርጡም? መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ለመለማመድ ልናደርግ የምንችለው ትልቅ ዝግጅት ይሄ ነው፡፡

ሁለንተናችሁን ለእግዚአብሔር እየሰጣችሁት ነው ወይስ ከፊል በሆነ መታዘዝ ረክታችሁ ተቀምጣችኋል? በልግስናችሁ፣ በትዳራችሁ፣ በወላጅነታችሁና በስራችሁ ሙሉ የሆነ መሰጠት እያሳያችሁ ነው? ምንም እንኳን የሚከብድ ቢሆንም፣ ትክክለኛ የሆነውን ነገር ምረጡ፡፡ ራሳችሁንም ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር ስጡ፡፡ የመሰጠታችን ጥልቀት በጣም ወሳኝ ነው፤ ለዚህም ነው እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን፣ ነፍሳችን፣ አእምሮአችንና ጥንካሬያችን እንድወደው የተነገረን (ሉቃ. 10፡27)፡፡

**በችግር ውስጥ ያሉ ሰዎችን አገልግሉ**

ከምወዳቸው የቴሌቭዥን ፕሮግራሞች መካከል አንደኛው «እየተገለገልክ ነውን? » የተሰኘውን የብሪታኒያ ኮሜዲ ነው፡፡ ፕሮግራሙ የሚያተኩረው በብሪታኒያ ውስጥ በሚከሰቱ አስቂኝ ነገሮች ላይ ነው፡፡ ነገር ግን ርዕሱ ክርስቲያኖች ደጋግመው ሊያስቡት የሚገባ ጥያቄን ያስታውሰናል፡- «የአገልጋይነትን ሕይወት እየኖርኩ ነው ወይ?»

እግዚአብሔር እንደ አገልጋይ እንድንኖር ይጠብቅብናል፡፡ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይጽፋል፡- «በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፤ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ፤ ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ፤ በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ፤ ለጌታ ተገዙ፤ ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው እርዱ፤ እንግዶችን ለመቀበል ትጉ።» (ሮሜ. 12፡ 10-13)፡፡ ይህ ግልጽ የሆነ ትዕዛዝ ነው፡፡ እርስ በርስ መከባበርና ሌላውን ማገልገል መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ለመለማመድ ማድረግ ያለብን አንዱ ትልቅ የዝግጅት ክፍል ነው፡፡

ስናገለግል ደግሞ፣ ልናደርግ የምንችለው እጅግ ትልቁ ነገር በኢየሱስ እግር ስር መቀመጥ እንደሆነ እናስታውስ(ሉቃ. 10፡40-42)፡፡ በችግር ውስጥ ላለ ሰው በክርስቶስ ስም አንድ ብርጭቆ ውሃ ስንሰጥ ክርስቶስን እያገለገልን እንደሆነ ጨምረን እናስታውስ (ማር. 9፡41)፡፡

አንድ ጊዜ፣ በአሜሪካ አገር አቀፍ በሆነው የቅርጫት ኳስ ግጥሚያ አንድ የመለያ ጨዋታ ከመጀመሩ በፊት ተጫዋቾች ሰውነታቸውን ሲያሟሙቁ ታላቁን የቅርጫት ኳስ ተጫዋች ሊቦርን ጄምስን ተመለከትኩት፡፡ ልክ እንደ ሌሎቹ የቡድኑ አባላት ከልቡ ይለማመድና ይዘጋጅ ነበር፡፡ በቀደሙት ጊዜያት ጄምስ ያሳየውን ክህሎት በደንብ ታዘበው ማስታወቂያ ተናጋሪ እንደ ቀልድ አድርጎ የሚከተለውን ተናገረ፡- «ለመሆኑ እርሱ እንዲህ መለማመድ ለምን አስፈለገው?» እኔም ጥያቄውን አሰላስልኩትና እንዲህ አልኩ፡- «ምናልባትም በታላቅነትና በልምምድ መካከል ቁርኝት አለ፡፡»

እናንተስ? መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ለመለማመድ የሚያስፈልገውን ዝግጅት ለማድረግ ፈቃደኞች ናችሁን? ወይስ ሳይዘሩ ሊያጭዱ እንደፈለጉት እንደ ቺካጎ ገበሬዎች ናችሁ? መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ለመልመድ ተዘጋጁ፡፡

## ራሳችሁን መንፈሳዊ ዲሲፕሊኖችን ለማስመድ የሚያግዟችሁ ወሳኝ እርምጃዎች

- እግዚአብሔርን ለማወቅ ያላችሁን ፍላጎት አሳድጉ
- ተስፋችሁን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ላይ አንጹ
- ክፋትን መጥላት ተማሩ
- በሰማያዊ ነገሮች ላይ ትኩረታችሁን አድርጉ
- ለሌሎች ያላችሁን ፍቅር አሳድጉ
- ይቅር ማለትን ተለማመዱ
- እግዚአብሔርን በሙላት ታዘዙ
- በችግር ውስጥ ያሉ ሰዎችን አገልግሉ

ክፍል ሁለት ፡-

# የመከራን ምንጮች ማድረቅ

# 17

# ፈተናዎቻችሁን ግሩአቸው

ዝነኛው አየርላንዳዊው ገጣሚ ኦስካር ዊልድ እንዲህ አለ ይባላል፡- «ከፈተና ውጪ ማንኛውንም ነገር መቋቋም እችላለሁ፡፡» ብዙዎቻችን ይህንን ስሜት እንጋራለን፡፡ የምንገባቸው ቃልኪዳኖችና የምናስተላልፋቸው የአቋም መግለጫዎች ልንጨብጣቸው የማንችል ከአሸዋ የተገመዱ ገመዶች ናቸው፡፡ ታዲያ ከዚህ የተነሳ ፈተናዎቻችንን መግራት የምንችልበትን ጥበብ ለማወቅ ሁላችን እንጓጓለን፡፡

በመከራዎችንን ውስጥ በረከትን ለማግኘት መዘጋጀት ከፈለግን ፈተናዎቻችንን መግራት ወሳኝ እርምጃ ነው፡፡ ይህንን እንድናደርግ እግዚአብሔርም ይጠባበቀናል፡፡ ያዕ. 4፡7 ላይ «ዲያቢሎስን ተቃወሙት፤ ከእናንተም ይሸሻል» ሲለን በኤፌ. 6፡11 ደግሞ «የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።» በማለት ይገዳደረናል፡፡ ታዲያ ፈተናን መግራት የምንችለው እንዴት ነው?

**የጠላታችሁን ችሎታ ጠንቅቃችሁ እወቁ**

የቼዝ ጨዋታን እጫወት ነበር፤ ይሁን እንጂ ከማሸንፍበት ይልቅ የምሸነፍበት ጊዜ እጅግ ብዙ ነበር፡፡ ይህ የሆነው ግን የትኩረት አቅጣጫዬን እስከለውጥ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ተጋጣሚዬ የሚያደርገውን ችላ ብዬ የራሴን ስትራቴጂ ብቻ እከተል ነበር፡፡ አሁን ግን ይህንን ስልት በመቀየር የባላንጣዬን ስትራቴጂዎችና ዘዴዎች ማክሸፍ ጀመርኩ፡፡ በዚህ በተከተልኩት አዲስ አቀራረብ ከምሸነፍባቸው ይልቅ የማሸንፍባቸው አጋጣሚዎች ተበራከቱ፡፡

ሰይጣንም በእኛ ላይ የሚጠቀምባቸው የራሱ ስትራቴጂዎች አሉት፡፡ ለመሆኑ ምን ያህል ጠንቃቃችሁ ታውቋቸዋላችሁ? ፈተናዎቻችንን መግራትን በመማር ረገድ «የዲያቢሎስን ሽንገላ» ማስተዋላችን ወሳኝ እርምጃ ነው፡፡ ስለ ሰይጣን ሲናገር ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ይላል፡- «በሰይጣን እንዳንታለል፤ የእርሱን አሳብ (ዘዴዎች) አንስተውምና።» (2 ቆሮ. 2፡11)፡፡

ለመሆኑ የእርሱ ዘዴዎች ምንድን ናቸው? በመጀመሪያ፣ የእግዚአብሔርን ቃል እንድንጠራጠር ይፈልጋል፡፡ ይህንን ስትራቴጂውን በኤደን የአትክልት ስፍራ በሔዋን ላይ ተጠቅሞበት ነበር (ዘፍ. 3)፡፡ ሁለተኛ፣ ልክ ሳምሶን ከደሊላ ጋር በነበረው ግንኙነት አስቦት እንደነበረው እኛም ኃጢአትን በራሳችን ጥረት ለመቋቋም አቅሙ እንዳለን እንዲሰማን ሊያደርገን ይፈልጋል(መሳ. 16)፡፡ በጣም ከሚወዳቸው ስልቶቹ መካከል አንደኛው ደግሞ እጅግ በዛልንበት ጊዜ በእኛ ላይ ጥቃትን መሰንዘር ነው፡፡ ኢየሱስ

ለአርባ ቀናት ከጾመ በኋላ በረሀብ ሲደክም፣ ዲያቢሎስ ሊፈትነው ወደ እርሱ መጣ (ማቴ. 4፡1-4)፡፡ በጣም የሚወዳቸው የመፈተኛ መሳሪያዎቹስ ምን ምን ናቸው? አንደኛ ዮሐንስ 2፡ 15-16 ጠላታችን ውስን፣ ነገር ግን ውጤታማ የሆኑ መሳሪያዎች እንዳሉት ይነግረናል፤ እነርሱም፦ የሥጋ አምሮት፣ የአይን ምኞትና የኑሮ ትምክህት ናቸው፡፡ ሁሉም ፈተናዎች ማለት ይቻላል ከእነዚህ ከሦስቱ አንዱን ወይም ከዚያ በላይ የሚያካትቱ ናቸው፡፡

**የኃጢአትን የረዥም ጊዜ መዘዝ አስቡ**

ወደ ኃጢአት የሚመራችሁን ፈተና መቋቋም የነበረባችሁን ጊዜና ለፈተናው እጅ ባለመስጠታችሁ ምክንያት ኋላ ላይ የተጸጸታችሁበት ኹናቴ ትዝ ይላችኋል? እንደዚህ የሚሰማው ሰው እስካሁን አላገኘሁም፡፡ ይልቁንም ወደ ኋላ መለስ ብለን ስናስብ በከፋት ላይ በተቀዳጀናቸው ትንሽ በሚመስሉ ድሎች እንኳን ሳይቀር ደስተኞች ነን፤ ምክንያቱም ጊዜ የኃጢአትን አስከፊ መዘዞች ይገልጣልና፡፡ ዮሴፍ በእስር ቤት በተጣለ ጊዜ እንኳን የጶጢፋራን ሚስት ወደ ወሲብ የሚገፋፋ ፈተና በመቋቋሙ ፈጽሞ መጸጸትን አላሳየም (ዘፍ. 40)፡፡ ኃጢአት የሚያስከትለውን የረዥም ጊዜ መዘዝ በማሰብ እንዲህ ብሎ ጠየቀ፦ «በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?» (ዘፍ. 39፡ 9)፡፡

ወደ ሞት የሚወስድ መንገድ ስለ መሆኑ በሚነገርለት መንገድ ላይ ማን ጉዞን መጀመር ይፈልግ ይሆን? ይሁን እንጂ አጥፊ ውጤቶች እንዳሉት እየተነገራቸው ብዙዎች በኃጢአት ጎዳና አዘውትረው ይጓዛሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና» (ሮሜ. 6፡23)፡፡ ይህንን በማስተዋል፣ ማንም ሰው በኃጢአት ወስጥ ያለውን ጥፋት ሳያጤን ተግባሩን ሊለማመደው አይገባም፡፡

**ምክንያት መስጠትን ተቃወሙ**

ብዙ ጊዜ ከስነ ምግባር ህግ ጋር የሚቃረነውን ድርጊታችንን በማሕበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን ሰበቦች በመፈለግ ስለ ኃጢአታችን ምክንያት ለመስጠት እንሞክራለን፡፡ ሃቀኝነትን ከመለማመድ ይልቅ፣ የሚጠበቅብንን ከማድረግ ለማፈንገጥ የምንችልባቸውን ትንንሽ ቀዳዳዎች እናስሳለን፡፡ ብዙ ጊዜ ራሳችንን ሕግ የማይመለከተን አድርገን እናስባለን፡፡ «እንደኔ ያለው በጣም አስፈላጊ ሰው ከእኔ ያነሰ ክህሎትና ስጦታ ካላቸው ሰዎች በተሻለ ትልቅ ነጻነት ሊሰጠው ይገባል» እንል ይሆናል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል፦ «እንደርሱ አይደለም» ጳውሎስ በሕሊናችን ልንመራ እንደሚገባን ያስተምረናል፦ «በእምነትም ያልሆነ ሁሉ ኃጢአት ነው» (ሮሜ. 14፡ 23)፡፡ በሌላ አነጋገር በእምነት ከመንቀሳቀስ ዘወር ብለን እኛ መልካም የመሰለንን ነገር ብቻ የምናደርግ ከሆነ፣ ኃጢአት እያደረግን ነው፡፡ ነገረ መለኮታዊ መረዳታችን መቶ በመቶ ትክክል በመሰለን ጊዜ እንኳን ሳይቀር፣ እግዚአብሔር እንድንመለከተው በሰጠን ችሎታ ልክ ብርሃንን መከተል ያስፈልገናል፡፡ እምነታችንንና ልባችንን ስንከተል፣ በነገረ መለኮታዊ መረዳታችንን ትክክል መሆን ሁለተኛ ደረጃን ይይዛል፤ ምክንያቱም በአስተምህሮ ጉዳዮች ላይ፣ ሁላችንም «በመስታወት እንደሚያይ ሰው፣ በድንግዝግዝ» እንመለከታለንና (1 ቆሮ. 13፡12)፡፡ ይህንን ስል እግዚአብሔር አስተማማኝ የሆኑ የእውነት አስተምህሮዎች የሉትም እያልኩ አይደለም፡፡ ምክንያቱም የሕጉ መጠይቆች ምንም

አይነት ድርድር ውስጥ የሚገቡ ጉዳዮች አይደሉምና፡፡ ይልቁንም፣ አንዳንድ ጊዜ ነገሮች በጥቁርና በነጭ ግልጽ ብለው መቀመጥ በማይችሉበት፣ ግራጫማ ገጽታ ውስጥ ሕይወት ልትከተን ትችላለች፡፡ ሁለት ትክክል በሆኑ ነገሮች መካከል እንድንመርጥ እንጠየቅ ይሆናል፡፡ ያን ጊዜ ታዲያ በህሊናችን ውስጥ ሹክ የሚለንን ድምጽ ልንሰማና በእምነትም ልባችን ያረፈበትን ነገር ለማድረግ ወደፊት መገስገስ ያስፈልገናል ማለት ነው፡፡

**አስፈላጊ ሲሆን በሩጫ ሽሹ**

ጳውሎስ የእምነት ልጁን ጢሞቲዎስን እንዲህ በማለት ይመክረዋል፡- «ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ግን ሽሽ፥ በንጹሕም ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን እምነትን ፍቅርን ሰላምን አጥብቀህ ተከተል።» (2 ጢሞ. 2፡22)፡፡ ራሳችንን ከፈተና ለማስመለጥ፣ አንዳንድ ጊዜ መሮጥ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡ እውነት ነው፣ አንዳንዴ በነገሩ ላይ መነጋገሩ አግባብ የሚሆንበት ሁኔታ አለ፤ ነገር ግን ብዙ ጊዜ መሮጡ ይበልጥ ይመረጣል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የጶጢፋራ ሚስት «ከእኔ ጋር ተኛ ስትል ልብሱን (የዮሴፍን) ተጠማጥማ ያዘች እርሱም ልብሱን በእጅዋ ትቶላት ሸሸ ወደ ውጭም ወጣ።» (ዘፍ. 39፡ 12)፡፡

ብዙ ጊዜ የዮሴፍን ምሳሌነት በመዘንጋት ከመጠን ባለፈ በራስ መተማመን ተሞልተን ፈተናን ፊት ለፊት ተጋፍጠን ማሸነፍ እንደምንችል እናስባለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ ካለ ስህተት እንድንጠበቅ ያስጠነቅቀናል፡- «ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ።» (1 ቆሮ. 10፡12)፡፡ ከዚህ ጥቅስ እንደምረዳው ራሳችንን ከኃጢአት ከምንከላከልባቸው ታላላቅ መንገዶች መካከል አንደኛው ጤናማ የሆነ ፍርሃት እና ራስን ዝቅ ዝቅ ማድረግ ነው፡፡ በሩጫ ለማምለጥ ፈቃደኛ በመሆን ፈተናችሁን ግሩት፡፡

**ኃፍረትን ለመከናነብ ፈቃደኛ ሁኑ**

ሃፍረትን የሚያከናንባችሁም እንኳን ቢሆን ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ፈቃደኛ ናችሁ? ንጉስ ሄሮድስ ግን ፈቃደኛ አልነበረም፡፡ ሃፍረትን አስወግዳለሁ ብሎ ሃቅን ለድርድር አቀረበ፡፡ ለራሱ በተዘጋጀው የልደት ግብዣ ላይ (ማቴ. 14) ሄሮድስ የሄሮድያዳ ልጅ ለፍትወተ ስጋ ፍላጎት በሚያነሳሳ መልኩ ለእርሱና ለታዳሚዎቹ እንድትጨፍር ፈለገ፡፡ በአቻዎቹ ተከብቦ በነበረበት በዚያ ሁኔታ፣ እርሱ ያዘዛትን ብታደርግ የመንግስቱን እኩሌታ ድረስ ሊሰጣት ቃል ገብቶ ነበር፡፡ እርሷም ተስማማች፡፡ ከጭፈራዋም በኋላ፣ ሄሮድስ እንዲህ ብሎ ጠየቃት፡- «ምን ትፈልጊያለሽ?» እርሷም ከእናቷ ጋር ከተማከረች በኋላ እንዲህ በማለት መልሷን ሰጠች፡- «የመጥምቁ የዮሐንስን ራስ በዚህ ወጭት ስጠኝ»

ሄሮድስ እጅግ አዘነ፡፡ ነገር ግን በእንግዶቹ ፊት ቃሉን በማጠፍ ሃፍረትን ከሚከናነብ ይልቅ የዮሐንስን አንገት ማስቆረጥ መረጠ፡፡ ምክንያቱም አደርጋለሁ ያለውን ቢቀይር፣ ዝናውን የሚያጣ መሰለው፡፡ ይልቁንም በአለማችን ከተነሱት ታላላቅ ነቢያት መካከል አንዱ የሆነውን ሰው አንገት እንዲቆረጥ አደረገ፡፡ በፈተና ከመሸነፍ የሚታደገን ከሆነ ሃፍረትን መለማመድንም ቢሆን በፈቃደኝነት ልናስተናግድ ይገባል፡፡

**የጸሎትን ኃይል ተጠቀሙ**

ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ካለፈበት ፈታኝ የሆነ ነገር ሁሉ እጅግ የሚበልጥ ልምምድ የተከሰተው በጌተሰማኔ የአትክልት ቦታ ነበር፡፡ በዚህ ሥፍራ ኢየሱስ በሰማያት ካሉ ኃይላት ሁሉ ጋር የተፋለመበት ሲሆን የተጠቀመበትም አንዱና ዋንኛ መሳሪያው ጸሎት ነበር (ማቴ. 14፡32)፡፡ የደቀ መዛሙርቱን የጸሎት ድጋፍ ፈልጎ የነበረም ቢሆን፣ እነርሱ ግን ከመማለድ ይልቅ መተኛትን መረጡ፡፡ ስለዚህም፣ ኢየሱስ ለብቻው በቀረበት ስፍራ ቀራኒዮን ለመጋፈጥ ጉልበትን ያሰባሰበው የጸሎትን ኃይል በመጠቀም ነበር፡፡

ይህ ደግሞ እምብዛም አስገራሚ አይደለም፡፡ ምክንያቱም እርሱ ራሱ የተስፋ መቁረጥ መድሃኒቱ ጸሎት እንደሆነ አስተምሮ ነበርና፡፡ እንዲያውም «ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው» (ሉቃ. 18፡1) ነግሮአቸው ነበር፡፡ የሕይወት ጎዳና ላይ ችግሮች ሊገረስሷችሁ ሲደርሱ፣ ፈተናዎቻችሁን በጸሎት መግራትን ተማሩ፡፡

የቀራኒዮን ፈተና ኢየሱስ የገራው በዚህ መልኩ ነበር፡፡ በመስቀል ላይ ሆኖ የተነፈሳቸው የመጀመሪያ ቃላት ጸሎት ሲሆኑ ደጋግመው መደመጥ የሚገባቸው ናቸው፡- «አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው » (ሉቃ. 23፡34)፡፡ ከዚያም ቆየት ብሎ ከመዝ. 22፡ 1 እንዲህ በማለት ጠቀሰ፡- «አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ?»፡፡ ይህንን
በማለቱ የተስፋ መቁረጥና የብቸኝነት ቃል እየተናገረ ሳይሆን፣ ነገር ግን በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተጻፈውን እየጸለየ ነበር፡፡ ጸሎት ፈተናን ድል ለመንሳት ተመራጭ የጦር መሳሪያ ነው፡፡

**ተጠያቂነትን የሚያለማምዱ ወዳጆች ይኑሯችሁ**

ኢየሱስ በጌተሰማኔ በጸለየበት ጊዜ አብረውት የነበሩ ወዳጆች ነበሩ፡፡ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ የልቡን ሁሉ የሚነግራቸው ወዳጆቹ ሲሆኑ ከእነርሱም መጽናናትን ሊቀበል ይችል ነበር፡፡ በተለያዩ ወሳኝ የሆኑ ጊዜያት ከኢየሱስ ጋር የነበሩ ሲሆን፣ የኢያኢሮስን ልጅ ሲያስነሳና በመገለጥ ተራራ ላይ አብረውት ነበሩ፡፡

ልክ እንደ ኢየሱስ እኛም እንዲህ ያለ ወዳጅነትን ልናዳብር ያስፈልገናል፡፡ በቡድን ውስጥ ኃይል አለ፡፡ ምናልባትም ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሁለት ሁለት እያደረገ የላከበት አንዱ ምክንያት ይሄ ሊሆን ይችላል (ሉቃ. 10)፡፡ በሁሉም ጊዜ ማለት ይቻላል፣ ሁለት ሰዎች ከአንድ የተሻለን መስራት ይችላሉ፡፡ በመክብብ መጽሐፍ ላይ እንደተቀመጠው፡- «ድካማቸው መልካም ዋጋ አለውና አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል።... ቢወድቁ አንዱ ሁለተኛውን ያነሣዋልና አንዱ ብቻውን ሆኖ በወደቀ ጊዜ ግን የሚያነሣው ሁለተኛ የለውምና ወዮለት። ...አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ ሁለቱ በፊቱ ይቆማሉ በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም።» (መክብብ 4፡ 9-10፣ 12)፡፡ በቡድን ውስጥ የሚገኘው ውጤት የቡድኑ አባላት አጠቃላይ ድምር ከሚያስገኘው በላይ ነው፡፡

**በእግዚአብሔር አላማ ላይ ትኩረታችሁን አድርጉ**

በጌተሰማኔ፣ ኢየሱስ ፈተናን ለመግራት ችሎ ነበር፡፡ እንዲህ ብሎም ጸለየ፡- «አባ አባት

ሆይ፥ ሁሉ ይቻልሃል፤ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን አንተ የምትወደው እንጂ እኔ የምወደው አይሁን» (ማር. 14፡ 36)፡፡ ድል ለመንሳቱ ተቀዳሚው ምክንያት በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ ትኩረቱን ማድረጉ ነበር፡፡

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ፍላጎቱ ሲኖረንና ከክፋት ጋር በምናደርገውም ውጊያ የእርሱ አላማ ተገልጦ ስንመለከት፣ ያ ብርታትን ይጨምርልናል፡፡ ጳውሎስ ያልፍበት ስለነበረው መከራ የተለየ መገለጥን አግኝቶ ነበር፡- «ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ይህ የደረሰብኝ በእውነት ወንጌልን ለማስፋት እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ።» (ፊል. 1፡12)፡፡ ፍትሃዊነት በጎደለው በዚያ እስራቱ ውስጥ እግዚአብሔር የሚያሸንፍበትን እድል ተመለከተ፡፡ ይህ አስተሳሰቡ ደግሞ ጨለምተኛ የሆነ አመለካከትን ከመያዝና ከተስፋ መቁረጥ ጠብቆት ፈተናውን እንዲገራ ረዳው፡፡

ሁሉም ነገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በአክብሮት ጋር አስካር ዊልዴ ካለው ጋር እንደማልስማማ መግለጽ እፈልጋለሁ፡፡ በእግዚአብሔር ጸጋ፣ ማንኛውም ነገር፣ ፈተናንም ጨምሮ መቋቋም ይቻላል፡፡ ምክንያቱም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአልና፡- «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።» (ፊል. 4፡13)

### ፈተናዎቻችሁን ለመግራት የሚያግዟችሁ ወሳኝ እርምጃዎች

- የጠላታችሁን ችሎታ ጠንቅቃችሁ እወቁ
- የኃጢአትን የረዥም ጊዜ መዘዝ አስቡ
- ምክንያት መስጠትን ተቃወሙ
- አስፈላጊ ሲሆን በሩጫ ሽሹ
- ሃፍረትን ለመከናነብ ፈቃደኛ ሁኑ
- የፀሎትን ኃይል ተጠቀሙ
- ተጠያቂነትን የሚያለማምዱ ወዳጆች ይኑራችሁ
- በእግዚአብሔር አላማ ላይ ትረኩረታችሁን አድርጉ

# 18

# ጭንቀትን አሸንፉ

መቼ ሃሳቡ ወደ አእምሮዬ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደገባ አላስታውስም፣ ነገር ግን አንድ ጊዜ «ከአባትህ እድሜ የበለጠ እድሜ አይኖርህም» የሚል ሃሳብ ያስጨንቀኝ ጀመር፡፡ አባቴ የሞተው በሃምሳ አራት አመቱ ነበር፤ እናም የእኔም ሕይወት ከዚያ የበለጠ እንደማይሆን ማሰቤ ፍርሃት ለቀቀብኝ፡፡

እያንዳንዱ የልደቴ በዓል ባለፈ ቁጥር፣ ወደ ፈራሁት የእድሜ ቁጥር ያቀርበኝ ነበር፡፡ በመጨረሻም ያ ቁጥር ላይ ስደርስ አባቴ ከአምሳ አራተኛ የልደት ቀኑ በኋላ ለምን ያህል ወራት እንደኖረ ማስላት ጀመርኩ፤ ይህንን ሁሉ ሳደርግ ሕይወቴ በዚያ ላይ ሊያበቃ እንደሚችል በማሰብ ነበር፡፡ ሃምሳ አምስተኛ አመት ልደቴን ሳከብር የተሰማኝን ደስታ የተለማመዱት ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡

አሁን የኋሊት ሳስበው፣ እንዲህ መሰረተቢስ በሆነ ነገር መጨነቅ ሞኝነት መስሎ ይታየኛል፡፡ ፍርሃቴን የማስደግፍበት ምንም አይነት ማስረጃ አልነበረኝም፡፡ የሆነው ነገር እንዲሁ ከአጉል እምነት የመነጨ ፍርሃት ሲሆን ሰላሜን ዘርፎኝ ነበር፡፡ ፈጽሞ ባልተከሰተ ነገር እየተጨነኩ አመታትን አቃጠልኩ፡፡

በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከጭንቀት ጋር ይፋለማሉ፡፡ ስለ ጤና፣ ስለ ጡረታ፣ ስለ ልጆቻችንና የልጅ ልጆቻችን፣ ስለ መሪዎቻችንና አገሮች፣ እንደዚሁም ስለ ዘላለማዊ ሕይወት እንጨነቃለን፡፡ ስለ ያለፈው፣ ስለ አሁኑና ስለ ወደፊቱ ስጋት ይገባናል፡፡ ጭንቀት እምቅ ችሎታችንን እስከ መጨረሻው መጠቀም እንዳንችል እንቅፋት የሚሆንብን ሲሆን፣ በፍርሃትም ጥፍንግ አድርጎ ያስረናል፡፡

ኢየሱስ የመጣው ከፍርሃት ነጻ ሊያወጣን ነው፡፡ በመሆኑም በተራራው ስብከቱ ላይ ይህንን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ ተናግሮ ነበር፡፡ በማቴ. 6፡ 25 ላይ፣ እንዲህ አለ፡- «ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ስለ ነፍሳችሁ... አትጨነቁ፤» ከዚያም በጭንቀት ላይ ለመጫማት የምንችልባቸውን ቁልፍ ሃሳቦች አቅርቦልናል፡፡

**በቁሳዊ ነገሮች አትጠፈሩ**

ወዳጄ ያለውን ሁሉ አጣ፡፡ ካትሪንና ሪታ የተባሉት አውሎነፈስን የቀላቀለ ከባድ ዝናብ ያስከተላቸው የተፈጥሮ አደጋዎች ንብረቱን ሁሉ ጠራርገው ወሰዱበት፡፡ የደረሰበትን መከራ በሰቆቃ ውስጥ ሆኖ ለልጁ ሲነግራት፣ አንድ ቀለል ያለ አርፍተ ነገር ብቻ

በመናገር እውነታውን ቁልጭ አድርጋ አስቀመጠች፡፡ እንዲህ ነበር ያለችው «አባዬ፣ ታዲያ ቂስ እኮ ነው ያጣኸው!» በእርግጥም የቁሳዊ ነገሮች እስረኛ እንዳይሆን ማስታወስ የሚገባው ትክክለኛ እውነታ ይኼው ነበር፡፡

ኢየሱስ የቁስ ባርያ ከመሆን ነጻ ሊያወጣን ይፈልጋል፡፡ እንዲህም ብሎናል፡- «ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት፥ ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ፤ ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ አይበልጥምን?» (ማቴ. 6፡25) በሌላ ጊዜ ደግሞ እንዲህ ብሎ ነበር፡- «የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ፥ ከመጐምጀትም ሁሉ ተጠበቁ» (ሉቃ. 12፡ 15)፡፡

በዩ.ኤስ. ሴኔት ሬስቶራንት ተቀምጬ ሳለሁ፣ አንድ ባለ ብዙ ሚሊዮን ባለ ሃብት ሴናተር በስተቀኜ ቁጭ ብሎ፣ እኔ ከማዝበት የምግብ ዝርዝር ሲያዝ ተመለከትሁ፡፡ 50 ሺህ ዶላር የሚያወጣ የእንቁላል ጥብስ የለም፡፡ በእርግጥም በሕይወት ውስጥ የሚያስፈልገንን ነገር ለማሟላት የሚያስፈልገን ከፍተኛ የገንዘብ መጠን አይደለም፡፡ ምናልባትም ለዚህ ይሆናል ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ በማለት የመከረን፡- «ምግብና ልብስ ከኖረን ግን፥ እርሱ ይበቃናል።» (1 ጢሞ. 6፡8)፡፡

**ምድራዊ ጥቅምን ከሰማያዊ ኢንቨስትመንት በላይ ማድረግን እምቢ በሉ**

በማቴዎስ 6 ኢየሱስ በጭንቀት ላይ የምንጫማበትን ሌላ ምሪት እንዲህ በማለት ይሰጠናል፡- «ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ ነገር ግን... በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤» (ማቴ. 6፡ 19-20)፡፡ ምድራዊውን ጥቅም ከሰማያዊው ኢንቨስትመንት በላይ እንዳያደርጉት ሰዎችን አደፋፈረ፡፡

እናቴ ካደረገቻቸው ኢንቨስትመንቶች ሁሉ ምርጥ የሆነው ምንም እንኳን ቤተሰባችን ጥቂት ገንዘብ ብቻ የነበረን ቢሆንም ለልጆቿ ሁሉ ክርስቲያናዊ ትምህርት እንዲያገኙ ማድረጓ ነበር፡፡ እናቴ ዘላለማዊ በሆነው ነገር ላይ ነበር «ኢንቨስት» ያደረገችው፡፡

እናንተስ ከዘላለማዊ አላማ አንጻር ሃብታችሁን እንዴት እየተጠቀማችሁ ትገኛላችሁ? የዋጋ አሰጣጥ ቅደም ተከተላችን ምድራዊ ነገሮችን ሳይሆን ሰማያዊ ነገሮችን ከላይ ካላስቀመጠ በስተቀር ብዙ ጊዜ በጭንቀት ላይ ድል መቀዳጀት አንችልም፡፡ የሚከተሉት ከሰማያዊ ጉዳዮች ተራ የሚመደቡ ናቸው፡- ረሐብተኛውን መመገብ፣ የታረዙትን ማልበስ፣ ህሙማንን መጠየቅ፣ በችግር ውስጥ ያሉትን ማገልገል፣ እንግዶችን መቀበል (ማቴ. 25፡ 31-46)፡፡ ከምድራዊ ትርፎች ይልቅ ሰማያዊ ጉዳዮችን ቅድሚያ መስጠት ምርጥ የሆነ ኢንቨስትመንት ነው፡፡

**ከእንስሳት ተማሩ**

«ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ፤ አይዘሩም አያጭዱምም በጎተራም አይከቱም፥ የሰማዩ አባታችሁም ይመግባቸዋል፤ እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን?» አለ ኢየሱስ፡፡ (ማቴ. 6፡26)፡፡ ከጭንቀት ነጻ የሆነን ሕይወት መኖርን አስመልክቶ እንስሳት ብዙ የሚያስተምሩን ትምህርት አላቸው፡፡ እርግጥ እንደ ሰብአዊ ፍጡራን የመምረጥ ነጻነት

ያላቸው ፍጡራን አይደሉም፤ ነገር ግን ፈጣሪያቸውን ይታዘዛሉ፡፡

በእስራኤል ረሐብ ተንሰራፍቶ በነበረበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ለነብዩ ኤልያስ ወደ ኮራት ፈፋ ወንዝ እንዲሄድ ነገረው፤ ምክንያቱንም ሲገልጽ እንዲህ አለ፡- «ቊራዎችም በዚያ ይመግቡህ ዘንድ አዝዣለሁ» (1 ነገ. 17፡4)፡፡ እግዚአብሔር በአስቸጋሪ ጊዜ አገልጋዩን እንዲመግቡለት ያዘዘው ወፎችን ነበር፡፡ እንስሳቶች ምርጫ የላቸውም፤ እግዚአብሔርን መታዘዛቸው ግድ ነው፡፡

በጭንቀት ላይ መጫማት የሚፈልጉ ሁሉ ከእንስሳት ትምህርት ቢቀስሙ መልካምን ያደርጋሉ፡፡ እንስሳት እግዚአብሔርን የሚታዘዙት ከዚያ ውጪ ማድረግ የሚችሉት ነገር ስለሌላቸው ነው፡፡ ታዲያ በቅዱስ ቃሉ በተቀመጠው መሰረት በምርጫችን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ መቻላችን ደግሞ ምንኛ የበለጠ ነገር ነው! ከእንስሳት መማር ያስፈልገናል፡፡

**የጭንቀትን መሠረተ ቢስነት ተረዱ**

ጭንቀት በአብዛኛው መሠረተቢስ ነው፤ የተጨነቅኹባቸው ብዙ ነገሮች ፈጽሞ ያልተከሰቱ ነገሮች ናቸው፡፡ የጭንቀትን መሠረተ ቢስነት ጌታችን በምሳሌ ሲገልጸው፡- «ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው?» (ማቴ. 6፡27)፡፡

የሳምሶን ወላጆች ጭንቀት መሠረተቢስ መሆኑን ዘንግተው ነበር፡፡ ልጃቸው ፍልስጥማውያን ሴቶችን ልቡ ፈልጎ በመውጣቱ ተጨንቀው ነበር (መሳ. 14)፡፡ እስራኤላዊ ሴት ማግባት እንዳለበት አስታወሱት፤ ነገር ግን እርሱ በራሱ መንገድ ለመሄድ መረጠ፡፡ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር በፍልስጤማውያን ላይ ምክንያት ይፈልግ ነበርና ከሳምሶን ልብ መኮብለል በስተጀርባ እርሱ እንደነበረ አላስተዋሉም ነበርና መጨነቃቸውን ቀጠሉ (መሳ. 14፡4)፡፡ የሳምሶን ወላጆች የተጨነቁት እግዚአብሔር ለራሱ ክብር በሚጠቀምበት ነገር ነበርና፣ ጭንቀታቸው መሰረተ-ቢስ ነበር፡፡

**ትንንሽ ነገሮችን በተመለከተ በእግዚአብሔር ታመኑ**

በሕይወት ትንንሽ ነገሮችም ቢሆን በእግዚአብሔር በመታመን በጭንቀት ላይ እንድንጫማ ኢየሱስ ያደፋፍረናል፡፡ እግዚአብሔር ጋላክሲዎችን መቆጣጠር ከቻለ፣ ለምንድን ነው የእኛን ትንንሽ አሳሳቢ ነገሮች መቆጣጠር እንደማይችል አድርገን የምናስበው? ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡- «ስለ ልብስስ ስለ ምን ትጨነቃላችሁ? የሜዳ አበቦች እንዴት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ፤ አይደክሙም አይፈትሉምም፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ሰሎሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከነዚህ እንደ አንዱ አልለበሰም።» (ማቴ. 6፡ 28-29)፡፡

«የሰውነት አካል» የተሰኘ ኤግዚቢሽን ከጎበኘሁ በኋላ፣ እግዚአብሔር የሰብአዊ ፍጥረትን አካል እንዴት አድርጎ እንዳበጀው በጣም በመገረም አሰብኩ፡፡ በዚህ ኤግዚቢሽን የደም ዝውውር፣ የአተነፋፈስ ስርአት፣ የምግብ አፈጫጨትና የስነ ተዋልዶ ስርአቶች ለየብቻ ሲታዩ እጅግ አስገራሚ ነበሩ፡፡ ያንን አይቼ ስጨርስ፣ ውስጤ

ፈጣሪውን ለማምለክ ተነሳሳ፡፡ ከመዝሙረኛ ጋር እኔም ተስማምቼ «ግሩም ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁ» አልኩኝ (መዝ. 139፡ 14)፡፡

በጫካ ውስጥ እየተጓዝን ሳለ አንድ የቅርጫት ኳስ ብናገኝ፣ በዚያ ስፍራ ከእኛ ቀድሞ የተገኘ ሰው እንደነበረ አስባለሁ፡፡ የኳሱ መኖር ሰብአዊ ፍጡር በዚያ እንደነበረ ያሳያል፡፡ በተመሳሳዩም፣ በዙሪያችን ስለ እግዚአብሔር የሚመሰክሩ ነገሮች ሁሉ በሕይወት ትንንሽ ጉዳዮች እርሱን ለመታመን እንድንችል ያግዙናል፡፡ ለትንንሽ ነገሮች በእርሱ መታመኔ ጭንቀትን እንድቆጣጠረው ይረዳኛል፡፡

**እግዚአብሔር የሚያስፈልጋችሁን እንደሚያሟላላችሁ ተጠባበቁ**

ኢየሱስ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ነገር እንደሚያሟላልን ተስፋ ገብቶልናል(ማቴ. 6፡ 31-32)፡፡ ይህ ሃሳብ ደግሞ በፊል. 4፡19 ላይም ተደግሞ ተጠቅሶ እናነባለን፡- «አምላኬም እንደ ባለ ጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል።» የሚያስፈልገንን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚሞላልን የተሰጠንን የተስፋ ቃል በእምነት በመጨበጥ በጭንቀት ላይ መጫማት እንችላለን፡፡

ይህንን ማስተዋል ፍጹም ሰላምን ያቀዳጀናል፡፡ በሕይወቴ አንድ ነገር ሲጎድለኝ፣ ነገሩ ለጊዜው የሚያስፈልገኝ እንዳልሆነ ጌታ ያረጋግጥልኛል፡፡ ምክንያቱም ቢያስፈልገኝ ኖሮ፣ ያሟላልኝ ነበርና፡፡ አለመታደል ሆኖ ግን፣ በምንፈልገውና በሚያስፈልገን መካከል ያለውን ልዩነት በትክክሉ አናስተውለውም፡፡ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር መሰረታዊ የሆኑትን አስፈላጊ ነገሮች ሊያሟሟላልን ቃል ከገባልን ምን ያስጨንቀናል?

**ከሁሉ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈልጉ**

በጭንቀት ላይ በድል መጫማት እንዴት እንደምንችል ያስተማረውን ትምህርት ኢየሱስ የቋጨው ከሁሉ አስቀድመን የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈለግ እንዳለብን በመናገር ነበር፡፡ እንዲህ አለ፡- «ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።» (ማቴ. 6፡33)፡፡ ባጭሩ፣ መቅደም ያለባቸውን ነገሮች ማስቀደም ያስፈልጋል፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ የእግዚአብሔርን መንግስት መፈለግ ማለት የእርሱን ፈቃድ ግንባር ቀደም አላማችን ማድረግ ማለት ነው፡፡

ሙሴ ማስቀደም ያለበትን ያስቀደመ ሰው ነበር፡፡ ዕብ. 11፡ 25 ላይ እዲህ ይላል፡- «ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አስቦአልና » ይህ አስገራሚ የሆነ ምርጫ ነው፡፡ ሙሴ አሳዳጊ ቤተሰቦቹ ባቀዱለት መንገድ ተጉዞ ቢሆን ኖሮ፣ ምናልባት በሂደት ፈርኦን ይሆን ነበር፤ በግብጻውያንም እንደ አማልክት ይቆጠር ነበር፡፡ እርሱ ግን በተቃራኒው ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሃቀኛ ለመሆን በመምረጥ ብዙዎች የማይመርጡትን መንገድ መረጠ፡፡ የሚቀድመውን አስቀደመ፡፡

**የየእለቱን ኑሩ**

በመጨረሻ፣ የየዕለቱን ኑሩ፡፡ «ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ ክፋቱ

ይበቃዋል።» (ማቴ. 6፡34)፡፡ ኢየሱስ፣ «የሳምንቱን እንጀራ ስጠኝ» ብላችሁ ጸልዩ አላላንም፡፡ ይልቁንም የየዕለቱን በማሰብ መኖር አለብን፡፡ በቀጣዩ ቀን ስለሚመጣብን ነገር ልንጨነቅ አይገባም፡፡ ይህ በዘዳ. 33፡ 25 ላይ እንዲህ ቀርቦአል፡- «እንደ ዕድሜህ እንዲሁ ኃይልህ ይሆናል።» በኢራ ስታነፊል የተደረሰው «ስለ ነገው ምንም አላውቅም» የሚለው መዝሙር ይህንን ሃሳብ ግሩም አድርጎ አቅርቦል፡-

ስለ ነገው ምንም አላውቅ
በየቀኑ እኖራለሁ
ብርሃኑንም አልዋስም
ሰማዩ እንዳይጨልም
ስለመጪው አላስብም
የጌታን ቃል አውቃለሁ
ሆኖም እርሱ ከእኔ ጋር ነው
በደሙም ተሸፈንሁኝ
(Ira Stanphill, "I Know Who Holds Tomorrow" (New Spring, 1950).)

## በጭንቀት ላይ ለመጫማት የሚያግዟችሁ ወሳኝ እርምጃዎች

- በቁሳዊ ነገሮች አትጠፈሩ
- ምድራዊ ጥቅምን ከሰማያዊ ኢንቨስትመንት በላይ ማድረግን እምቢ በሉ
- ከእንስሳት ተማሩ
- የጭንቀትን መሠረተ ቢስነት ተረዱ
- ትንንሽ ነገሮችን በተመለከተ በእግዚአብሔር ታመኑ
- እግዚአብሔር የሚያስፈልጋችሁን እንደሚያሟላላችሁ ተጠባበቁ
- ከሁሉ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈልጉ
- የየዕለቱን ኑሩ

# 19

# ከስቃይ ሲሳይን አግኙ

ስልኩ ጮኸ፤ እኔም አነሳሁት፡፡ «የብላክ መኖሪያ ቤት» አልኩኝ፡፡

በመስመሩ ሌላ ጫፍ የሚሰማው ድምጽ እንዲህ አለ፡- «ታዲያስ ቤሪ፣ ሚካኤል ነኝ፤ አንድ ነገር ካንተ ፈልጌ ነው፡፡»

ከእኔ የፈለገውም ዘ ላስት ሌክቸር እንደተባለው የራንዲ ፓውሼ መጽሐፍ ያለን ነገር ለማዘጋጀት በማሰቡ፣ «የመጨረሻው ስብከት» የተባለን አንድ ስብከት እንዳዘጋጅለት ነበር፡፡ በካርኒጌ ሜሎን ዩንቨርስቲ የኮምፒውተር ሳይንስ ፕሮፌሰር የሆነው ፓውሼ ይህ ዝነኛ መጽሐፉ በሚያስተምርበት ትምህርት ቤት ለሚገኙ ተማሪዎች ልክ እንደሚሞት አስቦ የመጨረሻውን ትምህርት ለማስተማር እድል ቢያገኝ እንዴት እንደሚያስተምር በምናቡ በመሳል ያዘጋጀውን ትምህርት በማስፋፋት የተጻፈ ነበር፡፡ ለመሆኑ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ለተማሪዎቹ ምን ይላቸው ይሆን? ምን አይነት ምክር ለመስጠትስ ይመርጥ ይሆን?

ፓውሼ የመጨረሻ ትምህርቱን በሚያዘጋጅበት ጊዜ፣ የጣፊያ ካንሰር እንዳለበት በምርመራ ተገኘ፤ ይህም በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ለሞት እንደሚዳርገው ተነገረው፡፡ ለፈጠራ ያህል በምናብ ተስሎ የነበረው ልብወለድ ድንገት እውነት ሆኖ አረፈው፡፡ አሁን እንደ በፊቱ በምናቡ ብቻ ነገሩን በማሰብና በማስመሰል መሆኑ ቀረ፤ በእርግጥም አሁን ለሚቀጥለው ትውልድ ጥበብን አትሞ ለማለፍ የመጨረሻው እድሉ የሚሆንበት እውነታ ተከሰተ፡፡ ዩ ቲዩብ በተባለው ቴክኖሎጂ የተለቀቀው የእርሱ የመጨረሻ ትምህርት በብዙ ሚሊዮኖች የታየ ሲሆን፣ መጀመሪያ ከታቀደውም በላይ እጅግ ትልቅ ዋጋ ያለው ሆነ፡፡

አሁን ደግሞ ማይክል እኔም ተመሳሳዩን እንዳደርግ ነበር እየጠየቀኝ የነበረው፡፡ እኔም ከዚያ በኋላ እድሜ እንደሌለኝ፣ እንደምሞት፣ ያለኝ እድል አንድና የመጨረሻ ስብከት መስበክ እንደሆነ በማሰብ ስብከት እንዳዘጋጅ ነበር የጠየቀኝ፡፡

እየታሰበ ስላለው ስለዚህ መጽሐፍና ማይክል በታላቅ ጉጉት ይህንን መጽሐፍ ሊያዘጋጅ ስለ መፈለጉ ሳስብ፣ ራሴን እንዲህ አልኩት፡- «ለመሆኑ ኢየሱስ በመጨረሻው ስብከቱ ወይም ትምህርቱ የተናገረው ምን ይሆን? ይህንን ርዕስ ለማጥናት አሁን ጊዜው መጥቶአል»

መጽሐፍ ቅዱሴን አነሳሁና ወደ ዮሐንስ ወንጌል 16 ከፈትሁ፤ በዚህ ክፍል ላይ ኢየሱስ በላይኛው ክፍል ደቀ መዛሙርቱን በመሰናበት ያደረገውን ንግግር እናገኛለን፡፡ በዚህ በመጨረሻው ስብከቱ ጥሩም መጥፎም የሆኑትን የሕይወት ገጽታዎች ለተከታዮቹ በማሳየት ከእውነታ ጋር ያጋፈጣቸው ሲሆን፣ ይህንንም ያደረገበት ምክንያት ስለ እርሱ የሚቀበሉትን መከራና የሚደርስባቸውን ተቃውሞ በተሳካ ሁኔታ መጋጠም እንዲችሉን ሊያስታጥቃቸው አስቦ ነበር፡፡

ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፣ « አንድ መጥፎ ዜና አለኝ፤ ሰዎች ያሳድዷችኋል፣ ሊገሏችሁም ይፈልጋሉ፡፡ ይህንን በሚያደርጉበት ጊዜም ብዙዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርጉ ይመስላቸዋል፡፡ ደግሞም ከእናንተ ልለይና ወደ አባቴም ልሄድ ግድ እንደሆነ ጨምሬ ልነግራችሁ ይገባል፡፡

«መልካም ዜናም አለኝ፡፡ እኔ ከእናንተ ከተለየሁ በኋላ፣ ሌላ አጽናኝ እልክላችኋለሁ- መንፈስ ቅዱስን፡፡ እርሱም ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፡፡» ይህንን የመጨረሻውን ስብከቱን ሲደመድም፣ እንዲህ በማለት አወጀ፡- «በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።» (ዮሐ. 16፡ 33)፡፡

የመጮኽ ያህል ድምጼን ከፍ አድርጌ፡- «ይኼ ነው! የሕይወትን መከራዎችና ተቃውሞዎች በድፍረት መጋፈጥ የተሰኘውን ኢየሱስ በመጨረሻ ስብከቱ ላይ ያተኮረበትን ተመሳሳይ ርዕስ እኔም ሃሳባዊውን የመጨረሻውን ስብከቴን እሰብክበታለሁ» አልኩኝ፡፡

### ሁሉን የሚያዘጋጀውን መለኮታዊ አመራር ተማመኑበት

ዳንኤል 2 ሊያስታወሰው ያልቻለውን ግን እረፍት የነሳውን አንድን ሕልም ስላለመ ንጉሥ አስደናቂ ታሪክ ይነግረናል፡፡ ጠቢባን ሰዎቹን ሰበሰበና እንዲህ አላቸው፡- «ህልሜን ረስቼዋለሁና ንገሩኝ»፡፡

«ንጉሥ ሆይ፣ አንተ ህልሙን ብቻ ንገረን፣ እኛ ደግሞ ፍቺውን እንነግርሃለን» አሉት፡፡

በዚህ ጊዜ ጠቢባኑ እስካሁን ድረስ ስለ ችሎታቸው ሲያታልሉት እንደቆዩ ለንጉሡ ለማወቅ ብዙም የመጠቀ አስተሳሰብ ያለው ብሩህ አእምሮ ባለቤት መሆን አላስፈለገውም፡፡ «ጠቢባኑ ከእነ ቤተ ሰዎቻቸው ይገደላሉ» በማለት አወጀ፡፡

የሚያስደስተው ክፍል ግን፣ ዳንኤልና ጓደኞቹም ከእነዚሁ ከጠቢባን ጎራ ይመደቡ የነበረ ሲሆን እነርሱ ግን እንደሌሎቹ አጭበርባሪዎች አልነበሩም፡፡ «ትንሽ ጊዜ ስጡን፤ እኛም ንጉሡ ያለውንና ትርጓሜውን ይዘን እንቀርባለን» በማለት ዳንኤል ተናገረ፡፡

ንጉሡም ለዳንኤል የጠየቀውን ጊዜ ሰጠው፡፡ ብዙም ሳይቆይ ዳንኤል በንጉሡ ፊት ይህንን መገለጥ ይዞ ቆመ፡- «ንጉሥ ሆይ፣ በሕልም ያየኸው የአካል ክፍሎቹ ከተለያዩ

ንጥረ ነገሮች የተሰራን አንድ ምስል ነው፤ የምስሉ ራስ ከወርቅ፣ ደረቱ ከብር፣ ጭኖቹ ከነሐስ፣ እንዲሁም እግሮቹ ከብረት የተሰሩ ናቸው፡፡ የእግር ጣቶቹ ደግሞ የብረትና የሸክላ ቅልቅል ነበሩ፡፡» በማለት ነገረው፡፡

«ያየሁት ህልም በትክክልም ይኼ ነበር!» በማለት ንጉሡ ጮኸ፡፡

«ሌላም ነገር ጨምረህ አይተሃል» በማለት ዳንኤል ንግግሩን ቀጠለ፡፡ «አንድ ትንሽ ድንጋይ ከተራራ ተፈንቅሎ በመምጣት ያንን ምስል ሲፈጨው አየህ፤ ድንጋዩም መላው አለምን እስኪሞላ ድረስ ገዘፈ፡፡» ከዚያም ዳንኤል የህልሙን ፍቺ ማቅረብ ሲቀጥል፣ የምስሉ የወርቅ ራስ በባቢሎን ንጉሥ የሚመሰል ሲሆን በቀጣይነት ያሉት ደግሞ ቀጥሎ የሚነሱትን መንግስታት በቅደም ተከተል የሚያስቀምጥና እስከ ሰብአዊ ዘር ታሪክ መደምደሚያ ድረስ ያለውን የሚያሳይ መሆኑን ተነተነለት፡፡ በዚህ ሂደት ጡዘት ላይ ታዲያ፣ የሰማይ አምላክ ለሌላ ሕዝብ የማይሰጥ ዘላለማዊ መንግስት ይመሰርታል (ዳን. 2)፡፡

ከስቃይ ውስጥ ሲሳይ ለማግኘት ልክ ናቡከደነጾር እንዳስተዋለው የእግዚአብሔር ኃይል በምድር ነገስታትና በማናቸውም ሁኔታዎች ሁሉ ላይ እንደሚያይል ማመን ያስፈልጋል፡፡ እንዲህ ያለው መተማመን የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ማንም ሊከለክለው የማይችለውን እርዳታውን ከመታመን የሚመጣ ነው፤ ምክንያቱም የሰብአዊ ዘር ታሪክ በእርሱ ቁጥጥር ስር ነውና፡፡ እርሱ በአለማችን ላይ በሚከሰቱት የተለያዩ ክስተቶች በመገረም አይሞላም፤ «ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገርን ሁሉ ለበጎ» ያደርጋልና (ሮሜ. 8፡28)፡፡

በማር. 4 ላይ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በላያቸው አልፎ ሊያሰጥማቸው ከፈለገ ማዕበል ጋር ሲታገሉ፣ በጀልባቸው ውስጥ ግን ኢየሱስ ተኝቶ ነበር፡፡ ጥረታቸው ሁሉ መና ሲቀር፣ ወደ ጌታቸው ለእርዳታ ጮኹ፡፡ እርሱም ተነስቶ ወጀቡን እንዲህ አለው፡- «ዝም በል፤ ጸጥ በል!» (ማር. 4፡ 39)፡፡ ንፋሳቱና ወጀቡም ታዘዙለት፡፡ ወደ ደቀ መዛሙርቱም ዘወር ብሎ፣ እንግዳ የሚመስልን ጥያቄ ጠየቃቸው፡- «እንዲህ የምትፈሩት ስለምን ነው?»

እኔ በዚያ ብሆን እንዲህ እል ነበር፡- «እንዴ ጌታ ሆይ ምን ማለትህ ነው? የፈራንበትማ ብዙ ምክንያት አለን? ውሃው እኮ ሊውጠን ነበር፤ ሰውነታችንም በትግል ደክሞአል፡፡ ጀልባዋ በውሃ ሞልታለች፡፡» የኢየሱስ ጥያቄ ግን የእርሱ ኃይል በሁሉ ነገር ላይ እንደሚያይል ማመን ከእነርሱ እንደሚጠበቅ የሚያስታውሳቸው ነበር፤ በእርግጥም እርሱ ሁሉን ይችላል ማለት እንዲህ ብሎ ማመን ማለት ነው፡፡ አሰቃቂ የሆነን ሁኔታ እየተጋፈጥንም ቢሆን፣ ሆራሺዮ ስፓፈርድ በመርከብ አደጋ አራት ሴት ልጆቹን ካጣ በኋላ በጻፈው መዝሙሩ ላይ እንዳሰፈረው «ሰላም ነው በልቤ» ብለን መናገርን መማር አለብን፡፡

## ተቃውሞዎችን ችላ በሉ

ከሕይወት ስቃይ ውስጥ ሲሳይን ለማግኘት ስንፈልግ ዳዊት ተቃውሞዎችን እንዴት መጋፈጥ እንዳለብን የሚያስተምረንን ልብ ልንል ይገባል፡፡ በ 1 ሳሙ. 17 ላይ እንደተመዘገበው ወደ ጦር ግንባሩ ሲደርስ፣ ዳዊት ግዙፉ ጎልያድ እስራኤልን ሲያስፈራራና እግዚአብሔርን ሲሳደብ አደመጠ፡፡ ዳዊትም እንዲህ በማለት ጠየቀ፣ «በሕያው አምላክ ሠራዊት ላይ እንዲህ ድፍረት ቃል የሚናገር ይህ ያልተገረዘ ሸለፈታም ማን ነው?» ይህ ጥያቄው ግን ከዳዊት ወንድም ከኤልያብ ተቃውሞ እንዲሰነዘርበት አደረገው፡፡

«አንተ ደግሞ እዚህ ምን ታደርጋለህ?» በማለት ጠየቀው፡፡ «እነዚያንስ ጥቂቶች በጎች በምድረ በዳ ለማን ተውሃቸው? እኔ ኩራትህንና የልብህን ክፋት አውቃለሁና ሰልፉን ለማየት መጥተሃል » (1 ሳሙ. 17፡28)፡፡

ዳዊትም እንዲህ በማለት መለሰ፡- «እኔ ምን አደረግሁ?» ይሁን እንጂ፣ ከዚህ ያለፈ ነገር አላለም፤ የደረሰበትን ተቃውሞ ችላ ብሎ፣ በዚያ የጦር ሜዳ የእግዚአብሔርን ክብር ለመመለስ ጥረቱን ቀጠለ፡፡

በነህ. 4፡1-6 ላይ ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለመገንባት በፈለገ ጊዜ ከሰንበላጥና ከጦቢያ ተቃውሞ ገጥሞት ነበር፡፡ እነዚህ ጠላቶቹ ነህምያን ትኩረቱን ሊበትኑበትና ተስፋ ሊያስቆርጡት ፈልገው ነበር፤ እርሱ ግን ችላ ብሏቸው የመገንባት ሥራውን ቀጠለ፡፡ ፈጽሞ የማይቻል ይመስል የነበረውን ተግባር በአምሳ ሁለት ቀናት አጠናቀቀው፡፡ ከሕይወት ስቃይ ሲሳይ ለማግኘት፣ አንዳንድ ጊዜ ተቃውሞዎችን ችላ ማለት ይጠበቅባችሁ ይሆናል፡፡

ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት በቆመ ጊዜ፣ የእርሱን ተቃወሞ ችላ ብሎ ነበር፡፡ በጣም ጥቂት ቃላትን ብቻ ከአንደበቱ በማውጣቱ ጲላጦስ እንዲህ አለ፡- «አትነግረኝምን? ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን?»

ኢየሱስ እንዲህ በማለት መለሰ፣ «ከላይ ካልተሰጠህ በቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን ባልነበረህም» (ዮሐ. 19፡11)፡፡ ጌታችን ለጲላጦስ ብዙም ቃላት ያልተናገረው የሚያመጣለት ለውጥ ስላልነበረ ነው፡፡ አንድ ጊዜ እንዲህ ብሎ ተናግሮ ነበር፡- «በእግራቸው እንዳይረግጡት ተመልሰውም እንዳይነክሱአችሁ፥ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ፥ ዕንቁዎቻችሁንም በእሪያዎች ፊት አትጣሉ።» (ማቴ. 7፡6)፡፡ እናም እንዲህ ብሎ የሰበከውን አሁን በጲላጦስ ፊት ተገበረው፡፡ ፋይዳ ለሌለው ተቃውሞ የሰጠው ምላሽ በቻልታ ማለፍን ነበር፡፡

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተቃውሞዎችን ችላ ትላላችሁን? ተቃውሞን ፊት ለፊት መጋፈጥ የሚያስፈልጋችሁ ሲሆን በድፍረት አድርጉ፤ ነገር ግን ትኩረታችሁን ሊበትኑ የሚፈልጉትን ሰዎች በማባረር ክቡር ጊዜና ጉልበታችሁን አታባክኑ፡፡ ይልቁንም ማንም ጠላት ሊዘጋ የማይችለውን በር እግዚአብሔር ሲከፍትላችሁ በማየት ሁሉን ማድረግ

በሚችለው እጁ ላይ ትኩታችሁን አድርጉ፡፡

**ጹሙና ጸልዩ**

በማር 9 ላይ አባቱ ይዞት የመጣውን በአጋንንት ተይዞ የነበረን ልጅ ነጻ ለማውጣት የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ያልተሳካ ሙከራ አድርገው ነበር፡፡ ይህ ውድቀታቸውም ወደ ኢየሱስ የትችት ቃላትን አምጥቶ የነበረ ሲሆን የቀረበውም በአባትየው ነበር፡- «ይህንን በአጋንንት የተያዘ ልጅ ወደ ደቀ መዛሙርትህ አምጥተን ነበር፣ እነርሱ ግን ሊያወጡለት አልቻሉም፡፡»

ወዲያውም፣ ደቀ መዛሙርቱ ማከናወን የተሳናቸውን ኢየሱስ በማከናወን አጋንቱን አስወጣለት፡፡ ይህ ሁናቴም ደቀ መዛሙርቱን ወደ ኋላ ላይ ከጌታ ጋር ለብቻቸው ለመሆን እድሉን ሲያገኙ እንዲህ የሚል ጥያቄ እንዲያነሱ ቀሰቀሳቸው፡- «ጌታ ሆይ፣ እኛ ልናወጣው ያልቻልን ስለ ምንድር ነው?»

ኢየሱስም እንዲህ በማለት መለሰላቸው፡- «ይህ ወገን በጸሎትና በጦም ካልሆነ በምንም ሊወጣ አይችልም፡፡»

ተቃውሞን በድፍረት ለመጋፈጥ፣ ኃይለኛ ጥምረት የሚጥሩትን የጾምና የጸሎት መንፈሳዊ የጦር መሳሪያዎች ማንገብ ያስፈልጋል፡፡ መጾም የድርጊታችንን ጠሊቅነት የሚያሳይ እንደመሆኑ ለጸሎት መንፈሳችን ጉልበትን ይጨምራል፡፡ ጥልቅና ከልብ የሆነ ጸሎት ደግሞ ዋጋ አለው፡፡ ያዕ. 5፡ 16 እንዲህ ይላል፡- «የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።» ሙብላትን እስከማቆም ድረስ ከልባችን አንድን ነገር ከእግዚአብሔር በጽናት ስንፈልግ፣ ብዙ ጊዜ አስደናቂ የሆነ ኃይል ይለቀቅልናል፡፡

መካከለኛው ልጄ፣ ብሬንዳ እጅግ ተፈላጊ ወደ ሆኑ ብዙ ዩኒቨርስቲዎች ለመግባት የሚያስችለውን ነጻ የትምህርት እድል አግኝቶ ነበር፡፡ የሚሳዝነው ግን እርሱ አንዳቸውንም መቀላቀል አልፈለገም፡፡ «አባዬና እማዬ እኔ ወደ ዬል (የታወቀ ዩንቨርስቲ ስም ነው) ነው መሄድ የምፈልገው» አለ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ዬል ነጻ የትምህርት እድል አይሰጥም፤ እዚያ መማር የሚቻለው በገንዘብ ክፍያ ሲሆን ያንን ክፍያ አከናውኖ የልጃችንን ህልም ማሳካት ደግሞ ከእኔና ከባለቤቴ ከብሬንዳን አቅድም በላይ ነበር፡፡

«ልጄ፣ ዬል እኮ በአመት 43 ሺጎ ዶላር ነው የሚያስከፍሉት፡፡ እባክህን ነጻ የትምህርት እድል ካገኘኸባቸው ትምህርት ቤቶች አንዱን ምረጥና ባይሆን እኛ የህክምና ትምህርት ለመማር የሚያስፈልገውን እንሸፍንልህ» ብዬ ተሜንኩት፡፡

«አባዬ፣ ግን እኮ መግባት የምፈልገው ዬል ነው» በማለት አንሾካሾከ፡፡

«ከቀረቡልህ ነጻ የትምህርት እድሎች መካከል አንዱን ከመረጥህ፣ አዲስ መኪና እገዛልሃለሁ» በማለት ድርድር ማድረግ ፈለግሁ፡፡

«ግን አባዬ፣ ወደ ዬል ነው መሄድ የምፈልገው፡፡»

ከዚያም እኔና እናቱ ልጄ ወደ ዬል ለመግባት ጽኑ ጉጉት ከማሳየቱ የተነሳ ክፍያውን ለማከናወን የምንችልበትን አቅም ለማግኘት መጸለይ ጀመርን፡፡

በሉቃ. 11፡13 ላይ «እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?» የልጄ ልባዊ ጥያቄ እጄን ወደ ገንዘብ ቦርሳዬ ለማንቀሳቀስ ከቻለ፣ ወደ ሰማያዊ አባታችን የምናቀርበው ልባዊ የሆነ ጥያቄ ከሰፊው ባለጠግነቱ ምን ያህል የበለጠ ግሩም በረከቶችን ይዞልን ይመጣ?

## ቅዱስ ሕይወት ለመኖር ጣሩ

በሕይወት ለመኖር የቀራችሁ ጥቂት ቀናት ብቻ እንደሆኑ ብታውቁ እንዴት ትኖሩ ነበር? ንጉሥ ሕዝቅያስ ነብዩ ኢሳያስ እግዚአብሔር ያለውን እንዲህ በማለት ሲነግረው፡- «ትሞታለህ እንጂ በሕይወት አትኖርምና ቤትህን አስተካክል»(ኢሳ. 38፡1) እጅግ አዘነ፡፡ ታሞ የነበረው ንጉሥ መስማት ይፈልግ የነበረው እንዲህ አይነቱን ዜና አልነበረም፡፡

ነገር ግን ሕዝቅያስ ስለ ቅድስና ኃይል ያውቅ ነበር፡፡ ፊቱን ወደ ግድግዳው አዞረና፣ በጥልቅ ስሜት የተሞላውን የሚከተለውን ጸሎቱን አቀረበ፡- «አቤቱ፥ በፊትህ በእውነትና በፍጹም ልብ እንደ ሄድሁ ደስ የሚያሰኝህንም እንዳደረግሁ ታስብ ዘንድ እለምንሃለሁ» (ኢሳ. 38፡3)፡፡ ከዚያም እጅግ አምርሮ አለቀሰ፡፡

እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰማው፤ እንባውም ተመለከተ፡፡ ነብዩ ኢሳያስ ቤተመንግስቱን ለቆ ከመመለሱም በፊት፣ እግዚአብሔር እንዲህ የሚልን ቃል ላከለት፡- «የአባትህ የዳዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ጸሎትህን ሰምቻለሁ፥ እንባህንም አይቻለሁ እነሆ፥ በዕድሜህ ላይ አሥራ አምስት ዓመት አጨምራለሁ።»

ተቃውሞን በድፍረት ለመጋፈጥ፣ ቅዱስ የሆነን ሕይወት ለመኖር መትጋት አለብን፡፡ ሕዝቅያስ በጸሎቱ ከእግዚአብሔር ጋር ለመከራከር ያቀረበው እርሱን ደስ ለማሰኘት ያደረገውን ጥረት ሲሆን በመዝ. 5፡12 ላይ የተጻፈውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነበር፡- «አንተ ጻድቁን ትባርከዋለህና አቤቱ፥ እንደ ጋሻ በሞገስ ከለልኸን።»

ይህ ማለት የምንጸድቀው በስራችን ነው ለማለት አይደለም፡፡ ነገር ግን ከልጆቻችን ታዛዦቹ ከአመጸኞቹ ይልቅ ብዙ መልካም ነገሮችን እንደሚቀበሉ፣ የቅድስና ኑሮን መጠማጠም እግዚአብሔር ያዘጋጀልንን በረከት ለመውረስ እንድንችል ያደርገናል፡፡ በመዝ. 84፡11 ላይ እንደተቀመጠው ይሆናል፡- «እግዚአብሔር በቅንነት የሚሄዱትን ከመልካም ነገር አያሳጣቸውም።»

## የድርጊት ሰዎች ሁኑ

በአስራዎቹ እድሜ ውስጥ ሳለሁ፣ በደረሰብኝ የመውደቅ አደጋ ጥርሴ ተሸረፈ፡፡ የቤተሰቤ

የኢኮኖሚ አቅም ወደ ጥርስ ሃኪም ጋር በመሄድ ጉዳቱን ለማስተካከል እንድችል ስለማይፈቅድልኝ ኑሮን በተሸረፈ ጥርስ መኖር ቀጠልኩ፡፡ የሁለተኛ ደረጃና የኮሌጅ ትምህርቴን እስከጨርስ ድረስ የተሸረፈውን ጥርሴን ነበር ለፈገግታ ብልጭ የማደርገው፡፡ በመጨረሻ፣ በኖርዝ ካሮላይና ውስጥ የቤተክርስቲያን ፓስተር ሆኜ ስሰራ፣ የቤተክርስቲያኑን አገልግሎት ጨርሰን ስንወጣ አንዱ አባል ያናግረኝ ጀመር፡፡ «ፓስተር፣ የተሸረፈውን ጥርስህን ማስተካከል እንደሚቻል ታውቃለህ፡፡ እኔ ደግሞ የጥርስ ሃኪም ነኝ፡፡ ወደ ቢሮዬ ብትመጣ ያለ ምንም ክፍያ አስተካክልልሃለሁ፡፡» እኔም የተባለውን አደረግኹሁኝና ብዙም ሳይቆይ ምንም ሳልሸማቀቅ በፈገግታ ጥርሶቼን ማብለጭለጭ ጀመርኩ፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ፣ ለብቻዬ ስቀመጥ፣ ስለ ጥርሴ አንድ ነገር ለማድረግ ለምን ይኼንን ያህል ጊዜ እንደወሰደብኝ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ የማስተካከሉ ስራ የፈጀው በጣም ጥቂት ደቂቃዎችን ብቻ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን ቀላልና ብዙም ውድ ያልሆነ ውጫዊ ገጽታዬን የማስተካከል እርምጃ ከመውሰዴ በፊት የቤተክርስቲያኔ አባል እኔን እስኪያነቃኝ ቆይቼ ነበር፡፡ በተለይ ተቃውሞን በምንጋፈጥበት ጊዜ የድርጊት ሰው ሆኖ አለመገኘት አደጋ አለው፡፡ በሕይወት ጎዳና የሚገጥሙንን ተቃውሞዎች በቆራጥነት ለመጋፈጥ ከፈለግን የድርጊት ሰዎች መሆን ያስፈልገናል፡፡

**አጋር ፈልጉ**

በሕይወት ውስጥ የሚገጥማችሁን ተቃውሞ ብቻችሁን ለመጋፈጥ አትሞክሩ፤ ይልቁንም አጋር ፈልጉ፡፡ ከውኃ ጥፋት በኋላ ኖህና ልጆቹ በዘሮቻቸው ምድርን ሲሞሏት ሳለ ሰናዖር ምድር የሚኖሩ ሰዎች ቀጥሎ ለሚመጣ የውሃ ጥፋት አደጋ ለመዘጋጀት አስበው ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ መስራት ጀመሩ (ዘፍ. 11፡1-4)፡፡ ሰማይ ጠቀስ የሆነውን ይህንን ግንብ ለመስራትም ህዝቡ አንድ ሆኑ፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡- «ኑ፥ እንውረድ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው።» (ዘፍ. 11፡ 7)፡፡ እግዚአብሔርም ቋንቋቸውን በመለዋወጥ እንዲምታታባቸው አደረገ፡፡

ለክፋት የተሰበሰበ ሰብአዊ ፍጥረት የማይቻል የሚመስልን ነገር ማድረግ ከቻለ፣ ለመልካምም የተሰበሰቡ ሰዎች ተመሳሳዩን የማከናወን ጉልበት ማግኘት ይችላሉ፡፡ ለዚህ ነው ተቃውሞን እየተጋፈጡ ያሉ ሰዎች አጋር መፈለግ ያለባቸው፡፡ መክ. 4፡12 ደግሞ እንደዚህ ይላል፡- «አንዱም አንዱን ቢያሸንፍ ሁለቱ በፊቱ ይቆማሉ በሦስትም የተገመደ ገመድ ፈጥኖ አይበጠስም።»

ይህ እንዴት እውነት ሊሆን ይችላል? አንዱ አንድ ሺህ ማባረር የሚችል ከሆነ፣ ሁለቱ ደግሞ ሁለት ሺኅ ማባረር አለባቸው፡፡ ይሁን እንጂ ወደ እግዚአብሔር ሂሳብ ስንመጣ የተለየን ስሌት ነው የምናገኘው፡፡ መልካም ሰዎች ህብረት ሲያደርጉ ህብረታቸው የሚፈጥረው ጉልበት እያንዳንዳቸው ከሚያመነጩት ድምር ውጤት በላይ ነው፡፡

ይህንን በዳዊትና በዮናታን ታሪክ ውስጥ መመልከት እንችላለን፡፡ የእስራኤል መንግስት አልጋ ወራሽ የነበረው ዮናታን የዳዊትን ሕይወት ከሞት ለመታደግ የእርዳታ

እጁን ዘረጋ (1 ሳሙ. 20)፡፡ የዮናታን አባት፣ ንጉስ ሳኦል፣ ዳዊትን ሊገለው ፈልጎ የነበረው የስልጣኑ ተቀናቃኝ እንደሆነ በማሰቡ ምክንያት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ዮናታን የአባቱን የግድያ ሴራዎች ለዳዊት በመንገር ህይወቱን እንዲያድን ያስጠነቀቀው ነበር፡፡ ምንም እንኳን ለዮናታን ይህንን ማድረግ በአባቱ እግር ተተክቶ ወደ ዙፋኑ ላይ እንዳይወጣ የሚያደርገውም ቢሆን እርሱ ግን ያደርገው ነበር፡፡ ዳዊት የንጉሡን ተቃውሞ በሚጋፈጥበት ጊዜ በንጉሱ ልጅ ዘንድ አጋር ማግኘቱ፣ ምን ያህል ትግሉን እንደለወጠው አስቡ! እናንተም አጋር ፈልጉ፤ ያን ጊዜ በሕይወት ወስጥ የሚገጥማችሁን ተቃውሞ ለየት ባለ መልኩ ለመጋፈጥ ትችላላችሁ፡፡

**በውሳኔ የሚጸና አእምሮን አጎልብቱ**

በየአዲስ አመት መጀመሪያ ላይ ብዙ ሰዎች ወሳኔዎችን በመወሰን ቃል የሚገቡም ቢሆን፣ ያንን ወሳኔያቸውን የሚተገብሩበት አቅም እንደሚያንሳቸው የሚያስተውሉት ብዙም ሳይቆይ ነው፡፡ ግባቸውን ለመምታት የሚያስችል ከውስጥ የሚፈነቅል ጉጉቱ የላቸውም፡፡

በአስቴር 4 ላይ የፋርስና የሜዶን ንግስት በሕዝቦቿ ላይ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ሊከናወን እንደሆነ አስተዋለች፡፡ አጎቷ መርዶክዮስ ጥንስሱን ሁሉ ነገራትና አንድ ነገር ማድረግ እንደሚጠበቅባት አስጠነቀቃት፡፡ አስቴርም እንዲህ አለች፡- «ሄደህ በሱሳ ያሉትን አይሁድ ሁሉ ሰብስብ፥ ለእኔም ጹሙ ሦስት ቀን ሌሊቱንና ቀኑን አትብሉም፥ አትጠጡም እኔና ደንገጥሮቼ ደግሞ እንዲሁ እንጾማለን ምንም እንኳ ያለ ሕግ ቢሆን ወደ ንጉሡ እገባለሁ ብጠፋም እጠፋለሁ።» (አስቴር 4፡16)፡፡

የሚደንቅ ነው! «ብጠፋም፣ እጠፋለሁ፡፡» እንግዲህ በውሳኔው የሚጸና አእምሮ ማለት ይኼ ነው፡፡ ይህም ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር ሲናገር ከተናገረው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ «እነሆ፥ ቢገድለኝ ስንኳ እርሱን በትዕግሥት እጠባበቃለሁ» (ኢዮ 13፡15)፡፡

ኢየሱስ በመሰናበቻ ንግግሩ ላይ በዚህ አለም ውስጥ ሲኖሩ ተቃውሞና መከራ እንደሚደርስባቸው አስጠነቀቃቸው (ዮሐ. 16፡33)፡፡ እኔና እናንተም እምነታችንን በእግዚአብሔር ላይ በማድረግ የሚደርሱብንን ተቃውሞዎች በድፍረት መጋጠም እንችላለን፡፡

**ከስቃይ ሲሳይን ለማግኘት የሚያግዟችሁ ወሳኝ እርምጃዎች**

- ሁሉን የሚያዘጋጀውን መለኮታዊ አመራር ተማመኑበት
- ተቃውሞዎችን ችላ በሉ
- ጹሙና ጸልዩ
- ቅዱስ ሕይወት ለመኖር ጣሩ
- የድርጊት ሰዎች ሁኑ
- አጋር ፈልጉ
- በውሳኔ የሚጸና አእምሮን አጎልብቱ

# 20

# በፈተናው ጽኑ

ከእግዚአብሔር የተቀበላችኋቸው መልካም ስጦታዎች ምን ምን ናቸው? በያዕ. 1፡17 ላይ፣ የመልካም ስጦታዎች ሁሉ ምንጭ ማን እንደሆነ ማስታወሻ ተቀምጦልናል፡- «በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥» ይህ እውነት ነው፡፡ በሕይወታችሁ ውስጥ የሚገኝ መልካም ነገር ሁሉ የመጣው ከአንድ ምንጭ ነው፣ ከእግዚአብሔር፡፡ እግዚአብሔር እንዴት እንደባረካችሁ ደጋግማችሁ ራችሁን ማስታወሱ ጠቃሚ ነው፡፡ እርሱ በየማለዳው ያነቃችኋል፤ ለቀኑ የሚበቃችሁን የልብ ምት ያበድራችኋል፡፡ የምትተነፍሱትን አየር ይሰጣችኋል፤ በሕይወት ለመቆየት የሚያስፍልጋችሁን ምግብና መጠጥ፣ መንፈሳችሁን የሚኮተኩቱ ወዳጆችንም ጭምር ይሰጣችኋል፡፡ እግዚአብሔርን ስለ ባርኮቱ ማመስገንን ልማዳችሁ አድርጉት፡፡

**የአመስጋኝነትን አመለካከት አዳብሩ**

የአመስጋኝነት አመለካከትን ማዳበር የሕይወትን ፈተና በጽናት ለመቋቋምና የኢየሱስንም የአመስጋኝነት ምሳሌነት ለመከተል ጥንካሬን ይሰጣችኋል፡፡ ኢየሱስ ሕይወቱን በአመስጋኝነት ሞልቶት ነበር፡፡ አምስት ሺዎችን ከመመገቡ ወይም አላዛርን ከሞት ከማስነሳቱ ወይም የፋሲካን ራት ከበላበት ከላይኛው ክፍል ወጥቶ ወደ ቀራንዮ ከማምራቱ በፊት ለአባቱ ምስጋና ይሰጥ ነበር፡፡ (ዮሐ. 6፣ 11፣ ማቴ. 26)፡፡ ኢየሱስ ወደ ቀራኒዮ ሲያመራ ለእግዚአብሔር የምስጋናን መዝሙር መዘመር ከቻለ፣ እኛ ደግሞ በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ ብንሆን ጌታን ለመባረክና የእርሱንም ምስጋና ያለማቋረጥ በከንፈራችን ለማቅረብ የማንችልበት ምንም ምክንያት አይኖረንም፡፡ (መዝ. 34፡1)፡፡

የአመስጋኝነትን አመለካከት ማዳበር ማለት አስቸጋሪ ነገሮችን በምንጋፈጥበትም ጊዜ ቢሆን እግዚአብሔርን ለማመስገን ዝግጁ መሆን ማለት ነው፡፡ ይህንን እንዴት ማድረግ እንደሚቻል ዳንኤል እንደ ምሳሌ ያገለግለናል፡፡ ዳንኤል ንጉሡ በሞኝነት የረቀቀ አዋጅ ላይ እንዲፈርም በተጭበረበረ ጊዜ፣ አዋጁን ባለማክበሩ ምክንያት የሞት አደጋ ወድቆበት ነበር፡፡ «ዳንኤልም ጽሕፈቱ እንደ ተጻፈ ባወቀ ጊዜ ወደ ቤቱ ገባ የእልፍኙም መስኮቶች ወደ ኢየሩሳሌም አንጻር ተከፍተው ነበር ቀድሞም ያደርግ እንደ ነበረ በየዕለቱ ሦስት ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ በአምላኩ ፊት ጸለየ አመሰገነም።» (ዳን. 6፡10)፡፡

ይህ እጅግ አስገራሚ ነገር ነው፡፡ ዳንኤል መጸለይ በአዋጅ በተከለከለ ጊዜ በምስጋና ተሞልቶ ጸለየ፡፡ መጸለይ በተራቡ አንበሶች መንጋጋ ተገነጣጥሎ ለመሞት የሚያበቃም እንኳን ቢሆን እርሱ ግን ከመጸለይ ወደ ኋላ አላለም፡፡ ዳንኤል በምስጋና በመኖር

እንዴት በሕይወት መከራ ውስጥ በጽናት ማለፍ እንደሚቻል ያሳየን በዚህ መልኩ ነበር፡፡

እግዚአብሔር እርሱ በሚከፍተው በር ለማለፍ ዝግጁ ይሆኑ ዘንድ ልጆቹን የሚያስታጥቅበት መንገድ አስገራሚ አይደለምን? አመስጋኝነትን በእኛ ውስጥ እንዲፈልቅ የሚያደርግ አንደኛው ምክንያት ይኼ ነው፡፡ በዘመናት ሁሉ፣ በመንገዳቸው የሚመጡትን ምቹ አጋጣሚዎች መጠቀም እንዲችሉ የሚያስችላቸውን ችሎታ እግዚአብሔር ለልጆቹ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ ዮሴፍና ዳንኤል ህልም መፍታት ይችሉ ነበር፡፡ አስቴር የቁንጅና ስጦታ ነበራት፡፡ ሳምሶን ደግሞ እጅግ የተለየ ጥንካሬ ተሰጥቶት ነበር፡፡ ዳዊት የጦረኝነትና የሙዚቀኝነት ክህሎት ተሰጥቶት የነበረ ሲሆን፣ ልጁ ሰለሞን ደግሞ የጥበብ ተሰጥኦ ነበረው፡፡

ከእኛ ዘመን በፊት የነበሩትን ሰዎች ይባርክ የነበረው እግዚአብሔር ዛሬም በመባረክ ስራ ላይ ነው፡፡ በአለማችን ላይ በጎ ተጽእኖ ለማምጣት የሚያስችለንን ችሎታ በመስጠት ዛሬም ይባርከናል፡፡

ምን ያህል እግዚአብሔርን ታመሰግናላችሁ? ህይወታችሁ በስቃይ ሲሞላ፣ በዚያም ውስጥ ቢሆን ለእግዚአብሔር ምስጋናን ትሰጣላችሁ? የዳንኤልንና የኢየሱስን ምሳሌ ከተከተላችሁ፣ ያላችሁበት ሁኔታ ምንም ቢሆን ምን ለእግዚአብሔር ምስጋናችሁን ታቀርባላችሁ፡፡

**ብድራታችሁን ተመልከቱ**

በሕይወት ፈተና ውስጥ ስታልፉ፣ በዚያ ውስጥ በጽናት መሻገር የሚያስከፍለውን ዋጋ መክፈል ምን ያህል ተገቢ እንደሆነ አስባችሁ ታውቃላችሁ? ደግሞስ፣ በዚያ ውስጥ ማለፉ ምን ጥቅም ያመጣላችኋል? ለታማኝነታችሁ እግዚአብሔር የሚሰጣችሁን ሽልማት ስታስቡ፣ የሕይወትን መከራዎች ታግሳችሁ በጽናት ለመሻገር ቀላል ይሆንላችኋል፡፡ ያዕቆብ የሚያደፋፍረን በዚህ መልኩ ነው፡- «በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና።» (ያዕ. 1፡12)

ይህ ግሩም የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚሰጠንን ሽልማት በጉጉት እንድንጠባበቀው እንደሚፈልግ ያሳየናል፡፡ አንድ ጊዜ ጴጥሮስ ለኢየሱስ እንዲህ ብሎ ነበር፡- «እነሆ፥ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ፤ እንኪያስ ምን እናገኝ ይሆን?» (ማቴ. 19፡27)፡፡ ኢየሱስም ጴጥሮስ በሚቀበለው ሽልማት ላይ ትኩረቱን በማድረጉ አልኮነነውም፡፡ መስዋዕትነት ከመክፈላችን የተነሳ ሽልማት መጠባበቅ ኢመንፈሳዊነት ነው የሚል አስተያየትም አልሰጠም፡፡ ኢየሱስ ምን ነበር ያለው? ጴጥሮስን እንዲህ ነበር ያለው፡- «ስለ ስሜም ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል።» (ማቴ. 19፡ 29)፡፡ ኢየሱስ ከፊት ለፊታችን የሚጠብቀን ሽልማት በማስታወስ ሊያበረታታን ይፈልጋል፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ የሰማዕትነት ሞቱን የተጋፈጠው ሽልማት ከፊት ለፊቱ እንደሚጠብቅ በማሰብ ነበር፡፡ ለመንፈሳዊ ልጁና ተማሪው ለጢሞቲዎስ ሲጽፍ፣ እንዲህ አለ፣ «መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፤ ሩጫዬን ጨርሻለሁ፤ ሃማኖትን ጠብቄአለሁ» (2ጢሞ. 4፡7)፡፡ ነገር ግን ጳውሎስ ሲቀጥል፦ «ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።» (2 ጢሞ. 4፡8) ይላል፡፡ በሽልማቶቹ እንድንበረታታ ባይፈልግ ኖሮ እግዚአብሔር ስለሰማይ እንዲህ ብዙ የሚናገር ይመስላችኋል? እርሱ ለልጆቹ መልካም ስጦታን መስጠት የሚፈልግና በዚያም እስከመጨረሻው እንዲጸኑ ሊያበረታታቸው ይፈልጋል፡፡ በገላ. 6፡9 ላይ በጳውሎስ በኩል እንደሚያስታውሰን፣ ምንም እንኳን ሥራው አድካሚም ቢሆን ለእርሱ መንግስት መልካም ከመስራት ለማይታክቱ ሁሉ የሚሰበስቡት መከር አለ፡፡ ሽልማታችሁን በተስፋ ስትጠባበቁ፣ ዘላለማዊ ሕይወት በሽልማታችሁ ውስጥ እንደተካተተም አስታውሱ፡፡ (ዮሐ. 3፡16)

**እግዚአብሔርን ተወቃሽ አታድርጉት**

በምንፈተንበት ጊዜ፣ ማንን ነው ተወቃሽ የምናደርገው? እግዚአብሔርን ተወቃሽ አታድርጉት! «የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት» (ያዕ. 1፡ 13)፡፡ እግዚአብሔር የፈተናችሁ ምንጭ አይደለም፡፡ የእርሱ እቅድ ለእናንተ ተስፋና ብሩህ መጻኢ ሕይወት እንዲኖራችሁ፣ ወደ አስደሳች ፍጻሜም ማድረስ ነው (ኤር. 29፡11-13)፡፡

ታዲያ የፈተናችሁ ሥር ምንድን ነው? ያዕ. 1፡ 14 መልሱን ይሰጠናል፦ «ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል።»፡፡ ሥሩ የእኛው ክፉ ምኞቶች ናቸው፡፡ አያችሁ በኃጢአት ተጸንሰን፣ በአመጻ የተወለድን ነን (መዝ. 51፡5)፤ የሚያሳዝነው የወረስነው ውርስ ወደ ኃጢአት ያጋደለ ሕይወት ነው፡፡ በፈተና ውስጥ ሲወድቅ የሚጋይ ተቀጣጣይ ክፍል በልባችን ውስጥ አለ፡፡ የእኔ ተቀጣጣይ ክፍል ከእናንተ ሊለይ ይችላል፤ ምክንያቱም ቶሎ የሚከበን ኃጢአት የሚለያይ ነውና (ዕብ. 12፡1)፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሁላችንም ህጉን ወደ መተላለፍ እንድናመራ የሚጎትተን ኃጢአተኛ ተፈጥሮ አለን፡፡ እንዲህ ያለውን ሕይወት ይዘን ተወልደናልና ዳግም መወለድ ያስፈልገናል (ዮሐ. 3)፡፡

ይህን አዲስ ልደት መለማመድ ማለት ደግሞ ምንም አይነት ፈተና ከዚያ በኋላ አይገጥመንም ማለት አይደለም፡፡ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ፣ ወደ ኃጢአት በሚመሩ ፍላጎቶች መጎተታችን አይቀሬ ነው፡፡ እንዲህ ያለው ፈተና ወደ እኛ ከሚመጣባቸው ብዙ መንገዶች መካከል አንደኛው ሃብት ለማግኘት ከሚኖረን ፍላጎት የሚመነጭ ነው፦ «ዳሩ ግን ባለ ጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ።» (1 ጢሞ. 6፡9)፡፡ አንዳንድ ሰዎች ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ- ከቤተሰቦቻቸው በመስረቅ፣ ስጋቸውን በመሸጥ (በግልሙትና)፣ እንደዚሁም ከእግዚአብሔር በመዝረፍ (ሚል. 3፡8) ሳይቀር ምን እንደሚያደርጉ ሁላችንም ሰምተናል፡፡ ብዙ ሃብት ለማጋበስ በሚያደርጉት ጥረት ለብዙ ፈተናዎች ራሳቸውን አጋልጠው ይሰጣሉ፡፡

እስቲ አስቡት፡፡ ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ከሰጠባቸው ምክንያቶች መካከል አንደኛው ገንዘብ ነበር፡፡ ለሰላሳ ብር ሲል ጌታውን ለጠላት አሳልፎ ሰጠ (ማቴ. 26፡ 15)፡፡ ይህ ደግሞ ቀላል ገንዘብ አይደለም፤ ለአንድ የቀን ሠራተኛ ከአራት ወራት የደሞዝ መጠኑ የሚበልጥ ወይም መሬት ለመግዛት የሚያስችል ነበር፡፡ ደግሞም ለሰጡት ሰዎች ሊመልሰው ሙከራ ባደረገው በዚያ የይሁዳ የደም ገንዘብ የተደረገው መሬት መግዛት ነበር (ማቴ. 27፡ 3-10)፡፡

የሚፈትነን ነገር ገንዘብ ብቻ አይደለም፡፡ በአራት የተለያዩ የመሬት አይነቶች ላይ ዘሩን በበተነው የዘሪው ምሳሌ ላይ፣ አንደኛው መሬት እሾሃማ የነበረ ሲሆን ዘሩ ባደገ ጊዜ በእሾሆች እንደታነቀ እናነባለን፡፡ ኢየሱስም እነዚህ እሾሆዎች ምን እንደሆኑ ለደቀመዛሙርቱ ሲያስረዳ «በእሾህ መካከል የተዘራውም ይህ ቃሉን የሚሰማ ነው፥ የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል፥ የማያፈራም ይሆናል።» (ማቴ. 13፡22) ነበር ያላቸው፡፡ እናም ከሚፈትኑን ዝርዝር ላይ ጭንቀትን ልንጨምር እንችላለን፡፡

ለሃያ ሰባት አመታት በዘለቀ የሚሊተሪ ቤት ቆይታዬ፣ በስራዬ ለማደግ፣ ልጨነቅ ከሚገባኝ በላይ በመጨነቅ ጊዜ አጥፍቻለሁ፡፡ በአብዛኛዎቹ የስራ ቀናት ወደላይ ላድግ ስለምችልባቸው ወደፊት ሊያጋጥሙኝ ስለሚችሉ ነገሮች ለማሰብ የሚቀሰቅሰኝ ነገር አላጣም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ስለራሴ በተጨነቅሁባቸው ነገሮች ከመቶው ዘጠናው እጅ እንኳን ፈጽሞ ባልተከናወነበት እጅግ የከበሩ ጊዜዎቼንና ጉልበቴን አባከንሁ፡፡ ጭንቀቶቻችሁ አላስፈላጊ በሆነ ፈተና ውስጥ እንዲጨምሯችሁ አትፍቀዱላቸው፡፡

**የኃጢአትን ደሞዝ አስታውሱ**

የሕይወትን ፈታናዎች በጽናት ለመሻገር፣ ያለማቋረጥ ለኃጢአት እጅ መስጠት የሚያስከትለውን ውጤት ማስታወስ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ያዕ. 1፡15 የኃጢአት የመጨረሻው ግቡ ምን እንደሆነ ያስታውሰናል፡- «ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።» ኃጢአት ማድረግ ስንቀጥል፣ በሂደት የምናመራው ወደ ሞት ነው፡፡

ይህ ወሳኝ የሆነ መረዳት ነው፡፡ ምን ጊዜም ቢሆን ፈተና ሲገጥማችሁ፣ የመጨረሻ ግቡ- ሞት መሆኑን አስተውሱ፡፡ ልክ እንደ ቼዝ ጨዋታ ሲሆን የእያንዳንዱ ተጫዋች ፍላጎት የባላጋራውን ንጉስ ማጥመድ ነው፡፡ ዲያቢሎስም እንደዚያው ሊያጠምደን ይፈልጋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን ጠላት የሚገልጸው፡- «የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ» (1 ጴጥ. 5፡8) ነው፡፡ የኃጢአትን የመጨረሻ መዳረሻ ማስወገድ የሚፈልጉ ሁሉ ዛሬ ፈተናውን በጽናት ማለፍ ያስፈልጋቸዋል፡፡

የኃጢአትን የመጨረሻ ውጤት በአእምሮችን በመያዝ፣ በኃጢአተኞች መቅናት ምንኛ ሞኝነት እንደሆነ ልንመለከት እንችላለን (ምሳ. 23፡17)፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ተቆርጠው ይጠፋሉ (መዝ. 37፡ 2) እንደዚሁም ይወገዳሉ ይለናል (ኢሳ. 1፡28)፡፡ በጣም በፈጣን

የእድገት አቅጣጫ ሲጓዝ የነበረ ሰው ባልተጠበቀ ጊዜ በሞት ሲቀጭ ስንት ጊዜ ነው የተመለከትነው? ኮከብ የተባሉ አትሌቶች በክለብ ውስጥ ሲዝናኑ መሳሪያ ተተኩሶባቸው ሲሞቱ ወይም ጠጥተው ሲነዱ በመኪና አደጋ ሲያልቁ ዜናውን እናነባለን፡፡ ምንም እንኳን ደስታን የሚያመጣ ቢመስልም፣ ኃጢአት ግን ጠላት ነው እንጂ ወዳጅ አይደለም፡፡ ይህንን ማስተዋል ታዲያ በሕይወት ውስጥ የሚያጋጥመንን ፈተና በጽናት ለመሻገር ይረዳናል፡፡ መጽሐፍ እንደሚለው «መልካም እውቀት ሞገስን ይሰጣል የወስላቶች መንገድ ግን ሸካራ ናት።» (ምሳ. 13፡15)፡፡

አንዳንድ ጊዜ በፍጥነት ህይወታቸው እየተተኮሰ የሚመስሉ ሰዎችን ሕይወት ለመኖር ተመኝታችሁ ታውቁ ይሆን? እነዚህን ምኞቶች ብዙ አትቆዩባቸው፡፡ ይልቁንም፣ እግዚአብሔር በሕይወታችን ያስቀመጣቸው ማዕቀቦች እኛን ከጉዳት ለመጠበቅና በእውነተኛ መትረፍረፍ መኖር እንድንችል ለማገዝ እንደሆነ አስታውሱ፡፡ እርሱ እኛን በሚያበጅበት ሂደት ታመኑትና በፈተና ጽኑ፡፡

**በመከራ ውስጥ የሚያልፉትን እርዱ**

እናንተ በፈተናችሁ ከጸናችሁ በኋላ ሌሎች የሚገጥማቸውን ግድድሮሽ ለመጋፈጥ እንዲችሉ ለመርዳት ተዘጋጁ፡፡ ይህንን ልታደርጉ የምትችሉበት አንዱና ትልቁ መንገድ ለእናንተ የሆነውን መልካም ዜና ማካፈል ነው፡፡ በፈተና ውስጥ እያለፈ ላለ ሰው ልታደርጉለት የምትችሉት ትልቅ ነገር ቢኖር እግዚአብሔር እናንተን በፈተናችሁ እንድትጸኑ እንዴት እንደረዳችሁ መንገር ነው፡፡

የንዕማን አገልጋይ፣ ያቺ ትንሽ ልጃገረድ ያደረገችው እንዲህ አልነበረምን? የጦርነት ምርኮኛ ሆና በሶርያ የጦር ጄነራል ቤት ውስጥ እያገለገለች ነበር (2 ነገ. 5)፡፡ ነገር ግን የደረሰባትን መከራ ተቀብላ፣ በፈተናዋ እየጸናች፣ ንዕማን እጅግ ከባድ ከሆነ የለምጽ በሽታ የተነሳ እየሞተ ነበርና የእርሷን ሁኔታ ረስታ ስለ እርሱ ማሰብ ጀመረች፡፡ ይህችም አገልጋይ ለእመቤቷ እንዲህ አለች፡- «ጌታዬ በሰማርያ ካለው ከነቢዩ ፊት ቢደርስ ኖሮ ከለምጹ በፈወሰው ነበር » (2 ነገ. 5፡3)፡፡ በሕይወቷ ያየችውን መልካም ነገር አካፈለች፡፡

ከዚህ የተለየ አመለካከት ሊኖራት ይችል ነበር፤ ይህ የህዝቧ ጠላት ሠራዊት ወታደር የሆነ ሰው እየሞተ በመሆኑ ደስ መሰኘት ትችል ነበር፡፡ ባርያ የሆነችበት ይህ ቤት እንደዚሁም ህዝቡ ሁሉ መለኮታዊ ቅጣትን እንዲቀበል ልትጸልይ ትችል ነበር፡፡ የእርሱንም ለምጽ እንደ መለኮታዊ ፍርድ አድርጋ ልታየው ትችል ነበር፡፡ ነገር ግን ከእነዚህ አንዳቸውንም አላደረገችም፡፡ ይልቁንም፣ ልትረዳው፣ ለቤቱም መትረፍረፍን የሚያመጣ መልካም ዜና ልታካፍለው ፈለገች፡፡

ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በኋላ፣ አሜሪካ አውሮፓ ወድቃበት ከነበረው የጦርነት ውድመት እንድታገግም «ማርሻል ፕላን» በሚል እቅድ የእርዳታ እጇን ዘርግታ ነበር፡፡ በዚህ እቅድም የአሜሪካ ሃብት አውሮፓን እንደገና ለመስራት እንዲያገለግል ሆነ፤ እቅዱም የተሰየመው በወቅቱ የአገሪቱ ጸሐፊ በነበሩት ጆርጅ ማርሻል ስም ነበር፡፡ በዚህ

እቅድም፣ በጦርነት ለወደሙ መንግስታት አሜሪካ መልካም ዜናን እንድታስደምጥ ሆነ፡፡ ይህ በአሜሪካ ታሪክ እጅግ ትልቅ ሰብአዊ ድርጊት የተደረገበት ዘመን ነው፡፡

እናንተስ ንብረታችሁን እንዲሁ ትቆልላችሁ ወይስ ከሌሎች ጋር ትካፈላላችሁ? የሕይወትን ፈተና ለመቋቋም እግዚአብሔር ሲባርካችሁ፣ የንዕማንን አገልጋይ ምሳሌነት ተከተሉና ለእናንተ የተደረገላችሁን መልካም ነገር ሊሰሙ ለሚገባቸው አሰሙ፡፡ ለኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥልቅ ነገር እንዲያስተውል እንዳስረዳውና ወደ ክርስቶስ እንደመራው እንደ ፊልጶስ ልትሆኑ ትችላላችሁ? (የሐዋ. 8)፡፡ በእነዚህ ከባድ ጊዜያት እግዚአብሔር መጽናናትን ለማምጣት የሚጠቀምባችሁ መሳሪያው ልትሆኑ ትችላላችሁ፡፡ ስቃያችሁ ወደ ሌሎች ሕይወት ሊያመጣ የሚችለውን ትርፍ በመመልከት ለወደፊት የሚገጥማችሁን ከባድ ጊዜ በበለጠ ጽናት ለመጋፈጥ እንድትቀጥሉ ያግዛችኋል፡፡

## በፈተና ለመጽናት የሚያግዟችሁ ወሳኝ እርምጃዎች

- የአመስጋኝነት አመለካከትን አዳብሩ
- ብድራታችሁን ተመልከቱ
- እግዚአብሔርን ተወቃሽ አታድርጉት
- የኃጢአትን ደሞዝ አስታውሱ
- ሌሎች በመከራ ውስጥ ያሉን እርዱ

# 21

# በማጣት አግኙ

ልግስና በማጣት ማግኘትን ስለሚያስታጥቀን የሕይወትን ቀውሶች መቋቋም እንድንችል ይረዳናል፡፡ በ 1 ነገ. 17፡9 ላይ እግዚአብሔር ለነብዩ ለኤልያስ እንዲህ አለው፡- ‹‹ተነሥተህም በሲዶና አጠገብ ወዳለችው ወደ ሰራፕታ ሂድ፥ በዚያም ተቀመጥ፡፡ እነሆም፥ ትመግብህ ዘንድ አንዲት ባልቴት አዝዣለሁ የሚል የእግዚአብሔር ቃል መጣለት፡፡›› በእኩይ ተግባር ከተሞላችው ከንግስት ኤልዛቤል ጋር ተመሳሳይ ዘርንና ኃይማኖትን የምትጋራው ይህቺ ሴት የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምታ ታዘዘች፡፡ ለመጨረሻ ጊዜ በልቼው ከዚያ በረሃብ እሞታለሁ ብላ ያሰበችውን ምግብ ለነብዩ ሰጠችው፡፡ በመታዘዟ ምክንያትም፣ እግዚአብሔር የረሃብ ዘመኑ እስከሚያልቅ ድረስ በማያቋረጥ የምግብ አቅርቦት ጎበኛት፡፡ ያላትን ነገር መስዋዕት ባታደርግ ኖሮ ልታጣ የምትችለውን ትርፍ የልግስና ድርጊቷ በእጇ አስገባላት፡፡ ከልግስናዋም የተነሳ በመከራዋ ውስጥ በረከትን ተለማመደች፡፡

ከብዙ አመት በኋላ፣ ኢየሱስ ስለዚህች ሴት እምነት እንዲህ በማለት ተናገረ፡- ‹‹ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፥ በኤልያስ ዘመን ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ሰማይ ተዘግቶ ሳለ በምድር ሁሉ ብርቱ ራብ በነበረ ጊዜ፥ በእስራኤል ብዙ መበለቶች ነበሩ፤ ኤልያስም በሲዶና አገር ወዳለች ወደ ሰራፕታ ወደ አንዲት መበለት እንጂ ከእነርሱ ወደ አንዷቱ አልተላከም፡፡›› (ሉቃ. 4፡25-26)፡፡ ምናልባት በቂ እምነት ያላቸው ወይም በማጣት ማግኘት የሚያስችለውን የልግስና ጎዳና ለመከተል የፈቀዱ መበለቶች በእስራኤል ጠፍተው ይሆን?

በመጀመሪያ፣ ልግስና በማጣት ማግኘትን እንድንለማመድ ልግስና የሚያስችለን ማቆሚያ የሌለውን የመዝራትና የማጨድን ህግ በተግባር ላይ ስለሚያውል ነው፡፡ ምድራችን በምህዋሯ ላይ መዞሯን እስከቀጠለች ድረስ፣ የመዝሪያና የማጨጂያ ጊዜ መኖሩ አይቀሬ ነው (ዘፍ. 8፡22)፤ እናም ልግስና ደግሞ ብዙ መከርን ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘርን የመዝሪያ መንገድ ነው፡፡ በሂደትም፣ ሰላሳም ይሁን ስልሳ ወይ መቶ እጥፍ፣ ብቻ ከዘራነው በላይ እናጭዳለን (ማር. 4፡8)፡፡ ይህቺ መበለት በመስዋትነት ተሞልቶ የነበረው ልግስናዋ የእርሷንና የልጇን ሕይወት ከረሃቡ ዘመን እንደሚታደግ አስቀድማ አላወቀችም ነበር፡፡ በእርግጥም ከዘራችው እጅግ የበዛን መከር ነበር የሰበሰበችው፡፡

ኢየሱስ አንድ ጊዜ እንዲህ ብሎ ነበር፡- ‹‹ነፍሱን ሊያድን የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋታል፥

ነፍሱንም የሚያጠፋ ሁሉ በሕይወት ይጠብቃታል» (ሉቃ. 17፡33)፡፡ ሕይወትን ከማጣት የበለጠ ጥልቀት ያላቸው ልግስናዎች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ ምናልባት ይህ ስለ ሰማዕትነት ይሆናል የሚያወራው፡፡ ነገር ግን ሕይወታችንን ከእኛ ምኞት ለበለጠ ነገር ማዋልንም (ኢንቨስት ማድረግንም) ያካትታል፡፡ በሌላ አነጋገር ሕይወትን በተገቢ መንገድ ለመኖር ከፈለጋችሁ የምትሞቱለትን ነገር ፈልጋችሁ ማግኘት አለባችሁ፡፡ በልግስና ሌሎችን ለማገልገል ራስን መስጠት፣ በማጣት ለማግኘት አስተማማኝ ጎዳና ሲሆን በሕይወት ውስጥ የሚገጥሙንን የመሰናከል ድንጋዮች ወደ መወጣጫ ደረጃነት ይቀይራቸዋል፡፡

ልግስና በማጣት ለማግኘት እንድንችል የሚዳን ሌላው ምክንያት በሐዋ. 20፡35 ላይ የሚገኘውን መለኮታዊ መርህ ስለሚያንጸባርቅ ነው፡- «ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው» ኢየሱስ በተናገረው ምሳሌ ውስጥ የሚገኘው መልካሙ ሳምራዊ በኢያሪኮ መንገድ ላይ ያገኘውን የቆሰለ አይሁዳዊ በልግስ ለመርዳት ህይወቱን አደጋ ላይ በመጣሉ፣ የእውነተኛ ባልንጀራት ምሳሌ ሆኖ በአድናቆት ተጥቅሶአል (ሉቃ. 10)፡፡

ሌላ በልግስናዋ ኢየሱስ ያሞገሳት ሴት ደግሞ የቢታኒያዋ ማርያም ነች (ዮሐ. 12)፡፡ ከፋሲካው በዓል ስድስት ቀን ቀደም ብሎ፣ በኢየሱስ መንገድ ላይ የመስቀሉ ጥቁር ጥላ ማረፍ ሲጀምር አቅጣጫውን ወደ ቢታኒያ መልሶ ብዙ ጊዜ ቤተሰባዊ የፍቅር ሕብረት ጸሐይን ወደ ሚሞቅበት ወደ ማርያም፣ ማርታና አላዛር ቤት አመራ፡፡ ወደ ቤታቸውም በመግባት፣ የማርታን እጅ የሚያስቆረጥም ምግብ አሸትቶ በቅርቡ ከሞት ወደተነሳው ወደ አላዛር ፊቱን በማዞር በአድናቆት ራሱን ነቀነቀ፡፡ ብዙም ሳይቆይ እራት ተሰናዳ፡፡

ሲበሉ ሳለም፣ ማርያም እጅግ ውድ የሆነ ሽቶ ወስዳ በኢየሱስ እግር ላይ አፈሰሰችው፡፡ ጣፋጩና አእምሮን የሚቆጣጠረውን መዓዛ ክፍሉን ሞላው፤ የመነጋጋሪያ አጀንዳም ሆነ፤ ክርክርም ተነሳ፡፡ በመጨረሻ፣ ይሁዳ ቡድኑን በመወከል ንግግር አደረገ፡፡ እንዲህም ብሎ ጠየቀ፡- «ይህ የማባከን ድርጊት ለምን ይፈጸማል? ይህ ሽቶ ለምን በሦስት መቶ ዲናር ተሽጦ ገንዘቡ ለድኾች አይሰጥም?»

በክፍሉ ውስጥ ጸጥታ ሰፈነ፤ ኢየሱስ ግን የማርያምን ልግስና በማድነቅና በመደገፍ ሲናገር ዝምታውን ሰበረው፡፡ ፍፁም ሙሉ በሆነ ጽናት «ተዋት» አለ፡፡ «እርስዋ ይህን ሽቱ በሰውነቴ ላይ አፍስሳ ለመቃብሬ አደረገች። ድሆች ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና፥ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም፤» ኢየሱስ በአደባባይ ይሁዳን በመቃወም በማጣት ለማግኘት የመረጠችውን ወዳጁን ተከላከለላት፡፡ ስለ ማርያምም እንዲህ አለ፡- «እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በማናቸውም ስፍራ በሚሰበከበት እርስዋ ያደረገችው ደግሞ ለእርስዋ መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል።» (ማቴ. 26፡13)፡፡

የማርያም ልግስና በመከራ ውስጥ በረከትን ለመለማመድ አስቻላት፡፡ ለመሆኑ መከራዋ ምን ነበር? ኢየሱስ እንደሚሞት ታውቅ ነበር፡፡ ወደ ቤታቸው ለጉብኝት በሚመጣበት ጊዜ ከእግሮቹ ስር በመቀመጥ፣ ከኢየሱስ አስራ ሁለት ደቀ መዛሙርት

የሚበልጥ ነገረ መለኮታዊ መረዳትን ሳታገኝ አልቀረችም፡፡ እነርሱ በምድራዊ መንግስት ውስጥ ስልጣንን ለማግኘት ሲሻኮቱ፣ የማርያም ልብ ግን ወደ ቀራኒዮ አመራ፡፡ ከመሞቱ በፊት ጌታዋን ለማክበር የነበራት ጽኑ ፍላጎት በእሁድ የትንሳኤ ጠዋት ወደ መቃብሩ እንዳትሄድ አደረጋት፡፡ የቢታንያዋ ማርያም እሁድ በማለዳ ተነስተው የኢየሱስን አስከሬን ሽቶ ለመቀባት ከሄዱት መካከል አልበረችም፡፡ ምክያቱም እርሱን በማጣት ለሚገጥማት መከራ አስቀድማ በማጣት ማግኘት በሚቻልበት ጎዳና በመሄድ ተዘጋጅታ ነበርና፡፡

አለማዊው አመለካከት በማጣት የማግኘትን መርህ ያገላብጠዋል፤ ከመስጠት ይልቅ መቀበል በረከት እንደሆነ ያውጃል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይኼ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ከተጠቀሱት አያሌ ታሪኮች ጋር የሚቃረን አካሄድ ነው፡፡ ታሪክ ለተቀባዮች ሳይሆን ለሰጭዎች ርህራኄን ያሳያል፡፡ ለምሳሌ፣ ስለ ሩዝቬልት ወይም ቸርችል ወይም ጋንዲ ወይም ሉተር ኪንግ የሃብት መጠን ማንም ሰው አያወራም፡፡ ይልቁንም እነዚህ ታላላቅ ሰጪዎች ለሰብአዊ ዘር ያበረከቱት ከነበራቸው ሃብት የሚበልጥን ነገር ነበር፡፡

በተመሳሳዩ፣ በሕዝቧ ላይ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ በተዘጋጀ ጊዜ፣ አስቴር ወደ ንጉስ አርጤክሰስ ሕይወቷን መስዋዕት አድርጋ በመግባት ሐማን በአይሁድ ላይ የጠነሰሰውን ሴራ አጋለጠች፡፡ በዚህም ድርጊቷ ማጣት ከሚመስል ድርጊት ማግኘትን እንደተለማመደችና መከራው ወደ በረከት እንደተለወጠ እንመለከታለን፡፡ እንዲሁም ሩት የኢየሱስ የዘር ሐረግ ውስጥ ልትገባ የቻለችው ኑኦሚንን በታላቅ መከራዋ ወቅት ትታት ላለመሄድ በልግስና መንፈስ ተሞልታ አሻፈረኝ በማለቷ ነበር፡፡ ሃናም ልጇን ለእስራኤል ታላቅ ነብይ ይሆን ዘንድ በልግስና መልሳ በቤተመቅደሱ እንዲያገለግል በሰጠችው ጊዜ ያገኘችውን ታላቅ ትርፍ እናስታውሳለን፡፡ ታሪክና ቅዱሳት መጻሕፍት በልግስና የመስጠትን ውጤታማነት ደግመው ደጋግመው ይመሰክራሉ፡፡

በሦስተኛ ደረጃ፣ ልግስና በማጣት ወደ ማግኘት የሚመራን የአለማችንን ስስት ስለሚያለዝበውና ስለሚዋጋው ነው፡፡ በሕይወታችሁ የምትጋፈጡት ቀውስ ምንም ቢሆን በመስጠትና አለማችንን የተሻለች ስፍራ በማድረግ ላይ አተኩሩ፡፡ አለምን የተሻለች ስፍራ ስታደርጓት የገጠማችሁ ቀውስ ሊፈታ የሚችልበትን የተሻለ ከባቢን መፍጠር ትችላላችሁ፡፡

በ1 ሳሙ. 30 ላይ ዳዊት በጠላቶቹ የተዘረፈውን ለማስመለስ ጥረት በማድረግ አማሌቃውያንን ያሳድዳቸዋል፡፡ ለወጣቱ ዳዊት ጠላቶቹ የወሰዱበትን ሁሉ እንደሚመልስለት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተስፋ ቃል ስለነበረው አሸንፋለሁ በሚል ታላቅ ተስፋ ነበር የሚዋጋው፡፡ ስኬትን ወደ ሚቀዳጅበት ስፍራ በሚገሰግስበት ጊዜ አንድ በሞትና በሕይወት መካከል የሚያጣጥርን ግብጻዊ አገልጋይ አገኘ፤ ሊረዳውም ጉዞውን አቆመ፡፡ ይህ የልግስና ተግባሩ ለዳዊት ጠቃሚ መረጃንና ምሪትን እንዲያገኝ ረዳውና ጠላቶቹን አሸነፈ፡፡ ዳዊት እጅግ በተቸገረበት ጊዜ እንኳን ሳይቀር በልግስና በመስጠት ትርፍ ማግኘት የቻለ ሰው ነበር፡፡ በችግር ውስጥ ያሉትን በመርዳት፣ የራሱን ችግር ለመቋቋም የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ በአለም ውስጥ መፍጠርን ችሎ ነበር፡፡

በማጣት ማግኘት ስንፈልግ የምናደርገው ነገር ብቻ ሳይሆን የግድ ልንለማመደው የሚገባን ነገር ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔርን መምሰል ያለማምደናልና፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ፍጽምና እንድንዘረጋ ሲጠራን እንዲህ ይለናል፡- «እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ» (ማቴ. 5፡ 48)፡፡ የእግዚአብሔር ፍጽምና ከሚገለጥባቸው ነገሮች መካከል አንዱ ልግስናው ነው፡፡ የፍጥረተ አለምን ውበት ስንመለከት፣ ያሸበረቁ ቀለማቱና ግርማው የእግዚአብሔርን ልግስና ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡ ወደ እግዚአብሔር ይበልጥ በቀረብን መጠንና እርሱንም ይበልጥ እየመሰልነው ስንሄድ፣ ይበልጥ በልግስና መንፈስ የተሞላን እንሆናለን፡፡ በእርግጥም እግዚአብሔር ራሱ የከፋትን ቀውስ የተቋቋመው በመስጠት ነበር፡፡ ሰብአዊ ዘርን ለማዳን ያቀደው እቅድ የሰማያዊ ልግስና አስገራሚ ምሳሌ ነው፡፡

ታዲያ እንደ እግዚአብሔር መስጠት የምንችለው እንዴት ነው? በመጀመሪያ፣ ያለንን ሁሉ መስጠት አለብን፡፡ እግዚአብሔር ሰማይ ሊሰጥ ከሚችለው ሁሉ የበለጠውን ልጁን ነበር የሰጠው፡፡ ሁለተኛ፣ ልግስናችን በሰዎች እጦት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይገባል፡፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ- «ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም» (ሉቃ. 5፡ 32)፡፡ እግዚአብሔር ልግስናችንን የሚመዝነው ረሃብተኛውን ባበላንበት፣ የታረዘውን ባለበስንበት፣ ለመጻተኛው ባሳየነው እንክብካቤ፣ የታመመውን በጠየቅንበት፣ እንደዚሁም የተቸገረውን ባገለገልንበት ልክ እንደሆነ በማቴ. 25 ላይ አስታውሶናል፡፡ በሉቃ. 4 ላይ ኢየሱስ አገልግሎቱ የተጨቆኑትን ነጻ የሚያወጣ፣ ለታወሩት ብርሃንን የሚሰጥ፣ ለታመሙት ፈውስን የሚያመጣ፣ የተቸገሩትንም የሚረዳ እንደሆነ ተናገረ፡፡ የጠፉትን፣ ብቸኞችንና ታናሾችን የትኩረታችን ማረፊያ አድርገን ስንሰጥ የእግዚአብሔርን በሚመስል የልግስና ልምምድ እናድጋለን፡፡ በምስጋና ተሞልተን፣ ከልብ ፈንቅሎ በሚወጣ ስሜት፣ ሳንዘገይ በወቅቱ፣ በጥበብና አደገኛ በሆነ ሁኔታ ውስጥ እየኖርን እንኳ ስንሰጥ እንደ እግዚአብሔር መስጠትን እንለማመዳለን፡፡

## በምስጋና ተሞልታችሁ ስጡ

ለመስጠት የሚያነሳሳን ዋንኛው ምክንያት አመስጋኝነት ሊሆን ይገባል፡፡ ለዮሴፍ የልግስናን ጉልበት ሰጥቶት የነበረው የአመስጋኝነት መንፈስ ነበር፡፡ የጠየቀችውን ነገር ለማድረግ እንደማይችል ለጶጢፋራ ሚስት ሲያስረዳ በሕይወቱ ስለተለማመደው የእግዚአብሔር ባርኮት በምስጋና ተሞልቶ ነበር የተናገረው፡፡ ሕይወቱ ከእግዚአብሔር ልግስና ከመቀበሉ የተነሳ፣ ዮሴፍ በኃጢአት ውስጥ መውደቅን አሻፈረኝ አለ፡፡ በተመሳሳዩም፣ የቢታኒያዋ ማርያም የተደረገላት ነገር የእሷን የልግስና ድርጊት ቀሰቀሰ፡፡ ኢየሱስም ከተደረገላት ነገር የተነሳ በምስጋና ተሞልታ ታላቅን ነገር ለማድረግ መፈለጓን በመገንዘብ የተሰነዘረባትን ክስ ተከላከለላት፡፡

በልባችን የሞላው የአመስጋኝነት መንፈስ የልግስናችን መሠረት ሲሆን፣ በ 2 ቆሮ. 9፡7 ላይ «እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም።» የሚለውን መታዘዝ እንችላለን፡፡ ከውድ ወዳጆቼ መካከል አንዱ የሆነው ታላቁ የወንጌል መዝሙር ዘማሪ ዊንትሊ ፊፐስ በአውሮፓን ላይ በአንደኛ ደረጃ ማዕረግ ሲሄድ አንድ ድምጽ ሰማ፡፡ «ዊንትሊ፣ የቀረውን ዘመንህን በምን አይነት የአኗኗር ዘይቤ መኖር ትፈልጋለህ? ብቻ ለኢየሱስ መዘመርህን አቁም እንጂ ከዚህ

የበለጠ የፈለግኸውን እንዲሆንልህ አደርጋለሁ» አለ ያ ድምጽ በሹክሹክታ፡፡ ወዳጇም ይህ ድምጽ የእግዚአብሔር ድምጽ እንዳልሆነ ያውቅ ነበር፡፡ ለክርስቶስ ለመዘመር ቃል ገብቶ ነበርና፤ አሁን ግን አጋንንታዊ ኃይሎች ከዚያ ቁርጥ አቋሙ እንዲንሸራተት እያባበሉት ነበር፡፡

ይሁን እንጂ፣ ዊንትሊ የእግዚአብሔርን መልካምነትና ከእርሱም የተቀበላቸውን የልግስና ስጦታዎቹን ሲያስብ፣ እርሱም ለእግዚአብሔር አጸፋውን ለመመለስ በመፈለግ «ሕይወቴን እሰጥሃለሁ»የሚለውን መዝሙር ጻፈ፡፡ አመስጋኝነት ለእግዚአብሔርም ሆነ ለሰው በደስታ ለመስጠት በመገረምና በኃይል የሚሞላ ቀስቃሽ ምክንያት ነው፡፡

### ከልብ ፈንቅሎ በሚወጣ ስሜት ስጡ

የቢታኒያዋ ማርያም ከልቧ ፈንቅሎ በሚወጣ ስሜት ነበር የሰጠችው፡፡ የጌታን ራስና እግር ስትቀባ፣ እግሮቹንም ለማድረቅ ጸጉሯን ስትጠቀም፣ ክርስቶስ ላደረገላት ነገር የተለመደ አይነት ምስጋናን እየሰጠች አልነበረም፡፡ ነገር ግን ከልቧ በመነጨ ጥልቅ ስሜት‹ደህና ሁን፤ አመሰግናለሁ› የምትል ሴት ነበረች፡፡

በ 1 ሳሙ. 1 ላይም ተመሳሳይ ከልብ ፈንቅሎ የሚወጣን ስሜት እንመለከታለን፡፡ ሃና ልጅ ለማግኘት ካህኑ ኤሊ የሰከረች እስኪመስለው ድረስ በትጋት ነበር የጸለየችው፡፡ እንደዚያ ያለ በጥልቅ ስሜት ውስጥ በመሆን ወደ ሚጸለይ ጸሎት የመራት መከራዋና ሰቆቃዋ እንደሆነ ሲገባው፣ እግዚአብሔር የለመነችውን እንደሚሰጣት ነገራት፡፡

እግዚአብሔርም የራሱን ድርሻ ተወጥቶ ወንድ ልጅ ሲሰጣት፣ ሐና ደግሞ የተስፋ ቃሏን ጠበቀች፡፡ ለተቀበለችው የልግስና ስጦታ የምትሰጠው ምላሽ ልጇ በእግዚአብሔር ቤት እንዲያድግ መፍቀድ እንደሆነ ገለጸችለት፡፡ ከዚያም ሳሙኤል ጡት ሲጥል፣ ልጇን ለካህኑ ለመስጠት ሐና ተመልሳ ወደ ቤተመቅደሱ መጣች፡፡ በቤተመቅደሱ ውስጥ በማደግ ለእስራኤል ታላቅ ነብይ እንዲሆን በመመኘት እናት ልጇን ከልቧ ፈንቅሎ በወጣ የደስታ ስሜት ሰጠች፡፡

### ሳይረፍድባችሁ በወቅቱ ስጡ

በልግስናችን መዘግየት የለብንም፡፡ የቢታኒያዋ ማርያም ጊዜ ሳታባክን ስጦታዋን ስለሰጠች እግዚአብሔር ይመስገን! ዘግይታ ቢሆን ኖሮ፣ ኢየሱስ ወደ ቀራኒዮ በጌተሰማኔ በኩል አልፎ የሄድ ነበር፤ እናም ለጌታዋ ይህንን ስጦታ ለመስጠት እድሉን ባለገኘች ነበር፡፡ ከሞተ በኋላ ስጦታዋን በወቅቱ ስለሰጠችው ቢያንስ ከመሰቃየቱ በፊት የእርሷን ጣፋጭ መአዛ ያለውን ሽቶ በመቀበሉ በመጠኑም ቢሆን ራሷን አጽናንታበት ይሆናል፡፡

ብዙዎች በማጣት ከማግኘት በረከት የሚጎድሉት ከረፈደ በኋላ ስለሚሰጡ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በሕይወት ውስጥ የዘገየ መታዘዝ እንደአለመታዘዝ ነው የሚቆጠረው፡፡ ሙሽራውን ለመገናኘት በጊዜ ሊያደርጉ የሚገባቸውን ዝግጅት እንዳላደረጉት በማቴ. 25 ላይ እንደሚገኙት አምስት ሰነፍ ቆነጃጅት ልንሆን እንችላለን፡፡

አንዳንዶች ልጆቻቸውን ለመውደድ የሚሞክሩ ለአመታት በስራቸው ተጠምደው ከረሷቸው በኋላ ነው፤ ነገር ግን ይሄን ጊዜ ልጆቻቸው የእነርሱን የዘገየ ትኩረት ለመቀበል በማይችሉበት ሁኔታ በብዙ ነገር ተወጥረው ያገኙዋቸዋል፡፡ በ1974 ሃሪ ቻፒንስ አውጥቶት የነበረው ‹‹ካትስ ኢን ክራድል›› (በህጻን አልጋ ውስጥ የተኛችው ድመት) የሚለው ዝማሬው በወቅቱ ከልጁ ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ስላልቻለ አባትና ከዚያም የእርሱ ልጅ ደግሞ ካደገ በኋላ እርሱም ለልጆቹ ምንም ጊዜ ሳይኖረው እንደቀረ የሚናገር ነበር፡፡

አንድ ጊዜ የቴሌቭዥን ፕሮግራም ስመለከት አባት ጆርጅ ቡሽ ከሚስታቸው ከባርባራ ጋር ቃለ መጠይቅ ይደረግላቸው ነበር፡፡ ሪፓርተሩ እንዲህ ብሎ ጠየቀ፡- ‹‹ለልደታችሁ የምትለዋወጡት ስጦታ ምንድን ነው?››

‹‹የልደት ስጦታ መለዋወጥ ትተናል፣›› አለች የቡሽ ባለቤት ፈጠን ብላ፡፡ ‹‹የምፈልገው ነገር ካለ ወይ ጆርጅ ያመጣልኛል፤ አልያም ራሴ ሄጄ እወስዳለሁ፡፡›› ከዚያም ወደ ሪፖርተሩ ፊቷን ዘወር አድርጋ እጇን እያወናጨፈች፣ ‹‹በዚህ ክፍል ውስጥ ልትወስደው የምትፈልገው ነገር አለ? እንደ ማርጀታችን መጠን ያለንን ነገር ሁሉ በመስጠት ላይ ነን፡፡››

ሊባኖሳዊና አሜካዊ የሆነው ገጣሚና ተፈላሳፊ ካህሊል ጊብራ አንድ ጊዜ እንዲህ በማለት ጽፎ ነበር፡- ‹‹ አንድ ቀን የእናንተ የሆነው ሁሉ ለሌሎች ይሰጣል፡፡ ስለዚህም የመስጠቱ እድል የወራሾቻችሁ ሳይሆን የእናንተ እንዲሆን ከፈለጋችሁ አሁኑኑ ስጡ፡፡›› ይህ ለራሳችሁ ልትገቡት የሚገባችሁ ጥሩ ቃል ኪዳን ነው፡፡ ተቀባዮቹ ሲስቁ ለመስማትና በደስታ የተሞላውን የምስጋና ቃሎቻቸውን ለማድመጥ እየቻላችሁ ሳለ ዛሬ ስጡ፡፡

በሕይወቴ እጅግ ከተደሰትኩባቸው ጊዜያት መካከል አንደኛው እናቴ ቤት እንድትገዛ የረዳሁበትን ጊዜ ነው፡፡ ለእኔና ለእህት ለወንድሞቼ ብዙ መስዋዕትነትን ከፍላ ነበርና ይህ ስጦታ ለእርሷ በጣም ትንሽ ነበር፡፡ እማዬ እጅግ አመስጋኝና በዚያ ቤት ውስጥ በመኖሯም ደስተኛ እንደሆነች ደጋግማ ትገልጽ ነበር፡፡ እኛም ከዚያ በኋላ ሕይወቷ ብዙም ረዥም እንደማይሆን አላወቅንም ነበር፡፡ በተፈጠረ የህክምና ስህተት ልትሞት በማይገባት እድሜ ለመሞት በቃች፡፡ ነገር ግን የመጨረሻውን የንግግር ልውውጥ ባደረግን ጊዜ አሁንም ስለቤቷ አንስታ ምስጋናዋን በድጋሚ ገለጸች፡፡

በቀብሯ ላይም እነዚያ የምስጋና ቃላቷ በአእምሮዬ ገና ትኩስ ነበሩ፤ እናም በስጦታዬ ስላልዘገየሁ እግዚአብሔርን አመሰገንሁት፡፡ በመሞቷ የተሰማኝ ሃዘን በስጦታዬ የተደሰተችውን መደሰት በማሰብ ቀለል አለልኝ፡፡

**በጥበብ ስጡ**

የማርያም ስጦታ በጥበብ የተሰጠ ስጦታም ጭምር ነበር፡፡ በጣም ከባድ በሆነው የሕይወቱ ምዕራፍ ሲያልፍ ኢየሱስን ለማጽናናት የታቀደ፣ በመከራው በረከት ላይ

ትኩረቱን እንዲያደርግ የሚያስችለው ስጦታ ነበር፡፡ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ፣ አብዛኞቹ ደቀ መዛሙርቱ ኮብልለው እንደሄዱ ያውቅ ነበር፡፡ የሃይማኖት መሪዎች ረግመውታል፤ ብዙሃንም እንዲሞት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ተናገረዋል፡፡ ምንም እንኳን በእግዚአብሔርም ሆነ በሰው የተተወ ቢመስለውም፣ ቢያንስ በዚያ ሁሉ ጨለማ ውስጥ ሆኖ አንዲት ብርሃን ስትፈነጥቅ ይመለከታል፡፡ በእርግጥም፣ የቢታንያዋ ማርያም ኃይለኛ ስብከትን ነበር የሰበከችው፡፡ ከጥቂት ቀናት በፊት ይህንን የሚደርስበትን መራር መከራ አስቀድማ ተመልክታ በጥበብ በተሞላው ልግስናዋ ሕይወቱን ለመባረክ ችላ ነበር፡፡

እናንተስ ምን ያህል በጥበብ ትሰጣላችሁ? መጥፎ አላማን ለመደገፍ ይሆን ብዙ ገንዘባችሁን የምታፈሱት? አንድ ጊዜ ከአንድ ሚኒስቴር ጓደኛዬ ጋር በዋሽንግተን ዲ ሲ ዩኒየን አደባባይ በእግራችን ስንሄድ ነበር፡፡ እኛም በዚያ ስናልፍ ድሆችና ችግረኞች ማንም የእርዳታ እጃቸውን ሳይዘረጋላቸው ተመለከተን፡፡ ወዳጄም ጉዞውን ቀጠለ፤ የእነዚህን ወደ ጎን የተተዉን የማሕበረሰቡን ክፍል ጩኸት እየሰማ እንዴት ጉዞውን በቸልታ እንደቀጠለ በማሰብ ተደነቅሁ፡፡ በተለይም የአንደኛው በልመና ላይ የነበረ ግለሰብ ልመና ግልጽ ሆኖ ወደ ጆሮ ይገባ ነበር፡- «ጌቶች፣ እርቦኛል፡፡ እባካችሁ የምበላውን ፍርፋሪ ለመግዛት ትንሽ ፍራክ ስጡኝ ፡፡»

እኔም እነዚህን ሁሉ የልመና ድምጾች ሰምቼ እንዳልሰማ በማለፍ ወዳጄን ተከትዬ ወደ ባቡር ጣቢያ አመራን፤ እዚያም ስንደርስ ከአንድ ሳንድዊች መሸጫ ሱቅ ብዙ ሳንድዊቾችን ገዛና በትልቅ ቦርሳ ውስጥ እንዲገቡ አደረገ፡፡ ከዚያም፣ ወደ እኔ ዞወር በማለት፣ «ተከተለኝ፣ የምንሰራው ሥራ ይኖረኛል» አለኝ፡፡ እነዚያ ችጋረኞች የልምና ድምጻቸውን ወደ ሚያሰሙበት ወደ አደባባዩ ተመለስን፡፡ ከዚያም ወዳጄ ትኩስና ጣፋጭ የሆነን ሳንድዊች ለተራቡት በሚሰጥበት ጊዜ እኔም እንድረዳው ጠየቀኝ፡፡

ይህ ሰው በጥበብ ነበር የሰጠው፡፡ ለጠየቀው ሰው ሁሉ ገንዘቡን ሰጥቶ ቢሆን ኖሮ፣ ተቀባዮቹ ገንዘቡን በምን ላይ እንደሚያውሉት በእርግጠኝነት ማወቅ አይችልም ነበር፡፡ እንዲሁ መስጠት አግባብ የሚሆንበት ጊዜ ቢኖርም፣ እግዚአብሔር የሰጠንን ንብረት እንደ ታማኝ ባለ ዐደራዎች ሆነን ልንይዝ ይገባናል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ተቀባዮቹን ሊባርካቸውና ሊያስታጥቃቸው በሚችልበት መንገድ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

አንድ ሴናተር ጓደኛዬ ያልተለመደ ችግር ስለነበረው አንድ መንደር ታሪክ መናገር ሁልጊዜ ይወዳል፡፡ ይህም ችግር ሰዎች በአቅራቢያ ወዳለ አንድ ገደል በመሄድ ከዚያ ገደል መውደቃቸው ነበር፡፡ ብዙዎች ከዚያ ገደል እየተከሰከሱ ጉዳት ይደርስባቸው ነበር፡፡ አንዳንዶች እንዲያውም ሞተዋል፡፡ የመንደሩ የህክምና ክፍል ለዚህ ችግር ምላሽ በመስጠት የሚወድቁ ሰዎችን በቶሎ ወደ ህክምና ቦታ ለማድረስ ከገደሉ ስር አንድ አምቡላንስ አስቀመጠ፡፡

ሌሎች ሰዎች ግን ከዚህ ይልቅ በጥበብ የተሞላው አካሄድ ሰዎች ከመጀመሪያውም መውደቃቸውን ለመከላከል ለድልድዩ አጥር እንዲሰራለት ማድረግ እንደሆነ ሃሳብ

አፈለቁ፡፡ እነርሱም ሃሳባቸውን ሲያቀርቡ ችላ ተባሉና ምንም አይነት አጥር ሳይሰራ ቀረ፡፡

ይሁን እንጂ ሰዎች አሁንም ከገደሉ መውደቃቸውን ሲቀጥሉ፣ ነገሩ አጣዳፊ ትረኩረት አገኘ፡፡ እስካሁን የችግሩን ምልክት እንጂ መንስኤውን ለማስወገድ ጥረት አለመደረጉ ታወቀ፡፡ ከዚያም የጠቢባኑ ድምጽ ተሰማ፡፡ አጥር ተሰራ፡፡ የመንደሯም ንብረት ከመባከን ተረፈ፡፡ ውጤቱን ለማከም ከመሞከር ይልቅ መንስኤውን ለማጥፋት ሃብቶች ዋሉ፡፡ በጥበብ መስጠት ማለት በጣም ትልቅ ጥቅም በሚሰጥበት ቦታ ላይ ስጦታችንን ማስቀመጥ ማለት ነው፡፡ እንዲህ ማድረግ ደግሞ ከመከራ ውስጥ በረከትን ያፈልቃል፡፡

## በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ እንኳ ስጡ

ኢየሱስ ለማርያም የልግስና ስጦታ የሰጠው ምላሽ በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ የተደረገ ስጦታ ነበር፡፡ ይህንንም ያደረገው የማርያምን ስጦታ እንዲህ በማለት ያብጠለጠለውን ይሁዳን በመገዳደር ነበር «ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለ ምን ነው?» (ዮሐ. 12፡5)፡፡

ኢየሱስ እንዲህ ያለውን አክብሮት የጎደው ምላሽ በፀጥታ አላስተናገደውም፤ «ተውአት» በማለት ነበር የመለሰው፡፡ «ለምቀበርበት ቀን እንድትጠብቀው ተውአት፤»

ይሁዳን በዚህ መልኩ በመገዳደር፣ ኢየሱስ አደገኛ የሆነን ነገር አደረገ፡፡ ይሁዳ በአደባባይ ተግሳጽ በመቀበሉ ተናዶ ኢየሱስን አሳልፎ ለመስጠት ውስጡ ተነሳሳ፡፡ «ስለሞቱና ስለመቀበሩ የሚያወራ ከሆነ፣ እንግዲያውስ እኔ አቀናጅለታሁ» በማለት ይሁዳ ሳያስብ አልቀረም፡፡ ኢየሱስ ይህ ተግሳፁ የሚያመጣበትን ያውቅ ነበር፤ ነገር ግን ማርያም ደግሞ ከጌታችን ምርጥ የሆነውን ነገር ማግኘት ይገባት ነበር፡፡ እርሱም ከምርጥ ያነሰ ነገር ሊሰጣት አልወደደም፡፡ እናም በአስጊ ሁኔታ ውስጥ እንኳን አድናቆቱን ሰጣት፡፡

በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ እንኳን መስጠት ማለት ልግስናችን የሚያስከፍለንን ዋጋ ከተመንን በኋላ፣ በድፍረት ድርጊቱን መፈጸም ማለት ነው፡፡ በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ መስጠት ማለት ትክክለኛውን ነገር፣ እጅግ ዋጋ የሚያስከፍለንም ቢሆን ማድረግ መቻል ማለት ነው፡፡

## በማጣት ለማግኘት የሚያግዟችሁ ወሳኝ እርምጃዎች

- በምስጋና ተሞልታችሁ ስጡ
- ከልብ ፈንቅሎ በሚወጣ ስሜት ስጡ
- ሳይረፍድባችሁ በወቅቱ ስጡ
- በጥበብ ስጡ
- በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ እንኳ ስጡ

ክፍል ሶስት ፡-

# መከራዎቻችሁን ወደ በረከት መለወጥ

# 22

# እምነታችሁን አግዝፉት

ጌታዬ ላግዝፍልዎት?›› ከዚህ ቀደም እንዲህ ያለ ጥያቄ ቀርቦልኝ ስለማያውቅ ምን መልስ እንደምሰጥ ፍንጩ አልነበረኝም፡፡ ‹‹ላግዝፍልህ ሲለኝ ምን ማለቱ ነው?›› ራሴን ጠየቅሁ፡፡ ነገሩ ትንሽ ገንዘብ ጨመር አድርጌ የምግቡን መጠን ደግሞ ገዘፍ አድርጎ ሊሰጠኝ ያቀረበልኝ ጥያቄ እንደሆነ ተረዳሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ተጨማሪ ካሎሪ (ከምግብ የሚገኝ ጉልበት) እፈልግ ስላልነበረ፣ ግብዣውን አልተቀበልኩም፡፡ ነገር ግን ምግብ ቤቱን ትቼ ስወጣ ሃሳቡን በአእምሮዬ ማውጠንጤን ላቆም አልቻልኩም ነበር፡፡

ምናለ በህይወታችን በእጅጉ የሚያስፈልጉንን እንደ ፍቅር፣ ትህትና፣ እምነት፣ ደስታና ግለትን ማግዘፍ ቢቻል ኖሮ? በሕይወት ውስጥ አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ዙሪያ ጥያቄ ብቻ በማቅረብ ከፍተኛ ተጫማሪ ማግኘት የሚቻል ቢሆን እንዴት ግሩም ይሆን ነበር?

ምናልባትም እንችል ይሆናል፡፡ ታላላቅ በረከቶች እየቀሩብን ያሉት ከእምነታችን ማነስ ሊሆን ይችል ይሆን? ‹‹አልጠየቃችሁምና አላገኛችሁም›› በማለት ያዕቆብ በመገረም ይናገራል (ያዕ. 4፡2)፡፡ ምናልባት አንድ ቀን እግዚአብሔር እጅግ የተትረፈረፈ በረከት ሊሰጠን እየፈለገ ‹‹እባክህን ያንን አግዝፍልኝ (ጨመር አድርገህ ስጠኝ) ብለን ካለመጠየቃችን የተነሳ እንዳመለጠን እናስተውል ይሆን? እይታችንን በዝቅተኛ ነገር ላይ ከማድረጋችን የተነሳ ወይም አንድን ነገር እንዲሰጠን ጌታን ለመጠየቅ በመስነፍ ተራ የሆነን ሕይወት መምራት እንዴት አሳዛኝ ነው?

በእርግጥም እምነታችንን ማግዘፍ በእጅጉ ያስፈልገናል፡፡ ይህ አስፈላጊ የሚሆንበትም ምክንያት እምነት እጅግ የከበረና ደግሞም በቀላሉ ተሰባሪ ከሆነ እቃ ጋር ስለሚመሳሰል ነው፡፡ የእምነትን ክቡርነት በተመለከተ በዕብ. 11፡6 ላይ ከተጻፈው እንረዳለን፡- ‹‹ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም››፡፡ እስቲ ይህንን አስቡት፤ እምነት ማለት ያለ እርሱ እግዚአብሔርን ማስደሰት የማንችልበት ነገር ነው፡፡ እምነት ክቡር ነው፣ ምክንያቱም ‹‹ጻድቅ በእምነት ይኖራልና›› (ሮሜ. 1፡17)፡፡ ነገር ግን ይህ ክቡሩ እምነት ሊጠፋ፣ ሊሰበር የሚችልም ነው፡፡ ኢየሱስ ይህንን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ የሚልን ወሳኝ ጥያቄ አንስቶ ነበር፡- ‹‹የሰው ልጅ በሚመጣት ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆን?›› (ሉቃ. 18፡8)፡፡

በ2 ነገ 13፡ 14-22፣ ነብዩ ኤልሳዕ ወደ ሞት ተቃርቦ እናገኘዋለን፡፡ ይህ ሰው የመምህሩን የኤልያስን ቅባት እጽፍ ተቀብሎ የነበረና እርሱ ከሰራቸው ተአምራቶች ቁጥር እጽፍ የሰራ ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን በመሞቻው አልጋ ላይ ወድቆ ሳለ በእስራኤል ንጉሥ በዮአስ ተጎበኘ፡፡ ንጉሱም ልቡ በሃዘን ተሞልቶ ኤልሳዕን ‹‹ወየው አባቴን! ወየው የእስራኤል ሠረገሎችና ፈረሰኞች!›› እያለ ያለቅስ ነበር፡፡ ንጉሡ በዚህ ንግግሩ ኤልሳዕ ለእስራኤል ያበረከተው አስተዋፅኦ ከአጠቃላይ የመከላከያ ጦር ሰራዊቷ አበርክቶት ሁሉ

በላይ እንደሆነ እየገለጸ ነበር፡፡

በነብዩ የበሽተኛ ክፍል፣ ንጉሡ አለቀሰ፣ ኤልሳዕም ያጽናናው ጀመር፡፡ መስኮቱን ከፍቶ ቀስቱን በዚያ እንዲያስፈነጥረው ነገረው፡፡ ንጉሡም እንደታዘዘው አደረገ፡፡ ኤልሳዕም ይህ እግዚአብሔር ለእስራኤል በጠላቶቹ ላይ ድልን በማቀዳጀት ረገድ የሚሰራውን የሚያመላከት መሆኑን ተናገረ፡፡ ከዚያም ኤልሳዕ ለንጉሡ ሌሎች ተጨማሪ ቀስቶችን በመውሰድ መሬቱን እንዲወጋ ጠየቀው፡፡ ዮአስ ተስማማና መሬቱን ሦስት ጊዜ ወጋ፤ ነገር ግን ነብዩ የተናደደ ይመስላል፡፡ እንዲህም በማለት ንጉሡን ጠየቀው፡- «መሬቱን አምስት ወይም ስድስት ጊዜ መውጋት ነበረብህ፤ እንዲህ ብታደርግ ኖሮ ሶርያን ታሸንፍና ፈጽመህ ትደመስሳት ነበር፤ አሁን ግን የምታሸንፈው ሦስት ጊዜ ብቻ ነው አለው፡፡» በሌላ አነጋገር፡- «ብትፈልግ ኖሮ እግዚአብሔር በጠላቶችህ ላይ ፍጹም የሆነ ድልን ይሰጥህ ነበር፡፡ አሁን ግን፣ በሚያመነታ ልብ ባደረገኸው ሙከራ፣ እግዚአብሔር የሚሰጥህ ከፊል የሆነ ስኬትን ብቻ ነው፡፡» ንጉሡ እምነቱን ማግዘፍ ነበር ያልቻለው፡፡

**የእግዚአብሔርን እቅድ ተቀበሉ**

እምነታችሁን ለማግዘፍ፣ እግዚአብሔር ለሕይወታችሁ ያለውን እቅድ ተቀበሉ፡፡ እኛ ለራሳችን ከምናቅዳቸው እቅዶች በላይ የእርሱ አላማ በእጅጉ የተሻለ ነው፤ እርሱ የጥበብና የእውቀት ሁሉ ባለቤት የሆነ ሁሉን አዋቂ ነውና፡፡ ምን ያህል ዘመን እንደምንኖርና ታላቅ ደስታ ይዞልን የሚመጣው ነገር ምን እንደሆነ እርሱ ያውቃል፡፡ አስደናቂ የሆነው ፍቅሩ አስደሳች ወደ ሆነው መዳረሻችን ሊያመጣን ይችላል (ኤር. 29፡11)፤ ነገር ግን የምርጫ ነጻነት ስላለን፣ የእግዚአብሔር ፍጹም የሆነው እቅዱ ከእኛ ታማኝነት ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ ወደ ሕይወት በሚወስደው ቀጭን መንገድ ላይ እንድንጓዝ በግድ ገፈታትሮ አይወስደንም (ማቴ. 7፡ 13-14)፤ ምንም እንኳን እኛ ከምንጠይቀውም ሆነ ከምናስበው በላይ ሊያደርግልን የሚችልም ቢሆን (ኤፌ. 3፡20)፡፡

ሙሴ የእግዚአብሔርን እቅድ በሕይወቱ በተቀበለ ጊዜ፣ ከእርሱ ግምት ውጪ የሆነን ነገር አደረገለት፡፡ ሙሴ የእስራኤልን ልጆች በምድረ በዳ ለአርባ አመታት ከመራ በኋላ፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት በእጅጉ ጓጉቶ ነበር፡፡ በዚያ ሁሉ ታዲያ እግዚአብሔርን በታማኝነት የፈለገና ከሞላ ጎደል ለእግዚአብሔር ትዕዛዛትም ታዛዥ ነበር፡፡ ከዚያም በከነአን ድንበር ላይ፣ አንዲት ቀላል ጥያቄን አቀረበ፡- « ጌታ ሆይ ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባት እፈልጋለሁ፡፡» እግዚአብሔር ግን አይሆንም አለ፡፡

ሙሴም የእግዚአብሔርን አሉታዊ ምላሽ ተቀበለና ወደ ኔቦ ተራራ ጫፍ ላይ ወጣ በዚያም ሞተ፡፡ ሆኖም ግን ይህንን የኃይማኖት አባት እንደገና በአዲስ ኪዳን በመገለጥ ተራራ ላይ ከኤልያስና ከኢየሱስ ጋር ቆሞ እናገኘዋለን (ማቴ. 17፡3)፡፡ በዚያ ተራራ ላይ፣ ሙሴ ከኢየሱስ ጋር እየተነጋገረ ነበር፡፡ ምንም እንኳን እግዚአብሔር ወደ ምድራዊቷ ከነአን እንዳይገባ ቢከለክለውም፣ እርሱ በፊት አስቦት ከነበረው እጅግ በሚልቅ ክብር ወደ ሰማይ እንደተወሰደ ግን እናያለን፡፡ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያለውን እቅድ መቀበል ምርጥ ነገር ነው፡፡

ሙሉ ጊዜዬን ሰጥቼ እግዚአብሔርን ከማገልገል ለመሸሽ የሞከርኩበትን ጊዜ በደንብ አስታውሳለሁ፡፡ ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ጥሪ ለሕይወቴ ይህ እንደሆነ ቢሰማኝም፣ ድሃ መሆን አልፈለግሁም ነበር፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ የማውቃቸው ሰባኪዎች ሁሉ ከድህነት ጋር የጠበቀ ትስስርን ያዳበሩ ነበሩና፡፡ ስለዚህም በተደጋጋሚ ለእግዚአብሔር

«አይሆንም» የሚል ምላሽ እሰጥ ነበር፡፡ «ጌታ ሆይ፣ ሌላ ሰው ምረጥ» ነበር የምለው፡፡ በመጨረሻ ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም በወሰንኩ ጊዜ ግን፣ እርሱን ለማገልገል የሚወዱኑ ሰዎች አንድም መልካም ነገር እንደማይነፍጋቸው ተረዳሁ (መዝ. 84፡11)፡፡ የእርሱን ጥሪ ለመከተል የወሰንኩት ውሳኔ በሕይወቴ ከወሰንኳቸው ጥበብን የተሞሉ ውሳኔዎች ሁሉ ትልቁ ውሳኔ ነው፡፡

በኤልሳዕ ሕይወት የእግዚአብሔርን እቅድ የመቀበልን ነገር እናያለን፡፡ የእግዚአብሔርን መንፈስ እጽፍ ቅባት ተቀብሎም የነበረ ቢሆን፣ ለሞት በሚያደርስ ሕመም ታሞ ነበር (2 ነገ. 13)፤ እንደ ኤልያስ ከመሞቱ በፊት ወደ ሰማይ የሚነጠቅበት ነገርም አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህ ሁሉ ያስጨነቀው አይመስልም፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን እቅድ መቀበልንና የሰማይንም ጥበብ ማክበርን ተምሮአልና፡፡ ይህ ጥበብ ደግሞ የተመሰረተው የእግዚአብሔርን ዝግጅት በመቀበል ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ንጉሡ ዮአስ ሊጎበኘው በመጣ ጊዜ ምንም አይነት የማማረር ነገር ከአንደበቱ አላወጣም ነበር፡፡ ንጉሡ የነብዩን መታመም አይቶ ባለቀሰ ጊዜ እንኳን፣ ኤልሳዕ ግን የዘመኑ ቁጥር በእግዚአብሔር እንደተወሰነ ያምን ነበር፤ የእግዚአብሔርን እቅድ ሙሉ በሙሉ ማስተዋል ባይችልም አምላኩን ለመታመን ወሰነ፡፡

እናንተስ እግዚአብሔር ለሕይወታችሁ ያለውን እቅድ ለመቀበል ፈቃደኛ ናችሁ? ከሆናችሁ፣ በፈቃደኝነት ለአባቱ ፈቃድ ራሱን ካስገዛው ከኢየሱስ ትምህርትን ውሰዱ፡፡ በጌተሰማኔ የአትክልት ቦታ ላይ የምሽቱ ጥላ ሲያርፍ፣ የአለም ሁሉ ሸክም በጀርባው ላይ ተሰማው፡፡ እንደዚሁም የምድሪቱ ሁሉ ኃጢአት መንፈሱን አጨናነቀው፤ ይሁን እንጂ ለአባቱ ፈቃድ ሲል የእርሱን ነገር ሁሉ ወደ ጎን ተወ፡፡

መሞት አልፈለገም ነበር፣ ለዚህም ነበር እንዲህ በማለት የጸለየው፡- «አባቴ ሆይ፣ ቢቻል ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ» (ማቴ. 26፡ 39)፡፡ ነገር ግን እንዲህ በማለት ጨመረበት «እኔ እንደምፈልገው ሳይሆን አንተ እንደምትፈልገው ይሁን፡፡»

ደቀ መዛሙርቱን «መንግስትህ ትምጣ፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን» በማለት ያስተማራቸው ኢየሱስ አልነበረምን (ማቴ. 6፡10)? ኢየሱስ የትኛውም ምስጋር፣ ዘበት፣ ፌዝ፣ ስቃይ ወይም ጥቃት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመቀበል ወደ ኋላ እንዲጎትቱት አልፈቀደም፡፡ መራራውን ጽዋ ጠጣ፡፡

የእግዚአብሔርን እቅድ መቀበል መራራውን ጽዋ እንድንጠጣ ግድ ይለን ይሆናል፡፡ በጌተሰማኔ አድርጎ ወደ ቀራኒዮ ከዚያም ወደ መቃብሩ ወደ ሚወስደው ወደ መስቀሉ መንገድ ይመራን ይሆናል፡፡ ነገር ግን ልክ እንደ ኤልሳዕ፣ እግዚአብሔር ምንም አይነት ስህተት እንደማይሰራ እርግጠኞች ልንሆን ያስፈልጋል፡፡ የእርሱ እቅዶች እንከን አልባ ናቸው፤ አላማውም ጽኑ ነው፡፡ ይህንን ማወቃችን ፍጹም የሆነውን ጸሎት፣ ‹ፈቃድህን አድርግ» የሚለውን፣ መፀለይ እንድንችል ይረዳናል፡፡

ይህንን ራስን የማስረከቢያ ጸሎት መጸለይ ይገባናል፤ ምክንያቱም እንዲህ ብናደርግ የተስፋ መቁረጥ መቃብር የሚመስለው ታሪክ የትንሣኤልን ድል የሚያስገኝ ይሆናልና፡፡ ክፋት እስከመጨረሻ እንዲያሸንፍ አብ አይፈቅድም፤ በልጆቹም ላይ አይኑን ተክሎ በመጠባበቅ እዚያው ከጨለማው አጠገብ ይቆማል፡፡ ዲያቢሎስ እኛን ከእርሱ እጅ ነጥቆ እንዲወስድ አይፈቅድም፡፡ በሁሉ ነገር፣ «እርሱን ለሚወዱትና እንደ ሃሳቡ ለተጠሩት» መልካምን ያደርጋል (ሮሜ. 8፡28)፡፡

አንድ ሰው አንዲት ቢራቢሮ ከቅርፊቷ ለመውጣት ስትታገል ይመለከታል። ይህ የለውጥ ሂደት ሲካሄድ እየተመለከተ ሳለ የእርዳታ እጁን ሊዘረጋ ፈልጎ፣ የኪስ ሰንጢውን አውጥቶ ቅርፊቱን ሰነጠቀው። ነገር ግን ቢራቢሮዋ ከቅርፊቷ ግልብጥ ብላ ወደ መሬት በመውደቅ፣ መሬቱ ላይ ክንፎቿን ድክም ባለ ጉልበት ጥቂት ካማታች በኋላ ሞተች። እግዚአብሔር ለዚያች ቢራቢሮ ከቅርፊቷ ለመውጣት በምታደርገው ትግል ውስጥ አላማ ነበረው። ቢራቢሮዋ የምታደርገው ትግል በክንፎቿ ውስጥ የደም ዝውውር እንዲዳብር የሚያደርግ ነበር። ከቅርፊቱ ለመውጣት የምታደርገው ትግል ነበር ቢራቢሮዋን ለመብረር የሚያዘጋጃት።

እግዚአብሔርም እናንተንና እኔን ለበረራ ሊያዘጋጀን ይፈልጋል፤ ነገር ግን በሚያታግል ነገር ውስጥ ሳናልፍ መሬቱን ለቀን በአየር ላይ መሆን አንችልም።

**የተቀደሰውን አክብሩ**

የእግዚአብሔርን እቅድ መቀበላችን ብዙ ጊዜ ለቅዱሱ ነገር ከምንሰጠው አክብሮት የሚመነጭ ነው። ንጉስ ዮአስ የኤልሳዕ በእስራኤል መኖር የሕዝቡን ደህንነት ተከላክሎ በመጠበቅ ረገድ ሚና እንዳለው አስተውሎ ነበር። ያለ ነብዩ ጥበብ አገሪቱ እንዴት ልትጸና እንደምትችል እንዳሳሰበው ንጉሡ መግለጹ ቅዱሱን በተመለከተ የነበረውን ግንዛቤና የትኛውም አገር ያለ መለኮታዊ እርዳታ ሊያብብ እንደማይችል ማስተዋሉን የሚያሳይ ነበር።

እምነታቸው የሚገዝፍላቸው ሰዎች ለቅዱሱ አክብሮት ያላቸው ናቸው። በአገልግሎቱ ጅማሬ ላይ ኤልሳዕን በተሳለቁበት ወጣቶች ዘንድ ይህ አክብሮት አልነበረም። አስተማሪውና ወዳጁ፣ ኤልያስ፣ በእሳት ሰረገላ ወደ ሰማይ ከተነጠቀ በኋላ፣ ይህንን ተአምር የሰሙ የተወሰኑ ወጣቶች ተሰብስበው በኤልሳዕ ላይ እንዲህ በማለት ጮኹ፡- «አንተ መላጣ፤ ውጣ! አንተ መላጣ ውጣ!» (2 ነገ 2፡23-24)። ይህም አሰቃቂ መዘዝን ያስከተለ ስህተት ነበር፣ ሁለት እንስት ድቦች ከዱር ወጥተው እነዚህን አክብሮት የጎደላቸውን ወጣቶች ሰባበሯቸው። በአጭሩ፣ ለተቀደሱ ነገሮች የሚኖራችሁ አክብሮት ሕይወታችሁን ሊያድን ይችላል።

እንዲህ ያለ አክብሮት በሕይወታችን የመኖሩ አንደኛው ምልክት አውጥተን አውርደን የምንሰራውን ኃጢአት ለማስወገድ መፈለግ ነው። ኃጢአትን በእንዲህ መልኩ በምንፈጽመው ጊዜ በእግዚአብሔር ዘንድ አጸያፊ ነው። ዳዊት ይህንን አስተውሎ እንዲህ አለ፡- «ባርያህን ከድፍረት ኀጢአት ጠብቅ፤ እንዳይሰለጥንብኝም እርዳኝ፤» (መዝ. 19፡13)። እንዲህ ያለው ልመና የአክብሮት አንድምታ ያለው ሲሆን እምነታቸውን የሚገዝፍላቸው ሰዎች የሚኖራቸው ባሕርይ ነው።

**በፍጥነት ታዘዙ**

ንጉሥ ዮአስ የዘገየ መታዘዝ ማለት ከአለመታዘዝ ጎራ እንደሚፈረጅ አስተውሎ የነበረ ሲሆን፣ እንዲህ ባለው ብልሹ ጠባይ ጥፋተኛ ሆኖ መገኘት አልፈቀደም። ኤልሳዕ በመስኮቱ በኩል ቀስቱን እንዲወረውር በጠየቀው ጊዜ፣ ወዲያውኑ ነበር መስማማቱን በድርጊቱ የገለጸው (2 ነገ. 13፡17)።

እምነትና መታዘዝ አብረው የሚሄዱ ናቸው (ያዕ. 2፡26)። እንዲያውም፣ የእምነት አንዱ ማስረጃ በፍጥረነት ወደ ድርጊት ለማምራት ፈቃደኛ መሆን ነው። ወደ አንድ ክፍል ገብቼ «እሳት!» ብዬ ብጮኽ ለዚያ ጩኸት የምትሰጡት ምላሽ በተናገርኩት

ማስጠንቀቂያ ላይ ያላችሁን የእምነት መጠን ያሳያል፡፡ ከክፍሉ ሮጣችሁ የምትወጡ ከሆነ፣ የተናገርኩትን አምናችሁ መቀባለችሁ እንደሆነ አድርጌ አስባለሁ፡፡ ነገር ግን ማስጠንቀቂያውን ከመስማታችሁ በፊት የምታደርጉትን ከቀጠላችሁ፣ የንግግሬን እውነትነት እንደተጠራጠራችሁት አሳማኝ የሆነ ማስረጃ ነው፡፡

በደቡብ ካሮላይና በፓስተርነት ስሰራ፣ አንድ እሁድ ጠዋት ስብከት ሰበኩና አንድ ወጣት ጌታን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ ለመቀበል ላቀረብኩት ጥሪ ምላሽ ሰጠ፡፡ ከአገለግሎቱ ቀጥሎ በነበረው በአንድነት ምግብ የሙብላት የእራት ጊዜ ላይ፣ እንዲህ አለኝ፡- «ፓስተር በሕይወቴ እጅግ ብዙ ሽክም ተሸክሜ ስላለሁ ዛሬ ላደረግኸው ጥሪ ምላሽ ላልሰጥ ነበር፡፡ ነገር ግን ምናልባትም ይህ በሕይወቴ ላገኘው የምችለው የመጨረሻ እድል ሊሆን እንደሚችል፣ አንድ ኃይል እንዲሰማኝ አደረገኝ፡፡

በማቴ. 25 ላይ የሚገኙት አምስቱ ሰነፍ ልጃገረዶች የዘገየ መታዘዝ ምን እንደሚመስል ለማየት እንደ ግሩም ምሳሌ ያገለግሉናል፡፡ ለሙብራታቸው ዘይት ለመግዛት እስከ አስራ አንደኛው ሰአት ከጠበቁ በኋላ፣ ሙሽራው በመጣ ጊዜ ለመግዛት ይሯሯጡ ነበር፡፡ በሠርጉም ላይ ለመሳተፍ የነበራቸውን እድል አጡ፡፡ አምስቱ ብልህ ልጃገረዶች ግን ዘይታቸውን ቀደም ብለው ገዝተው ነበር፡፡ የገዘፈው እምነታቸው በፍጥነት እንዲታዘዙ ረዳቸው፡፡

**የእግዚአብሔርን አላማ አታደናቅፉ**

ንጉሥ ዮአስን የመጀመሪያውን ቀስት እንዲያስፈነጥር ከነገረውና እንዲህ የማድረጉንም ጠቀሜታ ካብራራለት በኋላ፣ ኤልሳዕ ሌሎች ብዙ ቀስቶችን እንደዚሁ ደጋግሞ በማስፈንጠር መሬቱን እንዲወጋ ነገረው፡፡ አሁንም ንጉሡ ወዲያውኑ በመታዘዝ የተባለውን ያደረገ ሲሆን፣ ነገር ግን እምነቱ ውስን ነበር፡፡ መሬቱን በቀስቱ አቁም እስኪባል ድረስ ደጋግሞ መውጋት ሲገባው፣ ሦስት ጊዜ ብቻ ወግቶ አቆመ፡፡ ምላሹ ፈጣን ይሁን እንጂ ቀዝቀዝ ያለ ነበር፡፡ ኤልሳዕም ተናደደ፡- «አምስት ወይም ስድስት ጊዜ መትተኸው ቢሆን ኖሮ ሶርያን እስከታጠፋው ድረስ በመታኸው ነበር አሁን ግን ሦስት ጊዜ ብቻ ሶርያን ትመታለህ» (2 ነገ. 13፡ 17-19)፡፡ የንጉሡ ውሱን እምነት እግዚአብሔር ሊያደረግለት የነበረውን በመገደብ እንቅፋት ሆነበት፡፡

ምንም እንኳን እንዴት ሊሆን እንደሚችል ለማስተዋል ቢከብደንም፣ እኛም ቢሆን የእግዚአብሔርን አላማ ልናደናቅፍ እንችላለን፡፡ በማር 6፡ 5-6 ላይ ኢየሱስ ያደገበትን ከተማ ለመጎብኘት በሄደ ጊዜ የገጠመውን ስንመለከት ይህንን እንረዳለን፡፡ በወዳጆቹና በሚያውቃቸው የመንደሩ ሰዎች አለማመን ምክንያት ተአምራት እንዳያደርግ ሆነ፡፡ «ይህ የጠራቢው ልጅ አይደለምን?» አሉ፡፡ ከእነርሱ አለማመንም የተነሳ ኢየሱስ በናዝሬት ብዙ ተአምራቶችን ማድረግ አልቻለም፡፡

ምንም እንኳን አንዳንድ ባርኮቶች የሚመጡልን በመጠየቃችን ወይም ባለመጠየቃችን ላይ ተመርኩዘው ባይሆንም፣ ካልጠየቅን በስተቀር የማናገኛቸው ሌሎች ባርኮቶችም አሉ፡፡ እግዚአብሔር ለኃጢአንም ሆነ ለጻድቃን ዝናቡን ያዘንባል (ማቴ. 5፡ 45)፣ ነገር ግን አንዳንድ ባርኮቶችን በእምነት ካልጠየቃችሁ ደግሞ አታገኟቸውም (ያዕ. 4፡2)፡፡ ያዕ. 1፡5 እግዚአብሔር በእምነት ለሚጠይቀው ሁሉ ጥበብን እንደሚሰጥ ይናገራል፡፡ ሉቃ. 11፡ 13 ደግሞ እግዚአብሔር ለሚጠይቁት መንፈስ ቅዱሱን ሊሰጣቸው እንደሚጓጓ ያስታውሰናል፡፡ እግዚአብሔር የመምረጥ ነጻነት ያለን ፍጡራን አድርጎ ስለፈጠረን

እርሱን ለማገልገልም ሆነ ለመቃወም የመምረጥ ነጻነቱ አለን፡፡ አላማውን ፈቃደኛ ባልሆኑ ሰብአዊ ፍጡራ ላይ በግድ ጫና ፈጥሮ ማስፈጸም አይፈልግም፡፡ እግዚአብሔር ከሮቦቶች የበለጠን ነገር ይፈልጋል፡፡ ለዚህ ነው ኢየሱስ በእርሱ ለማመን አምጸው በነበሩት በገዛ ወገኖቹ መካከል ብዙ ተአምራቶችን ሊሰራ ያልቻለው፡፡ እነርሱም የእግዚአብሔርን አላማ አደናቀፉ፡፡

በማቴ. 16፣ ደቀ መዝሙር ጴጥሮስ ኢየሱስን ሲያደናቅፈው እናያለን፡፡ ኢየሱስ በቅርብ ሊሆን ስላለው ሞቱ ሲናገር፣ ጴጥሮስ በተቃውሞ እንዲህ በማለት ተናገረ፡- «ይህ በፍጹም ሊሆንብህ አይገባም» (ቁጥር 22)፡፡ ነገር ግን ሊሆንበት የግድ ይገባ ነበር፤ ምክንያቱም ያለ ቀራኒዮ መስቀል አለም አትድንም ነበረና፡፡ የጴጥሮስ መንፈሳዊ ነገሮችን ለማስተዋል አለመቻል በእርሱ ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር ሊሰራ የወደደውን ለጊዜውም ቢሆን በማሰናከል ክርስቶስን ሦስት ጊዜ ወደ መካድ መራው፡፡

## ከሚጠበቅባችሁ ርቀት በላይ ጨምራችሁ ሂዱ

ከሚጠበቅባችሁ በላይ ትሰጣላችሁ? ርብቃ እንዲህ አድርጋ ነበር፡፡ ግዙፉ እምነቷ የይስሐቅ ሚስት ለመሆን አበቃት፡፡ በዘፍ. 24 ላይ የአብርሃም አገልጋይ ኤልኤዘር ለጌታው ልጅ ሚስትን ለመፈለግ በወጣበት መንገድ የእግዚአብሔርን እርዳታ ፈለገ፡፡ እግዚአብሔርም በጣም በትጋት የተሞላ የስራ ስነምግባር ወዳዳበረች ሴት ወሰደው፤ ይህችም ሴት ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለግመሎቹ ሁሉ ውሃን ያጠጣች ነበረች፡፡ ርብቃ ወደ ውሃው ጉድጓድ በመቅረብ ይህንን ድርጊት አከናወነች፡፡ ይህ ደግሞ ቀላል መጠን ያለው ውሃ አይደለም ከ100 ጋሎኖች የሚበልጥ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን አደረገችው፡፡ እግዚአብሔርም እምነቷን አከበረላት፡፡ እኛም ከሚጠበቅብን ርቀት በላይ ጨምረን በመሄድ በመከራችን ውስጥ በረከትን ማግኘት እንችላለን፡፡

## እምነታችሁን ለማግዘፍ የሚያግዟችሁ ወሳኝ እርምጃዎች

- የእግዚአብሔርን እቅድ ተቀበሉ
- የተቀደሰውን አክብሩ
- በፍጥነት ታዘዙ
- የእግዚአብሔርን አላማ አታደናቅፉ
- ከሚጠበቅባችሁ ርቀት በላይ ጨምራችሁ ሂዱ

# 23

# ማዕበል የማይበግረውን ሕይወት ገንቡ

ከእኔ ራቅ ቻፕሌን፣» አለኝ ሴናተሩ፡፡

«ከእኔ ዞወር በል፣ ቻፕሌን፣» አሉ ሴናተሩ፡፡ ነገሩን በደንብ ለመመልከት ሞከርኩ እናም ምንም አይነት የቀልድ የሚመስል ነገር ላስተውል አልቻልኩም፡፡ እንደገና ፊታቸውን ጨምደድ አድርገው ራሳቸውን በመድገም፣ «ቻፕሌን፣ ከምሬ ነው ከእኔ ዞወር በል» አለኝ፡፡

ይህ ሴናተር በየሳምንቱ በማካሂደው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ ያለ ማቋረጥ ይከታተል ስለነበረ፣ የዚህ ችግር መንስኤው ምን እንደሆነ ለማወቅ ተገፋፋሁ፡፡ እንዲህም ብዬ ጠየቅሁ፡- «የሚያስከፋህን ነገር አድርጌ ይሆን?»

«አንተ አይደለህም ቻፕሌን፤ እግዚአብሔር ነው እንደዚያ ያደረገው፡፡ እርሱ እኔን ለማሳደድ ቆርጦ ተነስቷል፤ እናም አንተም ከእኔ ጋር ስትጎዳ ማየት አልፈልግም፡፡»

«ከልብህ ነው፣ አይደል?»

«አዎ፣ ቻፕሌን፣ በጣም ከልቤ ነው፡፡»

ነገሩን ኮስተር ብሎ መናገሩ አንድ ለከባድ ጥፋት ያጋለጠው አደጋ በሕይወቱ መከሰቱን የሚያንጸባርቅ ነበር፡፡ ካትሪንና ሪታ የተባሉት ዝናብ የቀላቀሉ ኃይለኛ አውሎነፋሶች የሴናተሩን ሁለት ቤቶች አውድመውበት ነበር፡፡ እንደዚሁም ከዚህ ማዕበል በሚደረገው ሽሽት ላይ እናቱ በመንገድ ሞታበት ነበር፡፡ እንዲህ ያሉ አጥፊ አደጋዎችን ከተጋፈጠ በኋላ፣ ሴናተሩ ሊስተዋል የሚችል የአእምሮ ህመም ነበር የገጠመው፡፡

ግን በእርግጥ እግዚአብሔር ሴናተሩን ለማሳደድ ወጥቶ ይሆን? ወራቶች እያለፉ ሲሄዱ፣ ሴናተሩና እኔ ወደ አንድ ድምዳሜ ደረስን፡፡ ይኸውም፣ ማዕበል በጻድቁም ሆነ ጻድቅ ባልሆነው በማንም ላይ የሚደርስ የሕይወት እጣ ፈንታ እንደሆነ ነበር፡፡ ይህም

እውነታ ማዕበል የማይበግረውን ሕይወት የመኖርን አስፈላጊነት እጅግ ከፍተኛ ያደርገዋል፡፡

ለመሆኑ ሕይወታችንን በማዕበል የማይበገር ልናደርገው የምንችለው እንዴት ይሆን? በማቴ. 7፡ 24-27 ላይ፣ ኢየሱስ እንዴት እንደሚቻል ይነግረናል፡፡ የእርሱን ቃል ሰምተው የሚያደርጉ (የሚታዘዙ) ሁሉ ማዕበልን መቋቋም በሚችል ዐለት ላይ ይገነባሉ፡፡ እንደዚሁም በዚሁ ንግግሩ ላይ ተዘጋጀንም አልተዘጋጀንም ማዕበል በሁሉም ህይወት ውስጥ የማይቀር ነገር እንደሆነ ግልጽ አድርጓል፡፡ ነገር ግን በትክክል የገነቡ ሰዎች በመጨረሻ በስኬት ይሞላሉ፡፡

## አስታውሱ፤ ብቻችሁን አይደላችሁም

ነብዩ ኤልያስ የሕይወትን ማዕበል በተጋፈጠ ጊዜ፣ ብቸኝነት ተሰማው፡፡ ለእግዚአብሔርም እንዲህ አለው፡- «ለሠራዊት አምላክ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀንቻለሁ የእስራኤል ልጆች ቃል ኪዳንህን ትተዋልና፥ መሠዊያዎችህንም አፍርሰዋልና፥ ነቢያትህንም በሰይፍ ገድለዋልና እኔም ብቻዬን ቀርቻለሁ» (1 ነገ. 19፡14)፡፡ ይህ አመለካከቱ የተሳሳተ ሲሆን፣ ሞትንም አስመኝቶት የነበረው ይኼው ነበር፡፡ እናም እግዚአብሔርን ሕይወቱን እንዲወስድ ጠየቀው፡፡

በማዕበል የማይበገር ሕይወት ለመገንባት ከፈለግን፣ የኤልያስን የተሳሳተ አስተሳሰብ ከአእምሮአችን ማስወገድ አለብን፡፡ እግዚአብሔር ልጆቹን ከቶ እንደማይጥል የሰጠውን ተስፋ የሙጥኝ ብለን ልንይዝ ይገባል (ዕብ. 13፡5) ደግሞም እስከ አለም ፍጻሜ ድረስ ከእኛ ጋር ሊሆን ቃል ገብቷል (ማቴ. 28፡20)፡፡

እግዚአብሔር እርሱን ያላሳዘኑና ጉልበታቸውም ለጣዖት ያላንበረከኩ ሰባት ሺ ቅሬታዎች እንዳሉት ለኤልያስ ገለጸለት፡፡ ኤልያስ በራሱ የግል ችግሮች በጣም ተውጦ ስለነበረ እነዚህን ሰባት ሺ ሰዎች አላስተዋላቸውም ነበር፡፡

የተሻለ እውቀት ሊኖረው ይገባ ነበር፡፡ የማዕበል ነጎድጓድ አድሎ አያደርግም፡፡ ጻድቁንም ኃጢአተኛውንም፣ ሃብታሙን ደሃውን፣ የታሰረ ወይም ነጻ ብሎ ሳይለይ ይመጣል፡፡ በተመሳሳዩ፣ የሕይወት ማዕበልም የሚነካው የእያንዳዱን ሰው ህይወት ነው፡፡ በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ ዝናብ መዝነቡ ግድ ነው፡፡

## እግዚአብሔርን መስማት ተማሩ

ሕይወታችንን ማዕበል እንዳይበግረው የምናደርግበት ሌላው ነገር ደግሞ የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በተፈጥሮ በኩል ይናገረናል፣ ምክንያቱም ሰማያት የእርሱን ክብር ይናገራሉ (መዝ. 19፡1) ተብሎ ተጽፎአልና፡፡ ጸጥ ባለ ሐይቅ ወይም ደረቱን ሰጥቶ በቆመ ተራራ በኩል እግዚአብሔር ሲናገረኝ እሰማለሁ፡፡ በከዋክብት ከደመቀው ሰማይም የእርሱ ድምጽ ሲንሾካሾክ እሰማለሁ፡፡ ነገር ግን በአብዛኛው፣ በቅዱሳት መጻሕፍቱ በኩል ይናገረኛል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔር ቃል ብሎ መጥራት ዘይቤያዊ አነጋገር ብቻ አይደለም፡፡ መዝሙረኛው

እንዲህ በማለት ነበር የገለጸው፡- «ህግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው፡፡» (መዝ. 119፡ 105)፡፡

የእግዚአብሔርን ድምጽ ምን ያህል አጥርታችሁ ትሰማላችሁ?

በ1 ሳሙ. 3 ላይ ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምቶ የነበረም ቢሆን ነገር ግን እንዳላስተዋለው ይነግረናል፡፡ በተደጋጋሚ ወደ ካህኑ ወደ ኤሊ ሲሄድ፣ በሂደት ካህኑ ድምጹ ተመልሶ ሲመጣ ለራሱ ለእግዚአብሔር ምላሽ እንዲሰጥ እንዲህ በማለት አስተማረው፡- «ጌታ ሆይ፣ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር» በል አለው፡፡ እኛ ግን ብዙ ጊዜ፣ የዚህን ጩኸት ሃሳብ ቀይረን «ስማ ጌታ ሆይ፣ ባሪያህ ይናገራል» ብለን ነው የምንጸልየው፡፡

ጴጥሮስም ቢሆን ከመስማት ይልቅ መናገር የሚቀናው ሰው ነበር፡፡ በማር 14፡30 ላይ ጴጥሮስ ለክርስቶስ ለመሞት የተዘጋጀ መሆኑን ከገለጸ በኋላ፣ ኢየሱስ ጴጥሮስ እንደሚክደው አስቀድሞ ተናገረ፡፡ ዶሮ ሁለት ጊዜ ከመጮኹ በፊት ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ አለው፡፡

ጴጥሮስ በእርግጥ የሚሰማ ሰው ቢሆን ኖሮ፣ የዶሮውን የመጀመሪያ ጩኸት ሰምቶ ይቅርታን ፍለጋ ወደ እግዚአብሔር በተመለሰ ነበር፡፡ ነገር ግን አልሰማም ነበር፡፡ በመንፈሳዊ ጆሮው በጣም ከመደንቆሩ የተነሳ የመጀመሪያውን የዶሮ ጩኸት አላስተዋለውም ነበር፡፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከለትን የማንቂያ ደውል እንኳን አልሰማም፡፡

አንድ ጊዜ ኃጢአት ለመስራት ያቀድኩበትንና ከእግዚአብሔር የተላከን ማስጠንቀቂያ የሰማሁበትን ጊዜ አስታውሳለሁ፡፡ ልሰራ የፈለግሁትን ኃጢአት ለመስራት ነገሮችን ለማመቻቸት ከፍሌን ትቼ እየወጣሁ ሳለ በዚያ የነበረውን ሰአት መቁጠሪያ ስመለከት 3፡16 ይል ነበር፡፡ ይህ በእርግጥም የጌታ ዝግጅት ውጤት እንደሆነ እርግጠኛ ነበርሁ፡፡ ምክንያቱም ወዲያውኑ ወደ አእምሮዬ የመጣው ዮሐ. 3፡16 ነበር፡፡ በዚያ የሰፈረውን የእግዚአብሔርን አስደናቂ ፍቅርና ልግስናውን ማሰብ ብቻውን እኔን ከክፋት ለመመለስ በቂ ኃይል ነበረው፡፡

እናንተስ የእግዚአብሔርን ድምጽ እየሰማችሁ ነው? ማዕበል የማይበግረው ሕይወት እንዲኖራችሁ ከፈለጋችሁ ይህንን ማድረግ ግድ ነው፡፡

**እምነታችሁን በድርጊት ግለጹ**

ኢየሱስ እንዳስቀመጠው ማዕበል የማይበግረው ሕይወት የሚታነጸው የእግዚአብሔርን ቃል በመስማትና በማድረግ ነው፡፡ በአፋችን የምናወራው ነገር ድርጊት ሊከተለው ይገባል፡፡ ልክ በእስር ቤት እንደዘመሩት፣ እንደ ጳውሎስና ሲላስ (የሐዋ. 16፡25)፣ በሕይወት ውስጥ የሚገጥሙንን ማዕበሎች መጋፈጥ የሚያስችለንን ጥንካሬ ታማኝነት በተሞላ መታዘዝ ውስጥ ልናሳድገው እንችላለን፡፡

ከጓደኞቼ መካከል አንደኛው ለሹመት ባልተመረጠ ጊዜ፣ ላጽናናው ደወልኩለት፤ ነገር ግን እጅግ በደስታና በተስፋ ተሞልቶ አገኘሁት፡፡ «ቤሪ» አለኝ « ሁሉም ሰው እኮ ሊሾም አይችልም፡፡ አንዱ ወደሌላው ደረጃ እንዲወጣጣ ሌላው ወደ ጎን መደረግ አለበት፡፡ ታዲያ ወደ ጎን የተደረገው ሰው እኔ ብሆን ምን አለበት?»

ይህንን ከአንደበቱ ስሰማ በጣም ተገረምኩ፡፡ ምክንያቱም ይህ ግለሰብ በብዙ ነገር በጣም አመርቂ ችሎታ ያለው ነበርና፡፡ ነገር ግን ይህ ሰው የሰበከውን ተለማመደ፤ በሕይወት የሚገጥሙ ያልተጠበቁ ዱብ እዳዎችንም በትህትናና በእምነት ለመቀበል በሚያምነው ነገር ላይ እርምጃን ወሰደ፡፡ ማዕበል የማይበግረውን ሕይወት ገንብቶ ነበር፡፡ (መልካሙ ዜና ታዲያ ይህ ሰው ከጥቂት አመታት ኋላ ለመሾም በቃ፡፡)

በሚያምኑበት ነገር ላይ በተግባር ለሚንቀሳቀሱ ሰዎች መልካም ነገር ይሆንላቸዋል፡፡ እምነት ያለ ተግባር ውጤት አልባ ነውና፡፡ ያዕ. 2፡26 ይህንን እንዲህ በማለት ግልጽ ያደርገዋል፡- «ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።»

ኢየሱስ ከሞት እንደተነሳ ከሚሰጡ ማረጋገጫዎች መካከል አንደኛው ተከታዮቹ ለእምነታቸው ሲሉ ለመሞት የነበራቸው ቁርጠኝነት ነው፡፡ ሃሰተኛ ሰዎች ስለ እነርሱ ሰማዕት የሚሆኑ ሰዎችን ሊያፈሩ አይችሉም፡፡ ነገር ግን የኢየሱስ ደቀመዛሙት በደስታ ነበር ሞትን የተጋፈጡት፡፡ ሕይወታቸውና ቃሎቻቸው ተመሳሳይ ነበሩ፡፡ በማዕበል የማይበገር ሕይወትን ለዘላለም አግኝተው ነበር፡፡

**ለሕይወት ማዕበል የተዘጋጃችሁ ሁኑ**

በ1 ቆሮ. 16፡9 ላይ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ምቹ እድልና ስለ አስቸጋሪ ሁኔታ ይናገራል፡፡ እንዲህ ነው የሚጽፈው፡- «ሥራ የሞላበት ትልቅ በር ተከፍቶልኛልና ተቃዋሚዎችም ብዙ ናቸው።» ይህ አርፍተ ነገር በእውነት የተሞላ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ በሕይወት ውስጥ ምቹ እድሎች የሚመጡት ከአስቸጋሪ ሁኔታዎች ጋር ተለጥፈው ነው፡፡

ዊንስተን ቸርችል ይህንን እውነታ ተረድቶ ነበር፡፡ በሁለተኛው የአለም ጦርነት ጊዜ አለምአቀፍ ተሰሚነት በነበረው መድረኩ ህዝቡንና አለምን ሁሉ ለማነቃቃት በንግግሩ ብዙ ተጽእኖን መፍጠር ችሎ ነበር፡፡ የቸርችል የንግግር ጥበብና ተሰሚነት ደግሞ ይበልጥ እያበበ የሄደው በጦርነቱ መፋፋም ውስጥ ነበር፡፡ ማርቲን ሉተር ኪንግ ደግሞ ሌላው በአደባባይ የመናገር ችሎታው በአሜሪካ በጥቁሮችና በነጮች መካከል የሚደረገውን መድሎና መለያየት በመቃወም ይናገር ነበር፡፡ ነገር ግን ጥረቶቹ በፖሊስ ውሾች፣ በእሳት አደጋ ፈረስና ደም በብዛት በሚፈስበት የዘር ጭፍጨፋ ውስጥ ማለፍ ነበረበት፡፡

ቸርችልም ሆነ ኪንግ የሕይወትን ማዕበል የተጋፈጡበት የተረጋጋ መንፈስ በሕይወት ወስጥ አስቸጋሪ ነገሮች እንዳሉ አስቀድሞ በማሰብ ተዘጋጅቶ መጠበቅ ምን ያህል ጠቃሚ እደሆነ ያሳያል፡፡ በ1960 ባደረገው ንግግር ላይ ማርቲን ሉተር ኪንግ ይህንን አስመልክቶ እንዲህ ብሎ ነበር፡፡ «አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ለመሰቃየት እንደዚሁም ለእውነት ምስክር ለመሆን ህይወታችንንም ቢሆን ለመስጠት ዝግጁዎች ነን፡፡ ይህ ስቃይንና መስዋዕትነትን እንደሚያመጣ አውቃለሁ፡፡ ወደ እስርቤት መግባት ሊሆን ይችላል...

አካላዊ ሞትም ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ልጆቹን ቋሚ ከሆነ የመንፈስ ሞት ነጻ ለማውጣት አንድን ሰው የሚያስከፍለው ይህንን አካላዊ ሞት መሞት ከሆነ ከዚህ የበለጠ ትልቅ ነገር የለም፡፡» (Martin Luther King Jr., *The Papers of Martin Luther King Jr.*, vol. 5, Clayborne Carson, ed. (Berkeley: University of California Press, 2005), 504–505). ዶክተር ኪንግ ለነጻነት የሚያደርገውን ትግል እጅግ ከባድ የሆነ ማዕበል እንደሚገጥመው ያውቅ ነበር፡፡ ይህም ማዕበል ለዚህ አላማ መሳካት ሊሰጥ የሚችለውን የመጨረሻውን ነገር እንዲሰጥ አደረገው፡፡

በመሆኑም ለሕይወት ማዕበሎች ራሳችንን አዘጋጅተን መጠበቅ አለብን፡፡ ለዚህ ነው በኢየሱስ ምሳሌ ላይ የተገለጸው ሰው ቤቱን በአሸዋ ላይ ሳይሆን በአለት ላይ ሰርቶ የጠበቀው፡፡ ተጨማሪ ጥረት የሚጠይቅ ግንባታ የገነባው ዝናብ፣ ጎርፍና ንፋስ ይመጣል ብሎ ስለተጠባበቀ ነው፡፡ በአሸዋ ላይ ቤትን ማነጽ ቀላል እንደሆነ ያውቃል፡፡ ነገር ግን ያንን ማድረግ ሊመጡ ላሉ ማዕበሎች በበቂ ሁኔታ አለመዘጋጀት መሆኑንም ጨምሮ ያውቅ ነበር፡፡ ይህ ሰው ራሱን ሊመጣ ላለው መከራ አዘጋጀ፡፡

**በንቃት ጠብቁ**

የሕይወት ማዕበል ሞገድ ሲያጓራ፣ ምንድን ነው ማድረግ ያለብን? አማኝ ያልሆኑ ሰዎችም ቢሆኑ ተመሳሳይ ግድድሮሾችን የሚጋፈጡም ቢሆን፣ እግዚአብሔርን ለሚያገለግሉ ሰዎች የህይወት ማዕበልን መጋፈጥ ከባድ ነገር ነው፡፡ እግዚአብሔር ከችግር የማያስመልጠን ለምንድን ነው? ብለን እንጠይቅ ይሆናል፡፡ እንዲህ ባሉ ጊዜያት፣ የህይወት ማዕበሎችን መጠባበቅና በንቃትም መጠበቅን ማስታወሱ በጥበብ የተሞላ አካሄድ ነው፡፡ ሂውጎ የተባለው ዝናብ የቀላቀለ አውሎ ንፋስ ሳውዝ ካሮላይናን በመታ ጊዜ፣ መላ ቤተሰቤ ጓዛችንን ከቤታችን አውጥተን ጥለን ለመሄድ ተገደን ነበር፡፡ ይህም የሆነው በማዕበሉ ላይ አይናቸውን ተክለው የሚጠባበቁት ሜትሮሎጂስቶች አደጋ ከፊት እየመጣ እንዳለ ስላሳሰቡን ነበር፡፡

ከፊት ለፊቱ ትልቅ እውቀትን የሚጠይቅ ሙያ ተዘርግቶለት ያንን በመተው ካህን የሆነው ወጣቱ ካህን ፉልቶን ሺን፣ ማቴ. 26፡40ን በሚያነብበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል በተለየ ሁኔታ እንደተሰማው ይገልጻል፡፡ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሺንን ኢየሱስ ከእንቅልፋቸው ባነው ለነቁት ሶስቱ ደቀ መዛሙት «ከእኔ ጋር አንድ ሰአት እንኳን ልትተጉ አልቻላችሁምን?» ብሎ ወደ ጠየቀበት ወደ ጌተሰማኔ ይዞት ሄደ፡፡ እነዚህ የኢየሱስ ቃላት የሺን ልብ ወጉት፡፡

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ከኢየሱስ ጎን ሊቆሙ አልቻሉም ነበር፡፡ ወደ ጎልጎታ በተቃረበ ጊዜ፣ ጌታችን ነፍሱ ለሞት እስኪደርስ ድረስ በእጅጉ ተጨንቃ ነበር፣ የሌሎችን ድጋፍ ፈልጎ ነበር፡፡ በእርግጥም ማዕበል ከፊት ለፊቱ ነበር፡፡ እነዚህ ሶስቱ ደግሞ ለእርሱ በጣም የሚቀርቡት ወዳጆቹ ነበሩ፡፡ በአገልግሎቱ ዘመን ሁሉ በእነርሱ ላይ በብዙ ይተማመን ነበር፡፡ አሁን ደግሞ እንዲህ በማለት ተማጸናቸው፡- «አብራችሁኝ ቆዩ፤ በተለይ በዚህ ማታ የእናንተ እርዳታ በእጅጉ ያስፈልገኛል፡፡» ይህንን ካላቸው በኋላ ወደ አትክልት ስፍራው ውስጥ ዘልቆ በመግባት በጭንቀት በተሞላ ጸሎት ልቡን ያፈስ ነበር፡- «አባት ሆይ፣ ፈቃድህስ ቢሆን ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን ያንተ ፈቃድ ይሁን፡፡» እጆቹን ወደላይ አንስቶ ከሚጸልይበት ስፍራ ወደ ደቀመዛሙርቱ

ሲመለስ፣ ያገኛቸው እንቅልፋቸውን ተኝተው ነበር፡፡ በሁኔታው በማዘን እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፡- «ከእናንተ አንዲት በትጋት የምትጸልዩበትን ጊዜ መጠየቄ ለእኔ ብዙ ነገር መጠየቄ ነውን?» ጌታ በንቃት ይጸልያሉ ብሎ ጠብቆባቸው ነበር፡፡ ምክንያቱም የድል ነሺ ሕይወት ሁለቱ ምሰሶዎች እነዚህ ናቸውና፡፡ ያለ ጸሎት የሆነ ንቃት ከቅጥ ያለፈ ፍርሃት እስረኞች ያደርገናል፤ ነገር ግን ያለ ንቃት መጸለይ ደግሞ አይንን ጨፍኖ መኪና እንደመንዳት ነው፡፡ ድል ነሺ ሆነን መቆም ከፈለግን ሁለቱም ምሰሶዎች ያስፈልጋሉ፡፡

ሺን ኢየሱስ ከሰዎች እንዲህ ያለውን የጸሎት ድጋፍ በመፈለጉ በጣም ልቡ ተነክቶ በልቡ አንድ ቃልኪዳን አደረገ፡፡ እንዲህ በማለት ጸለየ፡- «ጌታ ሆይ፣ በቀረኝ እድሜዬ ሁሉ፣ ያንን የፈለግኸውን አንድ ሰአት እሰጥሃለሁ፡፡ ከአንተም ጋር በንቃት እጠብቃለሁ» አለ፡፡ ለስድስት አስርት አመታት በቆየው አገልግሎቱ፣ ሺን በየቀኑ በቤተክርስቲያን ውስጥ ከክርስቶስ የመስቀል ምልክት ስር በመሆን ለአንድ ሰአት ላላነሰ ጊዜ ለመጸለይ መታገል ጀመረ፡፡ ሺን መንፈሱን አንቅቶ የመጠበቅና የመጸለይ አስፈላጊነት ገብቶት ነበር፡፡

ነህምያም እንዲህ ያለ በንቃት መጠባበቅ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ያውቅ ነበር፡፡ በነህ. 4፡9 ላይ፣ የኢየሩሳሌምን ቅጥር በሃምሳ ሁለት ቀናት ውስጥ በመጨረስ መከራውን ወደ በረከት እንዴት እንደለወጠው ይነግረናል፡፡ የእርሱን ጥረቶች በማንቋሸሽ ይዘብቱበት በነበሩት ጠላቶቹ ዛቻና ማስፈራሪያ ቢደርስበትም፣ ነህምያ ግን እንዲህ በማለት ይጽፋል፡- «ወደ አምላካችንም ጸለይን፥ ከእነርሱም የተነሣ በአንጻራቸው ተጠባባቂዎች በሌሊትና በቀን አደረግን።»

እንደ ነህምያ ተጠባባቂዎችን ማስቀመጥ እንዲሁ ከመጠበቅ ይለያል፡፡ ተጠባባቂዎችን ማስቀመጥ ነገሮችን አርቆ በማየት በእቅድና በተነሳሽነት መስራትን ያመለክታል፡፡ ክርስቲያኖች እንዲህ ያለውን የመጠበቅ ልምምድ የምንለማመደው እውነታዎችን በእግዚአብሔር የማይወድቅ ቃል መነጽር ማየት ስንጀምር ነው፡፡ ይህ ደግሞ በ2 ነገ. 6፡17 ላይ ኤልሳዕ በፍርሃት የሚንቀጠቀጠው አገልጋዩ አይኖቹ ተከፍተው እንዲያይ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይለት ያገኘውን አይነት አመለካከት መያዝ ማለት ነው፡፡ ኤልሳዕ፣ የእርሱ አገልጋይ ሊያይ ያልቻለውን እውነታ ማየት ችሎ ነበር፡፡ ይኼውም ነገሮች የማይሆኑ በመሰሉበት ጊዜ የመጣላቸውን መለኮታዊ እርዳታ ነበር፡፡ በእግዚአብሔር ቃል እንደተገለጠው፣ እውነታዎችን ከመለኮት እይታ አንጻር በማየት መከራችንን ወደ በረከት መለወጥ እችላለን፡፡

ነቅተን መጠባበቅ ካለብን፣ እንቅልፍን መዋጋት ያስፈልገናል፡፡ በሮሜ. 13፡11 ከእንቅልፋችን እድንነቃ እንዲህ በማለት ይነግረናል፡- «ካመንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን አሁን ወደ እኛ ቀርቦአል፡፡» መንፈሳዊ ልማዶቻችንን ችላ ስንል፣ ለመጸለይና መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ ጊዜ ስናጣ፣ ያን ጊዜ መንፈሳዊ እንቅልፍ ይወስደናል፡፡ ከልክ በላይ ራሳችንን ከፍ ከፍ አድርገን ስናይ፣ የቆሙ የሚመስላቸው እንዳይወድቁ ይጠንቀቁ (1 ቆሮ. 10፡12) የሚለውን መልእክት ስንዘነጋ እንቅልፍ ይዘን ይሄዳል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ በእጅጉ አሳዛኝ ከሆኑ ጥቅሶች መካከል አንደኛው፣ መሳ. 16፡20 ሲሆን፣ በዚህም ክፍል ላይ ሳምሶን መቼ ጌታ ከእርሱ እንደተለየው እንደማያውቅ ይናገራል፡፡ እግዚአብሔር በእርሱ ሕይወት ላይ ያኖረውን የተለየ ስጦታ

እንደ ዋዛ ቆጥሮ በጠላቱ ጭን ላይ ሳምሶን ተኝቶ ነበር፡፡ ነገር ግን ደሊላ ገንዘብ የተከፈላት አሳልፋ ሰጪ ነበረች፡፡ የኃይሉን ምስጢር እስኪነግራት ድረስ አዚም አድርጋበት ነበር፡፡ ሳምሶን ከእንቅልፉ ተነስቶ ራሱን ለመከላከል በቃጣ ጊዜ፣ ኃይል አልባ መሆኑን አስተዋለ፡፡ እግዚአብሔር ትቶት ነበር፤ ደህና ሁን እንኳን አላለውም፡፡ ሳምሶን ነቅቶ መጠበቅ ሲገባው እርሱ ግን ተኝቶ ነበር፡፡

መልካሙ ዜና ታዲያ ሳምሶን መከራውን ወደ በረከት ለውጦ ታሪኩን መደምደሙ ነው፡፡ ይህንንም ያደረገው ንስሃ በመግባት ነበር፡፡ በጠላቶቹ ቁጥጥር ስር ውሎ በግድ ባሪያ አድርገው እንዲያገለግል አደረጉት፡፡ ያን ጊዜ ሳምሶን እንደገና ወደ እግዚአብሔር ፊቱን መለሰ፡፡ ጸጉሩ ተመልሶ መብቀል ጀመረ፡፡ እግዚአብሔርም በሂደት የተወለደበትን አላማ ይኼውም ህዝቡን ከፍልስጤማውያ ነጻ ማውጣትን እንዲያሳካ አደረገው፡፡ የሳምሶን ሕይወት ሁልጊዜ ንቁ ሆነን በመንፈሳችን እንድንጠብቅ ያስተምረናል፡፡

**ነቅቶ በመጠበቅ ፈተናን አሸንፉ**

ነቅተን ሁልጊዜ መጠበቃችን ፈተናን ለማሸነፍ ይረዳናል፡፡ በጌተሰማኔ የነበሩት ደቀ መዛሙርት ለመተኛት ፈተና እጃቸውን የሰጡት ነቅተው በመጠበቅ ስላልቆዩ ነው፡፡ ኢየሱስም ውስንነታቸውን(ገደባቸውን) ከግምት በማስገባት «መንፈስ ዝግጁ ነው ስጋ ግን ደካማ ነው» (ማቴ. 26፡41) በማለት ተናገረ፡፡

ነቅቶ መጠበቅ አደጋን ገና ከሩቁ የማየትንና የማስወገድን ጥበብ ለማሳደግ ይረዳል፡፡ ዮሴፍ ወደ ፍትወት ፈተና ትገፋፋው ወደነበረችው የጶጢፋራ ሚስት ሊቀርብ እንኳን ባለመፈለግ በጥበብ የተሞላ አካሄድን ሄደ፡፡ (ዘፍ. 39፡10)፡፡ በ1 ተሰ. 5፡ 22 ላይ «ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ፡፡» የሚለው እንዲህ ያለውን አካሄድ ነው፡፡

**በሌሎች ዘንድ አመኔታ ማግኘትን አዳብሩ**

እግዚአብሔር ይታመንባችኋል? አስተማማኝ ናችሁ? እግዚአብሔር በኢዮብ ላይ የነበረው መተማመን በጣም ትልቅ ስለነበረ፣ ሰይጣንን እንዲህ ብሎ ጠይቆት ነበር፡- « ባሪያዬን ኢዮብን አይተኸዋል? በምድር ላይ እንደ እርሱ ያለ ማንም የለም» (ኢዮብ፣ 1፡8)፡፡ ለመሆኑ እግዚአብሔር ስለ እርስዎስ እንደዚህ ይላል?

ነቅተን መጠበቃችን በሌሎች ዘንድ አመኔታ እንዲጣልብን ያግዘናል፡፡ እግዚአብሔር እኔን እንደማይታመን ሰው አድርጎ እዲስለኝ አልፈልግም፡፡ አስተማማኝ ክርስቲያኖች ከትክክለኛው የሃቅ መንገድ ዝንፍ አይሉም፡፡

ማቴ. 24፡42 እንዲህ በማለት ይገዳደረናል፡- «ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ፡፡» ታማኝ ሆኖ መገኘት ማለት ይኼ ነው፡፡ ተጠያቂ የሆናችሁለት እርሱ ስራችሁን ሲመዝን፣ ይደሰት ይሆን? እርሱ ሳይታሰብ ድንገት ቢመጣ እንኳን በበቂ ሁኔታ ተዘጋጅታችኋል? ነገር ግን ከነቃችሁና ከጸለያችሁ ይህንን መለማመድ ትችላላችሁ፡፡

**በሕይወት የሚያጋጥሙንን አስጨናቂ ነገሮች ተጋፈጧቸው**

ማዕበል የማይበግረውን ሕይወት መገንባት በሕይወት የሚገጥሙንን መከራዎችና ፈተናዎችን መጋፈጥን ይጠይቃል፡፡ በእርግጥም እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚዱ

ሁሉ መከራን ይቀምሳሉ (2 ጢሞ. 3፡12)፡፡ ነገር ግን የሕይወት አስጨናቂ ነገሮች ሁለንተናችንን እንዲውጡት ካደረግን፣ ወደ ሽንፈት እናመራለን፡፡

ይህንን ጹሁፍ በምጽፍበት ጊዜ፣ በኒብራስካ የሚገኝ አንድ ልጅ ወደ ገበያ አደራሽ በመሄድ በጅምላ ብዙ ሰዎችን ከጨረሰ በኋላ ራሱን እንዳጠፋ የዜና ማሰራጫዎች እየዘገቡ ነበር፡፡ ይህ ልጅ ከስራ ሲባረርና ሴት ጓደኛውም ከድታው ስትሄድ የተሰማውን ምሬት ነበር በእንዲህ አይነት መልኩ የገለጸው፡፡

የዚህ አለም ጣጣ ወደ አላስፈላጊ ጫፍ ሊገፋን ሁልጊዜም ቢሆን ይፈልጋል፡፡ ለዚህ ነው ነቅቶ በመጠበቅና በመጸለይ የህይወት መከራ እሾሆዎችን መጋፈጥ በእጅጉ አስፈላጊ የሚሆነው፡፡

**በትንሽ ነገሮችም ታማኝ ሁኑ**

ዘጸ. 2፡ 3-4 ወንድሟን ከሞት ለመታደግ በተዘጋጀው እቃ ውስጥ በናይል ባህር ላይ የተቀመጠውን ሙሴን ስትጠብቅ የነበረችውን የሚሪያምን ታሪክ ይተርካል፡፡ ፈርኦን የእስራኤላውያን ወንዶች ልጆች እንዲገደሉ አዋጅ አውጥቶአል፡፡ የሙሴ ወላጆች ደግሞ ይህንን ህግ ተላልፈው ነበር፡፡ በልጃቸው በሚሪያም ላይ ተማምነው እስከ ተወሰነም ጊዜ ቢሆን ህጻኑን እናቆየዋለን ብለው አሰበዋል፡፡ «አደራሽን በደንብ አድርገሽ ጠብቂው» በማለት ወላጆቿ ለሚሪያም ይነግሯት ነበር ብዬ አስባለሁ፡፡ ሚሪያምም ይህንን አደረገች፤ የወንድሟን ሕይወት በመታደግ ረገድም የእግዚአብሔር መሳሪያ ሆና አገለገለች፡፡ በትንንሽ ነገሮች ላይ የነበራት ትጋት ከመከራ ውስጥ በረከትን ለማውጣት እድትችል አደረጋት፡፡ ባርኮቱም ታላቅ ከመሆኑ የተነሳ፣ የሙሴ እናት ራሷ ልጇን ለማሳደግ ወንዶች ልጆች እንዲሞቱ አዋጅ ባወጣው ንጉስ ደሞዝ እንዲከፈላት ሆነ፡፡

ኢየሱስም እንዲህ አለ፡- «ከሁሉ በሚያንስ የታመነ በብዙ ደግሞ የታመነ ነው» (ሉቃ. 16፡10)፡፡ የባሕርያችን እውነተኛ መፈተኛ ትንንሽ ነገሮችን አስመልክቶ ያለን ታማኝነት ነው፡፡ እግዚአብሔር ጌዲዮን ሰራዊቱን እንዲያደራጅ በረዳው ጊዜ፣ ተመልማዮቹን የፈተናቸው ውሃ እንዲጠጡ በማድረግ ነበር (መሳ. 7)፡፡ እንዴት ውሃውን እንደሚጠጡ እግዚአብሔር ሲመለከት፣ ማን ለስራው እንደሚጠቅመው ማን ደግሞ እንደማይጠቅም ተመለከተ፡፡ ድርጊቷ ትንሽ ናት፡፡ እግዚአብሔር የጠየቃቸው ውሃን መጠጣት ብቻ ነው፡፡ ይህንንም ፈተና ከአስር ሺኅ ሰዎች ሶስት መቶዎቹ ብቻ ናቸው ያለፉት፡፡

**ቀኖቻችሁን ቁጠሩ**

ነቅተን እንድንጠብቅ የሚያደፋፍረን ሌላው ነገር የሕይወት አላፊ መሆን ነው፡፡ በመዝ. 90 «ቀኖቻችን እድቆጥር» ተመክረናል፡፡ አመቶቻችንን፣ ወሮቻችንን ወይም ሳምንቶቻችንን አይደለም፡፡ ልናገኝ የምንችለው ቀኖችን ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ሕይወት መቼ እንደምታበቃ አናውቅምና፡፡ ሁልጊዜ ነቅተን መጠበቅ አለብን፡፡

ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፡- «እንግዲህ በማታ ቢሆን ወይም በእኩለ ሌሊት ወይም ዶሮ ሲጮኽ ወይም በማለዳ ቢሆን ባለቤቱ መቼ እንዲመጣ አታውቁምና» (ማር. 13፡ 35)፡፡

ታዲያ ለዚያ ጊዜ እንዘጋጃለን? በሃያ አምስት አመቱ በመኪና አደጋ ምክንያት ሕይወቱን ላጣ አንድ መልከ መልካም ወጣት ልጅ የቀብር ስነስርአት እያካሄድኩ ነበር፡፡ በዚያ አገልግሎት ላይ ይህ ሕይወት የምንለው ጉዞ ምን ያህል አጭር እንደሆነና አንዳንዶች የበጋውን ወቅት ኖረው ሲያልፉ ሌሎች ደግሞ ክረምቱን እንደሚኖሩ እየተናገርኩ ነበር፡፡ የክረምት ቀናት ከበጋ ጋር ሲነጻጸሩ አጫጭር ናቸው፡፡ መክ. 9፡12 የእኛ ጊዜ መቼ እንደሚመጣ እንደማናውቅ ይነግረናል፡፡ ፈጽሞ ባልጠበቁት ጊዜ በመረብ እንደተያዙ አሶች ወይም በወጥመድ እንደተያዙ ወፎች ነን፡፡ ሼክስፒር ማክቤዝ በተባለው ተውኔቱ ላይ የህይወትን አጭርነት በተመለከተ እንዲህ ጽፎአል፡- «ጥፊ፣ ጥፊ፣ አንቺ ለአጭር ጊዜ የምትነጂ ሻማ!» እንግዲያውስ የሕይወት አጭርነት በንቃት እንድንቆይና መጠበቃችንን እንድንቀጥል ሊያደፋፍረን ይገባል፡፡

## ከፊት ቀድመው ከተጓዙ ሰዎች ትምህርት ውሰዱ

ነቅተን እንድንጠብቅ የሚያደርገን የመጨረሻው ምክንያት ከእኛ በፊት የተጓዙት ሰዎች ምሳሌያዊ ሕይወት ነው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ወንድና ሴት ጀግኖች ደፋር ፣ አስተማማኝና የማይለዋወጥ ባህርያትን ቅርስ ትተውልን አልፈዋል፡፡ እንደ አስቴር፣ ዳንኤል፣ ዮሴፍ፣ ጳውሎስና ሌሎችም እዚህ ላይ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ የዕብራውያን ጸሐፊ እንዲህ ይላል፡- «እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደደመና በዙሪያችን አሉልን» (ዕብ. 12፡1)፡፡ በታማኝነት ሕይወታቸውን የመሩትን ሰዎች ምሳሌነት ይዘን ወደ ፊት ለመገስገስ መነሳሳት ያስፈልገናል፡፡ በመከራ ውስጥ በረከትን ለማግኘት የሚያስችል አስተማማኝ መንገድ ይሄ ነው፡፡

## በማዕበል የማይበገር ሕይወት ለመምራት የሚረዱ ተግባራት

- አስታውሱ ብቻችሁን አይደላችሁም
- እግዚአብሔርን መስማት ተማሩ
- በምታምኑበት ነገር ላይ የድርጊት እርምጃ ውሰዱ
- ለሕይወት ማዕበል የተዘጋጃችሁ ሁኑ
- በንቃት ጠብቁ
- ነቅቶ በመጠበቅ ፈተናን አሸንፉ፡፡
- በሌሎች ዘንድ አመኔታ ማግኘትን አዳብሩ
- በሕይወት የሚያጋጥሙን አስጨናቂ ነገሮች ተጋፈጧቸው፡፡
- በትንሽ ነገሮችም ታማኝ ሁኑ፡፡
- ቀኖቻችሁን ቁጠሩ፡፡
- ከፊት ቀድመው ከተጓዙ ሰዎች ትምህርት ውሰዱ፡፡

# የመጨረሻ ቃል

በሕይወቱ ያጠራቀመውን ጥሪቱን ሁሉ በአንድ የኮክ እርሻ ላይ አፍስሶ ስለነበረ አንድ ወጣት ክርስቲያን በአንድ ወቅት የሰማሁት ታሪክ ትዝ ይለኛል፡፡ ዛፎቹን በመግረዝ፣ አረሞቹን በማረም፣ ለኮክ እርሻው የሚያስፈልገውን እንክብካቤ ሁሉ በማድረግ በትጋት ሰራ፡፡ በጸደይ ወራትም የኮክ ተክሎቹ በጥሩ ሁኔታ አበቡ፤ ፍሬም ያዙ፡፡ ነገር ግን ከዚያ ቀጥሎ ከባድ የሆነ ውርጭ ተነሳና እርሻውን በጠቅላላ አወደመው፡፡ ይሄን ጊዜ ሰውየው በእግዚአብሔር ተበሳጨና ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ አቆመ፡፡

ወደ አምልኮ ፕሮግራም መሄዱን ካቋረጠ ከብዙ ሳምንታት በኋላ፣ ፓስተሩ ሊጎበኘው መጣ፡፡ «ቦብ ፊትህን በቤተክርስቲያን ካየሁት ሰነበትኩ፤» አለ ፓስተሩ፡፡ ቦብም «ፓስተር፣ ቤተክርስቲያን ከዚህ በኋላ ላልሄድ ወስኛለሁ» በማለት መለሰ፡፡ «የኮክ እርሻዬ በውርጭ ተመትቶ እንዲጠፋ የሚያደርግን ስለ እኔ ምንም የማይገደውን አምላክ የማመልክ ይመስሃል?» ፓስተሩም በእርጋታና በጥበብ እንዲህ በማለት መለሰ፡- «ልጄ ሆይ፣ እግዚአብሔር ያንተን የኮክ እርሻ ከሚወደው በላይ አንተን ይወድሃል፡፡ አየህ፣ እግዚአብሔር ኮክ የሚያድገው ያለ ውርጭ እንደሆነ ቢያውቅም፣ አማኞች ግን ያለ መከራ ሊያድጉ እንደማይችሉ ደግሞ ያስተውላል፡፡ የእርሱ ተቀዳሚ ስራ ደግሞ ኮክ ማሳደግ አይደለም፡፡ እርሱ የተሰማራው አማኞችን በማሳደግና ጠንካራም እንዲሆኑ በማድረግ ሥራ ላይ ነው፡፡ መከራ በሕይወታችሁ ሲመጣ፣ በመከራችሁ ውስጥ የእግዚአብሔርን በረከት ፈልጉ፡፡ እርሱ የሕይወትን ማዕበል መቋቋም የሚችሉ አማኞችን በማሳደግ ሥራ ላይ ነው፡፡

## ስለ ጸሐፊው

ሰኔ 27፣ 2003 ቀን ሪር አድሚራል ቤሪ ሲ ብላክ (ጡረታ ወጥተዋል)፣ የዩናይትድ ስቴትስ ሴኔት 62ኛ ቻፕሌን በመሆን በ1789 የተቋቋመን ቢሮ በኃላፊነት ተረከቡ፡፡ ወደ ካፒቶል ሂል ከመምጣታቸው ቀደም ብለው፣ ቻፕሌን ብላክ የዩ.ኤስ. ባሕር ኃይልን ከ27 አመታት በላይ ያገለገሉ ሲሆን፣ የባሕር ኃይሉ ቻፕሌኖቹ ዋና አለቃ የመሆንን ከፍተኛ ማዕረግ በማግኘት ነበር በዚያ የነበራቸውን አገልገሎት ያበቁት፡፡

በ1976 የባሕር ኃይሉ ቻፕሌን ለመሆን ከተመረጡ በኋላ፣ በተለያዩ ቦታዎችና ሃላፊነቶች ሰርተዋል፡፡ እንደ ሪር አድሚራል ብዙ ሜዳሎችንና ሽልማቶችን የተበቀሉም ሰው ናቸው፡፡

ቻፕሌን ብላክ የባልቲሞር፣ ሜሪላንድ ተወላጅና በኦክውድ ኮሌጅ፣ አንድሪውስ ዩንቨርስቲ፣ ኖርዝ ካሮላይና ሴንትራል ዩንቨርስቲ፣ ኢስተርን ባብፐቲስት ሰሜኒናሪ፣ ሳልቨ ሬጊና ዩኒቨርስቲ፣ እና ዩናይትድ ስቴትስ ኢንተርናሽናል ዩንቨርስቲ የከፍተኛ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል፡፡ በዲቪኒቲ፣ በካውንስሊንግና በማኔጅመንት ሁለተኛ ድግሪዎችን ከመስራታቸው በተጨማሪ፣ በሚኒስትሪና በሳይኮሎጂ ደግሞ ሁለት የዶክትሬት ዲግሪ አላቸው፡፡

ቻፕሌን ብላክ ስለ ብዙ ታላላቅ ስራዎቻቸው ይታወሳሉ፡፡ የባለቤታቸው ስም ብሬንዳ ፔረሳል ሲሆን ሦስት ወንዶች ልጆች አሏቸው፤ ቤሪ ሁለተኛ፣ ብሬንዳን ና ብራድፎርድ ይባላሉ፡፡